# ብሉይ ኪዳን

# በግእዝና በአማርኛ

ይህ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ፓትርያርክ፣ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
10ኛ ዓመተ ሢመተ ፓትርያርክና ለሁለተኛ ጊዜ ታተመ::

አሳታሚ:- ትንሣኤ
አዲስ አበባ
፲፱፻፺ ዓ.ም

ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ንብረት
Property of Saint Michael Cathedral
1106 N. Jupiter, Garland TX 75042
Tel. (972) 487 0825

# መ ግ ለ ጫ

እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ ነቢያት፣ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት አዝዞ ያጻፋቸውና ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የተቀበሏቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ሰማንያ አንድ መሆኑ በፍትሐ መንፈሳዊ (ፍትሐ ነገሥት) በተሰኘው መጽሐፍ አንቀጽ ሁለት ላይ ተደንግገዋል።

እነዚህም መጻሕፍት ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ( ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን) በመባል የሚታወቁ ሲሆን፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት፣ ሕግና ሥርዓት፣ ታሪክና ባሕል መሠረት በመሆናቸው በምዕመናን ሕይወት ጸንተውና ተጠብቀው እስከ አሁን ድረስ የኖሩና ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው። ( ኤፌ 2:19-20)

ብሉይ ኪዳን ልዑል እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ለነበሩት አበው በሕገልቡና፣ ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ልደት ለነበሩት ሕዝበ እስራኤል በሕገ መጽሐፍ (ኦሪት) በልዩ ልዩ ምሳሌና ትንቢት የተነገረው ተስፋ እንደሚፈጸም የገባው ቃል ኪዳን ( መሐላ) ነው። (ገላ 3:15-18)

ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን የድኅነት ተስፋ በጊዜው ጊዜ መፈጸሙን ያረጋገጠ አማናዊና ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን (መሐላ) ነው። (ዕብ 9:15)

የመጀመሪያው ክፍል ስምንቱ ብሔረ ኦሪትን አጠቃሎ የያዘ ነው። እነርሱም ኦሪት ዘፍጥረት፣ኦሪት ዘፀአት፣ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቊና ኦሪት ዘዳግም እንዲሁም መጽሐፈ ኢያሱ፣መጽሐፈ መሳፍንትና መጽሐፈ ሩት በመባል ይታወቃሉ።

መጽሐፈ ኢያሱን፣መጽሐፈ መሳፍንትንና መጽሐፈ ሩትን በየዘመኑ የነበሩ ነቢያትና ካህናት ጽፈዋቸዋል። ስምንት መሆናቸውም የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምግብና ሲፈጸም ከላይ እንደተገለጸው አማናዊት ሕገ ወንጌል እንደምትሠራ ለማጠየቅ ነው በማለት ሊቃውንቱ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

ይህም ኦሪት ዘጠኝ ነገሮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም ሕግ፣ ስምዕ፣ ትእዛዝ፣ አኰቴተ እግዚአብሔር ፣ ነገረ እግዚአብሔር፣ ተግሣጽ፣ ምዕዳን፣ ጥበብ ሥጋዊና ጥበብ መንፈሳዊ ናቸው።

እንደ ሊቃውንቱ እምነትና አስተያየት እነዚህ መጻሕፍት ሲነበቡና ሲተረጎሙ ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደርሰዋል። ሐዋርያትም ለቀለሚንጦስ ሰማንያ አንድ መጽሐፍትን ሲሰጡት ከብሉያት ስምንት በሐውርተ ኦሪት ብለው ቆጥረው ሰጥተውታል። እነዚህም ከላይ የጠቀስናቸውና አሁንም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ናቸው።

« ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጽ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው መጻሕፍት እኛ ልንመ ከርባቸውና ልንገሰጽባቸው እንጂ ለከንቱ አልተጻፉምና እያንዳንዱ ክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት ሊጠቀም ይገባል። ( ሮሜ 15:4)

ብሉይ ኪዳንንም ሆነ ሐዲስ ኪዳንን ቀደምት አባቶቻችን ከግእዝ ወደ አማርኛ በነጠላና በአንድምታ ተርጉመዋቸው ሁሉም በአገልግሎት ላይ የሚገኙ ቢሆኑም ቀደም ብለው የታተሙት እየታጡ በመሆናቸው ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት እንደገና እያሳተመና እያሠራጨ ይገኛል።

በዚህም መሠረት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ ሰባቱን

1. በነጠላ ትርጉም በግእዝና በአማርኛ፣
2. በአማርኛ ብቻ፣
3. ትርጓሜ ወንጌልን፣ ሠለስቱ ሐዲሳትንና የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት፣
4. ከብሉያት መጻሕፍት፤
   መጽሐፈ ሕዝቅኤልን፣ መጽሐፈ ሲራክን፣ መዝሙረ ዳዊትንና የመሳሰሉትን በነጠላና በአንድምታ ትርጓሜ አሳትሞ ለአገልግሎት አብቅቶአል።

አሁንም በኅትመት ላይ ያሉት ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ሥራቸውን እንደቀጠሉ ሲሆን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንም ዓቅም በፈቀደ መጠን በመጀመሪያ ግእዙንና አማርኛውን በነጠላ ትርጉም ወደ ፊትም አንድምታ ትርጓሜውን በቅደም ተከተል አሳትሞ ለማቅረብ ባለው ዕቅድ መሠረት ቀደም ሲል ታትሞ የነበረውን ስምንቱን ብሔረ ኦሪት በግእዝና በአማርኛ አሳትሞ ማቅረቡን በደስታ እያበሠረ፣ ሐዋርያት « ጸልዩ ለነ ከመ ይሩፅ ቃለ እግዚአብሔር » እንዳሉት ድርጅቱ ቀሪዎቹንም በተከታታይ አሳትሞ ለማቅረብ እንዲችል የእግዚአብሔር ቸርነት ፣ የብፁዓን አበው፣ የሊቃውንቱ፣ የካህናቱና የምእመናን ጸሎትና ድጋፍ እንደማይለየው እምነታችንና ተስፋችን ጽኑ ነው።

« ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ»

ማሳተሚያ ድርጅቱ
አ.አ ፲፱፻፺፬

# መጽሐፈ ምሳሌ

| ምዕራፍ ፩ ። | | ምዕራፍ ፩ ። |
|---|---|---|
| ምሳሌያተ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ዘነግሠ ለእስራኤል በኢየሩሳሌም ። | ፩ | ለእስራኤል በኢየሩሳሌም የነገሠ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን፣ የተናገረው ነገር ይህ ነው ። ፩ ነገ፡ ፬ ፴፪። |
| ለአእምሮ ጥበብ ወተግሣፅ ወለአእምሮ ቃለ ጥበብ ። | ፪ | ዘጠኙን ሕገጋትና ኢታምልክን ለማወቅ የፈሊጥን ነገር ለማሳወቅ ። |
| ወለተወክፎ መይጠ ቃል፣ ወለአእምሮ ጽድቅ ዘበአማን ። | ፫ | መልስ ማወቅን ለማስተዋል እውነተኛ ነገርንም ለማሳወቅ ። መዝ፡ ፲፯ ፪ ። |
| ወለአርትዖ ፍትሕ ከመ የሀበሙ ጥበበ ለየዋሃን፣ ለሕፃናት፣ ወለወራዙት ተዐውቆ ወአእምሮ ። | ፬ | ላልተማሩ ሰዎች ጥበብን፣ ለሕፃናት ማወቅን፣ ለጐልማሶች ዕውቀትን ያስተምራቸው ዘንድ ፍርድን ለማቅናት ሰሎሞን የተናገረው ነገር ይህ ነው ። |
| ዘንተ እምከመ ሰምዐ ጠቢብ ይዌስክ ጥበበ ። | ፭ | ብልህ ሰው ይህን በሰማ ጊዜ በጥበብ ላይ ጥበብን ይጨምራል ። |
| ወዘሰ አጥረየ ሐዳፈ የአምር ምሳሌ ወሥውረ ነገረ፣ ነገረ ጠቢባን በቅጽበት ። | ፮ | መምህርን ገንዘብ ያደረገ ሰው ሥውር ነገርንና ምሳሌን ያውቃል፣ የመምህራንም ነገራቸው በዓይን ጥቅሻ ነው ። እንባ፡ ፪ ፮ ። ምሳ፡ ፲፱ ፲፪ ። |
| ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር፣ ወአእምሮ ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር ቀዳሚ ተዐውቆ፣ ጥበበ ወተግሣፀ ይሜንኑ ረሲዓን ። | ፯ | የጥበብ መጀመርያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ ለሚያደርጋትም ሰው ሁሉ በጎ ዕውቀት ናት፣ እግዚአሔርንም መፍራት የዕውቀት መጀመርያ ናት፣ የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጉ ሰዎች ዘጠኙን ሕገጋትና አምልኮቱን ይንቃሉ። |
| ስማዕ ወልድየ ሕገገ አቡከ፣ ወኢትትኀየይ ትእዛዘ እምከ ። | ፰ | ልጄ የአባትህን ሕግ ስማ፣ የእናትህንም ትእዛዝ ቸል አትበል ። |
| አክሊለ ክብር ትነሥእ ለርእስከ፣ ወባዝግና ወርቅ ለክሳድከ ። | ፱ | ለራስህ ክብር ያለው ዘውድን ትቀዳጃለህ፣ ለአንገትህም ዝርግፍ ወርቅ ታሥራለህ። መሳ፡ ፰ ፳፮ ። |
| ኦ ወልድየ ኢያስሕቱከ ሰብአ ረሲዓን፣ ወኢትፍቅድ እመ አስተብቍዑከ እንዘ ይብሉ ነዓ ተሳተፍ ምስሌነ ደመ ። | ፲ | ልጄ ሆይ! የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጉ ሰዎች አያስቱህ፣ ከእኛ ጋራ ደም በማፍሰስ ተባበረን ብለው ቢለምኑህ አትውደድ ። |
| ወንድፍን ውስተ ምድር ብእሴ ጻድቀ በዓመፃ ። | ፲፩ | እውነተኛ ሰውን በግፍ ገድለን እንቅበረው ። |
| ወነኀጦ ከመ ገሃነም ሕያዎ፣ ወንስዕር እምድር ዝክሮ ። | ፲፪ | በሕይወትም ሳለ እንደ መቃብር እንዋጠው፣ ስም አጠራሩንም ከዚህ ዓለም እናጥፋ። መዝ፡ ፳፩ ፩ ። |
| ወጥሪቶ ብዙኀ ናስተጋብእ ወንምላእ አብያቲነ በርበሮ። | ፲፫ | ብዙ ገንዘቡንም ሰብስበን ገንዘቡን በቤታችን እንሞላ። |
| ወአንተኒ ኅበር ምስሌነ ወአሐዱ ቍናማት ይኩነነ ለኵልነ፣ ወመስነቅት አሐቲ ትኩነነ። | ፲፬ | አንተም ከእኛ ጋራ ተባበር፣ አንድ የዕቃ አቍማዳ ለሁላችን ይሁነን አንዲት የስንቅ ስልቻም ለሁላችን ትብቃን፣ ብለው ቢለምኑህ አትውደድ ። |
| ኢትሑር ወልድየ ምስሌሆሙ ፍኖተ ። | ፲፭ | ልጄ! ከነሳቸው ጋራ መንገድን አትሂድ። |

፲፮ እግኅሥ እገሪከ እምአሠርሙ ፣ እስመ ለእከይ ይረውፃ እገሪሆሙ ወያፈጥና ለክዒወ ደም ፡፡

፲፯ እስመ አከ በከ ዘይረብቡ መሥገርተ ለሰብእ ፡፡

፲፰ እሙንቱሰ እለ ቀቲለ ለመዱ ይዘግቡ ሎሙ እከየ ፣ ወድቀቶሙ ለሰብእ ኃጥአን እኩይ ፡፡

፲፱ ዝ ፍናው ውእቱ ለኵሎሙ እለ ይፌጽሙ ኃጣውእ ኃጢአት ወትፅግልት ነፍሰሙ ታኃጒል ፡፡

፳ ጥበብ በፍናው ትሴባሕ ፣ ወበመራኅብት ትሁብ ቃላ ፡፡

፳፩ ወውስተ አርእስተ ጥቅም ትሰበክ ፣ ወውስተ አናቅጺሆሙ ለኃያላን ትፀመድ ፣ ወውስተ አናቅጸ ሀገር ጥቡዐ ትብል ፡፡

፳፪ መጠነ መዋዕል የዋሃን በሙ ጽድቅ ወኢይትኃፈሩ ፡፡

፳፫ እስከ ማእዜኑ ረሲዓን ታፈቅሩ ስሕተተ ፣ ዓብዳንሰ ፈታውያነ ጽእለት እሙንቱ ፣ ወረሲዓነ ከዊኖሙ ጸልኡ አእምሮ ወርሱሐነ ኮኑ ለእለ ይዘልፍዎሙ ፣ ለምንት ትመይጡ ዘለፋየ ፡፡

፳፬ ወናሁ አነ እነግረክሙ እስትንፋሰ ቃልየ ወእሜህረክሙ ነገረ ዚአየ ፡፡

፳፭ እስመ ጸዋዕኩ ወኢያውሣእክሙኒ ፣ ሰፋሕኩ እደውየ ወኢያጽማእክሙኒ ፡፡

፳፮ ወአብዛኅኩ ነገረ ወኢተሰጠውክሙኒ ፣ ወምኑነ ረሰይክሙ ፣ ትእዛዝየ ወዘለፋየኒ ኢነጸርክሙ ፡፡

፳፯ ወአነሂ በኃጒልክሙ እስሕቅ ፣ ወእትፌሣሕ ሶበ ይመጽአክሙ ግብተ ተሠርዎ ፡፡

፳፰ ወሶበ ይመጽአክሙ ግብተ ሀከክ ወሙስናሂ ከማሁ ሶበ ይመጽአክሙ ለአሥግሮ ወሶበ ይመጽአክሙ ምንዳቤ ወተዌውዎ ሀሉኩ ሀየ ፡፡

፳፱ ወሶበ ትጼውዑኒ አነሂ ኢይሰምዐክሙ ፣ የኃሥሡኒ እኩያን ወኢይረክቡኒ ፡፡

፴ እስመ ጸልእዋ ለጥበብ ወቃለ እግዚአብሔርኒ ይሰምዑ ኢፈቀዱ ፡፡

፴፩ ወኢፈቀዱ ይነጽሩ ዘዚአየ ምክረ ፣ ወያስተራኵሱ ኵሉ ዘዚአየ ዘለፋ ፡፡

፴፪ እንከሰኬ ይበልዑ ፍሬ ምግባሮሙ ፣ ወበዘዚአሆሙ ኃጢአት ይጽገቡ ፡፡

፴፫ እስመ ኢተመይጠቶሙ ለዓብዳን ትቀትሎሙ እምእንተ ገፍዑ ደቂቀ ይትቀተሉ ወሐተታሆሙ ለረሲዓን ትቀትሎሙ ፡፡

፴፬ ወዘሰ ኪያየ ይሰምዕ ይኄሉ በተስፋ ወየዓርፍ ዘእንበለ ድንጋፄ እምኵሉ እኩይ ፡፡

እግሮቻቸው ለክፋት ይሮጣሉና ፣ ደምንም ለማፍሰስ ይፈጥናሉና ፡፡

ለሰው ወጥመድን የሚዘረጉ በከንቱ አይደለምና እግርህን ከፍለጋቸው አርቅ ፡፡ ሮሜ፣ ፫ ፲፭ ፡፡

ሰውን መግደል የለመዱ እነዚህ ብዙ መከራ ይቀበላሉ ፣ የኃጢአተኞችም ሰዎች ሞታቸው ክፉ ነው ፡፡

ይህ ሥራ ኃጢአትን ፈጽመው ለሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ነው ፣ ኃጢአት ፣ ቀሚያ ፣ ሰውነታቸውን ታጠፋለች ፡፡

ጥበብ በጐዳና ትመሰገን ነበር ፣ (በዘመነ አበው) በአደባባይ ቃሏን ትሰጥ ነበር ፡፡ (በዘመነ መሳፍንት) ፡፡

በቅጥሩም ራስ ላይ ትነገር ነበር ፣ (በዘመነ ነገሥት) በኃይለኞችም በሮች ታገለግል ነበር ፣ (በዘመነ ክህናት) በሀገር በሮችም የጨከናችሁ ሁኑ ትል ነበር ፣ (በዘመነ ሰማዕታተ ብሊት) ፡፡

ለየዋሆች ሰዎች ባለ በዘመናቸው ሁሉ ጽድቅ አላቸው ፣ ሐሰትም ተናግረው አያፍሩም ፡፡

እግዚአብሔርን የዘነጋችሁ ሰዎች እስከ መቼ ድረስ ስሕተትን ትወዳላችሁ ፣ ሰነፎች ግን ቢሰደቡ የሚወዱ ናቸው ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጉ ሆነው ዕውቀቱን ጠሉ ለሚያስተምሯቸው ለነቢያትም ቢያጥቡ አይጠራሁ ፣ ምክሬን ለምን ትለውጣላችሁ ፡፡

እነሆ እኔ ረቂቅ ቃሌን እነግራችኋለሁ ፣ ነገሬንም አስተምራችኋለሁ ፡፡ ኢዩ፣ ፪ ፳፰ ፡፡

በስተምራችሁ አልሰማችሁኝምና ፣ እጄንም ብዘረጋ አላደመጣችሁኝምና ፡፡ ኢሳ፣ ፳፭ ፲፪ ፡፡

ትምህርቴን በስተምራችሁ አልሰማችሁኝምና ፣ ትእዛዜንም የተናቀ አድርጋችኋልና ፣ ምክሬንም አልተመለከታችሁምና ፡፡ ምሳ፣ ፭ ፲፪ ፡፡ ሉቃ፣ ፯ ፴ ፡፡

እኔም በጥፋታችሁ ደስ ይለኛል ፣ ድንገት መከራ በመጣባችሁም ጊዜ ደስ ይለኛል ፡፡ መዝ፣ ፪ ፬

ድንገት ጸብ ፣ ክርክር ፣ በመጣባችሁ ጊዜ እንደዚሁም ለማጥፋት ጥፋት በመጣባችሁ ጊዜ ፣ መገረክና መከራም በመጣባችሁ ጊዜ ፣ እኔ በዚያ አለሁ ፡፡ ኢዮ፣ ፴ ፫ ፡፡

ከመከራም አድነን ብላችሁ በለመናችሁኝ ጊዜ እኔም ልመናችሁን አልሰማችሁም ፣ ክፉ ሰዎች ይፈልጉኛል አያገኙኝም ፡፡ ፩ ሳሙ፣ ፰ ፲፰ ፡፡ ኢሳ፣ ፩ ፲፭ ፡፡

ጥበብን ጠልተዋታልና ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ ዘንድ አልወደዱምና ፡፡

የኔን ምክር ይመለከቱ ዘንድ አልወደዱምና ፣ ሕጌንም ሁሉ ይሽራሉና ፡፡ መዝ፣ ፹፩ ፲፩ ፡፡ ሉቃ፣ ፯ ፴ ፡፡

እንግዲህስ የኃጢአታቸውን ፍዳ ይቀበሉ ፣ የራሳቸውንም ኃጢአት ፍዳ አብዝተው ይጥገቡ ፡፡

በንስሐ አለመመለሳቸው ሰነፎችን ታጠፋቸዋለችና ፣ ነቢያትንም ከመበደላቸው የተነሣ ደቂቀ (እስራኤል) ይጠፋሉ ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጉ ሰዎችን መመርመራቸው ታጠፋቸዋለች ፡፡

እኔን የሚሰማ ሰው ግን በእለኝታ ይኖራል ፣ ያለ ድንጋፄም ከመከራው ሁሉ ያርፋል ፡፡ መዝ፣ ፳፩ ፲፪—፲፫ ፡፡

## ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወልድየ ለእመ ተወከፍከ ቃለ ትእዛዝ ዘዚአየ ወኀበ እከ በልብከ ።

፪ ትሰምዕ ዕዝንከ ጥበበ ወትሁብ ልብከ ለአእምሮ ወታቀርብ ለተግሣፅ ልበከ ።

፫ ወለእመኒ ለጥበብ ጸዋዕከ ወለአእምሮ ወሀብከ ቃለከ ወለለብዎ ኃሥሥከ በዓቢይ ግብር ።

፬ ወለእመኒ ኃሥሥከ ከመ ብሩር ወከመ መድፍን ፈተንከ ።

፭ አሜሃ ተአምር ፈሪሀ እግዚአብሔር ወጠይቆ እግዚአብሔር ትረክብ ።

፮ እስመ እግዚአብሔር ይሁብ ጥበበ ፡ ወእምቅድመ ገጹ ለብዎ ወአእምሮ ።

፯ ወይዘግብ ሎሙ ለእለ ይገብሩ መድኃኒተ ወቃውም ለፍኖቶሙ ከመ ፍኖተ ጽድቅ ፡ ወፍኖተ እለ ይፈርህዎ የዓቅብ ።

፰ አሜሃ ተአምር ፍትሐ ወጽድቀ ፡ ወታረትዕ መንኰራኵረ ሠናያተ ።

፱ እስመ እመ መጽአት ጥበብ ውስተ ሕሊና ዚአከ ወአእምሮ ለነፍስ ዚአከ ሠናይተ ኮነት ።

፲ በምክር ሠናይ ተዓቅበከ ፡ ወበሕሊና ጽድቅ ትከድነከ ።

፲፩ ከመ ታድኅንከ እምፍኖት እኪት ፡ ወእምብእሲ ዘኢይነብብ ወኢምንተኒ ህልወ ቃለ ።

፲፪ ወይ ሎሙ ለእለ የኀድጉ ፍኖወ ርቱዓተ ፡ ከመ ይሑሩ በፍኖወ ጽልመት ።

፲፫ ወእለ ይትፌሥሑ በእኩይ ወእለ ይትኃሠዩ በሚጠተ እኪት ።

፲፬ እለ ፍናዊሆሙ መብእስ ፡ ወደጋን መንኰራኵሮሙ ከመ ያርኅቁከ እምፍኖት ርትዕት ፡ ወነኪር እምፍኖተ አእምሮተ ጽድቅ ።

፲፭ ወልድየ ፡ ኢትርከብከ ምክር እኪት ፡ እንተ ታኃድግ ተምህርተ በውርዙትከ ።

፲፮ ወልድየ ፡ ዕቀብ ቃልየ ከመ ይባልሕከ እምብእሲት እኪት ወነኪርት ፡ እንተ ቃላ ትምይንት ዘኃደገት ምታ ዘንእሳ ወሥርዓተ እግዚአብሔር እንተ ረስዓት ።

፲፯ ወአንበረት ኀበ ሞት ቤታ ፡ ወኀበ ሲኦል ወምስለ ኃያላን እምድር አርትዓት መንኰራኵራ ።

፲፰ ኵሎሙ እለ የሐውሩ በቲ ኢይትመየጡ ወኢይረክቡ ፍኖወ ርቱዓተ ፡ ወኢይትረከቡ በዓመተ ሕይወት ።

፲፱ ሰበሰ የሐውሩ ፍኖወ ርቱዓተ እምረከቡ ፍኖወ ጽድቅ ልሙያተ ፡ ኄራነ ይከውኑ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር ፡ ወየዋሃን ይተርፉ ውስቴታ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

ልጄ ! ያዘዝኩህን ነገር ብትቀበል በልቡናህም ሠውረህ ብትይዘው ። ምሳ፡ ፪ ፯ ። ፩ ፳፩ ።

ጆሮህም ጥበብን ብትሰማ ፡ ልብህንም ለዕውቀት ብትሰጥ ፡ ልቡናህንም ለምክር አዝናት ብታቀርብ ።

ጥበብንም ብትጠራት ፡ (ፈልገህ ብትማራት) ቃልህን ለዕውቀት ብትሰጥ ፡ በቃልህ ዕውቀትን ብትማር ፡ በፍጹም ሥራ ዕውቀትን ብትፈልጋት ።

እንደ ብር እንደ ተቀበረ ወርቅም ተግተህ ብትፈልጋት ። ምሳ፡ ፫ ፲፬ ። ማቴ፡ ፯ ፲፯ ።

ያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ ፡ እግዚአብሔርንም መረዳት ታገኛለህ ።

እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና ፡ ከፊቱም ፈጽሞ ዕውቀት ያገኛልና ። ዮሐ፡ ፯ ፵፭ ።

ዓሠርቱ ቃላተ ኦሪትን ለሚሠሩ ሰዎች ክብር ይደልብላቸዋል ፡ እውነተኛ ሕጉንም ይጠብቁ ዘንድ ለሥራቸው ጠበቃ ነው ፡ የሚፈሩትንም ሰዎች ሥራ ይጠብቃል ።

ያን ጊዜ እውነት ፍርድን ታውቃለህ ፡ በጎ ሥራንም ታቀናለህ ። ምሳ፡ ፩ ፫ ።

ጥበብ በልቡናህ ብታድር ፡ ዕውቀትም ለሰውነትህ በጎ ብትሆን ።

በበጎ ምክር ትጠብቅሃለች ፡ በእውነተኛም ሐሳብ ትሠውርሃለች ።

ከክፉ ሥራ ታድንኅ ዘንድ ምንም ቀኖሚ ነገርን ከማይናገር ሰውም ታድንኅ ዘንድ ።

በድንቍርና ሥራዎች ጸንተው ይኖሩ ዘንድ የቀና ሥራዎችን ለሚተዉ ሰዎች ወዮላቸው ።

በክፉ ነገር ደስ ለሚላቸው ፡ ክፉ መልስ በመመለስም ደስ ለሚላቸው ሰዎች ። ኤር፡ ፲፩ ፲፭ ።

ሥራዎቻቸውም ጐጸጐጽ ለሚሆኑ ከቀና ሥራ ያርቁህ ዘንድ እውነትን ከማወቅ ሥራ በዕድ ያደርጉህ ዘንድ ሥራዎቻቸው ጠማማ ለሚሆኑ ሰዎች ወዮላቸው ።

ልጄ ! በሕፃንነትህ ትምህርትን የምታስተው ክፉ ምክር አታግኝህ ። ምሳ፡ ፯ ፭ ።

ልጄ ! ከክፉ ሴት ይጠብቅህ ዘንድ ፡ ቃሏም ተንኰል ከሆነ ከጋለ ሞታ ያጸናህ ዘንድ ፡ የሕፃንነት ባሏን ከፈታች የእግዚአብሔርንም ሥራ ከዘነጋች ሴት ያድንኅ ዘንድ ቃሌን ጠብቅ ። ኤር፡ ፫ ፬ ።

ቤቷንም ከመቃብርና ከሞት ዘንድ ከኖረች ፡ ሥራዋንም ከኃያላኑ ጋራ ከቀናች ከጋለ ሞታ ያድንኅ ዘንድ ቃሌን ጠብቅ ። ። ምሳ፡ ፯ ፳፯ ።

ወደሷ የሚሄዱ ሰዎች ሁሉ በሕይወት አይመለሱም ፡ የቀኑ ሥራዎችንም አያገኙም ፡ ሕይወት በታዘዘበት ወራትም አይገኙም ።

በቀና ሥራዎችስ ፀንተው ቢኖሩ ፡ በጎ ሥራዎችን ባገኙ ነበር ፡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ደጋግ ሰዎች ናቸው ፡ የዋሃን ሰዎችም በሷ ይኖራሉ ።

፳ እስመ ራትዓን የኃድርዋ ለምድር ፡ ወጻድቃን ይተርፉ
ውስቴታ ።
፳፩ ፍናወ ረሲዓን እምድር ይሤረዋ ወዓማፅያንሰ ይሰደዱ
እምውስቴታ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወልድየ ሕገገ ዚአየ ኢትርሳዕ ፡ ወቃላትየ ይዕቀብ ልብከ ።
፪ ኑኀ መዋዕል ፡ ወዓመታተ ሕይወት ፡ ወሰላም ይትዌሰ
ኩከ ።
፫ ምጽዋት ፡ ወሃይማኖት ኢይርኃቃ ፡ እንቆ ውስተ ክሳ
ድከ ፡ ወጸሐፎ በጽሌ ልብከ ።
፬ ወትረክብ ሞገሰ ፡ ሐሊ ሠናየ በቅድመ እግዚአብሔር
ወሰብእ ።
፭ ሀሉ ተወኪለከ በእግዚአብሔር በኵሉ ልብከ ፡ ወበ
ጥበብከ ኢትትዓበይ ።
፮ በኵሉ ፍናዊከ አከብራ ከመ ታርትዕ ፍናዊከ ።
፯ ኢትኩን ጠቢበ ዘበርእሰከ ፡ አላ ፍርሆ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ወተገኀሥ እምኵሉ እኩይ ።
፰ ወሰቤሃ ፈውሰ ይከውነከ ለሥጋከ ፡ ወሥራየ ለአዕፅም
ቲከ ።
፱ አክብር ለእግዚአብሔር እምዘ በጽድቅ ጥሪትከ ፡ ወአ
ብእ ሎቱ ቀዳሜ ማእረርከ ወእምፍሬ ጽድቅከ ።
፲ ከመ ይስፍኑ መዛግብቲከ ብዙኀ ሥርናየ ፡ ወወይነ
ማኅበቲከ ይስፍፍ ።
፲፩ ወልድየ ፡ ኢትትአንተል ተግሣፀ እግዚአብሔር ፡
ወኢትድከም እምኀቤሁ በተዛልፎቱ ።
፲፪ እስመ ዘአፍቀረ ይጌሥፅ እግዚአብሔር ከመ አብ
ዘይሠምር ወልዶ ፡ ወይቀሥፍ ኵሎ ውሉዶ ዘኢይ
ትዌከፉ ።
፲፫ ብፁዕ ብእሲ ዘይረክባ ለጥበብ ፡ ወኢ መዋቲ ዘአእ
መረ ሐኪከ ።
፲፬ ይኄይስ ኪያሃ ተገብር ፡ እምተገብሮ ወርቅ ወብሩር ፡
ወእምብዙኅ መዛግብት ።
፲፭ ክብርት ይእቲ እምዕንቍ ዘብዙኅ ሤጡ ፡ ወኢይትቃ
ወማ ምንትኒ እኩይ ።
፲፮ ሠናይት ሀገሪት ይእቲ ለኵሎሙ እለ ይቀርብዋ ፡ ወ
ኵሉ ክብር ኢኮነ መጠና ፡ ኑኀ መዋዕል ወዓመተ ሕይወት
ውስተ የማና ።
፲፯ ወውስተ ጸጋማ ክብር ወብዕል ፡ ወእምአፉሃ ይወጽእ
ጽድቅ ፡ ሕገ ወምጽዋተ በልሳና ትለብስ ፡ ፍናዊሃ ፍናወ
ሕይወት ፡ ወኵሉ አሠራ በሰላም ።
፲፰ ዕፀ ሕይወት ይእቲ ለኵሎሙ እለ ይትመረጐዝዋ ወለ
እለ ይትአመኑ ባቲ ዘበእግዚአብሔር ዕኑዕ ።

የቀኑ ሰዎች በዓለም ይኖሩባታልና ፡ ደጋግ ሰዎች በዷ ይኖራሉና ። ምሳ፡ ፲ ፴ ።
እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሥራ ከምድር ይጠፉሉ ፡ በደለኞች የሚሆኑ ከርሷ ወጥተው ይሄዳሉ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ልጄ ! ሕጌን አትዘንጋ ፡ ልቡናህም ቃሌን ይጠብቅ ።
ይህን ያደረግህ እንደሆነ ፡ የደስታና የሕይወት ዘመኖች ይጨመሩልሃል ። ምሳ፡ ፫ ፲፮ ።
ምጽዋት (ምግባር) ሃይማኖት ፡ አይራቅህ ፡ በክሳድ ልቡናህ አጽንተህ ያዘው በልቡናህ ሰሌዳነትም ጻፈው ።
በለሟልነትም ታገኛለህ ፡ በሰውና በእግዚአብሔርም ፊት በጎ ነገርን አስብ ። ፩ ሳሙ ፪ ፳፮ ።
በፍጹም ልቡናህ በእግዚአብሔር አምነህ ኑር ፡ በጥበብህ አትታበይ ። ኤር፡ ፱ ፳፫ ።
ሥራሕን ታቀናልህ ዘንድ በሥራህ ሁሉ አክብራት ።
እግዚአብሔርን ፍራው ፡ ከክፉ ሥራም ራቅ እንጂ ፡ ከራስህ በነቃሽው ጥበብ ብልህ ነኝ አትበል ።
ያን ጊዜ ለአንተ ድኅነት ይሆንልሀል ፡ ለልጆችህም ድኅነት ይሆንላቸዋል ። ኢዮ፡ ፳፩ ፳፬ ።
ወጥተህ ወርደህ ካገኘኸው ገንዘብህ ሰጥተህ እግዚአብሔርን አክብረው ፡ ያዝመራህንም መጀመርያ ከእውነተኛ ገንዘብህ አግባለት
ጎተሮችህ ብዙ ሥንዴን ይመሉ ዘንድ ፈቀኖችህም ወይንን ይመሉ ዘንድ አግባ ።
ልጄ ! የእግዚአብሔርን ተግሣፅ ቸል አትበል ፡ መከራ በማምጣቱም ከሱ ዘንድ ንስሓ መግባትን አትድከም ።
አባት የሚወደውን ልጅ እንዲቀጣ ፡ እግዚአብሔርም የሚወደውን ይቀጣልና ፡ ትእዛዙን የማይቀበሉ ልጆቹን እንዲገርፍ እግዚአብሔርም በመከራ ይገርፋልና ፡ አትድከም ። ዘዳ፡ ፰ ፭ ። ዕብ፡ ፲፪ ፭ ።
ጥበብን የሚያገኛት ሰው ንኡድ ክቡር ነው ፡ ኃፊረ ገጽንም የሚያውቅ ሰው ሕያው ነው (በነፍስ) ።
ብርና ወርቅን መናገሻ ከማድረግ ይልቅ ጥበብን መናገሻ ማድረግ ይሻላል ፡ ከብዙ ድልብም ይሻላል ።
ዋጋው ብዙ ከሆነ ከዕንቍም የከበረች ናት ፡ ክፉ ነገርም ምንም አይቃወማትም ።
ለሚቀርቧት ሰዎች ሁሉ መልካም አገር ናት ፡ ክብርም ሁሉ መጠኗ አይደለም ፡ በቀኟም የሕይወት ዘመንና የዘመን ብዛት አለ ፡ (በነፍስ የሚገኘው) ። ምሳ፡ ፫ ፪ ።
በግራዋም ብዕልና ክብር አለ ፡ (በሥጋ የሚገኘው) ከአፏም እውነት ነገር ይወጣል ፡ በአንደበቷ ምግባረ ሃይማኖትን ታስተምራለች ፡ ሥራዎቿም የሕይወት ሥራ ናቸው ፡ ሥራዋም ሁሉ በተድላ በደስታ ፀንቶ የሚኖር ነው ። (ኢታምልክ) ። ማቴ፡ ፲፩ ፳፱ ።
ለሚመረኰዟት ሰዎችም ሁሉ የሕይወት ዛፍ ናት ፡ ያመኑባትም ሰዎች በፅኑ በእግዚአብሔር እንዳመኑ ሰዎች ናቸው ። ዘፍ፡ ፪ ፱ ።

| | | |
|---|---|---|
| እግዚአብሔር በጥበብ ሣረራ ለምድር፡ ወአስተዳለወ ሰማያተ\በአእምሮ ። | ፲፱ | እግዚአብሔር በባሕርይ ጥበቡ ምድርን ፈጠራት፡ በባሕርይ ዕውቀትም ሰማያትን አዘጋጀ ። |
| ወበተንውቆቱ ቀላያት ነቅዑ፡ ወደመናትኒ ያውኅዙ ጠላተ ። | ፳ | በባሕርይ ዕውቀቱ ወንዞች መነጩ፤ ደመናዎችም ጠልን ያስገኛሉ ። ዘፍ፡ ፩ ፱ ። ኢዮ፡ ፴፯ ፳፰ ። |
| ወልድየ፡ ኢትትሀከይ ዕቀብ ምክርየ ወሕሊናየ ከመ ትሕየው ነፍስከ ። | ፳፩ | ልጄ! ቃል አትበል፡ ሰውነትህ በሕይወት ትኖር ዘንድ አስቤ የነገርኩህን ምክሬን አስተውል ። |
| ወጥገሰ ይከውነከ ውስተ ክሳድከ፡ ወይከውን ፈውሰ ለሥጋከ ወሥራየ ለአዕፅምቲከ፡ ከመ ትሑር ጥቡዐ በሰላም በኵሉ ፍናዊከ ። | ፳፪ | ለሰውነትህ ባለሟልነትን ይሆንልሃል፡ ለሥጋህም ድኅነት ይሆናሃል፡ በሥራው ሁሉ በተድላ በደስታ የፀናህ ትሆን ዘንድ፡ ለነፍስህም ሕይወት ይሆናሃል ። |
| ወእገሪከ ኢይትዓቀፉ፡ እመሂ ትነብር ኢትፍራህ ። | ፳፫ | እግሮችህም አይሰነከሉም፤ ብትቀመጥም አትፈራም። |
| ወእመኒ ሰከብከ ሐዋዘ ትነውም፡ ወኢተፈርህ ዘይመጽእ ሀከክ፡ ወመራደ ረሲዓን ዘይመጽእ ። | ፳፬ | ብትተኛም የጤና እንቅልፍ ትተኛለህ፡ የሚመጣብህንም ጠብ ክርክር አትፈራም፡ የሚመጣብህንም የአሕዛብ ወራሪነት አትፈራም ። መዝ፡ ፺፩ ፭ ። |
| እስመ እግዚአብሔር ይሄሉ ምስሌከ ውስተ ኵሉ ፍናዊከ፡ ወያቀውሞን ለእገሪከ ከመ ኢያንቀልቅላ ። | ፳፭ | በሥራው ሁሉ እግዚአብሔር ከንተ ጋራ ይኖራልና፡ እንዳይነቀወጡም እግሮችህን ያፀናቸዋል ። |
| ወኢትትሀከይ ገቢረ ሠናይ ለዐኑስ፡ ሶበ ቦ ውስተ እዴከ ርድእ ። | ፳፮ | ለተቸገረው በጎ ነገር ማድረግን ቃል አትበል፡ በእጅህ ያለውንም ገንዘብ ሰጥተህ ርዳው ። ገላ፡ ፮ ፲ ። |
| ወኢትበል ሑር ወገባእ ጌሠመ እሁበከ እንዘ ትክል ገቢረ ሠናይ፡ እስመ ኢተአምር ዘትወልድ ሳኒታ ። | ፳፯ | ማግስት የምትወልደውን አታውቅምና ገንዘብ መስጠቱ ሲቻልህ ዛሬ ተመልሰህ ሂድ፡ ነገ እሰጥሀለሁ አትበለው። |
| ወኒ ኢተሐሊ እኩየ ላዕለ ዓርክከ ዘየኃድር ወይትዌከል ብከ፡ ወኢትፍቅድ ተጻልኦ ምስለ ሰብእ በከ፡ እመ አልቦ ዘይገብር እኩየ ላዕሌከ ። | ፳፰ | ዳግመኛም አንተን አምኖ በሚኖር ወዳጅህ ላይ ክፉ ነገር አታስብ፡ በአንተ ላይ ያደረገው ክፉ ነገር የሌለምና ከሰው ጋራ በከንቱ መጣላትን አትውደድ ። |
| ኢታጥፊ ዝንጓጔ በኀበ ሰብእ እኩያን፡ ከመ ኢትኩን ከማሆሙ ። | ፳፱ | እንደሰቸው እንዳትሆን፡ ከክፉ ሰዎች ሽሙጥን አትማር ። ሮሜ፡ ፲፪ ፲፰ ። |
| ወኢትቅናእ በፍናዊሆሙ እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ኵሉ ኃጥእ ወምስለ ጻድቃን ኢይዴመር ። | ፴ | ኃጢአተኛ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነውና፡ ከደጋጎችም ሰዎች ጋራ አንድ አይሆንምና፡ በሥራቸውም አትቅና ። መዝ፡ ፴፯ ፩ ። |
| መርገመ እግዚአብሔር ውስተ አብያተ ረሲዓን ። | ፴፩ | የእግዚአብሔር ርግማን ሕገ እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች ቤት ፀንቶ ይኖራል ። ምሳ፡ ፪ ፲፭ ። |
| ወውስተ አብያተ ጻድቃን በረከተ እግዚአብሔር፡ ወለዕቡያን ይትቃወሞሙ ንዴት ። | ፴፪ | የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ወገኖች ፀንቶ ይኖ ራል፡ ትዕቢተኞችን ግን ችጋር ይቃወማቸዋል ። |
| ወለትሑታን ይሁቦሙ ክብረ፡ ወክብረ ይወርሱ ጠቢባን ። | ፴፫ | ራሳቸውን ለሚያዋርዱ ሰዎች ክብርን ይሰጣቸዋል፡ ብልህ የሆኑ ሰዎችም ክብርን ይወርሳሉ ። |
| ወረሲዓንሰ አዕበዩ ኃሣረ ። | ፴፬ | ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ችጋርን አበዙ። |
| ምዕራፍ ፬ ። | | ምዕራፍ ፬ ። |
| ስምዑ ውሉድየ ተግሣፀ አብ፡ ከመ ይኩን ብዙኀ መዋዕለ ሕይወትክሙ ። | ፩ | በሕይወት የምትኖሩት ዘመናችሁ ብዙ ይሆን ዘንድ፡ ልጆቼ! የአባታችሁን ተግሣፅ ስሙ ። ምሳ፡ ፭ ፯ |
| ወአጽምኡ በአእምሮ ሕሊና እስመ ሠናየ ጸጋ እጼግወክሙ፡ ወሕገገ ዚአየ ኢትኅድጉ ። | ፪ | በጎ ስጦታን እሰጣችኋለሁና፡ በልቡና ዕውቀት ፀንታችሁ ስሙ፡ ሕጌንም አትተዉ ። |
| እስመ ከንኩ አነሂ ወልደ ሰማዔ አብ ወአትፈቀር በገጸ እምየ ። | ፫ | እኔም አባቴን የምሰማ ልጅ ነበርኩና፡ በእናቴም ፊት የምወደድ ልጅ ነበርኩና ። ፩ ዜና፡ ፳፱ ፩ ። |
| እንዘ ይሜህሩኒ ወይብሉኒ ይበአ ቃለ ዚአነ ውስተ ልብከ፡ ዕቀብ ትእዛዛቲነ ። | ፬ | ሲያስተምሩኝ ነገሩችን በልብህ ይደር ትእዛዛችንም ጠብቅ ሲሉኝ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፳፰ ፱ ። ምሳ፡ ፯ ፪ ። |
| ወኢትርሳዕ ወኢትትሀየይ ንባበ አፉነ ወኢትኅድጋ ። | ፭ | በአፋችን የምንናገረውን ነገር አትርሳ፡ ቃልም አትበል አትተዋት ። ምሳ፡ ፪ ፪—፫ ። |
| ወአጥሬ አእምሮ፡ ወትትዌከፈከ አፍቅራ ። | ፮ | ዕውቀትን ገንዘብ አድርግ፡ በረድኤት ትቀበልሀለች ውደዳት ። ፪ ተሰሎ፡ ፪ ፲ ። |
| ወተዓቀበከ ውዳ ወታሌዕለከ ። | ፯ | ትጠብቅሃለች ሽት፡ ከፍ ከፍ ታደርግሃለች ። |

፰ ስማዕ ወልድየ ወተወከፍ ንባበ ዚአየ፡ ከመ ይብ
ዝኀ ዓመታተ ሕይወትከ ወከመ ይኩን ፍናወ ሕይወ
ትከ ብዙኀ ።
፱ እስመ ፍኖተ ጥበብ እሜህረከ ወአፀንዓከ ዲበ መን
ኩራኵር ርቱዕ ።
፲ እመሂ ተሐውር ኢይትዐፀው አሠርከ፡ ወእመሂ ሮፅከ
ኢትደክም፡ ወተወከፎ ቃለ ዚአየ ኢትኅድግ ።
፲፩ ዕቀበ ለርእስከ ወኢትኅድጋ ለሕይወትከ ።

፲፪ ፍኖተ ረሲዓን ኢትኪድ፡ ወኢትቅናእ በፍናወ ኃጥ
አን ፡ ወመከነ እንተ ኀበ ግእዙ ኢትሑር ህየ ተገኀሥ
እምኔሆሙ ወተመየጥ ።

፲፫ እስመ ኢይነውሙ እመ ኢገብሩ እኩየ፡ ተመሥጠ
ንዋም እምአዕይንቲሆሙ ።
፲፬ ወኢይነውሙ እመ ኢደወዩ እለ ይበልዑ መብልዐ
ኃጢአት፡ ወበወይነ ዓመፃ ይሰክሩ ።
፲፭ ወፍኖተ ጻድቃንሰ ከመ ብርሃን ይበርህ የሐውሩ ወያ
በርሁ እስከ ሰበ ታረትዕ ዕለት ።

፲፮ ወፍኖተ ኃጥንሰ ጽልመት ወኢየአምሩ ከመ ይት
ዓቀፉ ።
፲፯ ወልድየ፡ ንባበ ዚአየ ነዕር፡ ወቃለ ዚአየ ያጽምእ ዕዝ
ንከ ከመ ኢይንጽፉ ዓዘቃቲከ ።
፲፰ ዕቀበን ውስተ ልብከ እስመ ሕይወት ውእቶን ለእለ
ይረክብዎን፡ ወለኵሉ ዘሥጋ ።
፲፱ ወበኵሉ ተዓቅበ ዕቀብ ልበከ እምዝንቱ ፍኖት፡
እስመ ውእቱ ነቅዐ ሕይወት ።
፳ ወአርኅቅ እምኔከ አፈ እኩየ ወከናፍረ ዓመፃ አንኀ
አርኅቆ እምኔከ ።
፳፩ አዕይንቲከኒ ርቱዐ ይርአያ፡ ወቀራንብቲከ ይቅጽበ ጽ
ድቀ ።
፳፪ ርቱዐ መንኩራኵረ ግበር ለእገሪከ ወፍናዊከ አርትዕ ።

፳፫ ወኢትትገኀሥ ኢ ለየማን ወኢ ለጸጋም፡ አግኅሥ
እገሪከ እምፍኖት እኪት፡ እስመ ፍናወ ዘየማን ያፈቅር
እግዚአብሔር ።
፳፬ ጠዋያት እማንቱ እለ በጸጋም ፡ ወውእቱ ርቱዐ መን
ኩራኵረ ይገብር ለእገሪከ፡ ወሑረትከኒ በሰላም ያሜኒ ።

ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወልድየ፡ ጥበበ ዚአየ ነጽር ወንባበ ዚአየ ያጽምእ
ዕዝንከ ከመ ትዕቀብከ በሕሊና ሠናይት ።
፪ ወአእምሮ እምከናፍርየ ዘእኤዝዘከ ።
፫ ኢትነዐር ብእሲተ እኪተ እስመ መዓር ይውኅዝ እም
ከናፍረ ብእሲት ዘማ እንተ ለጊዜሁ ያመዓርዕር ለጉርዔከ ።
፬ ወእምድኅሬሁሰ ዘይመርር እምሐሞት ትረክብ፡ ወስ
ሑል ፈድፋደ እመጥባሕት ዘክልኤ አፉሁ ።

ልጄ ! በሕይወት የምትኖርባቸው ዘመኖችህ ይበዙ
ልህ ዘንድ የዘመንህም ቍጥር ብዙ ይሆን ዘንድ የምመክ
ርህን ስማ፡ ነገሬንም ተቀበል ።
የጥበብን ሥራ አስተምርኻለሁና፡ በቀና ሥራ ላይም
አፀናኻለሁና ። ፩ኛ ሳሙ፡ ፲፪ ፳፫ ።
ብትሄድም ፍለጋህ አይጠፋም፡ ብትሮጥም አትደክ
ምም የኔንም ነገር መቀበል አትተው ። ፪ኛ ሳሙ፡ ፳፪ ፴፯።
ለራስህ ብለህ ሕግን ጠብቃት፡ ሕይወትም ልትሆንህ
አትተዋት ።
እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች መንገድ አትሂድ፡ በኃ
ጢአተኞችም ሥራ አትቅና፡ ወደዚያ ወደ ተጓዙበትም
ቦታ አትሂድ፡ ከነሱም ሥራ ተመልሰህ ራቅ፡ እነዚያንም
ከመከተል ተመለስ ።
ኃጢአት ካልሠሩ አይተኙምና ከዓይናቸውም እን
ቅልፍ ጠፋ ።
የኃጢአትን መብል የሚበሉ በዓመፅ ወይንም የሚሰ
ከሩ እነዚህ በደዌ ኃጢአት ካልተያዙ አይተኙም ።
የጻድቃን ሥራቸው እንደ ብርሃን ይበራል፡ ዕለተ
ሞታቸው ከብራቸውን እስከትገልጥላቸው ድረስ በዚህ
ዓለም ሲያበሩ ይኖራሉ ።
የኃጥአን መንገድ ግን ጨለማ ነው፡ በመከራም እን
ዲሰነካከሉ አያውቁም ።
ልጄ ! የኔን ነገር ተመልከት ወንዞችህም እንዳይደርቁ
ጆሮህ ነገሬን ያድምጥ ። ፩ኛ ሳሙ፡ ፪ ፱ ።
በግብር ለሚያገኙዋቸው ሕይወት ናቸውና፡ ለሥጋዊ
ለደማዊም ሁሉ ድኅነት ናቸውና በልቡናህ ጠብቃቸው ።
ከዚህ ሥራ በፍጹም መጠበቅ ልቡናህን ጠብቅ እሱ
የሕይወት ምንጭ ነውና ። ምሳ፡ ፫ ፳፩ ።
ክፉ ነገርን ከአንተ አርቅ፡ የሐሰት ከንፈሮችንም ከአ
ንተ ፈጽመህ አርቅ ።
ዓይኖችህም የቀና ሥራን ይመልከቱ ቅንድቦችህም እው
ነት ነገርን ይጥቀሱ (ቀራንብተ ልቡናህ በጎ ነገርን ያስቡ)።
ለእግረ ልቡናህ የቀና ሥራን አድርግ፡ ጐዳናህንም
አቅና ። ማቴ፡ ፲፪ ፴፱ ። መዝ፡ ፳፰ ፳ ።
ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፡ እግረ ልቡናህን ከክፉ
ሥራ አርቅ፡ እግዚአብሔር የቀኙን መንገድ ይወዳልና ።

በግራ የሚሠሩ ሥራዎች ጠማሞች ናቸው እሱ ለእ
ግረ ልቡናህ የቀና ሥራን ያደርግልኻል፡ አነዋወርህንም
በተድላ በደስታ የበጀ ያደርግልኻል ።

ምዕራፍ ፭ ።

ልጄ ! የኔን ጥበብ ተመልከት፡ በበጎ ዕውቀት ትጠብ
ቅህ ዘንድ ጆሮህም የኔን ነገር ይስማ ።
በከንፈሬ የማዝህንም አስተውል ።
ከአመንዝራ ሴት ከንፈር ለጊዜው ጕሮሮህን የሚያጣፍ
ጠው ማር ወለላ ይፈሳልና፡ አመንዝራ ሴትን አትመልከት።
ከዚህ በኋላ ግን ከሐሞት የሚመር ልሳኑ ሁለት ከሆነ
ሾተል የተሳለ ነገር ታገኛለህ ። መክ፡ ፯ ፳፮ ።

፭ ወኀበ ዕበድ እገሪሃ ያወርዱ፣ ወሑረታ ያበውእ ውስተ ሞት ወሲኦል ።

፮ ወአሠረ ኢይትሐወስ እመከነ ኃጢአት፣ ወውስተ ፍናወ ሕይወት ኢይቀርብ ወእቡስ መንኰራኵራ፣ ወአከ ዘይትዐወቅ ።

፯ ወይእዜኒ ወልድየ ስምዐኒ ወምኑነ ኢትረሲ ነባበ ዚአየ።

፰ ርኁቀ ረሲ እምኔሃ ፍኖተከ፣ ወኢትቅረብ ኀበ ኆኅተ ቤታ ።

፱ ከመ ኢትወስከ ለባዕድ ሕይወተከ ወንብረተከ ለእለ ዘእንበለ ምሕረት ።

፲ ከመ ኢይጽገቡ ነኪራን ኃይለከ ወፃማ ዚአከ ቤተ ባዕድ ኢይባእ ።

፲፩ ወትኔስሕ ድኅረ አመ ደክመ ሥጋ ነፍስከ ።

፲፪ ወትብል እፎ ጸላእኩ ትምህርተ እምንእስየ ወእምተግሣፅ ተግኅሠ ዕዝንየ ።

፲፫ ወኢሰማዕኩ ቃለ ዘይሜህሩኒ ወይጌሥፁኒ፣ ወኢያፅማእኩ በእዝንየ ።

፲፬ ዘእንበለ ንስቲት ኮንኩ ውስተ ኵሉ እኩይ ።

፲፭ ማእከለ ማኅበር ወእንግልጋ ስተይ ማየ እምቀሱትከ፣ ወእምነቅዐ ዐዘቅትከ ወየኀዛ ማያት እምዐዘቅትከ ወውስተ መራኅብቲከ ይሑሩ ማያቲከ ።

፲፮ ወትኩን ለከ ለባሕቲትከ ወአልቦ ነኪር ዘይነሥእከ ወዓዘቅተ ማይከ ትኩን ለከ ።

፲፯ ወተፈሣሕ ምስለ ብእሲተ ንእስከ ።

፲፰ በፍቅረ ኃየል ወዕዋል ተፋቀር ምስለ ብእሲትከ ።

፲፱ ሞገሰ ፍቅራ ያረውየከ እንቲአከ ትኩንከ ለከ፣ ወተሀሉ ምስሌከ በኵሉ ጊዜ ።

፳ በዛቲ ፍቅር እንዘ ትትፋቀር ብዙኀ ትከውን፣ ወኵልንታከ ኢየሀሉ ኀበ ነኪርት ።

፳፩ ወኢታውትር እዴከ ኀበ እንተ ኢኮነት እንቲአከ ።

፳፪ እስመ ቅድመ አዕይንተ እግዚአብሔር ውእቱ ፍናወ ብእሲ፣ ወውስተ ኵሉ መንኰራኵሪሁ ያስተሐይጽ ።

፳፫ ኃጢአት ያሜግር ብእሴ፣ ወበኀብለ ኃጢአት ኵሉ ይትሐሰል ።

፳፬ ዝንቱ ይመውት ምስለ ዓብዳን፣ ወእምብዝኀ ዕበዱ ተገድፈ ሕይወቱ ወተኀጕለ በእንተ ዕበዱ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወልድየ እመ ተኀበይከ ለዓርክከ ትሁብ እዴከ ለእድው ።

፪ መሥገርት ጽኑዕ ውስተ ከናፍሪሁ ለብእሲ ወይትኃጕል በከናፍረ አፉሁ ።

፫ ግበር ወልድየ ዘአነ እኤዝዘከ ውኄረ ዓል፣ እስመ እመ መጻእከ ውስተ እደው እኩያን በእንተ ዓርክከ ኰን ኢተሀኬ፣ ወመሀኮ ለዓርክከ ዘተሀበይከ ።

እግሮቿም ወደ ስንፍና ያወርዳሉ፣ መንገዷም ወደ መቃብርና ወደ ሞት ያደርሳል ። ምሳ፡ ፯ ፳፯ ።

ፍለጋዋም ከኃጢአት ሥራ አይርቅም፣ ወደ ሕይወት ሥራዎችም አይቀርብም ሥራዋም ጕጸጕጽ ነው፣ በደግነት የሚታወቅ አይደለም ።

አሁንም ልጄ ስማኝ! የኔም ነገር የተናቀ አታድርግ።

ሥራሕንም ከሷ የራቀ አድርግ፣ ወደ ቤቷ ደጃፍም አትቅረብ ። ምሳ፡ ፬ ፩ ፤ ፯ ፳፬ ።

ከብትህን ለባዕድ እንዳትሰጥ ርኅራኄ ለሌላቸው ዳኞችም ንብረትህን እንዳትሰጥ ።

ልዩ የሆኑ ዳኞች ብዕልህን እንዳይጠግቡት የፃርክበትም ገንዘብህ ወደ በዕድ ቤት እንዳይገባ ።

ሰውነትህ በደከመ ጊዜ ኋላ ትፀፀታለህ ።

ከሕፃንነቴ ጀምሬ ትምህርትን ለምን ጠላሁ ፤ ከምክር አዝናትስ ጆሮዬ ለምን ራቀ ። ምሳ፡ ፲፪ ፩ ።

የሚያስተምሩኝን የሚቈጡኝን ሰዎች ነገር በጆሮዬ ለምን አልሰማሁ ፤ ትላለህ ።

ከአንዲት (ከኢትዜሙ) በስተቀር ሳላፍር ሁሉን በማፍረስ ተያዝኩ ትላለህ ። መዝ፡ ፺፬ ፲፯ ።

በሸንጎና በብዙ ሰው መካከል ከጕድጓድህ ምንጭና ከጋንህ ውኃን ጠጣ፣ ከጕድጓድህም ውኆች ይፍሰሱ ።

ሚስትህ ላንተ ብቻ ትሁንህ፣ የሚወስድብህም በዕድ ሰው አይኑር ልጅ የወለደችልህ ሚስት ላንተ ብቻ ትሁን።

በሕፃንነትህ ካገባኻት ሚስትህ ጋራ ደስ ይበልህ ።

ከሕፃንነት ሚስትህ ጋራ በውርንጫና በዋልያ ፍቅር ተፋቀር ።

የፍቅሯ መወደድ ደስ ያሰኝኻልና ላንተ ትሁንህ በየጊዜው ካንተ ጋራ ትኑር ። መኃ፡ ፪ ፯ ፤ ፫ ፭ ።

በዚህች ፍቅር ፀንተህ ስትጫወት ብዙ ትሆናለህ (ትወልዳለህ) ሁለንትናህም ከጋለሞታ ዘንድ አይኑር ።

ያንተ ወደ አልሆነች እጅህን አራምደህ አትቈንጥጥ።

የሰው ሥራው በእግዚአብሔር ፊት ነውና ወደ ሥራውም ሁሉ ይመለከከታልና ። መዝ፡ ፯ ፲፭ ።

ኃጢአት ሰውን ያስነክከላል፣ ሁሉም በኃጢአት ልብብ ይለበበል (በኃጢአት ፍዳ ይያዛል) ።

ይህ እንዲህ ያለው ሰው ከአላዋቂዎች ጋር ይሞታል ከስንፍናውም ብዛት የተነሣ ሕይወቱ ጠፋ (ስለ ስንፍናውም ጠፋ ይባላል) ።

## ምዕራፍ ፮ ።

ልጄ! ለባልንጀራህ ብትዋሰው፣ እጅህን ለጃኛ ትሰጣለህ ።

በሰው ከንፈር ጽኑ ወጥመድ አለ፣ (እዋሰለሁ ማለት) በአፉ በተናገረውም ነገር ይጠፋል (እዋስ በማለቱ) ።

ልጄ! እኔ የማዝህን አድርግ (አትዋስ) በጎም ዋል ወደ ክፉዎች ዳኞች ከመጣህ እጅህን ትሰጣለህና፣ ስለ ወዳጅህ ሀኬተኛ አትሁን፣ የተዋስከው ወዳጅህንም ወትውተው ።

፬ ወኢተሀበን ንዋመ ለአዕይንቲከ፡ ወኢ ድቃሰ ለቀራንብቲከ ።

፭ ከመ ትድኃን ከመ ወይጠል እመሥገርት፡ ወከመ ዖፍ እመጽፈርት ።

፮ ተመየጥ ኀበ ቃሕም አ ሀካይ፡ ወኢትኩን ሀካየ፡ ወቅናእ ርእየከ ፍናዊሁ ወኩን ጠቢበ እምኔሁ ።

፯ ወውእቱ እንዘ ወፍር አልቦ ወዘሂ አልቦ ዘያጌብሮ፡ ወእንዘ እግዚእ አልቦ፡ ያስተጋብእ በሐጋይ ሲሳዮ ብዙኀ እመ ማእረር፡ ወይትጌበር ዘያነብር ።

፰ አው ሑር ኀበ ንኅብ ወአእምር ከመ መስተገብርት ይእቲ ወትግብርታሂ ከመ ሠናየ ትገብር እንተ ፃማሃ ነገሥት ዓብዳን ይነሥኡ ለሕይወት እንተ ትትፈቀድ ይእቲ በኀበ ኵሉ ወክብርት ይእቲ ወበኃይል ጽብስት ወበግብራሰ ጽንዕት ።

፱ ጥበበ አክቢራ አስተርአየት፡ እስከ ማእዜኑ ሀካይ ትሰክብ፡ ወማእዜ እምንዋምከ ትነቅሕ ።

፲ ሕቀ ትነውም፡ ወሕቀ ትነብር፡ ሕቀ ትዴቅስ፡ ወሕቀ ታስተጋብእ እዴከ ዲበ እንግድዓከ ።

፲፩ ወእምዝ ይመጽአከ ግብተ ከመ እኩይ ሐዋርያ ንዴት ወተፅናስ ከመ ኄር ረዋጺ ።

፲፪ ወእመሰ ኢኮንከ ሀካየ፡ ይመጽአከ ከመ ነቅዐ ማእረርከ፡ ወንዴትሰ ከመ እኩይ ረዋጺ ለሊሁ ይርኅቅ እምኔከ ።

፲፫ ብእሲ ዓብድ ወዓማፂ የሐውር ፍናወ ዘኢኮና ኄራተ ወውእቱ ይቀጽብ በዓይን፡ ወያኤምር በእግር፡ ወያኤምር በቅጽበተ አፃብዕ ።

፲፬ ወዕሉት ልብ ትሔሊ እኩየ በኵሉ ጊዜ ዘከመዝ ያመጽእ ሀከከ ላዕለ ሀገር ።

፲፭ በእንቲአሁ ይመጽእ ግብተ ሕጕለት ወዝብጠት፡ ወቅጥቃጤ ዘኢየሐዩ ።

፲፮ እስመ ይትፌሣሕ በኵሉ ዘይጸልእ እግዚአብሔር፡ ወይትቀጠቀጥ በእንተ ርኵሰ ነፍሱ ።

፲፯ ናሁ ስሱ ዘይጸልእ እግዚአብሔር፡ ወሳብዖምሰ ሰቆራረ ነፍሱ ።

፲፰ ዓይነ ጸአሌ፡ ወልሳነ ዓማፄ፡ ወእደ ዘይከዑ ደመ ጻድቅ ።

፲፱ ወልበ እንተ ትወልድ እኩየ ሕሊና፡ ወእእጋረ እለ ይትወላወሉ ለገቢረ እኩይ ።

፳ ወዘያነድድ ስምዐ ዓማፂ ወይፌኑ ጋእዘ ማእከለ አኀው ።

፳፩ ዕቀብ ወልድየ ሕገገ አቡከ፡ ወኢትትኀየይ ትእዛዘ እምከ ።

፳፪ ደዮ ውስተ ልብከ በኵሉ ጊዜ፡ ወጠብልሎ ውስተ ክሳድከ ።

፳፫ ወሶበኒ ተሐውር ንሥኦ ምስሌከ ወየሀሉ፡ ወሶበኒ ትነውም የዓቅበከ፡ ወሶበኒ ትትነሣእ ይትናገረከ ።

፳፬ እስመ ማኅቶት ትእዛዝ፡ ወሕግ፡ ብርሃን ወፍኖተ ሕይወት፡ ተግሣፅ ወትምህርት ።

ለዓይኖችህ እንቅልፍን አትስጣቸው፡ ለቅንድቦችህም ሽልብታን አትስጣቸው ። መዝ፡ ፻፴፪ ፬ ።

ፈቶ ከዕንጨት ወጥመድ ወፍም ከጭራ ወጥመድ እንድታመልጥ ወዳጅህን አውከው ።

አንተ ሀኬተኛው ወደ ጕንዳን ተመለስ፡ ሥራውንም አይተህ ቅና ከሱ አብነት ነሥተህ ብልህ አዋቂ ሁን ።

እሱ ስንኳ የሚሠማራበት መሠማርያ ሳይኖረው ግድ የሚያዘውም ሳይኖር፡ ጌታም ሳይኖረው፡ የሚያኖረውን ብዙ ምግቡን ጥሮ ግሮ በመከር ጊዜ ይሰበስባል ።

ወይም ወደ ንብም ሂድ ፃሬ ጋሬ እንደሆነች በሥራዋም በጎ ሥራ እንድትሠራ ዕወቅ፡ የደከመችበት ማሯንም አላዋቂዎች ነገሥታት ሕይወት ሊሆናቸው ይወስዱታል በሁሉ ዘንድ የምትወደድ ናት፡ የከበረችም ናት፡ በኃይሏ ደካማ ናት፡ በሥራዋ ግን የፀናች ናት ።

ጥበብን አክብራ አሳየች አንተ ሀኬተኛው እስከ መቼ ድረስ ትተኛለህ፤ ከእንቅልፍህስ መቼ ትነቃለህ ።

አንድ ጊዜ ትተኛለህ አንድ ጊዜ ትቀመጣለህ አንድ ጊዜም ታንጐላቻለህ አንድ ጊዜ እጅህን ሰብስበህ ከብብትህ አግብተህ ትቀመጣለህ ።

ከዚህ በኋላ ችጋር እንደ ክፉ ቀላጤ ድንገት ይመጣብኻል፡ ጦም አደርም እንደ በጎ ቀላጤ ይደርስብኻል ።

ሀኬተኛ ባትሆን ግን በለጸግነትህ እንደ ምንጭ ይመጣልኻል ችጋርም እንደ ክፉ ቀላጤ ከአንተ ይርቃል ።

አላዋቂና በደለኛ ሰው በጎ ባልሆኑ ሥራዎች ፀንቶ ይኖራል፡ እርሱ በዓይን ይጠቀሳል በእግሩም ያመለክታል በጣቱም ጠቅሶ ያሳያል ።

ወንጀለኛ ልቡና በየጊዜው ክፉ ነገርን ታስባለች ይህ እንዲህ ያለው ሰው በአገር ላይ ፀብ ክርክርን ያመጣል ።

በሱ ምክንያት ድንገት፡ ጥፋት፡ መቀረዳድም፡ የማይድን ጥፋትም ያመጣል ። ኢሳ፡ ፴ ፲፫ ። ኤር፡ ፲፱ ፲፩ ።

እግዚአብሔር በሚጠላው ሥራ ሁሉ ደስ ይለዋልና ስለ ሰውነቱ ኃጢአት ይጠፋል ።

እነሆ እግዚአብሔር የሚጠላቸው ሥራዎች ስድስት ናቸው፡ ሰባተኛው ግን ልቡናውን የሚያስጸይፈው ነው።

ሐሰተኛ አንደበትንና ትዕቢተኛ ዓይንን፡ የደግ ሰው ደምን የሚያፈስ እጅን ይጠላል ።

ክፉ ሐሳብን የምታስብ ልቡናን ይጠላል ክፉ ነገር ለማድረግ ወድያና ወዲህ የሚሉ እግሮችንም ይጠላል ።

ሰውን የሚያጠፋ ሐሰተኛ ምክርን አምጥቶ በወንድሞቹ መከከል ጠብ የሚያመጣውን ይጠላል ።

ልጄ! የአባትህን ሥርዓት ጠብቅ፡ የእናትህንም ትእዛዝ ቸል አትበል ። ምሳ፡ ፩ ፰ ።

በየጊዜው በልቡናህ አኑረው በአንገትህም ጠምጥመህ ያዘው ።

በሄድከም ጊዜ ይዘኸው ሂድ ከአንተ ጋራ ይኑር በተኛህም ጊዜ ይጠብቅኻል በተነሣህም ጊዜ ያነጋግርኻል ።

በሐልዮ የሚሠራ ሥራ የፋና ብርሃን ነውና በገቢር የሚሠራው ሥራ የፀሐይ ብርሃን ነውና ተግሣፅና ትምህርትም የሕይወት ጐዳና ነውና ።

| | | |
|---|---|---|
| ወልድየ ዕቀብ ትእዛዝየ፡ ከመ ትዕቀብከ እምብእሲተ ብእሲ፡ ወእምውዴተ ልሳን እኩይ። | ፳፭ | ከጐልማሳ ሚስት ትጠብቅህ ዘንድ ክፉ የሚሆን የነገረ ሠሪ አንደበት ከሚያመጣው ጠብ ትጠብቅህ ዘንድ። |
| ኢይማዕከ ሥነ ፍትወታ፡ ወኢትሠገር በአዕይንቲሃ ወኢትትመሠጥ በቀራንብቲሃ። | ፳፮ | መወደድ ያለው ደም ግባቷ ድል አይንሣህ፡ በዓይኗ ብትጠቅስህ በቅንድቧም ብትጠቅስህ ወደ እሷ አትሳብ። |
| ፍቅራ ለዘማ እስከ አሐቲ ኅብስት፡ ወብእሲትሰ ለእደው ክቡራን ታኀጕል ነፍሶሙ ወታሜግር። | ፳፯ | የዘማ ፍቅሯ አንዲት እንጀራ እስከ ማሳጣት ድረስ ነው፡ እንዲህ ያለቺቱ ሴት የከበሩትን ሰዎች ሰውነት ታጠፋለች። |
| መኑ ዘየዓቍር እሳተ ውስተ ኅፅኑ ወአልባሲሁ ኢይውዕያ። | ፳፰ | በልብሱ እሳት የሚቋጥር፡ ልብሶቹ የማይቃጠሉበት ማን ነው፤ |
| ወመኑ ዘየሐውር ዲበ አፍሐመ እሳት፡ ወእገሪሁ ኢይውዕያ። | ፳፱ | በእሳት ፍሕም ላይ የሚሄድ፡ እግሮቹ የማይቃጠሉ ማን ነው! ኢ.ሳ፡ ፵፫ ፪። |
| ከማሁ ዘይበውእ ቤተ ብእሲተ ብእሲ ኢይነጽሕ፡ ወኵሉ ዘይለክፋ። | ፴ | እንደዚሁ ሁሉ ወደ ጐልማሳ ሚስት ቤት የሚገባ ሰው ከፍዳ አይነጻም፡ የሚቀርበትም ሰው ሁሉ ከዝሙት አይነጻም። |
| አኮ መንክር እመ ተእኅዘ ሰራቂ ዘይሰርቅ፡ እስመ ይሰርቅ ከመ ያጽግብ ነፍሶ ርኅብተ። | ፴፩ | የሚሰርቅ ሌባ ቢያዝ ድንቅ አይደለም፡ የተራበች ሰውነቱን ያጠግብ ዘንድ ይሰርቃልና። ኢ.ዮ፡ ፴፰ ፴፱። |
| ወለእመ ተእኅዘ ይፈዲ ምስብዒተ፡ ወኵሎ ጥሪቶ ይሁብ ከመ ያድኅን ነፍሶ። | ፴፪ | ቢያዝም ሰባት እጅ ይከፍላልና፡ ቢጸናበትም ሰውነቱን ከሞት ያድን ዘንድ ገንዘቡን ሁሉ ይሰጣልና። |
| ወመሐዝስ በንዴተ አእምሮ ኀጕለ ነፍሱ ይትጌበር። | ፴፫ | አመንዝራ ሰው ግን ከዕውቀት በመቸገር ሰውነቱ የሚጠፋበትን ሥራ ይሠራል፡ ምሳ፡ ፯ ፯። |
| ሕማመ ወኀሣረ ይጼውዕ፡ ወጽእለቱ ኢይደመሰስ ለዓለመ ዓለም። | ፴፬ | መከራውን ተዋርዶውን ይጠራል፡ ስድቡም ለዘለዓለም አይጠፋም (አመንዝራ ሲባል ይኖራል)። |
| እስመ ምሉእ ምታ ቅንአተ መዓት፡ ወኢይምሕር በዕለተ ኰነኔ። | ፴፭ | ባሏ ቅንአትን ቍጣን ተመልቷልና፡ ዳኛ በፈረደለት ቀን አይምረውም። ዘሌ፡ ፳ ፲። ምሳ፡ ፳፯ ፬። |
| ወኢይትዌለጥ በምንትኒ ቤዛ ጽልእ፡ ወኢይትዓረቆ በብዙኅ ሀብት። | ፴፮ | የጠቡም ካሣ በምንም በምን አይለወጥለትም በብዙ ገንዘብም አይታረቀውም። |

ምዕራፍ ፯።

ምዕራፍ ፯።

| | | |
|---|---|---|
| ወልድየ፡ ዕቀብ ነገረ ዚአየ፡ ወትእዛዘ ዚአየ ይባእ ኅቤከ። | ፩ | ልጄ! የኔን ነገር ጠብቅ፡ ትእዛዜም በልቡናህ ይደር። |
| ወልድየ፡ አክብር ለእግዚአብሔር ወትጸንዕ እምኵሉ ወዘእንበሌሁሰ ኢትፍራህ ባዕደ፡ እስመ አልቦ ዘይቀትለከ ወአልቦ ዘያሐይወከ። | ፪ | ልጄ! እግዚአብሔርን አክብረው፡ ከሁሉ ይልቅ ትጸናለህ የሚያድንኅና የሚገድልህ የለምና፡ ያለሱ ሌላውን ሰው አትፍራ። |
| ወልድየ፡ ትእዛዘ ዚአየ ዕቀብ ወተሐዮ፡ ወንባበ ዚአየ ዕቀብ ከመ ብንተ ዓይንከ። | ፫ | ልጄ! ትእዛዜን ጠብቅ፡ በሕይወት ትኖራለህ የኔንም ነገር እንደ ዓይንህ ብለኔ አድርገህ ጠብቅ። |
| ደዮ ውስተ አፃብዒከ፡ ወጸሐፎ ውስተ ራኅበ ልብከ። | ፬ | በአጻብዐ ልቡናህ አኑረው፡ በልቡናህ ሰሌዳነትም ጻፈው። ምሳ፡ ፫ ፫። |
| በላ ለጥበብ እኅተ ዚአየ አንቲ ወለአእምሮ ሀገሬተከ ረስያ። | ፭ | ጥበብን እኅቴ በላት (ውደዳት) እውቀትንም አገርህን አድርጋት። |
| ከመ ትዕቀብከ እምብእሲት ነኪርት ወእኪት፡ ወእም ነገረ ዘርቅ አምጽአት ብከ። | ፮ | ከሴሰኛ ከአመንዝራ ሴት ትጠብቅህ ዘንድ ዋዛ ዘበሬታም ብታመጣብህ ትጠብቅህ ዘንድ እምቢ በላት። |
| እስመ እመስኮተ ቤታ ውስተ መራኅብት ትሔውጽ። | ፯ | በቤቷ መስኮት ሁና ወደ አደባባይ ትመለከታለችና። |
| እመበ ዘርእየት እምኅብዳን ውሉድ ወሬዛ ነዳየ አእምሮ ዘየሐውር ውስተ ፍናወ ማዕዘንተ ቤታ፡ (ትጼውዮ ወትብሎ)። | ፰ | ከሰነፎች ልጆች ወገን በቤቷ አጠገብ መንገድ የሚሄድ ከዕውቀት የተቸገረ ጐልማሳ ያየችው ማየት ቢኖርና ብላ ትጠራዋለች። |
| ወይትናገር በጽልመት ሠርከ ሶበ ይከውን ጽማዌ ወጽልመተ ሌሊት። | ፱ | እሱም ጸጥ ባለ የሌሊት ጨለማ በሆነ ጊዜ ማታ እመጣለሁ ብሎ ይናገራል። |
| ወሶቤሃ ትዳደቆ እንተ ባቲ ትርኢተ ዝሙት እንተ ትሬሲ ታሥርር ልበ ወራዙት። | ፲ | ያን ጊዜ የምንዝር ጌጥ ያላት የጐልማሶችን ልቡና ብር ብር የምታደርግ ትገናኘዋለች። |

፲፩ ሥርርት ይእቲ ወምርዕት ወሥርጡት ወበቤታኒ ኢያ ዓርፉ እገሪሃ ።

፲፪ ወምዕረ ኀዳጠ አፍአ ታንጎጉ ወምዕረ ኀዳጠ ውስተ መራኅብት ወውስተ ማዕዘንት ትጸንሕ ።

፲፫ ወአኀዞቶ ወሰዓመቶ ወዘእንበለ ኃፍረት በገጽ ትብሎ ።

፲፬ መሥዋዕተ ሰላምየ ውእቱ ፡ ዮም ብፅዓትየ እሁብ ።

፲፭ በእንተ ዝንቱ መጻእኩ እትቀበልከ ወእንዘ አፈቅር ገጸ ዚአከ ረከብኩከ ።

፲፮ በቀጠንት ገለድኩ ምስካብየ ፡ ወዘርቤታተ ነጸፍኩ ዘእምግብፅ ነስነስኩ ምስካብየ በመጽርይ ወቤትየኒ በቀናንሞስ ፡ ነዓ ናስተሐውዝ በተሳዕሞ እስከ ነግህ ።

፲፯ ወናንገርግር በተፋቅሮ ፡ እስመ ኢሀሉ ምትየ ውስተ ቤቱ ።

፲፰ ወሖረ ርኁቀ ብሔረ ዕቍረ ወርቅ ነሚኦ ውስተ እዴሁ ወመዋዕለ ብዙኀ እመ ገብአ ውስተ ቤቱ ።

፲፱ ወአስሐተቶ በብዙኅ ነገር ፡ ወበመሥገርተ ከናፍሪሃ ሰሐበቶ ።

፳ ወተለዋ ደኪና ከመ ላሕም ዘየሐውር ለተጠብሖ ወከመ ከልብ ለተአስሮ ።

፳፩ ወከመ ኃየል ዘተነድፈ ወተሐይጸ ከብዶ ወይጔጕእ ከመ ዖፍ ለመሥገርት ።

፳፪ ወኢየአምር ከመ በነፍሱ ይረውፅ ።

፳፫ ወይእዜኒ ስምዑኒ ወልድየ ወአጽምእ ቃለ አፉየ ።

፳፬ ወኢይትመየጥ ልብከ ውስተ ፍናዊሃ ፡ ወኢትስሐት ውስተ አሠራ ።

፳፭ ወብዙኃነ አስሐታ አቍሰለት ፡ ወአልቦሙ ኍልቍ ለእለ አስሐተቶሙ ።

፳፮ ፍናወ ሲኦል ቤታ እለ ያወርዱ ውስተ መዛግብተሁ ለሞት ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ አንተሰ ጥበበ ስብክ ከመ እአምሮ ታውሥእከ ።

፪ እስመ ውስተ ጽንፈ ነዋኃት ይእቲ ወማእከለ ፍናው ቆመት ፡ ወውስተ አናቅጸሙ ለኃያላን ትጸንሕ ።

፫ ወበውስተ ፍናው ትሴባሕ ፡ ኪያከሙ ሰብእ አስተበቍዕ ፡ ወእነግር ቃለ ዚአየ ለውሉደ ሰብእ ።

፬ አእምሩ የዋሃን ተጠብበ ፡ ወዓብዳን አጥርዩ ልበ ።

፭ ስምዑኒ እስመ መፍትወ እየድዕ ፡ ወአወፅእ እምከና ፍርየ ርቱዐ ።

ብር ብር ያለች ናት ደራተኛ ደረሞኛ ናት ፡ ነቃላ ማጭድም ናት ፡ እግሮቿም በቤቷ አያርፉም ።

አንድ ጊዜ ወደ ውጭ ትቅበዘበዛለች ፡ አንድ ጊዜ በአደባባይ ትቅበዘበዛለች በቤቷም ዙርያ ተቀምጣ ትጠብቃለች ።

ይዛ ትስመዋለች ፡ ሳታፍርም ፊት ለፊት እንዲህ ትለዋለች ።

የፍቅሬ መሥዋዕት አንተን የምሠዋበት ቀን ነው ፡ አንተን ቢያገናኝኝ ብዬ የተሳልኩት ስለቴንም ዛሬ እሰጣለሁ።

ስለዚህ ልቀበልህ መጣሁ ፊትህንም ማየት ስወድ አገኘሁህ ።

መኝታዬን ቍጥኒ በሚባል ግምጃ ጋርጀዋለሁ ከግብፅ የመጣ ሰይፍ ወላንሳ አንጥፌአለሁ ፡ ቤቴንም ደርሰኒ በሚባል ሽቱ ረፍርፌዋለሁ ፡ እስኪነጋ ድረስ በመሳሳም ና ተድላ ደስታ እናድርግ ትለዋለች ።

ባለ ቤቱም በቤቱ የለምና በመፋቀር ከብለል ከብለል እንበል ትለዋለች ።

የተቋጠረ ወርቅ በእጁ ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሂዷልና ፡ ወደ ቤቱም ቢመለስ በብዙ ቀን ነውና ።

በብዙ ነገር ታስተዋለች ፡ በከንፈሯም በተናገረችው ነገር ትስበዋለች ።

ለመታሰር እንደ ተጠራ ውሻ፡ ለመታረድ እንደሚነዳ ፍሪዳ አንገቱን ደፍቶ ይከተላታል ።

ልቡን እንደ ተወጋ ዋልያ ይሆናል ፡ ወፍንም ለወጥመድ እንዲ ቸኩል (ለጥፋት) ይቸኩላል ። ምሳ፡ ፮ ፲፭።

ከዚህ በኋላ በሰውነቱ ጥፋት እንደሚመጣበት አያውቅም ። መክ፡ ፱ ፲፪ ።

አሁንም ልጄ ስማኝ ከአፌ የሚወጣውንም ነገር ተመልከት ።

ልቡናህ ወደ መንደሯ ለመሄድ አያስብ ፡ እሷን በመከተል አትሳት ።

ብዙዎችን አስታ አቍስላለች ፡ ለአሳተቻቸውም ሰዎች ቍጥር የላቸውም ።

የቤቷ የሲኦል መንገዶች ሞት እየገደለ ወደሚጥልበት ወደ ገሃነም የሚያወርዱ ናቸው ። ምሳ፡ ፪ ፲፰ ።

ምዕራፍ ፰ ።

አንተስ እወቂ ታሰኝህ ዘንድ ጥበብን አስተምር ።

በረዢሞች ዳርቻዎች ነበረችና (በአዳምና በሔዋን) በጐዳናዎችም መካከል ቁማለችና (በዘመነ አበው) በኃይለኞች አደባባይ (በዘመነ መሳፍንት) ትጠብቅ ነበርና ።

በመንገድም ትመሰገን ነበርና ፡ (በዘመነ ነገሥት) ባለ አእምሮ የምሆን እኔ እማልዳችኋለሁ ፡ ለአዳም ልጆችም ነገሬን እነግራለሁ ።

ያልተማራችሁ ሰዎች ጥበብን ተማሩ ፡ አላዋቆችም ዕውቀትን ገንዘብ አድርጉ ።

የተወደደ ትምህርትን አስተምራለሁና ፡ የቀና ነገርንም ከከንፈሬ አውጥቼ እናገራለሁና ስሙኝ ። ምሳ፡ ፩ ፪

፮ እስመ ጽድቀ ትሜህር ጕርዔየ ወርኩሳት በቅድሜየ ከናፍረ ሐሰት ።

አንደበቴ እውነት ነገርን ታስተምራለች፣ ሐሰት የሚናገሩ ከንፈሮችም በፊቴ የረከሱ ናቸው ።

፯ ወጽድቅ ኵሉ ቃለ አፉየ፣ ወአልቦ እምውስቴቶሙ ጠዋይ ወማዕቅፍ ።

ከአፌ የሚወጣው ነገር ሁሉ እውነት ነው፣ ከምናገራቸውም ነገሮች ሁሉ ጠማማና የሚያሰናክል የለም ።

፰ ኵሉ ርቱዕ በቅድሜሆሙ ለእለ የአምሩ፣ ወርቱዕ ለእለ ይረክቡ ልቡና ።

በአዋቆች ፊት ሁሉ የቀና ነው፣ ዕውቀትንም ለሚያገኙ ሰዎች የቀና ነው ። ዘዳ፡ ፲፪ ፴፩ ።

፱ ንሥኡ ትምህርተ እምብሩር ወአእምሮ እምወርቅ ፍቱን ወተወከፉ ተዓውቆ እምወርቅ ጽሩይ ።

ከብር ይልቅ ትምህርትን ገንዘብ አድርጉ፣ ከጸሩ ወርቅም ይልቅ ዕውቀትን ገንዘብ አድርጉ፣ ከጠራ ወርቅ ይልቅ ዕውቀትን ተቀበሉ ። ኢዮ፡ ፳፰ ፲፭ ።

፲ እስመ ትኄይስ ጥበብ እምዕንቍ ዘብዙኅ ሤጡ፣ ወኵሉ ክብር ኢይመጠና ላቲ ።

ዋጋው ብዙ ከሆነ ዕንቍ ይልቅ ጥበብ ትሻላለችና፣ የዚህም ዓለም ክብር ሁሉ ለጥበብ መጠኗ አይደለም ።

፲፩ አነ ጥበብ አኅደርኩ ምክረ ወአእምሮ፣ ወሕሊና አነ ጸዋዕኩ ።

አዋቂ የምሆን እኔ ዕውቀትንና ምክርን በሰው ልቡና አሳደርሁ፣ ዕውቀትንም አስተማርሁ ። ምሳ፡ ፰ ፭ ።

፲፪ ፈሪሆ እግዚአብሔር ይጸልእ ዓመፃ፣ ጽልአ ወትዕቢተ ወፍናወ እኩያተ ጸላእኩ ።

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ዓመፅን ይጠላል፣ ትዕቢትንና ጥልን ጠማማ ሥራዎችንም ጠላሁ ።

፲፫ ወዓዲ ጸላእኩ ጠዋያተ ፍናወ እኩያን፣ ሊተ ምክር ወእዘዝ፣ ሊተ አእምሮ ወሊተ ጽንዕ ።

ዳግመኛም የክፉ ሰዎች ሥራዎች ጠማማ ናቸው፣ ምክር የኔ ገንዘብ ነው፣ ትእዛዝም ጽናትም የኔ ገንዘብ ናቸው ።

፲፬ ብየ ነገሥት ይነግሡ፣ ወኃያላን ይጽሕፉ ጽድቀ ።

ነገሥታቱ በኔ ምክር ይነግሣሉ ኃይለኞችም እውነት ነገርን ይጽፋሉ ዳን፡ ፪ ፳፩ ።

፲፭ ብየ ዓቢያን ይከብሩ፣ ወመኳንንት ይእኅዙ ምድረ ።

ታላላቆች በኔ ይከብራሉ፣ መኳንንቱም በኔ ምድረ አሕዛብን ይወርሳሉ ።

፲፮ አነ እለ ያፈቅሩኒ አፈቅር ወእለ የኀሥሡ ኪያየ ይረክቡ ሞገሰ ።

እኔ የሚወዱኝን እወዳለሁ፣ እኔን የሚፈልጉም ባለሟልነትን ያገኛሉ ። ዮሐ፡ ፲፬ ፳፩ ።

፲፯ ክብር ወብዕል ኀቤየ ሀሎ፣ ወጥሪት ብዙኅ ወጽድቅ ይኄይስ ኪያሃ ኀሪይ፣ እምወርቅ ወእምዕንቍ ክቡር ።

ባለጠግነትና ክብር ከኔ ዘንድ አለ፣ ብዙ ገንዘብ እውነት ነገርም ከኔ ዘንድ አለ፣ ከከበረ ዕንቍና ከወርቅ ይልቅ እሷን መምረጥ ይሻላል ።

፲፰ ወፍሬ ዚአየ ይኄይስ እምብሩር ጽሩይ ።

ከጠራ ወርቅ ይልቅ የኔ ትምህርት ይሻላል ።

፲፱ ወውስተ ፍናወ ጽድቅ አንሶሱ ወማእከለ አሠረ ጽድቅ እትመየየጥ ።

እውነተኛ የሚሆኑ ዘጠኙን ሕጋጋት በያዘ ሰው አድሬ እኖራለሁ፣ እውነተኛ ሕግ ኢታምልክን በጠበቁም ሰዎች አድራለሁ ። ምሳ፡ ፫ ፲፱ ።

፳ ከመ እክፍሎሙ ጥሪተ ለእለ የአምሩኒ፣ ወመዛግብቲሆሙ እምላእ ተድላ ።

በሕግ በአምልክ ለማያውቁኝ ሰዎች ዋጋቸውን አድላቸው ዘንድ ሕዋሳታቸውንም ተድላ ደስታ እመላው ዘንድ።

፳፩ እመ ነገርኩክሙ እንተ ጸብሐት ዘይከውን፣ ወዓዲ እዜክር ዘእምዓለም ኍልቄ ።

እየመሸ እየነጋ የሚደረገውን ከነገርኋችሁ፣ ዳግመኛ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ልደተ አበው አስበላሁ ።

፳፪ እግዚአብሔር ፈጠረኒ ቀዳሜ ኵሉ ተግባሩ እምቅድመ ይግበር ዓለመ ።

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ሁሉ አስቀድሞ ሰማይን ሳይፈጥር ፈጠረኝ ። ምሳ፡ ፰ ፴፭ ።

፳፫ ወዘእንበለ ይግበር ምድረ ወዘእንበለ ይግበር ቀላያተ ወዘእንበለ ይፃኡ አንቀዕተ ማያት ።

ምድርን ሳይፈጥር፣ ወንዞችንም ሳይፈጥር፣ የውኃዎችም ምንጮች (ተመጥነው) ሳይፈጠሩ ።

፳፬ ወዘእንበለ አድባር ይተክሉ (ይጠዓጥዑ)፣ ወእምቅድመ አውግር ወለደኒ ።

ከረብታዎችና ተራሮች ተከናውነው ሳይፀኑ ወለደኝ።

፳፭ ወእምቅድመ ይግበር በሐውርተ ወአጽናፈ ዘይትኀደር እምሰማይ ።

መንደሮችን ሳይፈጥር ጠፈር ፀንቶበት የሚኖር አድማስንም ሳይፈጥር ወለደኝ ። ኢዮ፡ ፰ ፲ ።

፳፮ እመ ያስተዴሉ ሰማያተ ሀሎኩ፣ ወእመ ያጸንዕ መንበረ ዚአሁ ላዕለ ነፋሳት ።

ሰማዮችን በዘጋጀ ጊዜ መኖርያቸው ጠፈርንም በነፋስ በፀና ጊዜ አብሬው ነበርኩ ። ምሳ፡ ፫ ፲፱ ።

፳፯ ወእመ ጽኑዐ ይገብር በመልዕልተ ደመናት ወእመ ያፀንዕ አንብሮ አንቀዕተ ማያት ።

የደመናትንም አካል የፀና ባደረገ ጊዜ፣ የውኃዎችንም ምንጮች በፀና ጊዜ ።

፳፰ ወእመ ያነብር ወሰነ ለባሕር፣ ወማያት ኢይፃኡ እምአፈ ዚአሁ ።

ውኆች ከወደቡ እንዳይወጡ ለባሕር ወሰንን በደረገ ጊዜ ። ዘፍ፡ ፩ ፱-፲ ። መዝ፡ ፻፬ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወአመ ጽኑዐ ይገብር መሠረታተ ምድር ሀሎኩ ምስሌሁ እንዘ አስተዋድድ ። | ፳፱ | የምድር መሠረቶች የሚሆኑ ነፋሳትን አፅንቶ በፈጠረ ጊዜ ፡ አብሬው ስፈጥር ነበርኩ ። |
| አነ ይእቲ እንተ እትፌሣሕ እንተ ጸብሐት ወእትኃሠይ በበገጹ በኵሉ ጊዜ ወአመ ይትፌሣሕ ዓለመ ፈጺሞ ወፍሥሓየኒ በደቂቀ እጓለ እመሕያው ። | ፴ | እየመሸ እየነጋ ፍጥረት እየተፈጠረ ደስ ይለኝ ነበር ፡ በየሰዓቱ በየወገን በየወገኑ ሁሉ ፍጥረት ሲፈጠር ደስ ይለኝ ነበር ፡ ይህን ዓለም ፈጥሮ በጨረሰ ጊዜ ፡ ይልቁንም በአዳም ልጆች መፈጠር ደስ ይለኝ ነበር ። |
| ወይእዜኒ ወልድየ ስምዓኒ ፡ ብፁዓን እለ የዓቅቡ ፍኖትየ ። | ፴፩ | አሁንም ልጄ ስማኝ ፡ ሕጌን የሚጠብቁ ሰዎች ንኡዳን ክቡራን ናቸው ። መዝ፡ ፻፲፰ ፳፪ ። |
| ስምዑ ጥበበ ወጥበቡ ወኢትትፈፀሙ ፡ ብፁዕ ብእሲ ዘይሰምዓኒ ቃልየ ። | ፴፪ | ጥበብን ስሙ ፡ ብልህ አዋቂዎች ሁኑ ፡ ምላሽንም አትጡ ፡ ነገሬን የሚሰማኝ ሰው ንኡድ ክቡር ነው ። |
| ወብፁዕ ዘየዓቅብ ፍኖትየ ወይተግህ ውስተ አናቅጺየ እንተ ጸብሐት ወዘየዓቅብ ራግዛተ ሙባእየ ። | ፴፫ | ሕጌን የሚጠብቅ ሰው ንኡድ ክቡር ነው ፡ እየነጋ እየጸባ በበሮቼ የሚተጋ ንኡድ ክቡር ነው ፡ የምገባባቸው መቃን መድረኮችንም የሚጠብቅ ሰው ንኡድ ክቡር ነው። |
| እስመ ፍናውየ ፍናወ ሕይወት ዘረከበኒ ረከበ ሕይወተ ወይደለው ፈቃዱ በኀበ እግዚአብሔር ። | ፴፬ | መንገዶቼ የሕይወት መንገዶች ናቸውና ፡ እኔን ያገኘኝ ሰው ሕይወት አገኘ ፡ በእግዚአብሔርም ዘንድ ፈቃዱ ይፈጸምለታል ። |
| ወእለሰ ይኤብሱ ላዕሌየ ይጌግዩ ላዕለ ነፍሶሙ ፡ ወእለ ይጸልኡኒ ያፈቅሩ ሞተ ። | ፴፭ | እኔን የሚበድሉ ሰዎች ራሳቸውን ይበድላሉ ፡ የሚጠሉኝም ሰዎች ሞትን ይወዳሉ ። ኢዮ፡ ፭ ፳፬ ። |
| **ምዕራፍ ፱ ።** | | **ምዕራፍ ፱ ።** |
| ጥበብ ሐነፀት ላቲ ቤተ ፡ ወአቀመት ሰብዓተ አዕማደ። | ፩ | ጥበብ ወልድ ዓለምን ፈጠረች ፡ ምሰሶዎችንም (ሰብቱን ዕለታት) አቆመች ። ምሳ፡ ፲፬ ፩ ። |
| ዘብሐት ዘዚአሃ ጥብሐ ፡ ወቶስሐት ውስተ ስያሓ ዘዚአሃ ወይነ ። | ፪ | የቧን እርድ አረደች (የሚበላውንም ፈጠረች) ወይኗን በማድጋዋ ጨመረች የሚጠጣውን ፈጠረች ። |
| ወፈነወት ዘዚአሃ አግብርተ እንዘ ትጼውዕ በነዋኅ ስብከት ። | ፫ | ብዙ ትምህርትን ለማስተማር ሰውን ስትጠራ በሮቿን (ፀሐይ ጨረቃ) ሰደደች ። |
| እንዘ ትብል ዘዓብድ ውእቱ ይግኅሥ ኀቤየ ፡ ወለእለሂ የሐፀሙ አእምሮ ። | ፬ | አላዋቂ የሆነ ሰው ወደኔ ይምጣ ፡ ዕውቀት ያነሳቸውም ወደኔ ይምጡ ። ምሳ፡ ፱ ፲፯ ። |
| ትቤ ንዑ ብልዑ ኅብስትየ ወስትዩ ወይንየ ዘቀዳሕኩ ለክሙ ። | ፭ | እንጀራዬን መጥታችሁ ብሉ ፤ የቀዳሁላችሁንም ወይኔን ጠጡ ስትል (ፀሐይ ጨረቃን) ላከች ። |
| ወኅድግዋ ለዕበድ ፡ ወኅሡ አእምሮ ከመ ትሕየዉ ። | ፮ | ስንፍናን ተውዋት ፡ በሕይወትም ትኖሩ ዘንድ ዕውቀትን ፈልጉ ። ምሳ፡ ፲፱ ፲፭ ፡ ፬ ፲፬ ። |
| አርትዑ አእምሮ በጠይቆ ፡ ወዘይሜህሮሙ ለእኩያን ይነሥእ ሎቱ ኃሣረ ። | ፯ | በመረዳት ዕውቀትን አቅንታችሁ ተማሩ ፡ ክፉ ሰዎችን የሚያስተምር ሰው ውርደትን ይቀበላል ። |
| ወዘይጌሥፆ ለረሲዕ ፡ የሐይስ ርእሶ ። | ፰ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው የሚያስተምር ፡ ራሱን ያስነቅፋል ። መዝ፡ ፻፵፩ ፭ ። |
| ኢትዝልፎሙ ለዓብዳን ከመ ኢይጽልኡከ ። | ፱ | እንዳይጠሉህ ክፉ ሰዎችን አታስተምራቸው ። |
| ዝልፎ ለጠቢብ ወያፈቅረከ ዓብድሰ ይጸልአከ ፡ ሀብ ለጠቢብ ምክንያተ ወያፈደፍድ ጥበበ ፡ አምር ለጠቢብ ወይዌስክ ተወክፎ ። | ፲ | ብልህን ሰው አስተምረው ይወዳኻል ፡ አላዋቂ ግን ይጠላኻል ፡ ለብልህ ሰው ምክንያትን ስጠው ጥበብን ያበዛል ፡ ለብልህ ሰው አመልክተው በጥበብ ላይ ጥበብን ይጨምራል ። |
| ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር ወምክረ ቅዱሳን አእምሮ ፡ ወአእምሮ ሕግሰ ለልብ ኄር ውእቱ ። | ፲፩ | የጥበብ መጀመርያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፡ የቅዱሳንም ምክር ዕውቀት ነው ፡ ሕግን ማወቅ ግን ለበጎ ልቡና ስምሙ ነው ። ምሳ፡ ፩ ፯ ። |
| በዝ ሥርዓት ብዙኀ መዋዕለ ተሐዩ ፡ ወይትዌሰከከ ዓመታተ ሕይወት ። | ፲፪ | በዚህ ሥርዓት ብዙ ዘመን ትኖራለህ በሕይወት የምትኖርባቸው ዘመኖችም ይጨመሩልኻል ። |
| ወልድየ ፡ እመ ጠቢበ ኮንከ ለርእስከ ጠቢበ ትከውን ለቢጽከ ወእመሰ እኩየ ኮንከ ለባሕቲትከ ትቀድሕ እኪተ። | ፲፫ | ልጄ ! ለራስህ አዋቂ ብትሆን ለባልንጀራህም አዋቂ ትሆናለህ ፡ ለራስህ ክፉ ብትሆን ግን ክፋትን ትማራለህ። |

፲፬ ዘያስተዳሉ ሐሰተ ይመስል ከመ ዘያስተዳሉ ነፋሳተ
ወውእቱ ከመ ዘይዴግን ዖፈ ዘይሠርር ።
፲፭ ወኀደገ ፍናወ ዓፀዱ ወይኑ ወመንኰራኵረ ወፍሬ ዚ
አሁ ረስዐ፡ ወየሐውር ውስተ በድው ገዳመ ወውስተ
ምድር እንተ ተሠርዓት ለጽምእ፡ ወያስተጋብእ በእዴሁ
ዘኢይፈሪ ወኢይበቊል ።
፲፮ ብእሲት ዓብድ ወመገዝእት ጽንስተ ኅብስት ትከውን
እንተ ኢተአምር ኀፈረ ምንተኒ፡ ወነበረት ውስተ አን
ቀጸ ቤታ ።
፲፯ ወውስተ መንበሩ ገሃደ ወውስተ መርኅብ፡ ትጼውዕ
ኃላፍያነ ፍኖት እለ ያረትዑ ፍኖቶሙ ።

፲፰ እለ እምውስቴቶሙ ዓብድ ይቀርብ ኀቤሃ ወለዘሂ የሐ
ፅፆ አእምሮ ትኤዝዞ ።
፲፱ ወትብሎ ኅብስተ ኅቡአ አስተሐዊዘከ ግሥሥ፡ ወማየ
ሰርቅ መዓርዒረ ስተይ ።

፳ ወውእቱሰ ኢየአምር ከመ እምኃያላን በኀቤሃ ይትኀ
ጐሉ ወመጽፈርተ ሲኦል ይትረከብ ውስተ ቤታ ።
፳፩ ወበሕቱ ቅንጽ ወኢትጐንዲ ውስተ መከና፡ ወኢታ
ውትር ዓይነከ ኀቤሃ ከመ ትትዓደው ፈለገ ነኪር ።

፳፪ ወእማየ ነኪር ረኀቅ፡ ወእምዓዘቅተ ነኪር ኢትስተይ
ከመ ብዙኀ መዋዕለ ትሕየው፡ ወይትወሰከከ ዓመታተ
ሕይወት ።

ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወልድ ጠቢብ ያስተፌሥሕ አባሁ፡ ወወልድ ዓብድ
ያኃዝና ለእሙ ።
፪ ኢይበቊዕ መዛግብት ለኃጥአን፡ ጽድቅሰ ታድኅን
እሞት ።
፫ ኢያስተቴንስ እግዚአብሔር ነፍሰ ጻድቅተ፡ ወሕይ
ወተ ረሲዓንሰ ያአትት እምድር ።

፬ እድ ሀከይ ብእሴ ያቴሕት፡ ወእድ ጽኑዕ ብእሴ ያብ
ዕል ።
፭ ወልድ ምሁር ጠቢበ ይከውን ወዓብድሰ ላእከ ይሬሲ
ርእሶ፡ ድኅነ እመርቄ ወልድ ጠቢብ ።

፮ ወልድ ጠቢብ ይትጌበር በማእረር፡ ወወልድሰ ዓብ
ድ ይነውም በማእረር፡ ነዛኢ ነፍስ ይከውን በውስተ ዓ
ውድ ወልድ ኃጥእ ።
፯ በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርእሰ ጻድቃን፡ አፈ
ረሲዓንሰ ይፌጽም ላሀ ግብተ ።

፰ ዝክረ ጻድቃን ምስለ ውዳሴ፡ ወስመ ረሲዓንሰ ይጠ
ፍእ ።

ሐሰትን የሚያዘጋጅ ሰው ነፋሳትን የሚያዘጋጅ ሰውን
ይመስላል፡ እሱም የሚበር ወፍን እንደሚከተል ነው ።
የወይኑ በታ መንገዱን ተወ፡ የሚሠማራበትንም መን
ገድ ዘነጋ፡ ወደ ምድረ በዳ ይሄዳል ለጥም ወደ ተሠራች
ምድር ሂዶ የማያፈራ የማይጠቅም ገንዘብን በእጁ ይሰ
በስባል ። ኢዮ፡ ፳፱ ፱ ።
ሰነፍ ተነዛናዥ ሴት አንድ እንጀራን የተቸገረች ትሆ
ናለች ምንም ኃፍረትን የማታውቅ ሴት በቤቷ አደባበይ
ትቀመጣለች ። ምሳ፡ ፱ ፲፰፡ ፭ ፯ ።
ተገልጾ በመንበሯ ተቀምጣ ወደ አደባበይ ትመለከታ
ለች መንገዳቸውን አቅንተው የሚሄዱትንም ሰዎች ትጠ
ራቸዋለች ።
ከነዚህ አላዋቂ ሰነፍ የሆነ ሰው ወደሷ ይቀርባል ዕው
ቀት ያነሰውን ታዝዘዋለች ።
የላቀ እንጀራ እንዲወደድ የምወደድ እኔን አሠማም
ረህ ያዘኝ የስርቆት ውኃም እንዲወደድ የምወደድ እኔን
አጠፋፍጠህ ያዘኝ ትለዋለች ።
እሱ ግን ከኃያላኑ ወገኖች በሷ ዘንድ እንዲጐዱ የመ
ቃብርም ወጥመድ በሷ ዘንድ እንዲገኝ አያውቅም ።
ነገር ግን ፈጥነህ ሂድ በበታዋም አትዘገይ በዓይንህም
ወደሷ አትመልከት፡ በልዩ በታ ከለ ውኃ ፈጥነህ እንድ
ትሄድ ፈጥነህ ሂድ ።
ብዙ ዘመን ትኖር ዘንድ በልዩ በታ ከለ ውኃ ራቅ፡
በሕይወት የምትኖርባቸውም ዘመናት ይጨመሩልህ ዘን
ድ ከልዩ ጉድጓድ ውኃ አትጠጣ (ከጐልማሳ ሚስት ፈቃ
ዴን እፈጽማለሁ አትበል)። ኢዮ፡ ፳፯ ፭ ።

ምዕራፍ ፲ ።

የተማረ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፡ ያልተማረ ልጅ
ግን እናቱን ያሳዝናታል ። ምሳ፡ ፲፭ ፳ ።
ለኃጢአተኞች ድልብ አይጠቅማቸውም፡ ምጽዋት
ግን ከሞተ ነፍስ ታድናለች ። ሉቃ፡ ፲፪ ፲፱ ።
እግዚአብሔር ደግ ሰውነትን አያስቸግርም፡ እግዚአ
ብሔርን የዘነጉ ሰዎች አኗኗር ግን ከምድር (መንግሥተ
ሰማይ) ያርቃል ።
ሀኬተኛ እጅ ሰውን ያዋርዳል፡ የጠና እጅ ግን ሰውን
ያከብራል ።
የተማረ ልጅ ብልህ ይሆናል፡ ያልተማረ ልጅ ግን ራ
ሱን መልእክተኛ ያደርጋል፡ የተማረም ልጅ ወደ ቄላ
ከመላክ ዳነ ።
የተማረ ልጅ በመከር ይጥራል (ይሠራል)፡ ያልተማረ
ልጅ ግን በመከር ጊዜ ይተኛል፡ ኃጢአተኛ ልጅ በሸንጎ
ሐሰት መስክሮ ነፍስን የሚያስገድል ይሆናል ።
የእግዚአብሔር በረከቱ በደጋጎች ራስ ላይ ፀንቶ ይኖ
ራል፡ የኃጢአትኞች አፍ ግን ድንገት መከራ መጥቶበት
ልቅሶን ይጨርሳል ።
የደጋግ ሰዎች ስም አጠራር ከምስጋና ጋር ነው፡ እግ
ዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ስም አጠራር ግን ይጠፋል ።

፱ ልብ ጠቢብ ይትዌከፍ ትእዛዘ ፡ ወዘኢይትዔገሥ በከ
ናፍሪሁ በማዕቅፍ ይወድቅ ።
፲ ዘየሐውር በየዋሃት የሐውር እሙነ ወዘይትሀወክ
ፍናዊሁ ይትከሠት ።
፲፩ ዘይትቃጸብ በአዕይንቲሁ ለእከይ ያስተጋብእ ለሰብእ
ኃዘነ ፡ ወዘሰ ይዘልፍ ገሃደ ሰላመ ይገብር ።

፲፪ ነቅዐ ሕይወት ውስተ አፈ ጻድቃን ፡ ወለአፈ ረሲዓን
ይከድኖ ኃጕል ።

፲፫ ጽልእ ያነሥእ መዓተ ፡ ወለኵሎሙ እለ ኢይትገአዙ
ይከድኖሙ ፍቅር ።
፲፬ ብእሲ ጠቢብ እምከናፍሪሁ ያወጽእ ጥበበ ፡ በበትር
ይዘብጥ (ይዘበጥ) ብእሲ ዘአንበለ ልብ ።
፲፭ ጠቢብ የኃብእ አእምሮ ፡ ወአፍ ጕጕእ ይቀርብ ለቅጥ
ቃጤ ።
፲፮ ጥሪቶሙ ለአብዕልት ሀገር ጽንዕት ፡ ወቅጥቃጤሆሙ
ለረሲዓን ንዴተ አእምሮ ።
፲፯ ግብረ ጻድቃን ሕይወተ ይገብር ፡ ወፍሬ ረሲዓን ኀጢ
አት ።
፲፰ ፍናወ ሕይወት የዓቅብ ተግሣፅ ፡ በተግሣፅ ዘኢይዘ
ለፍ ይስሕት ።
፲፱ ከናፍር ልሙጻት ይከድና ጽልአ ፡ ወእለሰ ያወጽኡ
ጽእለተ ዓብዳን እሙንቱ ።
፳ እምብዝኀ ነገር ኢያመስጥ ኃጥእ እምኃጢአት ፡ ወዘ
ይምህክሰ በከናፍሪሁ ማእምረ ይከውን ።

፳፩ ብሩር ርሱን ልሳነ ጻድቅ ፡ ወልበ ረሲዓንሰ የሐፅፅ ።

፳፪ ከናፍረ ጻድቃን የአምራ ነዋኀ ፡ ወዓብዳንሰ በንዴተ
አእምሮ ይመውቱ ።
፳፫ በረከተ እግዚአብሔር ላዕለ ርእሰ ጻድቃን ይእቲ ታብ
ዕል ፡ ወኢታመጽእ ኀዘነ ውስተ ልብ ።
፳፬ ውስተ ሐጕል ይትመየጥ ረሲዕ ፡ ፍትወቱ ለጻድቅ
ሥምረት በኀበ እግዚአብሔር ።

፳፭ በኀልፈተ ዓውሎ ይማስን ረሲዕ ፡ ጻድቅሰ ተግኂሦ
ለዓለም ይድኅን ።

፳፮ ከመ ቆፅ ከንቱ ለስነን ፡ ወጢስ ለዓይን ፡ ከማሁ ኃጢ
አት ለእለ አጥረይዋ ።

፳፯ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያነውኅ መዋዕለ ፡ ወዓመተ ረሲ
ዓንሰ ይውኅድ ።
፳፰ ትጕንዲ ትፍሥሕት ምስለ ጻድቃን ፡ ተስፋሆሙሰ ለረ
ሲዓን ትትኀጐል ።
፳፱ ፅንዐ ለኄር ፈሪሀ እግዚአብሔር ፡ ወቅጥቃጤ ለእለ
ይገብሩ እኩየ ።
፴ ጻድቅ ለዓለም ኢይኤብስ ፡ ወረሲዓንሰ ኢየኀድሩ

ብልህ ልቡና ያዘዙትን ትእዛዝ ይቀበላል ፡ በከንፈሩ
ብዙ ነገር ከመናገር የማይታገሥ ሰው በመከራ ይወድቃል።
በቅንነት ፀንቶ የሚኖር ሰው የታመነ ሁኖ ይኖራል ፡
ኃጢአት ለመሥራት የሚታወክ ግን ሥራው ይገለጥበታል።
ለክፉ ነገር በዓይኑ የሚጠቃቀስ ሰው በሰው ኃዘንን
ያመጣል ፡ ሰውን በግልጥ የሚቈጣ ሰው ግን ዕርቅን ያደ
ርጋል ።
የሕይወት መገኛ የሚሆኑ ዓሠርቱ ቃላት በመምህራን
አፍ ይነገራሉ ፡ የኃጥአንን ሰዎች አፍ ግን ጥፋት ይሸ
ፍነዋል ።
ቍጣ ጽልእን ያነሣል ፡ የማይጣሉ ሰዎችን ሁሉ ፍቅር
ይሸፍናቸዋል ። ያዕ፡ ፭ ፳ ። ፩ኛ ጴጥ፡ ፬ ፰ ።
ብልህ ሰው ከከንፈሩ ጥበብን ያወጣል ፡ አእምሮ የሌ
ለው ሰው ሰውን በብትር ይመታል ። ምሳ፡ ፲፱ ፳፱ ።
ብልህ ሰው ዕውቀትን ይሠውራል ፡ ችኩል አፍ ግን
ለጥፋት ይቀርባል ።
የባለጸጎች ገንዘባቸው የጠናች አገር ናት ፡ እግዚአብ
ሔርን የዘነጉ ሰዎች ከዕውቀት መቸገራቸው ነው ።
የጻድቃን ሥራቸው ሕይወትን ያደርጋል ፡ እግዚአብ
ሔርን የዘነጉ ሰዎች ፍሬ ነገራቸው ኃጢአት ነው ።
ምክር እዝናት ዓሠርቱ ቃላትን እንዲጠብቁ ያደርጋል
በምክር በእዝናት የማይዘለፍ ሰው ይስታል ።
ግብዝ አንደበቶች ጠባቸውን ይሠውራሉ ፡ በደላቸ
ውን የሚናገሩ ሰዎች ግን አላዋቆች ናቸው ።
ኃጢአተኛ ሰው ብዙ ነገርን ከመናገሩ የተነሣ ከኃጢ
አት አያመልጥም ፡ በከንፈሩ ብዙ ነገር መናገርን የሚሸ
ልግ ሰው ግን አዋቂ ይሆናል ።
የደግ ሰው አንደበት የጠራ ብር ነው ፡ እግዚአብሔርን
የዘነጉ ሰዎች ግን አእምሮአቸው (ከዕውቀት) የጐደለ ነው ።
የደጋግ ሰዎች ከንፈሮች መጻእያትን ያውቃሉ ፡ አላ
ዋቆች ሰዎች ግን ከዕውቀት በመቸገር ይሞታሉ ።
የእግዚአብሔር በረከት በደጋግ ሰዎች ራስ ፀንታ ትኖ
ራለች ይህች ታከብራለች በልቡናም ኃዘንን አታመጣም ።
እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ወደ ጥፋት ይመለሳል ፡
የደግ ሰው (ሕዝቅያስ) ጸሎቱ (ምጽዋቱ) በእግዚአብሔር
ዘንድ የተወደደች ናት ።
እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው (ሰናክሬም) በነፋስ መም
ጣት ይጠፋል ፡ ደግ ሰው (ሕዝቅያስ) ከመከራው ተሠውሮ
ለዘለዓለም ይድናል ። መዝ፡ ፶፰ ፱ ። ማቴ፡ ፯ ፳፬ ።
ጨርቋ ለጥርስ እንዳይመች ፡ ጢስም ለዓይን እንዳይ
መች ፡ ኃጢአትም ገንዘብ ላደረጓት ሰዎች እንዲሁ አት
መቻቸውም ።
እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜን ያበዛል ፡ እግዚአ
ብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ዘመናቸው ያንሣል ።
ተድላ ደስታ ከደጋጎች ሰዎች ጋራ ትኖራለች ፡ እግዚ
አብሔርን የዘነጉ ሰዎች አለኝታቸው ግን ትጠፋለች ።
የደግ ሰው ጽንዓቱ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ።

እውነተኛ ሰው ለዘለዓለሙ አይበድልም ፡ እግዚአብ

ውስተ ምድር ።

፴፩ አፈ ጻድቃን ይነብብ ጥበበ፡ ወልሳነ ዓማፅያን ይትኀጐል ።

፴፪ ከናፍረ ጻድቃን ያውኀዛ ሞገሰ፡ ወአፈ ረሲዓንሰ ይትከላአ እምአእምሮ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ መዳልወ ዓመፃ ርኩስ በኀበ እግዚአብሔር፡ መዳልወ ጻድቅሰ ኅሩይ ውእቱ ።

፪ ኀበ ሀሎ ጽእለት ህየ ሀሎ ኃሣር፡ አፈ የዋሃንሰ ይትሜሀር ጥበበ ።

፫ ተፍጻሜቶሙ ለጻድቃን ትመርሖሙ፡ ወዕቅፀቶሙሰ ለረሲዓን ትሄውዮሙ ።

፬ ኢይበቍዕ ንዋይ በዕለተ መዓት፡ ወጽድቅሰ ታድኅን እሞት፡ መዊቶ ጻድቅ ኀደገ ንስሐ ጉቡአን በእድ ይከውን ወሰሐቀ ሞቱ ለረሲዕ ።

፭ ወጽድቁ ለንጹሕ ያረትዕ ፍኖቶ፡ ወኃጢአትሰ ትወርድ ዲበ ረሲዓን ።

፮ ጽድቆሙ ለራትዓን ሰብእ ትባልሖሙ፡ ወበኢያእምሮቶሙ ይትአኀዙ ኃጥአን ።

፯ መዊቶ ብእሲ ጻድቅ ኢየኀጐል ተስፋሁ፡ ትምክሕቶሙሰ ለረሲዓን ትጠፍእ ።

፰ ጻድቅሰ እማዕገት ያመሥጥ፡ ወቤዛ ዚአሁ ይትወሀብ ረሲዕ ።

፱ ውስተ አፈ ረሲዓን መሥገርት ለሀገር፡ ወተዓውቆ ጽድቅሰ ፍኖት ሠናይት ።

፲ በኂሩተ ጻድቃን ትረትዕ ሀገር፡ ወበኃጕሎሙ ለረሲዓን ትትፈሣሕ ።

፲፩ በበረከቶሙ ለራትዓን ትትሌዓል ሀገር፡ ወበአፉሆሙ ለረሲዓን ትትገፈታዕ ።

፲፪ ይሜንኖ ሰብአ ሀገር ነዳየ ጠቢበ፡ ወብእሲሰ ጠቢብ ጽሚዌ ያመጽእ ።

፲፫ ብእሲ ዘክልኤ ልሳኑ ይከሥት ምክረ ማኅበር፡ ወምእመን እስትንፋሰሰ የኀብእ ምክረ ።

፲፬ እለ አልቦሙ ኃዳፍ ይትነገፉ ከመ ቈጽል፡ መድኃኒት በብዙኀ ምክር ይሄሉ ።

፲፭ እኩይ የአኪ ሶበ ይዴመር ምስለ ጻድቅ፡ ወይጸልእ ድምፀ ሁታቤ ።

፲፮ ብእሲት ኄርት ታነሥእ ክብረ ለምታ፡ ብእሲትሰ እንተ ትጸልእ ጽድቀ መንበረ ኃሣር ይእቲ ።

፲፯ ሀካይያን እምብዕል ይነድዩ፡ ወፅኑዓንሰ ይዴግኑ ብዕለ ።

፲፰ ለነፍሱ ይገብር ሠናየ ብእሲ መሐሪ፡ ወያማስን ሥጋሁ ዘኢይምሕር ።

ሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በዚህ ዓለም ኃጢአት ሳይሠሩ አይኖሩም ። መዝ፡ ፪፻፳ ፮፡ ምሳ፡ ፲፩ ፭ ።

የደጋግ ሰዎች አፍ ጥበብን ይናገራል፡ የበደለኞች አንደበት ግን ይጠፋል ።

የደጋግ ሰዎች ከንፈር የተወደደ ስውቀትን ይናገራል የረሲዓን አፍ ግን ከዕውቀት ይከለከላል ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

አባይ ሚዛን በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ ነው፡ እውነተኛ ሚዛን ግን በሱ ዘንድ የተመረጠ ነው ።

መሰደብ ካለ ዘንድ በዚያ ተዋርዶ አለ፡ የየዋሆች አፍ ግን ጥበብን ይማራል ። ምሳ፡ ፳፱ ፳፫ ።

ጻድቃን በክብር ፍጹም መሆናቸው ወደ ገነት ትመራቸዋለች፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በኃጢአት መሰነካከላቸው (ወደ ገሃነም) ትማርካቸዋለች ።

ሰማያዊ ንጉሥ በተቈጣበት ቀን ገንዘብ አይጠቅምም ምጽዋት ግን ከሞተ ነፍስ ታድናለች ጻድቅ ሰው ከሞተ በኋላ በሰው ልቡና ፀፀትን ተወ፡ እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ሞቱ በእጅ እንደተያዘ ወርቅ ይሆናል፡ (ደስም ያሰኛል)። ምሳ፡ ፲ ፪ ።

የደግ ሰው በጎ ሥራውን ያቀናለታል፡ ኃጢአት ግን እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች ትወርዳለች ።

የቅኖች ሰዎች ሥራቸው ታድናቸዋለች፡ ኃጢአተኞች ግን ባለማወቃቸው በኃጢአት ይያዛሉ ።

ጻድቅ ሰው ከሞተ በኋላ አለኝታውን አያጣም እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ትምክሕታቸው ትጠፋለች ።

ደግ ሰው ግን ከመከራ ያመልጣል፡ እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰውም ለሱ ቤዛ ሁኖ ይሰጣል ።

እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች አፍ መከራ በገር ይመጣል፡ እውነተኛ ሕግን ማወቅ መረዳት ግን በጎ ሥራ ናት ።

በደጋግ ሰዎች ደግነት አገር ትቀናለች እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች ጥፋት ግን ደስ ይላታል ።

በደጋጎች ሰዎች ጸሎት አገር ከፍ ከፍ ትላለች እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች አፍ ግን ትጠፋለች ።

በገር ያሉ ሰዎች ብልህ ደኻውን ይንቃሉ፡ ብልህ ሰው ግን ጸጥታን ያስገኛል ። ምሳ፡ ፯ ፴፪ ።

አንደበቱ ሁለት የሆነ ሰው በሸንጎ የተመከረውን ምክር ይገልጣል፡ ሰውነቱ የታመነ ሰው ግን የተመከረውን ምክር ይሠውራል ። ዘሌ፡ ፲፱ ፲፯ ።

መምህር የሌላቸው ሰዎች እንደ ቅጠል ይረግፋሉ፡ ዓሠርቱ ቃላት በብዙ ምክር ፀንቶ ይኖራል ።

ክፉ ሰው ከደግ ሰው ጋር አንድ በሆነ ጊዜ ይከፋል (ክንቱ ይገለጣል) ያሠርቱ ቃላትን መጠበቅ ይጠላል ።

ልባም ሴት ለባሏ ክብርን ታስገኛለች፡ በጎ ሥራን የምትጠላ ሴት ግን የውርደት መንበር ናት ።

ሀኬተኞች ሰዎች ከባለጠግነት ይቸገራሉ፡ ልባሞች ሰዎች ግን ባለጠግነትን ያገኛሉ ። ሉቃ፡ ፲፩ ፳፩ ።

የሚመጸውት ሰው ለነፍሱ በጎ ሥራን ይሠራል የማይመጸውት ሰው ግን ሰውነቱን ያጠፋል ። ማቴ፡ ፭ ፮ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፲፱ | ረሲዕ ይገብር ምግባረ ዓመፃ ፡ ወለዘርአ ጻድቃንሰ ዐስብ ህልው ። | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ክፋት ይሠራል ፡ ለደጋግ ሰዎች ልጆች ግን ነዋሪ ዋጋ አላቸው ። ሆሴ፡ ፲ ፲፱ ። |
| ፳ | ወልድ ጻድቅ ይትወለድ ለሕይወት ፡ ወልደተ ረሲዓንሰ ለሞት | ደግ ልጅ ለሕይወት ይወለዳል እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች መፈጠር ግን ለሞት ነው ። |
| ፳፩ | ርኩሳት በኀበ እግዚአብሔር ፍናው ጠዋያት ፡ ወኅሩያን በቅድሜሁ ኵሎሙ እለ ንጹሓን በፍኖቶሙ ። | ጠማማ ሥራዎች በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሱ ናቸው ፡ በሥራቸው ንጹሕ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ግን በፊቱ የተመረጡ ናቸው ። |
| ፳፪ | እደ በእድ ዘይእኅዝ በግፍዕ ኢይድኅን እምኃጢአት፡ ወዘይዘርእሰ ጽድቀ ዐስበ መሀይምናን ይነሥእ ። | በግፍ የጒልማሳ ሚስት ተደፋፍሮ በእጁ የሚይዝ ሰው ከፍዳ አይድንም ፡ በጎ ሥራን የሚሠራ ሰው ግን የደጋጎች ሰዎችን ዋጋ ይቀበላል ። ምሳ፡ ፲፪ ፯ ፤ ፲፯ ፭ ። |
| ፳፫ | ከመ ውዕበ ወርቅ ውስተ ጽንፈ አንፈ ሐራውያ ኅሡም ከማሁ ላህያ ለብእሲት እኪት ። | በእርያ አፍንጫ ያለ የወርቅ ቀለበት ክፉ እንደሆነ እንደዚሁ የክፉ ሴት ደም ግባቷ ክፋቷን ይገልጥባታል ። |
| ፳፬ | ፍኖተ ጽድቅ ኵሉ ሠናይ ፡ ተስፋሆሙሰ ለረሲዓን ይትኀጐል ። | እውነተኛ ሕግ ሁሉ በጎ ነው ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች አለኝታቸው ይጠፋል ። ሮሜ ፪ ፳-፱ ። |
| ፳፭ | ቦ እለ ዘዚአሆሙ ይዘርኡ ወያፈደፍዱ ፡ ወቦ እለ እንዘ ያስተጋብኡ የሐፅፁ ። | የራሳቸውን እርሻ እየዘሩ በለጠግነታቸውን የሚያበዙ አሉ ፡ እየሰበሰቡ ብዕላቸውን የሚያሳንሱም አሉ ። |
| ፳፮ | ወኵላ ነፍስ እንተ ትትባረክ ስፍሕት ፡ ወብእሲሰ መዓትም ሕሡም ። | እግዚአብሔርን የምታመሰግን ሰውነት ሁሉ በአእምሮ የሰፋች ናት ፡ ቍጡ ሰው ግን ክፉ ነው ። |
| ፳፯ | ዘያበዝኅ ሥርናዮ የኃድጎ ለአሕዛብ ፡ ወይረግምዎ ነዳያን ፡ ወበረከት ውስተ ርእሱ ለዘይምሕር ወይሁብ ። | ሥንዴውን የሚያበዛ ሰው ለአሕዛብ ትቶት ይሞታል ድኾችም ይረግሙታል በሚሰጥና በሚመጸውት ሰውነት በረከት ፀንቶ ይኖራል ። ምሳ፡ ፳፪ ፳፬ ። |
| ፳፰ | ዘይሔሊ ሠናየ ይፈቅድ ክብረ ሠናየ ፡ ወዘሰ የኃሥሣ ለእኪት ትረክቦ ። | ምጽዋትን ለመመጽወት የሚያስብ ሰው በጎ ክብርን ይወዳል ፡ ማጠራቀም የሚወዳትን ሰው ግን ፍዳ ታገኘዋለች ። መዝ፡ ፯ ፲፭ ። አስ፡ ፯ ፲ ። |
| ፳፱ | ዘይትወከል በብዕሉ ውእቱ ይወድቅ ፡ ወዘይትዌከፎሙሰ ለጻድቃን ይሠርፅ ። | በባለ ጠግነቱ የሚታመን ሰው በመከራ ይወድቃል ፡ ድኾችን የሚቀበላቸው ሰው ግን በረድኤት ይለመልማል ። |
| ፴ | ዘኢየዓውቅ ቤቶ ይወርስ ነፋስ ፡ ወይትቀነይ ዓብድ ለጠቢብ ። | ቤቱን ዐውቆ የማይሠራ ሰው ነፋስ ያፈርስበታል ፡ አላዋቂ ሰው ግን ለብልህ ሰው ይገዛል ። |
| ፴፩ | እምፍሬ ጽድቅ ይወጽእ ዕፀ ሕይወት ፡ ወይሴስላ ግብተ ነፍሳተ ዓማፅያን ። | የሕይወት ዕንጨት ከእውነተኛ ፍሬ ይገኛል ፡ የበደለኞች ሰዎች ሰውነቶች ድንገት በሞት ይርቃሉ ። |
| ፴፪ | ወሰበ ጻድቅ እምዕፁብ ይድኅን ፡ ረሲዕ ወኃጥእ ወዓማፂ በአይቴ ያስተርኢ ። | ደግ ሰው በጭንቅ የሚድን ከሆነ በደለኛና ኃጢአተኛ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ በባለሟልነት እንዴት ይገለጣል ። ኤር፡ ፳፭ ፳፱ ። ፩ኛ ጴጥ፡ ፬ ፲፰ ። |

ምዕራፍ ፲፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | ዘያፈቅር ተግሣፀ ያፈቅር አእምሮ ፡ ወዘይጸልእሰ ተግሣፀ ዓብድ ውእቱ ። | ምክር አዝናትን የሚወድ ሰው ዕውቀትን ይወዳል ፡ ምክር አዝናትን የሚጠላ ሰው ግን አላዋቂ ነው ። |
| ፪ | ይኄይስ ዘረከበ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ፡ ወብእሲሰ ዓማፂ ይትኄየይ ። | በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን ያገኘ ሰው ይሻላል ፡ በደለኛ ሰው ግን ቸል ይባላል ። |
| ፫ | ዘኢያረትዕ ሰብእ እምዓመፃ ይትኀጐል ፡ ወሥርወ ጻድቃንሰ ኢይትመሐው ። | ምስክርነትን የሚያቃና ሰው በግፍ ይጠፋል ፡ የጻድቃን አባትነት ግን አይጠፋም ። ምሳ፡ ፲ ፳፭ ። |
| ፬ | ብእሲት አዛዝ አክሊል ለምታ ፡ ወከመ ዕፄ ለዕፅ ፡ ከማሁ ብእሲት እኪተ ምግባር ታኀጒል ልበ ብእሲ ። | ልበም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት ፡ ነቀዝ ዕንጨትን ውስጥ ውስጡን እንዲበላው ግብረ ክፉ ሴትም የባሏን ልቡና እንደዚሁ ታሳዝነዋለች ። ምሳ፡ ፲፫ ፳፬ ። |
| ፭ | ሕሊናሆሙ ለጻድቃን ፍትሕ ፡ ወይሔድፉ ረሲዓን ሕብለ ። | የደጋጎች ሰዎች አሳባቸው ፍርድ ነው ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን የሐሰት ትምህርትን ያስተምራሉ ። |
| ፮ | ነገረ ረሲዓን ጕሕሉት ፡ ወአፈ ረሲዓንሰ ታድኅኖሙ ። | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ነገራቸው ሽንገላ ነው ፡ የቅኖች ሰዎች ግን አፋቸው ከመከራ ታድናቸዋለች ። |

፯ ኅበ ተመይጠ ረሲዕ ይማስን፡ አብያተ ጻድቃንሰ ይሄልው ።

እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ወደ ክፉ ሥራ ከተመለሰ ዘንድ ይጠፋል ፡ (ሰናክሬም) የደጋጎች ሰዎች ወገኖች ግን በተድላ በደስታ ይኖራሉ ። መዝ፡ ፴፯ ፴፯ ።

፰ አፈ ጠቢብ ይትዌደስ በኀበ ኵሉ ሰብእ ፡ ወእዩየ ልብሰ ይትሜነን ።

የብልህ ሰው ነገር በሰው ሁሉ ዘንድ ይከበራል ፡ ልበ በከና ሰው ግን ይናቃል ።

፱ ይኄይስ ብእሲ ዘበኃሣሩ ይትቀነይ እምነ ዘያነብር ክብረ ሎቱ ፡ ወይትፈአም ኅብስተ ።

ክብርን ለራሱ ከሚያኖር ዙሮ ከሚቀላውጥም ሰው በመከራው ጊዜ የሚያርስ የሚቈፍር ሰው ይሻላል ።

፲ ይምሕር ጻድቅ ነፍሰ እንስሳሁ ፡ ወምሕረቶሙሰ ለረሲዓን ኢ ምጽዋት ።

ደግ ሰው ለከብቶቹ በሕርይ ይራራል ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ርኅራኄያቸው አለመመጽወት ነው።

፲፩ ዘይትጌበራ ለምድር ያበዝኃ ኅብስተ ፡ ወዘሰ ይዴግን ጽርዓተ ያስተጋብእ ንዴተ ፡ እስመ ውእቱ ነዳየ አእምሮ።

ምድርን የሚያርሳት ሰው እንጀራን ያበዛል ፡ በዘንን የሚከተል ሰው ግን ችጋርን ያበዛል ፡ ከዕውቀት የተቸገረ ሁኗልና ።

፲፪ ዝ ውእቱ ምዑዝ ለመትልወ ወይን፡ ወበኀይለ ዚአሁ የኃድግ ኃሣረ ።

ይህ እንዲህ ያለው ሰው ወይንን ለሚከተል ስሙሙ ነው ፡ በሰውነቱም አሣርን ተዋርዶን ያመጣል ።

፲፫ ፍትወተ ረሲዓን እኪት ፡ ወሥርዎሙሰ ለኄራን ውስተ ጽንዕ ።

የክፉ ሰዎች ፈቃድ ክፋት ነው ፡ የደጋጎች ሰዎች አበትነታቸው ግን በፅኑ ረድኤት ተጠብቀው ይኖራል ።

፲፬ በኃጢአተ ከናፍሪሁ ይወድቅ ኃጥእ ውስተ መሥገርት ወያመሥጥ እምኔሁ ጻድቅ ።

ኃጢአተኛ ሰው በከንፈሩ በተናገረው ነገር በመከራ ይወድቃል ፡ ደግ ሰው ግን ከኃጢአተኞች መከራ ያመልጣል ።

፲፭ ዘይኔጽር ስፉሐ ይትሜሀር ፡ ወዘሰ ይዳደቅ በአናቅጽ ያመነድብ ነፍሶተ ።

አብዝቶ የሚመለከት ሰው ብዙ ይማራል ፡ በደጅ የሚገናኝ ሰው ግን ሰውነቶችን ያስጨንቃል ።

፲፮ እምፍሬ አፉሁ ነፍሰ ብእሲ ይመልእ በረከተ ፡ ወዕሤተ ከናፍሪሁ ይትወሀብ ሎቱ ።

ሰው በአፉ በጸለየው ጸሎት በረከትን ይመላል ፡ በከንፈሩ የጸለየውም የጸሎቱ ዋጋ ይሰጠዋል ።

፲፯ ፍኖተ ዓብዳን ርቱዕ በቅድሜሆሙ ፡ ወይሰምዕ ምክረ ዕዝነ ጠቢብ ።

ያላዋቆች ሰዎች ሥራቸው በፊታቸው የቀና መስሎ ይታያቸዋል ፡ የብልህ ሰው ጆሮ ግን ምክርን ይሰማል ።

፲፰ ዓብድ እንተ ጸብሐት ይነግር መዓቶ ፡ ማእምርሰ የኀብእ ኃሣሮ ።

አላዋቂ ሰው እየነጋ እንዲህ ብሎ ተቈጡኝ ይላል ፡ አዋቂ ሰው ግን የተቈጡትን አይናገርም ።

፲፱ እንተ ታስተርኢ ሃይማኖተ ይነግር ብእሲ ጻድቅ ፡ ወሰማዕተ እኩያንሰ ሕብል ።

ደግ ሰው የተገለጠች ሃይማኖትን ያስተምራል ፡ የክፉ ሰዎች ምስክርነት ግን ሐሰት ነው ።

፳ እለሰ ይከውኑ ስምዐ በሐሰት ይቀትሉ በመጥባሕት እስመ ንቡር ውስተ አፉሆሙ መጥባሕት ፡ ወልሳነ ጠቢባንሰ ይፌውስ ዘቈሰለ ።

በሐሰት ምስክር የሚሆኑ ሰዎች በነገራቸው ሰውን ያጠፋሉ ፡ እንደ ሾተል የሚቈርጥ ነገር ባንደበታቸው አለና የብልሆች አንደበት ግን የቈሰለውን ያድናል (ያዘነውን ደስ ያሰኛል) ። ምሳ፡ ፲፩ ፳፱ ።

፳፩ ከናፍረ ጻድቃን ያረትዓ ስምዐ፡ ወሰማዕት ጕጉዕ በልሳን እኩይ ።

የደጋጎች ሰዎች ከንፈሮች ምስክርነትን ያቀናሉ በንደበቱ ሐሰት ለመመስከር የሚቸኵል ሰው ምስክር ግን ክፉ ነው ።

፳፪ ሕብል ውስተ ልቡ ለዘይሔሊ እኩየ፡ ወእለሰ ይፈቅዱ ሰላመ ይትፌሥሑ ።

ክፉ ነገር በሚያስብ ሰው ልቡና ሐሰት ፀንቶ ይኖራል ፡ ፍቅር አንድነትን የሚወዱ ሰዎች ግን ደስ ይላቸዋል።

፳፫ ኢያሠምሮ ለጻድቅ ምንትኒ እኩይ ፡ ወረሲዓንሰ ያበዝኁ እከየ ።

ደግን ሰው ክፉ ነገር ምንም ደስ አያሰኘውም ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ክፋትን ያበዛሉ ።

፳፬ ምኑናት በኀበ እግዚአብሔር ከናፍረ ሐሰት ፡ ወዘይገብርሰ ሃይማኖተ ሥሙር በኀቤሁ ።

ሐሰት የሚናገሩ ከንፈሮች በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቁ ናቸው ፡ ሃይማኖትን የሚያደርግ ሰው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው ። ምሳ፡ ፮ ፲፮ - ፲፯ ።

፳፭ ብእሲ ማእምር መንበረ ጥበብ ፡ ወልበ ዓብዳንሰ ይዳደቅ መርገመ ።

አዋቂ ሰው የጥበብ መገኛ ነው ፡ አላዋቂዎች ሰዎች ልቡና ግን መርገምን ይገናኛል ። ምሳ፡ ፲፫ ፲፮ ።

፳፮ እደ ኅሩያን ይእኅዝ ፍጡነ ፡ ወሕቡላንሰ ይከውኑ ለጺቀዊ ።

የተመረጡ ሰዎች ቃል ፈጥኖ ይጠፋል ፡ ትዕቢተኞች ሰዎች ግን ለምርኮ ይሆናሉ ። ኢዮ፡ ፲፫ ፯ ።

፳፯ መደንግፅ ቃል የሀውክ ልበ ብእሲ ጻድቅ ፡ ወዜና ሠናይሰ ያስተፌሥሖ ልበ ብእሲ ጠቢብ ።

የሚያስደነግፅ ቃል የደግ ሰው ልቡናን ያውካል ፡ በጎ ወሬ ግን የብልህ ሰው ልቡናን ደስ ያሰኛል ።

| | | |
|---|---|---|
| ማእምረ ርእሱ ጻድቅ ውእቱ ለርእሱ፣ ወግዕዘሙሰ ለረሲዓን እኩ አዳም ። | ፳፰ | ራሱን አውቆ የሚያሰድር ሰው ለራሱ ደግ ነው፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሥራ ግን በጎ አይደለም ። |
| ለእለ ይኤብሱ ይዴግኖሙ እኩይ፣ ወፍኖቶሙሰ ለረሲዓን ታስሕቶሙ ። | ፳፱ | ለሚበድሉ ሰዎች ክፉ ነገር ይከተላቸዋል፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ሥራቸው ታስታቸዋለች ። |
| ይዳደቅ ሕብል ለአስግሮ ጥሪት፣ ወክቡር ብእሲ ንጹሕ ። | ፴ | ለማጥፋት ሐሰት ይገናኛቸዋል ንጹሕ ሰው ግን የከበረ ገንዘብ ነው ። ምሳ፡ ፲፪ ፳፬ ። |
| ውስተ ፍናወ ጽድቅ ሕይወት፣ ወእለሰ ይዜክሩ እኩየ ውስተ ሞት ይሄልዉ ። | ፴፩ | ሕገጋትን በመጠበቅ ሕይወት ይገኛል፣ ክፉ ነገርን የሚያስቡ ሰዎች ግን በሞተ ነፍስ ተይዘው ይኖራሉ ። |
| **ምዕራፍ ፲፫ ።** | | **ምዕራፍ ፲፫ ።** |
| ወልድ ማእምር ሰማዔ አብ ይከውን፣ ወወልድሰ ዘኢይሰምዕ ይከውን ለኀጕል ። | ፩ | አዋቂ ልጅ የአባቱን ምክር የሚሰማ ይሆናል፣ የአባቱን ምክር የማይሰማ ልጅ ግን ለጥፋት ይሆናል ። |
| ወእምፍሬ ጽድቁ ይበልዕ ኄር፣ ወነፍሰ ዓማፅያንሰ ይትኀጐል ቀዖሙ ። | ፪ | ደግ ሰው ከእውነተኛ ገንዘቡ ይመገባል የበደለኞች ሰዎች ሰውነት ግን በሕፃንነታቸው ይቀሠፋል ። |
| ዘየዓቅብ አፉሁ ይትመኀፀና ለነፍሱ፣ ወጐጕእሰ በከናፍሪሁ ያወድቅ ርእሶ ። | ፫ | አፉን ክፉ ነገር ከመናገር የሚጠብቅ ሰው ሰውነቱን ይጠብቃታል፣ በከንፈሩ ክፉ ነገር ለመናገር የሚቸኵል ሰው ግን ራሱን ያጠፋል ። መዝ፡ ፻፵፩ ፫ ። |
| ኵሉ ዘኢይትቀነይ ውስተ ፍትወት ሀሎ ወእዴሆሙ ለኄራን ያስተሐምም ። | ፬ | የማያርስ የማይቆፍር ሰው ሁሉ በምኞት ይኖራል፣ የደጋግ ሰዎች እጅ ግን ለሥራ ይተጋል ። |
| ቃለ ዓማፂ ይጸልእ ጻድቅ፣ ወረሲዕሰ የኀፍር ወኢይመጽእ ገሃደ ። | ፭ | የበደለኛ ሰው ቃል እውነት ነገርን መናገር ይጠላል፣ እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ግን ያፍራል ተገልጦም አይመጣም ። ዮሐ፡ ፫ ፳-፳፩ ። |
| ጽድቅ ተዓቅቦሙ ለየዋሃን በፍኖት፣ ለረሲዓንሰ እኩሰ ይሬስዮሙ ኃጢአት ። | ፮ | የዋሆች ሰዎችን እውነተኛ ሥራቸው ትጠብቃቸዋለች፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ኃጢአት በደለኛ ታደርጋቸዋለች ። ምሳ፡ ፲፩ ፫ ። |
| ብ እለ ያሌዕሉ ርእሶሙ እንዘ ምንትኒ አልቦሙ፣ ወብ እለ ያቴሕቱ ርእሶሙ እንዘ ብዙኅ ብዕሎሙ ። | ፯ | ምንም ሳይኖራቸው ራሳቸውን የሚያስታብዩ ሰዎች አሉ፣ በባለጠግነታቸው ብዙ ሆኖ ሳለ ግን ራሳቸውን የሚያዋርዱ አሉ ። ማቴ፡ ፭ ፫ ። |
| ቤዛ ነፍሱ ለብእሲ ጥሪተ ብዕሉ፣ ወነዳይሰ ኢይትቃወም መዓተ ። | ፰ | ለሰው የሰውነቱ ቤዛ ገንዘብ ማጠራቀሙ ነው፣ ድኻ ግን የንጉሡ ቍጣ አይቃወምም ። |
| ብርሃን ለጻድቃን በኵሉ ጊዜ፣ ወብርሃነ ረሲዓንሰ ትጠፍእ ። | ፱ | በየጊዜው ለጻድቃን ተድላ ደስታ ይደረግላቸዋል፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ተድላ ደስታ ግን ትጠፋለች ። |
| ነፍሳተ ሕቡላን ይስሕታ በኃጢአት፣ ወጻድቃንሰ ይምሕሩ ወይመጽውቱ ። | ፲ | የደፋሮች ሰዎች ሰውነታቸው በኃጢአት ይስታል፣ ደጋጎች ሰዎች ግን ራርተው ይመጸውታሉ ። |
| እኩይ ዘምስለ ጽእለቱ ይገብር እኩየ፣ ወእለሰ የአምሩ ርእሶሙ ጠቢባን እሙንቱ ። | ፲፩ | ክፉ ሰው ከመሰደቡ ጋራ ክፋትን ይሠራል፣ ራሳቸውን አውቀው የሚያርሙ ሰዎች ግን ብልሆች ናቸው ። |
| እጥርዮ ዘይጕጕእ በኃጢአት ውኁደ ይከውን በደኃሪቱ፣ ወዘሰ ያስተጋብእ ለርእሱ በጽድቅ ይፈደፍድ ሉቱ ጻድቅኒ ይምሕር ወይሌቅሕ ። | ፲፪ | ቀምቶ ለመክበር የሚቸኵል በፍጻሜ ዘመኑ ድኻ ይሆናል፣ ወጥቶ ወርዶ የሚሰበስብ ሰው ግን በለጸግነቱ ይበዛለታል፣ ደግ ሰውም ይመጸውታል ያበድራልም ። |
| ይኄይስ ዘይዌጥን ይርዳእ ነፍሰ እምነ ዘይብዕል ወያጸንዕ ለተስፋ ። | ፲፫ | ለሰበ ለሰማንያ ዘመን ይሆነኛል ብሎ ከማይበላ ከማይጠጣ ባለ ጸጋ ይልቅ፣ በልቶ ጠጥቶ ሰውነቱን የሚረዳ ሰው ይሻላል ። |
| ዕፀ ሕይወት ይእቲ ፍኖት ሠናይት ። | ፲፬ | በጎ ነገር የምትሆን ኢታምልክ የሕይወት ዕንጨት ናት ። ምሳ፡ ፲፫ ፲፱ ። |
| ዘያሰትት ግብረ እግዚአብሔር ውእቱኒ ያሰትቶ፣ ወዘሰ ይፈርሀ ትእዛዘ የሐዩ በቱ ። | ፲፭ | የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያቃልለውን ሰው እሱ ያቃልለዋል፣ ትእዛዙን የሚፈራ ሰው ግን በሕይወት ይኖራል ። |
| ለወልድ ሕቡል አልበቱ ምንትኒ ሠናይ፣ ለገብርሰ ጠቢብ ሠናየ ይከውን ምግባሩ ወይረትዕ ፍኖቱ ። | ፲፮ | ለደፋር ልጅ ምንም በጎ ነገር የለውም፣ የ፣ልሀ ባርያ ግን ምግባሩ የበጀ ይሆናል፣ ሥራውም ይቀናል ። |

| | | |
|---|---|---|
| ሕገ ጠቢብ ነቅዐ ሕይወት፥ ወዘአንበለ ልብሰ በአበሳ ይመውት ። | ፲፯ | የብልህ ሰው ሕግ የሕይወት መገኛ ነው፥ አእምሮ የሌለው ሰው ግን በኃጢአት እንደተያዘ ይሞታል ። |
| አእምሮ ሠናይ ይሁብ ጥበበ ወሞገሰ፥ ወፍናዊሆሙሰ ለኅዩያን ውስተ ኀጕል ። | ፲፰ | በጎ ዕውቀት ባለሟልነትንና ዕውቀትን ይሰጣል፥ የቸልተኞች ሰዎች ሥራ ግን ወደ ጥፋት ነው ። |
| ኵሉ ማእምር ይገብር በምክር፥ ወዐብድሰ አሥረረ እከየ ዚአሁ ። | ፲፱ | አዋቂ ሰው ሁሉ ሥራውን በምክር ይሠራል፥ አላዋቂ ሰው ግን ክፋቱን ለሁሉ አዳረሰ ። ዘፀ፡ ፴፯ ፱ ። |
| ላእክ ዐብድ ይወድቅ ውስተ እኪት፥ ወሐዋርያሰ ጠቢብ ያድኅን ርእሰ ። | ፳ | አላዋቂ መልእክተኛ በመከራ ይወድቃል፥ ብልህ መልእክተኛ ግን ራሱን ያድናል ። ምሳ፡ ፳፭ ፲፫ ። |
| ንዴተ ወኃሣረ ያሴስል ትምህርት፥ ወለየዓቅብሰ ተግሣፀ ይከብር ። | ፳፩ | ትምህርት መከራንና ችግርን ያርቃል፥ ሕግን የሚጠብቅ ሰው ግን ይከብራል ። |
| ፍትወተ ኄራን ያጥዒ ነፍሰ፥ ወምግባረ ረሲዓንሰ ርኁቅ እምአእምሮ ። | ፳፪ | የደጋግ ሰዎች ሥራ ሰውነትን ያድናል፥ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሥራ ግን ከዕውቀት የራቀ ነው ። |
| ዘይደመር ምስለ ጠቢብ ጠቢበ ይከውን፥ ወዘሰ ያንዘሐልል ምስለ ዓብዳን ዐብደ ይከውን ። | ፳፫ | ከብልህ ሰው ጋራ የሚኖር ሰው ብልህ ይሆናል፥ ከላዋቆች ሰዎች ጋራ አለል ዘለል የሚል ሰው ግን አላዋቂ ይሆናል ። ምሳ፡ ፲፩ ፲፭ ። |
| ለእለ ይኤብሱ ይዴግኖሙ እኩይ፥ ወለጻድቃንሰ ይረክቦሙ ሠናይ ። | ፳፬ | የሚበድሉትን ሰዎች ክፉ ነገር ያገኛቸዋል፥ ደጋግ ሰዎችን ግን በጎ ነገር ያገኛቸዋል ። |
| ኄር ብእሲ ይሬኢ ውሉደ ውሉድ፥ ወይዘገብ ለጻድቃን ብዕለ ረሲዓን ። | ፳፭ | ደግ ሰው የልጅ ልጅን ያያል፥ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ባለጠግነት ግን ለደጋጎች ሰዎች ይደልበል ። |
| ጻድቃን ይሄልዉ በብዕል ዓመታተ ብዙኀ፥ ወዓማፅያንሰ ይትኀጐሉ ፍጡነ ። | ፳፮ | ደጋግ ሰዎች በባለጠግነት ብዙ ዘመን ይኖራሉ፥ በደለኞች ሰዎች ግን ፈጥነው ይጠፋሉ ። ኤር፡ ፱ ፫ ። |
| ዘይምህክ በትሮ ጸልአ ወልዶ፥ ወዘያፈቅርሰ ወልዶ ወትረ ይጌሥፅ ። | ፳፯ | ልጁን በበትር መምታት የሚጠላ ሰው ልጁን ጠላ፥ ልጁን የሚወድ ሰው ግን ዘወትር ልጁን ይቀጣል ። |
| ጻድቅሰ እንዘ ይበልዕ ይመልእ ነፍሶ፥ ነፍሰ ረሲዓንሰ ፅኑስ ። | ፳፰ | ደግ ሰው እየበላ ሆዱን ይመላል፥ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሰውነት ግን የተቸገረ ነው ። |
| **ምዕራፍ ፲፬ ።** | | **ምዕራፍ ፲፬ ።** |
| ጠባባት አንስት ሐነፃ አብያተ፥ ወዐብዳትሰ ነሠታ አብያቲሆን በእደዊሆን ። | ፩ | ብልሀተኞች ሴቶች ቤታቸውን ሠሩ፥ ሰነፎች ሴቶች ግን በእጃቸው ቤታቸውን አፈረሱ ። ማቴ፡ ፳፭ ፩ ። |
| ዘየሐውር ፍኖተ ርቱዐ ይፈርሆ ለእግዚአብሔር፥ ወዘሰ ያጠዊ ፍኖቶ ይትሜነን ። | ፪ | በቀና ሥራ ፀንቶ የሚኖር እግዚአብሔርን ይፈራዋል፥ በጠማማ ሥራ ፀንቶ የሚኖር ሰው ግን ይናቃል ። |
| እምአፈ ዐብዳን ይወፅእ በትረ ጽእለት፥ ወከናፍረ ጠቢባንሰ ተዓቅቦሙ ። | ፫ | ከላዋቆች አፍ የስድብ ብትር ይወጣል፥ የብልሃተኞች ሰዎች ከንፈራቸው ግን ትጠብቃቸዋለች ። ሆሴ፡ ፮ ፲፮ ። |
| ወእደ አልቦ አልሕምት ምጽንጋዕ ንጹሕ፥ ወእደሰ ብዙኀ እክል ይትዓወቅ እምኃይለ ላሕሙ ። | ፬ | ላሞች ከሌሉ ዘንድ በረቱ ከፍግ ከእበት ንጹሕ ነው፥ ብዙ እኽል ካለ ዘንድ ግን ከበሬ ብዛት እንደሆነ ይታወቃል ። |
| ስምዐ መሃይምናን ኢይሔሱ፥ ወያነድድ ነፍሰ ሰማዕተ ሐሰት ። | ፭ | የደጋግ ሰዎች ምስክርነት ሐሰት አይሆንም፥ ሐሰተኛ ምስክር ግን ሐሰት መስክሮ ሰውን ይጐዳል ። |
| ተኃሥሣ ለጥበብ በኀበ እኩያን ወኢትረክበ፥ ወአእምሮሰ በኀበ ጠቢባን ቀሊል ። | ፮ | ጥበብን በክፉ ሰዎች ዘንድ ትፈልጋታለህ አታገኛትም፥ ዕውቀት ግን በአዋቆች ዘንድ ቀላል ናት ። |
| ኵሉ ርቱዕ በቅድሜሁ ለብእሲ ዐብድ፥ ወወልታ አእምሮ ከናፍረ ጠቢባን ። | ፯ | በላዋቂ ሰው ፊት ሁሉ የቀና ይመስለዋል፥ የብልሆች ከንፈሮች አመካከት የሚያውቅ እጅ እንደ ተመከተ ጋሻ ነው ። ዘፍ፡ ፳፩ ፲፮ ። |
| ጥበብ ለማእምራን ተአምር ፍኖቶሙ፥ ወለእለ ዘእንበለ ልብሰ ውስተ ስሒት ይከውን ፍኖቶሙ ። | ፰ | ያዋቆች ጥበባቸው ሥራቸውን ትገልጥባቸዋለች፥ አእምሮ የሌላቸው ሰዎች ግን ሥራቸው ወደ ስሕተት ይወስዳቸዋል ። |
| አብያቲሆሙ ለኃጥአን ይፈድዩ ለንጹሐን፥ ወአብያተ ጻድቃንሰ ሥሙር ። | ፱ | ኃጢአቶኞች (ዓሥሩ ነገድ) ቤቶቻቸውን ንጹሐን ለሆኑ ይሰጣሉ፥ ጻድቃን የሚሆኑ (የሁለቱ ነገድ) ቤት ግን የተወደደ ነው፥ (ለሁልቱ ነገድ) ። ምሳ፡ ፲ ፳፫ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ልበ ብእሲ ማእምር ኀዘን ለነፍሱ ፣ ወሶበሂ ይትፌሣሕ ኢይትሐወሶ ጽልእ ። | ፲ | ያዋቂ ሰው ልቡና ለሰውነቱ ኀዘን ነው ፣ ደስ በለውም ጊዜ ኃዘን ከልቡናው አይርቅም ። |
| አብያተ ረሲዓን ይማስኑ ፣ ወማኅደረ ራትዓንሰ ይቀውም ። | ፲፩ | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ቤቶቻቸው ይጠፋሉ ፣ የቅኖች ሰዎች ማደሪያ ግን ፀንቶ ይኖራል ። |
| በ ፍኖት እንተ ትመስል ርትዕተ በኀበ ሰብእ ፣ ወደኃሪታሰ ታበጽሕ ውስተ ማዕምቅተ ሲኦል ። | ፲፪ | በሰዎች ዘንድ ቀና የምትመስል ሥራ አለች ፣ በፍጻሜዋ ግን ሆድ መቃብር ወደ ገሃነም ታደርሳለች ። |
| ውስተ ፍሥሓ ኢይደመር ኃዘን ፣ ደኃሪታሰ ለፍሥሓ ውስተ ላሀ ትገብእ ። | ፲፫ | ኃዘን ከደስታ ጋራ አንድ አይሆንም ፣ የደስታ ፍጻሜዋ ግን ወደ ልቅሶ ትመለሳለች ። |
| እምፍኖተ ዚአሁ ይመልእ ዕቡየ ልብ ፣ ወብእሲ ኄር እምሕሊናሁ ይ መልእ በረከተ ። | ፲፬ | ልበ ትዕቢተኛ ሰው ከክፉ ሥራው የተነሣ መርገምን ይመላል ፣ ደግ ሰው ግን ከበጎነቱ የተነሣ በረከትን ይመላል ። |
| የዋህ የአምን ኵሎ ነገረ ፣ ማእምር በሕቱ ይገብእ ውስተ ንስሓ ። | ፲፭ | ያልተማረ ሰው የነገሩትን ሁሉ ያምናል ፣ የተማረ ሰው ግን እንዳለ አውቆ ወደ ንስሐ ይመለሳል ። |
| ጠቢብ ፈሪሖ ተግኅሠ እምእኩይ ፣ ወዐብድሰ ተአሚኖ ርእሶ ይጸመር ምስለ ዐብዳን ። | ፲፮ | ብልህ ሰው ፈርቶ ከክፉ ነገር ይርቃል ፣ አላዋቂ ሰው ግን ራሱን ተማምኖ ከላዋቂዎች ሰዎች ጋራ አንድ ይሆናል ። ምሳ፡ ፳፪ ፪ ። |
| መዓትም ይገብር ዘእንበለ ምክር ፣ ብእሲሰ ጠቢብ ብዙኀ ይትዔገሥ ። | ፲፯ | ቍጡ ሰው ሥራውን ያለ ምክር ይሠራል ፣ ብልህ ሰው ግን ብዙ ይታገሣል ። ምሳ፡ ፲፬ ፳፱ ። |
| ይትካፈሉ ዓብዳን እከየ ፣ ማእምራንሰ ይእኅዝዎ ለጠይቆ ። | ፲፰ | አላዋቂዎች ሰዎች ክፋትን ይከፈላሉ ፣ አዋቆች ሰዎች ግን ጥበብን ፈጥነው ይረዱታል ። |
| ይድኀፁ እኩያን በቅድመ ኄራን ፣ ወረሲዓንሰ ይትቀነዩ በኆኅተ ጻድቃን ። | ፲፱ | ክፉዎች ሰዎች በደጋግ ሰዎች ፊት ይሰነካከላሉ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በደጋግ ሰዎች ደጃፍ ይገዛሉ ። |
| አዕርክተ አብዕልት ይጸልኡ አዕርክተ ነዳያን ፣ አዕርክተ አብዕልትሰ ብዙኃን ። | ፳ | የባለጸጎች ወዳጆች የድኾች ወዳጆችን ይጠላሉ ፣ የባለጸጎች ወዳጆች ግን ብዙዎች ናቸው ። |
| ዘይሜንኖ ለነዳይ ይነዲ ፣ ወዘይምሕሮሰ ለዕጐስ ብፁዕ ውእቱ ። | ፳፩ | ድኻውን የሚንቅ ሰው ይቸገራል ፣ ለችጋረኛ የሚመጸውት ሰው ግን ንኡድ ክቡር ነው ። መዝ፡ ፵፩ ፩ ። |
| ስሑታን ይሔልዩ እከየ ፣ ወሣህለ ወጽድቀ ይሔልዩ ኄራን ፣ ወኢየአምሩ ሣህለ ወምሕረተ ጸረብተ እኪት ። | ፳፪ | ከሕገ እግዚአብሔር ወጥተው የሳቱ ሰዎች ክፋትን ያስባሉ ፣ ደጋግ ሰዎች ግን ይቅርታን ቸርነትን ያስባሉ ፣ ክፉ ሥራን የሚሠሩ ሰዎች ቸርነትንና ይቅርታን አያውቁም ። |
| ምሕረት በሕቱ ወሃይማኖት ኀበ ጸረብት ኄራን በኵሉ ሕሊና ትሩፍ ውእቱ ፣ ወላህይሰ ዘኢየሐምም ዕኑስ ውእቱ ። | ፳፫ | ነገር ግን ሃይማኖትና ቸርነት በጎ ሥራን ከሚሠሩ ሰዎች ዘንድ ይገኛል ፣ በፍጹም ልቡና ማረስ መቈፈርን ማሰብ ፍጹም ሥራ ነው ፣ በሥራ የማይደክም ሰውነት ግን የተቸገረ ነው ። ምሳ፡ ፲፩ ፳፭ ። |
| አክሊሎሙ ለጠቢባን ማእምር ወመምህሮሙ ለዐብዳን እኩይ ። | ፳፬ | የአዋቆች መምህራቸው አዋቂ (ክርስቶስ) ነው ፣ ያላዋቆች መምህራቸው ግን ክፉ (ዲያብሎስ) ነው ። |
| ያድኅን ነፍሰ እምእኩይ ሰማዕት ማእምር ፣ ወያነድድ ባሕቱ በሐሰት ሰማዕት መዓምፅ ። | ፳፭ | አዋቂ ምስክር እውነት መስክሮ ሰውነቱን ከክፉ ነገር ያድናል ፣ በደለኛ ምስክር ግን ሰውን በሐሰት መስክሮ ሰውን ያጠፋል ። |
| በፍርሃተ እግዚአብሔር ተስፋ ኃያል ወየኀድግ ለደቂቁ ጽንዐ ። | ፳፮ | እግዚአብሔርን በመፍራት ብዙ ተስፋ ይገኛል ፣ ለልጆቹም የፀና ሃይማኖትን ይተዋል ። |
| ትእዛዘ እግዚአብሔር ነቅዐ ሕይወት ፣ ወይሬሲ ከመ ይትገኃሡ እመሥገርተ ሞት | ፳፯ | እግዚአብሔር አዝዞ የሠራቸው ዓሠርቱ ቃላት የሕይወት ምንጭ ናቸው ፣ ሞት ከመጣው መከራ እንዲርቁም ያደርጋል ። ምሳ፡ ፲ ፲፩ ። |
| በብዝኀ አሕዛብ ክብሩ ለንጉሥ ፣ ወበውኀደተ አሕዛብ ድቀቱ ለመኰንን ። | ፳፰ | የንጉሥ መከበሩ በሠራዊት ብዛት ነው ፣ የንጉሥ መዋረዱ በሠራዊት ማነስ ነው ። |
| ብእሲ ነዊኀ መንፈስ ወርኂበ ልብ ጠቢበ ይከውን ። | ፳፱ | ነገር አሳሳፊ ልበ ሰፊ ሰው ብልህ ይባላል ። |
| ብእሲ መስተዐግሥ ብዙኀ ጠቢበ ይከውን ፣ ወኅፀፀ ነፍሱሰ ዕኑስ ዓብድ ውእቱ ። | ፴ | የታገሠ ሰው ፍጹም አዋቂ ይሆናል ፣ አእምሮ ያነሰው ሰው ግን ፍጹም አላዋቂ ነው ። ምሳ፡ ፲፭ ፲፰ ። |

| | | |
|---|---|---|
| አራቲ ብእሲ መፈውሰ ልብ ፡ ከመ ነቀዝ ለአዕፅምት ቅንአት ፡ ወትዝኅርት እኩይ ለልበ ማእምር ። | ፴፩ | ሰውን የሚያስታርቅ ሰው ልብን ደስ ያሰኛል ፡ ነቀዝ ለዕንጨት ክፉ እንደሆነ ፡ ትዕቢትና ቅንአትም ለአዋቂ ሰው ክፉ ነው ። |
| ዘይትዔገል ነዳየ ይዌህኮ ለፈጣሬሁ ፡ ወዘያከብሮሰ ይምሕር ነዳየ ። | ፴፪ | ድኻውን የሚቀማ ሰው ፈጣሪውን ያሳዝናል ፡ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሰው ግን ለድኻ ይመጸውታል ። |
| በእከዩ ይትአተት ረሲዕ ፡ ወዘይትአመንሰ ኂሩቶ ጻድቅ ውእቱ ። | ፴፫ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው በሞት ይርቃል ፡ በእግዚአብሔርም ቸርነት የሚታመን ሰው ግን ጻድቅ ነው ። |
| ውስተ ልብ ኄር ተኃርፍ ጥበብ ፡ ወውስተ ልበ ዐብድሰ ኢትትአመር ። | ፴፬ | ጥበብ በደግ ሰው ልቡና ታድራለች ፡ በላዋቂ ሰው ልቡና ግን በማደር አትታወቅም ። ምሳ፡ ፲፪ ፲፮ ። |
| ጽድቅ ታሌዕል ሕዝበ ፡ ወያሐፅፅ ኃጢአት ሕዝበ ። | ፴፭ | ጽድቅ ወገኖቿን ታከብራለች ፡ ኃጢአት ግን ወገኖቿን ያሳንሳል ። ዘፍ፡ ፳፯ ፳፱ ። |
| ሥሙር ለንጉሥ ላእክ ማእምር ፡ ወበተዓቅቦቱ ያርኅቅ ኃሣረ እምነፍሱ ፡ ወመዓት ታኀጉል ጠቢባነ ። | ፴፮ | አዋቂ መልእክተኛ በንጉሡ ዘንድ የተወደደ ነው ፡ በመጠበቁም ከሰውነቱ ተዋርዶን ያርቃል ፡ ቍጣ ብልሆችን ትጐዳለች ። ምሳ፡ ፲፮ ፲፫ ። |

## ምዕራፍ ፲፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| በነገር ዘይትጋነይ ይመይጥ መዓተ ፡ በሕቱ ቃል ማኅዝኒ ያነሥእ ጋእዘ ። | ፩ | በነገር የሚለማመጥ ሰው መዓትን ይመልሳል ፡ የሚያሳዝን ቃል ግን ጸብ ክርክርን ያነሣል ። |
| ልበ ጠቢባን ሠናየ ተአምር ፡ ወአፈ ዐብዳንሰ ይዜኑ እኩየ ። | ፪ | የብልሆች ልቡና በጎ ነገርን ያውቃል ፡ ያላዋቆች አንደበት ግን ክፉ ነገርን ይናገራል ። ምሳ፡ ፲፪ ፳፫ ። |
| ውስተ ኵሉ መከን አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ፡ ወያስተሐይፅ እኩያነ ወኄራነ ። | ፫ | የእግዚአብሔር ዓይኖቹ በቦታው ሁሉ የሞሉ ናቸው ፡ ክፉዎችንም በጎዎችንም ይመለከታል ። |
| መፈውሰ ልሳን ዕፀ ሕይወት ውእቱ ፡ ወዘሰ የዓቅብ ይመልእ መንፈሰ ። | ፬ | አንተም ተው ፡ አንተም ተው ብሎ የሚያስታርቅ አንደበት የሕይወት ዕንጨት ነው ፡ ምክር እዝናትን የሚጠብቅ ሰው ግን ጸጋ ክብር ያገኛል ። ምሳ፡ ፫ ፲፫ ። |
| ወልድ ዓብድ ያስተአኪ ተግሣፀ አብ ፡ ወዘሰ የዓቅብ ተግሣፀ ጠቢብ ውእቱ ። | ፭ | አዋቂ ልጅ የአባቱን ምክር እዝናት ያከፋፋል ፡ ምክር እዝናትን የሚጠብቅ ልጅ ግን ብልህ አዋቂ ነው ። |
| ወእደ ትበዝኅ ጽድቅ ኃይል ብዙኅ ፡ ወረሲዓንሰ እምሥርዎሙ እምድር ይሤረዉ ። | ፮ | እውነት ነገር ካለ ዘንድ ብዙ ተአምራት ይደረጋል ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ከዚህ ዓለም ከሥር መሠረታቸው ይጠፋሉ ። |
| ከናፍረ ጠበብት እሡር በአእምሮ ፡ ወልበ ዐብዳንሰ አከ ጽኑዕ ። | ፯ | የመምህራን ከንፈሮች በዕውቀት የፀኑ ናቸው ፡ ያላዋቆች ልቡና ግን በዕውቀት የፀና አይደለም ። |
| መሥዋዕተ ረሲዓንሰ ርኩስ በኀበ እግዚአብሔር ፡ ወጸሎተ ኄራንሰ ሥሙር በኀቤሁ ። | ፰ | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች መሥዋዕታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው ፡ የደጋግ ሰዎች መሥዋዕት ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው ። |
| ርኩስ በኀበ እግዚአብሔር ፍኖተ ረሲዓን ፡ ወለእለሰ ይዴግንዋ ለጽድቅ ያፈቅሮሙ እግዚአብሔር ። | ፱ | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው ፡ ሥራን የሚከተሉ ሰዎች ግን እግዚአብሔር ይወዳቸዋል ። |
| ትእምርተ የዋሃን ትትዓወቅ በኀበ እለ የኀልፉ ፡ ወእለሰ ይጸልኡ ዝልፈተ ይመውቱ በእኩይ ። | ፲ | የደጋግ ሰዎች ትምህርታቸው አልፈው በሚሄዱ ሰዎች ትታወቃለች ፡ ማስተማርን የሚጠሉ ሰዎች ግን በክፉ ስንፍና እንደ ተያዙ ይሞታሉ ። ፩ኛ ነገ፡ ፳፪ ፲ ። |
| ገሃነም ወሞት ክሡታን በኀበ እግዚአብሔር ፡ እፎ እንከ ልበ ሰብእኒ ። | ፲፩ | ሞትና መቃብር በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጡ ናቸው ፡ የሰው ልቡናማ እንዴት የተገለጠ አይሆን ፤ |
| ኢያፈቅር ዓብድ እለ ይጌሥፅዎ ፡ ወምስለ ጠቢባን ኢይትናገር ። | ፲፪ | አላዋቂ ሰው የሚመክሩትን ሰዎች አይወድም ፡ ከመምህራንም ጋራ አይጫዋወትም ። |
| ልብ እምከመ ትትፌሣሕ ትበርህ ገጽ ፡ ወእመሰ ተኀዝነ ትደምን ። | ፲፫ | ልቡና ደስ ካላት ፊት የበራች ትሆናለች ፡ ልቡና ብታዝን ግን ፊት ትጠቍራለች ። ምሳ፡ ፲፯ ፳፪ ። |
| ልብ ርትዕት ተኀሥሥ አእምሮ ፡ አፈ ዓብዳንሰ የኀሥሥ እከየ ኵሉ መዋዕለ ። | ፲፬ | የቀናች ልቡና ዕውቀትን ትፈልጋለች ፡ ያላዋቆች አፍ ግን በለ ዘመናቸው ሁሉ ክፉትን ይፈልጋል ። |

| | | |
|---|---|---|
| አዕይንተ እኩያን ይሴፈዋ እኩየ ፡ ወኄራንሰ ያረምሙ በኵሉ ጊዜ ። | ፲፭ | የክፉ ሰዎች ዓይኒ ልቡና ክፋትን ተስፋ ያደርጋል ፡ ደጋግ ሰዎች ግን በጊዜው ሁሉ ዝም ይላሉ ። |
| ትኄይስ ንስቲት መክፈልት ዘበፍርሃተ እግዚአብሔር እመዛግብት ዓበይት ዘበኢፈሪሀ ። | ፲፮ | እግዚአብሔርን በለ መፍራት ካለ ብዙ በለ ጠግነት እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋራ ያለ ጥቂት ሃብት ይሻላል ። |
| ይኄይስ ፍተ ሐምል ፍቅር ዘበቱ ፡ እምላሕም መግዝዕ ዘበቱ ጽልእ ። | ፲፯ | ጠብ ካላበት ጮማ ፍሪዳ፡ ፍቅር ያለበት የጎመን ቅርጻጅ ይሻላል ። ምሳ፡ ፲፯ ፩ ። |
| ብእሲ መዓትም ያስተዴሉ ጋእዘ ፡ ወመስተዓግሥኒ ብእሲ እንተ ከነትኒ ያጠፍኢ ፡ ወረሲዕሰ ያነሥእ ጥቀ ጽልአ ። | ፲፰ | ቍጡ ሰው ጸብ ክርክርን ያዘጋጃል ፡ ታጋሽ ሰው ግን ትንታግን ስንኳ ያጠፋል ፡ እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ግን ፈጽሞ ጠብን ያነሣል ። ምሳ፡ ፲፯ ፳፰ ። |
| ፍናወ ሃካይያን ንጹፍ አሥዋክ ፡ ወዘጽኑዓንሰ መጽያሕት ። | ፲፱ | የሀኬተኞች ሰዎች መንገዳቸው እሾኽ ተነጥፎበታል የልበሞች ሰዎች ግን መንገዳቸው ጥርጊያ ነው ። |
| ወልድ ጠቢብ ያስተፌሥሕ አበሁ ፡ ወወልድ ዓብድ ያጼእል እሞ ። | ፳ | አዋቂ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል ፡ አላዋቂ ልጅ ግን እናቱን ያሰድባል ። ምሳ፡ ፲ ፩ ። |
| ፍናወ ዓብድ ነዳየ አእምሮ ጠዋያት ፡ ወብእሲሰ ጠቢብ አርቲዖ የሐውር ። | ፳፩ | ከዕውቀት የተቸገረ ሰው ሥራዎች ጠማሞች ናቸው ፡ ብልህ ሰው ግን በቀን ሥራ ፀንቶ ይኖራል ። |
| ያጠርዩ ሕሊና እለ ያከብሩ ማኅበረ ፡ ወውስተ ልበ መከርያን ትነብር ምክር ። | ፳፪ | ዓሥርቱ ቃላተ ኦሪትን የሚያከብሩ ሰዎች ዕውቀትን ገንዘብ ያደርጋሉ ፡ በመከሮችም ልቡና ምክር ፀንታ ትኖራለች ። ምሳ፡ ፲፩ ፲፬ ። |
| ወኢይሰምዓ ላቲ እኩይ ፡ ወእልበ ዘይብል ጥዑም ወሠናይ ለማኅበር ። | ፳፫ | ክፉ ሰው ምክሩን አይሰማትም ዓሥርቱ ቃላተ ኦሪት ይህ ክፉ ነው ፡ ይህ ደግ ነው የሚል የለም ። |
| ፍናወ ሕይወት ሕሊናሁ ለጠቢብ ከመ ተግኂሦ እምሲኦል ይድኀን ። | ፳፬ | ከክፉ ነገር ርቆ ከሲኦል ይድን ዘንድ ፡ የብልህ ሰው አሳቡ የሕይወት መንገድ ነው ። ቆላስ፡ ፫ ፩-፪ ። |
| አብያተ ጸአልያን ያነኅል እግዚአብሔር ወያጸንዕ ወሰነ መበለት ። | ፳፭ | የተሳዳቢዎችን ቤት እግዚአብሔር ያፈርሳል (ያሥሩ ነገድ) የደኻይቱን ድንበር ግን (የሁለቱን ነገድ) ያፀናል ። |
| ምኑን በኀበ እግዚአብሔር ሐልዮ ዓመፃ ፡ ወለንጹሐንሰ ነገሮሙ አዳም ። | ፳፮ | ዓመፅን ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነው ፡ የንጹሐን ሰዎች ግን ነገራቸው ያማረ ነው ። |
| ያኀጕል ርእሶ ዘሕልያነ ይነሥእ ፡ ወዘይጸልእሰ ነሢአ ሕልያን ይድኀን ። | ፳፯ | መማለጃን የሚቀበል ሰው ራሱን ያጠፋል ፡ መማለጃን መቀበል የሚጠላ ሰው ግን ከፍዳ ይድናል ። |
| በምጽዋት ፡ በሃይማኖት ፡ ይሠረይ ኃጢአት ፡ ወበፈሪሃ እግዚአብሔር ይትገኃሥ ኵሉ እኩይ ። | ፳፰ | በሃይማኖትና በምጽዋት ኃጢአት ይቃለላል ፡ እግዚአብሔርን በመፍራት መከራ ሁሉ ይርቃል ። |
| ልበ ጻድቃን ይትሜሀር ሃይማኖተ ፡ ወአፈ ረሲዓንሰ ያወሥእ እኩያተ ። | ፳፱ | የደጋጎች ልቡና ሃይማኖትን ይማራል ፡ የክፉ ሰዎች አፍ ግን ክፉ ነገርን ይናገራል ። |
| ሥሙራት በኀበ እግዚአብሔር ፍናወ ሰብእ ጻድቃን ፡ ወበእንቲአሆሙ ጸላእትኒ አዕርክተ ይከውኑ ። | ፴ | የደጋግ ሰዎች ሥራቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደዱ ናቸው ፡ ስለ ደጋግ ሰዎች ደግነት ጠላቶች ወዳጆች ይሆናሉ ። መዝ፡ ፴፯ ፴ ። |
| ነዋኅ ይርኅቅ እግዚአብሔር እምረሲዓን ፡ ወጸሎተ ጻድቃንሰ ይሰምዕ ፡ ይኄይስ ኅዳጥ ኅብስት ምስለ ጽድቅ ፡ እምብዙኅ ፍሬ ዘምስለ ዓመፃ ። | ፴፩ | እግዚአብሔርን ከዘነጉ ሰዎች እግዚአብሔር ፈጽሞ ይርቃል ፡ (ልመናቸውን አይሰማቸውም) የደጋጎች ልመና ግን ይሰማል ፡ ከዓመፅ ጋራ ካለ ብዙ በለጠግነት ከእውነት ጋራ ያለ ጥቂት ሃብት ይሻላል ። |
| ልበ ብእሲ ኄር ይሔሊ ጽድቀ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ይረትዕ አሠሩ ፡ ዓይን ዘይኔጽር ሠናየ ያስተፌሥሕ ልበ ፡ ወዜና ኂሩት ያጠልል አዕፅምተ ። | ፴፪ | ሥራው ከእግዚአብሔር ይቀናለት ዘንድ የደግ ሰው ልቡና በጎ ነገርን ያስባል ፡ በጎ ነገርን የሚመለከት ዓይን ልቡናን ደስ ያሰኛል ፡ በጎ ወሬ አጥንትን ያለመልማል ። |
| ዘይሰምዖ ዘለፋ ጠቢብ ፡ ምስለ ጠቢባን ይዴመር ። | ፴፫ | የብልህን ምክር የሚሰማ ሰው ከብልሆች ጋራ አንድ ይሆናል ። ምሳ፡ ፲፭ ፭ ፤ ፲፱ ፴፫ ። |
| ወዘይትከላእ እምተግሣፅ ይጸልእ ርእሶ ፡ ዘያፈቅርሰ ተግሣፀ ያፈቅር ርእሶ ። | ፴፬ | ከምክር እዝናት የሚከለከል ሰው ራሱን ይጠላል ፡ ምክር እዝናትን የሚወድ ሰው ግን ራሱን ይወዳል ። |

| ምዕራፍ ፲፮ ። | | ምዕራፍ ፲፮ ። |
|---|---|---|
| ፈሪሀ እግዚአብሔር አእምሮ ሠናይ ወጥበብ፡ ቀዳሚት ክብር ይእቲ ለዘያወሥአ ላቲ ፡ ወትተልዎሙ ለየዋሃን ክብር ። | ፩ | እግዚአብሔርን መፍራት ዕውቀትንና በጎ ዕውቀት ናት ፡ እሷን ለሚያስተምራት ሰው የክብር መጀመርያ ናት ለደጋግ ሰዎች ክብር ትከተላቸዋለች ። |
| ኵሉ ምግባሩ ለትሑት ሥሙር በኀበ እግዚአብሔር፡ ወረሲዓንሰ ይትኀጐሉ በዕለት እኪት ። | ፪ | ራሱን የሚያዋርድ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ሥራው ሁሉ የተወደደ ነው ፡ ስመ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን መከራ በታዘዘችበት ቀን ይጠፋሉ ። |
| ርኩስ በኀበ እግዚአብሔር ዕቡየ ልብ፡ እደ በእድ ዘይእኀዝ በዓመፃ ኢይነጽሕ ። | ፫ | ልበ ትዕቢተኛ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው ፡ በእጁ የጒልማሳ ሚስትን እጅ የሚይዝ ሰው ከፍዳ አይነፃም ። ኢሳ፡ ፵፫ ፯ ። ሮሚ ፲፩ ፴፯ ። |
| ቀዳሚት ፍኖት ኄርት ገቢረ ጽድቅ፡ ሥሙር በኀበ እግዚአብሔር ጥቀ እምዘቢሐ መሥዋዕት ። | ፬ | የዘጠኙ ሕግጋት አበጋዝ የምትሆን ኢታምልክ ደግ ናት ፡ በጎ ሥራ መሥራት መሥዋዕትን ከመሠዋት ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደ ነው ። |
| ዘየኀሥሥ ለእግዚአብሔር ይረክብ አእምሮ በጽድቅ። | ፭ | እግዚአብሔርን በአምልኮት የሚፈልገው ሰው ፡ በእውነት ዕውቀትን ያገኛል ። ምሳ፡ ፫ ፫ ። |
| ወእለሰ ርትዐ የኀሥሡ ይረክቡ ሰላመ ። | ፮ | የቀና ነገርን የሚፈልጉ ሰዎች ፍቅር አንድነትን ያገኛሉ ። |
| ኵሉ ምግባሩ ለእግዚአብሔር ዘምስለ ጽድቅ ። | ፯ | የእግዚአብሔር ሥራው ሁሉ ከቸርነት ጋራ ነው ። |
| ይትዓቀብ ረሲዕ ለዕለት እኪት ። | ፰ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ለክፉ ቀን ይጠበቃል ። |
| ሰገል ውስተ አፈ ንጉሥ ፡ ወበፍትሕ ኢይጌጊ አፉሁ ። | ፱ | ጥበብ በንጉሥ አፍ አለ ፡ በፍርድም ጊዜ አፉ ተግተግ አይልም ። |
| ከመ ለጸሊጸ ልሳነ መዳልው ፍትሐ እግዚአብሔር ወምግባሩሂ አእባነ ቍናማት ። | ፲ | የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ሚዛን አንደበት ውልብልቢት ነው ፡ ሥራውም በአቍማዳ እንደ ደንጊያዎች ነው ። ኢሳ፡ ፵ ፲፪ ። |
| ምኑን በኀበ እግዚአብሔር መዳልወ ዓመፃ ፡ ወምኑን በኀበ ንጉሥ ዘይገብር እኩየ ወምስለ ጽድቅ ይነብር መንበረ ምኩናን ። | ፲፩ | በእግዚአብሔር ዘንድ አበይ ሚዛን (ዳኛ) የተናቀ ነው ክፉ ሥራንም የሚሠራ ሰው በንጉሥ ዘንድ የተናቀ ነው ፡ የአገዛዝ ዙፋን ከበጎነት ጋር ፀንቶ ይኖራል ። |
| ሥሙር በኀበ ንጉሥ ከናፍረ ጽድቅ ፡ ወነገረ ርቱዐ ያፈቅር እግዚአብሔር ። | ፲፪ | እውነት ነገርን የሚናገር ከንፈር በንጉሥ ዘንድ የተወደደ ነው ፡ የቀና ነገርን እግዚአብሔር ይወዳል ። |
| መዓተ ንጉሥ ከመ መልአከ ሞት ፡ ወብእሲ ጠቢብ ይዌውሆ ። | ፲፫ | የንጉሥ ቍጣ እንደ መልአከ ሞት ነው ፡ ብልሀ ሰው ግን ያቈላምጠዋል ። ምሳ፡ ፲፱ ፲፪ ። |
| ከመ ብርሃነ ፀሐይ ገጸ ንጉሥ ፡ ወበእለ ኢያሠምርዎሰ ከመ ደመና ምሴት ። | ፲፬ | የንጉሥ ፊት እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው ፡ ደስ ባላሰኙት ሰዎች ግን ጨለማ እንደ ተከተለው ደመና ነው ። |
| አጥርዮታ ለጥበብ ይትበደር እምወርቅ ፡ ወአጥርዮታ ለአእምሮ ይኄይስ እምብሩር ። | ፲፭ | ጥበብን ገንዘብ ማድረግ ከወርቅ ይልቅ ይወደዳል ፡ ብርን ገንዘብ ከማድረግ ዕውቀትን ገንዘብ ማድረግ ይሻላል። |
| ፍናወ ሕይወት ያግኅሣ እምእኩይ ፡ ወኑኀ መዋዕል ፍናወ ጽድቅ ። | ፲፮ | የሕይወት ሕግጋት የሚሆኑ ዐሠርቱ ቃላት ከክፉ ነገር ያርቃሉ ፡ የዘመንም ብዛት እውነተኛ ሕግጋቱን በመጠበቅ ይገኛል ። |
| ዘይትዌከፍ ትምህርተ ውስተ ሠናይ ይሄሉ ፡ ወዘየዓቅቦ ተግሣፀ ይጠበብ ። | ፲፯ | ትምህርትን የሚቀበል ሰው በበጎ ነገር ይኖራል ፡ ምክር አዝናትን የሚጠብቅ ሰው ብልህ አዋቂ ይሆናል ፡ ሰውነቱን ይጠብቃል ። |
| ፍናዊሁ ይትመኀፀና ለነፍሱ ፡ ወዘያፈቅር ሕይወቶ ይዕቀብ አፉሁ ። | ፲፰ | ሕጉን የሚጠብቅ ሰው ሰውነቱን እንደ አደራ ዕቃ ያስጠብቃታል ፡ ኑሮውን የሚወድ ሰው አፉን ከፉ ነገርን ከመናገር ይጠብቅ ። |
| እምቅድመ በእስ ይቀድም ጽኢል ፡ ወእምቅድመ ድቀት አእምሮ እኩይ ። | ፲፱ | ከመቀራደዱ ስድቡ ይቀድማል ፡ መከራ ከመምጣቱም አስቀድሞ የሚጠፋበትን ማወቅ ይቀድማል ። |
| ይኄይስ ኀራቄ መዓት ዘበአትሕቶ ፡ እምዘይትካፈል በርበረ ምስለ ጸአልያን ። | ፳ | ከተሳዳቢዎች ጋራ ምርኮን ከሚካፈል ሰው ፡ አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ቍጣን የሚያርቅ ሰው ይሻላል ። |

፳፩ ማእምር ዘበምግባሩ ረከቢሆን ለኄራት ፣ ወዘይትዌከል በእግዚአብሔር ፡ ብፁዕ ፡፡

፳፪ ለጠቢብ ማእምረ ይሰምዩዎ ፣ ወለጥዑመ ቃል ፈድፋደ ይጼውዕዎ ፡፡

፳፫ ነቅዐ ሕይወት ሕሊና ሠናይት ለእለ አጥረይዋ ፣ ወትምህርተ ዐብዳንሰ እኪት ፡፡

፳፬ ልበ ጠቢብ ይትአመር እምአፉሁ ፣ ወውስተ ከናፍሪሁ ይለብስ ተዓውቆ ፡፡

፳፭ ጸቃውዓ መዓር ነገር ሠናይ ፣ ወመዓርዒሮን ፈውሰ ነፍስ ፡፡

፳፮ በ ፍናው ዘይመስላሁ ለብእሲ ርቱዓት ፣ ወጽንፎንኒ ይኔጽሩ ማዕምቅተ ሲኦል ፡፡

፳፯ ብእሲ በሕማሙ የሐምም ለርእሱ ፣ ወይትኄየል በርእሱ ኃጕል ፣ ወበሕቱ ጠዋይ ውስተ አፉሁ ይለብስ ኀጕለ ፡፡

፳፰ ብእሲ ዓብድ ይከሪ ለርእሱ እከየ ፣ ወውስተ ከናፍሪሁ ይዘግብ እሳተ ፡፡

፳፱ ብእሲ ጠዋይ ይልእክ እከየ ፣ ወማኅቶተ ሐብል ታውዕዮሙ ለእኩያን ፣ ወትሌሊ አዕርክተ ፡፡

፴ ብእሲ እኩይ የሐብል አዕርክተ ፣ ወይወስዶሙ ፍናወ እለ ኢኮና ኄራተ ፡፡

፴፩ ዘያወትር በአዕይንቲሁ ይሐሊ ጠዋየ ፣ ወዘያቤይድ በከናፍሪሁ ኵሎ እኩየ ዘእቶነ እከይ ውእቱ ፡፡

፴፪ አክሊለ ምክሕ ርሥዕ ሠናይ ፣ ወውስተ ፍናወ ጽድቅ ይትረከብ ፡፡

፴፫ ይኄይስ ብእሲ ዕጉሥ እምኃያል ፣ ወብእሲ ዘጥበብ በቱ እምወፍር ዓቢይ ፡፡

፴፬ ዘይሜለጥ በመንፈሱ እምዘይመልክ ሀገረ ፣ ወዘይትዔገሥ መዓተ ይኄይስ እምዘ ያስተጋብእ ሀገረ ፡፡

፴፭ ለብእሲ ዓማፂ ውስተ ኅፅኑ ይገብእ ኵሉ ዓመፃሁ ፣ ወእምኀበ እግዚአብሔር ኵሉ ጻድቅ ፡፡

## ምዕራፍ ፲፯ ፡፡

፩ ይኄይስ ፍት ጥዑም ምስለ ሰላም እምቤት ዘምሉእ ብዙኀ ሠናያተ ወእምዘ ዓመፃ ጥብሕ ምስለ ጋእዝ ፡፡

፪ ገብር ጠቢብ ይሜብል አጋእዝተ ዐብዳነ ፣ ወምስለ አኃው ይትከፈል ርስተ ፡፡

፫ በከመ ይትፈተን ወርቅ ወብሩር በከውር ከማሁ ኅሩያነ ልብ በኀበ እግዚአብሔር ፡፡

፬ እኩየ ያሰምዕ ልሳኖሙ ለእለ ዘእንበለ ሕግ ፣ ጻድቅሰ ኢይኔፅር ከናፍረ ሐሰት ፡፡

በጎ የሚሆኑ ዐሠርቱ ቃላትን በግብር የሚሠራቸው ብልህ ዐዋቂ ነው ፣ በእግዚአብሔርም የሚያምን ሰው ንኡድ ክቡር ነው ፡፡ መዝ፡ ፪ ፲፪ ፤ ፳፭ ፪ ፡፡

የተማረን ሰው ዐዋቂ ይሉታል ፣ ነገርን የሚያውቅ ሰውን ይልቁንም ይጠሩታል ፡፡

በጎ ዕውቀት የምትሆን ሕገ እግዚአብሔር ገንዘብ ላደረጓት ሰዎች የሕይወት መገኛ ናት ፣ ያላዋቂዎች ትምህርት ግን ክፉት ናት ፡፡ ምሳ፡ ፲ ፲፩ ፡፡

የብልህ ሰው ዕውቀቱ በአፉ ይታወቃል በከንፈሩም ዕውቀትን ይናገራል ፡፡ መዝ፡ ፴፮ ፴ ፡፡ ማቴ፡ ፲፪ ፴፬ ፡፡

መልካም ነገር እንደ ማር ወለላ ነው ፣ ጣዕማቸው ደግሞ እውነትን የሚያድስ መድኃኒት ነው ፡፡

ለሰው የቀና የሚመስሉ ሥራዎች አሉ ፍጻሚያቸው ግን ወደ መቃብር ያደርሳሉ (ዓለም ሹመት ሴት) ፡፡

ሰው በደከማ ባሕርዩ ራሱን ለመጥቀም መከራን ይቀበላል ፣ ችጋርም በራሱ ይሰለጥንበታል ፣ ነገር ግን ጠማማ ሰው በአፉ ጥፋትን ይናገራል ፡፡ ኢዮ፡ ፭ ፳፪ ፡፡

አላዋቂ ሰው ራሱን ለመጕዳት ክፋት ይሠራል ፣ በከንፈሩ በተናገረው ነገር መቅሠፍትን ይደልበል ፡፡

ጠማማ ሰው ክፋትን ከሁሉ ያደርሳል ፣ ሐሰትን መርምረው መሥራታቸው ኃጢአተኞችን ታጠፋቸዋለች ፣ ይህችም ሐሰት ወዳጅ ከወዳጅ ትለያለች ፡፡

ክፉ ሰው ነገር ሠርቶ ወዳጅንና ወዳጅን ያለያያል ፣ በጎ ወዳይደሉ ሥራዎችም ይወስዳቸዋል ፡፡

በዓይኖቹ ክፉ የሚመለከት ሰው ጠማማ ነገርን ያስባል ፣ ክፉውን ሰው ሁሉ በከንፈሩ ወዳጅ የሚያደርግ ይህ ሰው የክፋት ምድጃ ነው ፡፡

በጎ እርጅና የሚያስመካ ዘውድ ነው ፣ ይኸውም እውነተኛ ሥራዎችን በመጠበቅ ይገኛል ፡፡

ከኃይለኛ ሰው የታገሠ ሰው ይሻላል ፣ ብዙ ርስተ ጕልት ካለው ጥበብ ያለው ሰው ይሻላል ፡፡

አገርን ከሚገዛ ሰው በሰውነቱ የሠለጠነ ሰው ይሻላል አገርን ከሚሰበስብ ሰው ቍጣን የሚታገሥ ሰው ይሻላል ፡፡ ምሳ፡ ፲፱ ፲፩ ፤ ፳፭ ፳፰ ፡፡

በደለኛ ሰው ፍዳው ሁሉ ወደ ሰውነቱ ይመለሳል ፣ ደግ ሰው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋውን ያገኛል ፡፡

## ምዕራፍ ፲፯ ፡፡

ብዙ ተድላ ደስታን ከተመላ ጠብ ክርክር ካለበት ጮማ ፍሪዳም ፣ ከፍቅር ጋራ ያለ ጥቂት ቍራሽ ይሻላል ፡፡

ብልህ በርያ ሰነፎች ጌቶችን ይገዛል ፣ ከወንድማማቾችም ጋራ ርስትን ይከፈላል ፡፡

ወርቅ ብር በከውር እንዲፈተን ፣ በዕውቀት የተመረጡም ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ እንደዚሁ በመከራ ይፈተናሉ ፡፡ ምሳ፡ ፳፯ ፳፩ ፡፡ መዝ፡ ፳፯ ፪ ፡፡

ያልተማሩ ሰዎች አንደበት ክፉ ምስክርነትን ይመሰክራል ፣ ደግ ሰው ግን በከንፈሩ ሐሰትን አይመሰክርም ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ለምእመን ኵሉ ዘበዓለም ንዋዩ ወለዘኢምእመንሰ ኢፀሬቅ ሉቱ ። | ፭ | የሚያምን ሰው በዓለም ያለው ሁሉ ገንዘቡ ነው፣ ለማያምን ሰው ግን ሻሚ መሐልቅ ስንኳ የለውም ። |
| ዘይስሕቆ ለነዳይ ይዌህኮ ለፈጣሪሁ፣ ወዘይትፌሣሕ ላዕለ ዘይትኀጐል ኢይድኅን ወዘይምሕርሰ ይትሜሐር ። | ፮ | በድኻው የሚስቅ ሰው ፈጣሪውን ያሳዝነዋል፣ በቀጠና ተይዞ በሚሞት ሰው ደስ የሚለው ከፍዳ አይድንም የሚመጸውት ሰው ግን ይቅር ይባላል ። |
| አክሊሎሙ ለአእሩግ ውሉደ ውሉድ፣ መምክሖሙ ለውሉድ አበዊሆሙ ። | ፯ | የሽማግሌች ዘውዳቸው የልጅ ልጅ ማየት ነው፣ የልጆችም መመኪያቸው አባቶቻቸው ናቸው ። |
| ኢይትዋደዶ ለዐብድ ከናፍረ መሃይምንት፣ ወኢ ጻድቅ ከናፍረ ሐሰት ። | ፰ | የታመነች ከንፈር ላላዋቂ ሰው አትስማማውም፣ ለእውነተኛ ሰውም የሐሰት ከንፈር አትስማማውም ። |
| ዓስበ ሞገስ ትምህርት ለእለ አጥረይዋ ኀበ ተመይጠ ቃሜኒ ፍኖቶ ። | ፱ | ትምህርት ገንዘብ ላደረጋት ሰው መወደድ ያለው ዕንቊ ናት፣ ወደሷ ከተመለሰ ዘንድ መንገዱን ታቃናለታለች። |
| ዘየኀብእ አበሳሁ ይፈቅድ ዕርቀ፣ ወዘይጸልእሰ ኀቢአ ይሌሊ አዕርክተ ወሰብአ ቤት ። | ፲ | በደሉን የሚሠውር ሰው እርቅን ይወዳል፣ በደሉን መሠወር የሚጠላ ሰው ግን ቤተ ሰብንና ወዳጅን ይለያል። |
| የኃዝን ትምክሕት ልበ ጠቢብ፣ ወዐብድሰ ተቀሢፎ ኢይትዓወቆ ቅሥፈቱ ። | ፲፩ | ትምክሕት የብልህ ሰው ልቡናን ያሳዝናል፣ ሰነፍ አላዋቂ ግን ከተገረፈ በኋላ ግርፋቱ አያሳዝነውም ። |
| ቅስተ ያነሥእ ኵሉ እኩይ፣ ወእግዚአብሔር ይፌኑ መልአከ ዘእንበለ ምሕረት በቱ ። | ፲፪ | ክፉ ሰው ሁሉ ክርክርን ያነሣል፣ እግዚአብሔርም ርኅራኄ የሌለው መልአኩን ይልክበታል ። |
| ይወድቅ ብእሲ ማእምር ውስተ ትካዝ፣ ወዐብዳንሰ ይሔልዩ እኩየ ። | ፲፫ | አዋቂ ሰው በኃዘን ይኖራል፣ አላዋቆች ሰዎች ን ክፋትን ያስባሉ ። ፪ኛ ሳሙ፣ ፲፯ ፰ ። |
| ዘየዓሢ እኩየ ህየንተ ሠናይ፣ ኢያንቀለቅል እኩይ እምነ ቤቱ ። | ፲፬ | ስለ በጎ ሥራ ክፉ ሥራን የሚመልስ ሰው፣ ከቤ. ከወገኑ ክፉ ነገር አይርቅም ። ማቴ፣ ፭ ፴፱ ። |
| ዐቢወ ማይ ቀዳሚ ጽልእ፣ ወመኰንና ለንዴት ጋእዝ ወበእሰ ሥልጣን ነገር ይሁብ ቀዳሚ ጽድቅ ። | ፲፭ | ውኃን መድፈን የጠብ መጀመርያ ነው፣ የዘጠኙ ሕግጋት አበጋዝ ኢታምልክ በነገር መሠልጠንን ይሰጣል፣ የችግርም አበጋዝ ፀብ ክርክር ነው ። |
| ዘከመ ጻድቅ ይኴንኖ ለኃጥእ ወዘከመ ኃጥእ ለጻድቅ ርኩስ ምኑን በኀበ እግዚአብሔር ። | ፲፮ | ይሙት በቃውን ይድን በቃ፣ ይድን በቃውን ይሙት በቃ ብሎ መፍረድ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጸይፍ ነው የተናቀም ነው ። ኢዮብ ፴፬ ፲፯ ። |
| ለምንት ጥሪት ለዐብድ አጥርዮታ ለጥበብ ዘእንበለ ልብ ኢይትከሀል ። | ፲፯ | ላላዋቂ ሰው (ሹመት) ገንዘብ ለምኑ ነው፣ ያለ ዕውቀት ጥበብን ገንዘብ ማድረግ አይቻልም ። |
| ዘያነውኅ ቤቶ የኃሥሥ ቅጥቃጤ ለርእሱ ወዘያስተ ዓዕብ ለተምህሮ ይወድቅ ውስተ እኪት ። | ፲፰ | ቤቱን ከፍ ካለ ቦታ ላይ የሚሠራ ሰው ለራሱ ጥፋትን ይፈልጋል፣ ተማር ሲሉት ዕፁብ ዕፁብ የሚል ሰው በመከራ ይወድቃል ። |
| በኵሉ ጊዜ አጥሪ ዓርከ ወአኃወ፣ በምንዳቤ በቋዕያኒ ይከውኑ እስመ በእንተዝ ይትወለዱ ። | ፲፱ | በየጊዜው ወዳጅን ወንድሞችንም አብጅ፣ ስለዚህ ይወለዳሉና በመከራ ጊዜ የሚረቡ የሚጠቅሙ ይሆናሉ ። |
| ብእሲ ዓብድ ይጠፍሕ እዴሁ ወይትኄሠይ በርእሱ ከመ ዘይትሀበይ ሀቢተ ለዐርኩ ። | ፳ | አላዋቂ ሰው ወዳጁን የሚዋስ ሰው ደስ እንዲለው፣ ራሱን ለመጕዳት ለጠላቱ የሚዋስ ሰውም ደስ ብሎት እጁን ያጨበጭባል ። |
| መፍቀሬ ጋእዝ ይትፌሣሕ በባእስ ወጽኑዐ ልብሰ ኢይዳደቅ ሠናየ ። | ፳፩ | ጸብ ክርክርን የሚወድ ሰው በፀቡ በክርክሩ ደስ ይለዋል፣ ልቡናው በኃጢአት የጸና ሰው ግን በጎ ነገርን አይሠራም ። |
| ብእሲ መያጤ ልሳን ይወድቅ ውስተ እኪት፣ ወልበ ዐብድሰ ኃዘን ለዘአጥረያ ። | ፳፪ | አንደበቱን የሚለዋውጥ ሰው በመከራ ይወድቃል፣ የሰነፍ ሰው ልቡናም ገንዘብ ላደረጋት ኃዘን ናት ። |
| ኢይትፌሣሕ አብ በወልድ፣ ዘእንበለ ትምህርት ወልድ ጠቢብ ያስተፌሥሕ እሞ ። | ፳፫ | ባልተማረ ልጅ አባቱ ደስ አይለውም፣ የተማረም ልጅ እናቱን ደስ ያሰኛል ። ምሳ፣ ፲፯ ፳፭ ። |
| ልብ ፍሥሕት ሠናየ ትገብር፣ ብእሲ ኃዛኒ ያየብስ አዕፅምቲሁ ። | ፳፬ | ደስ የምታሰኝ ልቡና በጎ ትሠራለች፣ የብስጭት ኀዘን የሚያዝን ሰው ሰውነቱን ይጐዳል ። |
| ዘይነሥእ ሕልያነ ውስተ ጎዕኑ በዓመፃ ኢያረትዕ ፍኖተ ወረሲዕሰ ይትገኀሥ እምፍናወ ጻድቃን ። | ፳፭ | በዓመፅ በእጁ መማለጃን የሚቀበል ሰው ፍርድን አያቀናም፣ እግዚአብሔርንም የዘነጋ ሰው ከደጋጎች ሥራ ይርቃል ። |

| ግዕዝ | ቁ. | አማርኛ |
|---|---|---|
| ገጹ ማእምር ለብእሲ ጠቢብ ፣ ወአዕይንቲሁ ለዓብድ ውስተ ከተማ ምድር አዕይንቲሁሰ ለጠቢብ ዲበ ርእሱ ። | ፳፮ | የብልህ ሰው ገጽ ልቡናው አዋቂ ነው ፣ ያላዋቂ ሰው ዓይኖቹ ወደ ምድር ይመለከታሉ ፣ (ምድራዊ ነገርን ይመለከታሉ) ፣ የብልህ ሰው ዓይነ ልቡናዎቹ ግን በራሱ ላይ ናቸው ፣ (ሰማያዊ ነገርን ያስባሉ) ። ምሳ፡ ፲፬ ፯ ። |
| መዓት ለአብ ዐብድ ውሉድ ወኃዘን ለእንተ ወለደቶ ። | ፳፯ | ያልተማረ ልጅ ለአባቱ መዓት ነው ፣ ለወለደችው ለናቱም ኃዘን ነው ። |
| አኀሥሮቱ ለጻድቅ ብእሲ አኮ ሠናይ ወአኮ ሠናይ ለመኳንንተ ጽድቅ ሐቢል ። | ፳፰ | ደግን ሰው ማዋረድ በጎ አይደለም ፤ እውነት ነገርን ለሚፈርዱ መኳንንትም ሐሰት ነገርን መናገር በጎ አይደለም ። |
| ዘይምህክ አውፅኦ ቃለ ንቁጸ ማእምር ውእቱ ወመስተዓግሥ ብእሲ ጠቢብ ። | ፳፱ | ሸካራ ነገርን አውጥቶ መናገር የሚሸልግ ሰው ብልህ ነው ፣ የሚታገሥ ሰው ግን ብልህ ዐዋቂ ነው ። |
| ዓብድ ለእመ ተሰአለ ጥበበ ይከውኖ ፣ በአርምሞስ ወበተሐክሞ ይመስል ጠቢበ ። | ፴ | አላዋቂ ሰው ቢጠይቅ ዕውቀት ይሆነው ነበር ፣ ዝምክም በማለቱ ግን ብልህ ይመስላል ። ኢዮብ፡ ፲፫ ፭ ። |

## ምዕራፍ ፲፮ ።

| ግዕዝ | ቁ. | አማርኛ |
|---|---|---|
| ምክንያተ የኃሥሥ ብእሲ ዘይፈቅድ ይትፈለጥ እም አዕርክቲሁ ፣ ወበኵሉ ጊዜ ዝንጓጌ ይከውን ። | ፩ | ከወዳጆቹ ሊለይ የሚወድ ሰው ምክንያት ይፈልጋል፣ በየጊዜውም ሁሉ አሽሟጣጭ ይሆናል ። |
| ኢይፈቅድ ጥበበ ነዳየ አእምሮ ፣ ወበሕቱ ይመልክ ዕበድ ። | ፪ | ከእውቀት የተቸገረ ሰው ጥበብን አይወድም ፣ ነገር ግን ስንፍና ይሠለጥንበታል ። |
| ሶበ መጽአ ረሲዕ ውስተ ዕመቀ እከያት ይትሔየይ ፣ ወያመጽእ ኃሣረ ወዝንጓጌ ። | ፫ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ወደ ጥልቅ ክፋት በመጣ ጊዜ ቸል ይባላል ፣ ተዋርዶን ሽሙጥን ያመጣል ። |
| ማይ ዕሙቅ ውስተ ልበ ብእሲ ጠቢብ ፣ ወፈለግ ዘይፈለፍል ነቅዐ ሕይወት ። | ፬ | በብልህ ሰው ልቡና ጥልቅ ውኃ (ትምህርት) አለ ፣ የሕይወት መገኛ (ዐሥርቱ ቃላት) ፈሳሽ ውኃ ነው ። |
| አንክር ገጸ ረሲዓን አኮ ሠናይ ፣ ወአኮ አዳም አግኅሦ ጽድቅ በፍትሕ ። | ፭ | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ፊት ማድነቅ በጎ አይደለም ፣ በፍርድ ጊዜም እውነት ነገርን ማራቅ በጎ አይደለም ። መዝ፡ ፹፪ ፪ ። |
| ከናፍሪሁ ለዐብድ ያበጽሖ ውስተ እከይ ፣ ወአፉሁ ለጉጉዕ ይጼውዕ ሞተ ለርእሱ ። | ፮ | ያላዋቂ ሰው ከንፈሩ ወደ ክፉ ነገር ያደርሰዋል ፣ የችኩልም ሰው አፍ ራሱን ሊጐዳ ሞትን ይጠራል ። |
| አፉሁ ለዐብድ ቅጥቃጤሁ ፣ ወከናፍሪሁ መሥገርተ ነፍሱ ። | ፯ | ያላዋቂ ሰው አፉ የራሱ መጥፊያ ነው ፣ ከንፈሩም የሰውነቱ መሰናክል ነው ። ምሳ፡ ፲ ፲፬ ። |
| ሀካይያን ያበዝኁ ፍርሃተ ፣ ወመንፈሰ ሰብእሰ ዕኑሳን ይርኅብ ። | ፰ | ሀኬተኞች ሰዎች ፍርሃትን ያበዛሉ ፣ የችግረኞች ሰዎችም ሰውነት ይራባል ። ምሳ፡ ፳፮ ፳፪ ። |
| ዘኢይፌውስ ርእሶ በምግባሪሁ ፣ እኁሁ ውእቱ ለዘርአሶ ይበልዕ ። | ፱ | ሠርቶ ራሱን የማይረዳ ሰው ፣ ራሱን የሚበላ (የጅብ) ወንድም ነው ። ምሳ፡ ፳፰ ፳፱ ። |
| ዓቢይ ኃይል ስመ እግዚአብሔር ፣ ወኪያሁ በጼግና ጻድቃን ይትሌዓሉ ። | ፲ | የእግዚአብሔር ስም ደገኛ ኃይል ነው ፣ እሱንም በመከተል ደጋግ ሰዎች ከፍ ከፍ ይላሉ ። ኢሳ፡ ፪ ፲፩ ። |
| ጥሪቱ ለብእሲ ባዕል ሀገር ጽንዕት ፣ ወበክብራ ዓቢየ ትጼልል ። | ፲፩ | የባለጸጋ ገንዘቡ የጸናች አገር ናት ፣ በክብረቷም ደገኛ መኰንን ታሳድራለች ። ምሳ፡ ፲ ፲፭ ። |
| ዘእንበለ ቅጥቃጤ ይትዔበይ ልበ ብእሲ ፣ ወዘእንበለ ክብር ይቴሐት ። | ፲፪ | የሰው ልቡና ጥፋት ሳይመጣበት ይታበያል ፣ ሳይከብርም ይዋረዳል ። ምሳ፡ ፳፱ ፳፫ ። |
| ዘይነብብ ቃለ ዘእንበለ ይስማዕ ዐብድ ውእቱ ፣ ወሉቱ ይደሉ ምናኔ ። | ፲፫ | ሳይሰማ ነገርን የሚናገር አላዋቂ ነው ፣ ለሱም መናቅ ይገባዋል ። ፩ ሳሙ፡ ፲፯ ፵ ። |
| መዓተ ንጉሥ ያኃሥዕ ገብረ ጠቢብ ፣ ለሕፁፀ ነፍስሰ ብእሲ መኑ ይክሉ ። | ፲፬ | ብልህ ባርያ የንጉሡን ቍጣ ጸጥ ያደርጋል ፣ አእምሮ የጐደለውን ሰው ግን ማን ይችለዋል ። |
| ልበ ብእሲ ጠቢብ ያጠሪ አእምሮ ፣ ወዕዝነ ጠቢባን የኃሥሥ ቃለ ተግሣፅ ። | ፲፭ | የብልህ ሰው ልቡና ዕውቀትን ገንዘብ ያደርጋል ፣ የብልሆች ሰዎች ጆሮም ምክር አዘናትን ለመስማት ይፈልጋል ። |
| ሀብት ብእሴ ያሌዕል ፣ ወምስለ መኳንንት ያነብር ። | ፲፮ | ስጦታ ሰውን ከፍ ከፍ ያደርጋል ፣ ከመኳንንትም ጋራ ያስቀምጠዋል ። ዘፍ፡ ፴፪ ፳ ። |

፲፯ ጻድቅ መስተዋድየ ርእሱ እምቅድመ ነገር፡ ወበዘአ
ምጽአ እድው ይዘልፍ ።

፲፰ ጋእዝ ያኀድግ ዕፃ ወማእከለ ዕኑዓን ይፈልጥ ።

፲፱ ወካሕደ ያኀድግ እርግሚ ወበኀበ መኳንንት ይሠርዕ ።

፳ እኁ ምስለ እኁ ዘይትራዳእ ከመ ሀገር ጽንዕት፡ ወል
ዕልት ወጽኑዕ ከመ መሠረት ሡርርት ።

፳፩ እምፍሬ አፉሁ ይመልእ ብእሲ ከርሦ፡ ወእምፍሬ
ከናፍሪሁ ይጸግብ ።

፳፪ ሞት ወሕይወት ውስተ እደ ልሳን፡ ወእለሰ ያጸንዕዋ
ይበልዑ ፍሬሃ ።

፳፫ ዘረከበ ብእሲተ ኄርተ ረከበ ሞገሰ፡ ወነሥአ እምኀበ
እግዚአብሔር ውኀዌ ።

፳፬ ዘያወፅእ ብእሲተ ኄርተ አውፅአ ሠናያተ፡ ወዘያነብ
ርሰ ብእሲተ ዘማዊተ ዐብድ ወረሲዕ ውእቱ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ዕበዱ ለብእሲ ያጠፍእ ፍናዊሁ፡ ወለእግዚአብሔር
ያስተጋፍዖ በልቡ ።

፪ ባዕል ይዌስክ አዕርክተ ብዙኀነ፡ ወነዳይሰ ኪያሁኒ
ዘቦ የኀጥእ ።

፫ ሰማዕተ ሐሰት ርኩስ ውእቱ፡ ወዘየኀሥሥ በገፍዕ
ኢያመስጥ ።

፬ ወብዙኃን ይትለአኩ በቅድመ ነገሥት፡ ወባሕቱ ጽድ
ቁ ወሀብቱ ለብእሲ እምኀበ እግዚአብሔር ።

፭ ወኵሉ እኩይ ይከውን ዝንጓጌ፡ ብእሲ ኵሉ ዘአኃወ
ነዳያነ ይጸልእ እምታአኀኃሁ ርኁቅ ውእቱ ።

፮ ሕሊና ሠናይት ለእለ አጥረይዋ ትቀርብ፡ ወብእሲ ጠ
ቢብ ይረክባ ።

፯ ዘብዙኃ እከዩ ይፌጽም እከየ፡ ወዘያስዖዝዝ ነገረ
ኢይድኅን ።

፰ ዘአጥረያ ለጥበብ ያፈቅር ነፍሶ፡ ወዘያፈቅር አእምሮ
ይረክብ ኄረ ።

፱ ሰማዕተ ሐሰት ኢይድኅን እምሁነኔ፡ ወዘያስተውዕያ
ለእከይ ይትኃጐል ባቲ ።

፲ ኢይደልዎ ለዐብድ ተድላ፡ ወለእመ ገብረ ሁንኔ ዘም
ስለ ጽእለት ይትኄየል ።

፲፩ መሐሪ ብእሲ ይትዔገሥ ወትምክሕተ ምሕረቱ ይትቃ
ወሞሙ ለኃጥአን ።

፲፪ መዓተ ንጉሥ ከመ ጣሕረ አንበሳ፡ ወከመ ጠል ዘይ
ወርድ ዲበ ሣዕር፡ ከማሁ ውእቱ ውኀዌሁ ።

፲፫ ኃፍረት ለአብ ዐብድ ወልድ፡ ወኢኮነ ንጹሐ ጸሎት
ምስለ ዐስበ ክልአት ።

ዳኛ ከሚፈረድበት ፍርድ አስቀድሞ በደለኛ ነኝ ብሎ
ራሱን የሚያጣላ ሰው ደግ ነው፡ በለጋራው በመጣውም
ነገር ራሱን ይዘልፋል ።

ዕጣ ጸብ ክርክርን ያስተዋል፡ በኃይለኞች መከከልም
ይለያል ።

ሚዛን ክሕደትን፡(ዳኛ አሉታን) ያስተዋል፡ በመኳንን
ትም ዘንድ ይሠራራል ።

ወንድም ከወንድም ጋራ የሚራዳዳ እንደ ፀናች ከፍ
ያለች እንደሆነች ሀገር ነው፡ መሠረቷም በጽኑዕ መሠረት
እንደታነፀ ሕንፃ የፀና ነው ።

ሰው ብፉ በጸለየው ጸሎት ሰውነቱን ጸጋ ክብርን ይመ
ላል፡ በከንፈሩም በጸለየው ጸሎት ይጸግባል ።

ሰው በንደበቱ በተናገረው ቃል ሕይወት ሞት ይገ
ኛሉ፡ ክፉትዋን ያጸኗት ሰዎች ግን ፍሬዋ ሞትን ይበላሉ ።

ልባም ሴትን ያገኘ ሰው በለሟልነትን አገኘ፡ ከእግዚ
አብሔርም ዘንድ በረድኤት መጐብኘትን አገኘ ።

ልባም ሴትን ፈቶ የሰደደ ሰው ተድላ ደስታውን አጣ፡
አመንዝራን የሚያኖር ሰው ግን አላዋቂ ነው፡ እግዚአብ
ሔርንም የዘነጋ ነው ። ምሳ፡ ፲፪ ፬

ምዕራፍ ፲፱ ።

የሰው ስንፍናው ሥራውን ያጠፋበታል፡ በልቡናውም
እግዚአብሔርን ገፋዒ ይለዋል ። መዝ፡ ፴፯ ፯ ።

ባለ ጸጋ ሰው ብዙ ወዳጆችን ይጨምራል፡ ድኻ ግን
ያለውን አንዱን ያጣል ። ምሳ፡ ፲፬ ፳ ።

ሐሰተኛ ምስክር ርኩስ ነው፡ በግፍ የሰው ክብት (የጐ
ልማሳ ሚስት) የሚፈልግ ሰው ከፍዳ አያመልጥም ።

ብዙ ሰዎች በነገሥታት ፊት ያገለግላሉ፡ ነገር ግን
የሰው ሹመቱ ሽልማቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ።

ክፉ ሰው ሁሉ ሰውን የሚያሸሚጥጥ ይሆናል፡ ድኾ
ች ወንድሞችን የሚጠላ ሰው ሁሉ ወንድሜ ወንድሜ
ከመባባል የራቀ ነው ። ምሳ፡ ፲፯ ፰ ።

በጎ ሐሳብ (ዐሠርቱ ቃላት) ገንዘብ ላደረጓት ሰዎች ትቀ
ርባለች፡ ብልህ ሰውም ያገኛታል ።

ክፋቱ ብዙ የሆነ ሰው ክፋትን ይፈጽማል፡ ሰውነትን
ሰቅጠጥ ሰቅጠጥ የሚያደርግ ነገርን የሚናገር ሰው ከፍዳ
አይድንም ። ምሳ፡ ፳፯ ፲ ።

ጥበብን ገንዘብ ያደረጋት ሰው ሰውነቱን ይወዳል፡
ዕውቀትንም የወደደ ሰው በጎ ነገርን ያገኛል ።

የሐሰት ምስክር ከፍርድ አይድንም፡ ክፋትንም ከሁ
ሉ የሚያደርሳት ሰው በሷ ይጠፋል ።

መፍረድ መተቸት ለማያውቅ ሰው ሹመት አይገባ
ውም፡ ባርያም ከስድብ ጋራ ቢገዛ ይበረታል ።

የሚመጸውት ሰው ይታገሣል፡ የሚያስመካ ምዕዋ
ቱም ኃጢተኞችን ይቃወማቸዋል ።

የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ጩኸት ነው፡ መጐብኘ
ቱም እንዲሁ በሣር ላይ እንደ ወረደ ጠል ነው ።

ያልተማረ ልጅ ለአባቱ ኀፍረት ነው፡ ገንዘብን ከመ
ንሣት ጋራ ያለ ስእለትን (መባ) ንጹሕ አይደለም ።

የቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ንብረት
Property of Saint Michael Cathe

፲፬ አብያተ ወንዋየ ይከፍሉ አበው ለውሉዶሙ፣ ወብሕቱ በኀበ እግዚአብሔር ትትዋደዶ ብእሲት ለብእሲሃ ።

አባቶች ለልጆቻቸው ገንዘብ ከፍለው ሰጥተው ይድራሉ፣ ነገር ግን ሴት ባሏን መውደዷ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። ፪ ቆሮ፡ ፲፪ ፲፬ ።

፲፭ ምምዓ ይእኅዝ ለብእሲ ዕኑስ፣ ወነፍስ ዘኢይትቀነይ ይርኅብ ።

ችጋረኛን ሰው ሽብር ይይዘዋል፣ የማያርስ የማይቈፍር ሰውነት ይራበል ። ምሳ፡ ፮ ፲፩ ።

፲፮ ዘየዓቅብ ተግሣፀ ወትእዛዘ ይትመኀፀን ነፍሶ፣ ወዘያሰትትስ ፍናዊሁ ይትኃጐል ።

ያዘዘውን ትእዛዝና ምክር አዝናትን የሚጠብቅ ሰው ሰውነቱን ይጠብቃታል፣ ሕጉን ትእዛዙን የሚያቃልል ሰው ግን ይጠፋል ። ሉቃስ ፳ ፰ ።

፲፯ ይሌቅሖ ለእግዚአብሔር ዘይምሕር ነዳየ፣ ወበከመ ሀብቱ ይፈድዮ ።

ለድኻ የሚመጸውት ሰው ለእግዚአብሔር ያበድረዋል፤ እንደ መስጠቱም ዋጋውን ይሰጠዋል ።

፲፰ ዝብጦ ወልደከ ከመ ይኩንከ ለተስፋ፣ ወለተጽእሎሰ ኢታልዕል እዴከ ።

አለኝታ ይሆንህ ዘንድ ልጅህን ሥራ ቅጣ፣ ነገር ግን ይህን አለኝ ብለህ ለማሰደብ እጅህን አታንሣበት ።

፲፱ ብእሲ እኩይ ብዙኀ ያኀጕል፣ ወእመሰ ዓቢይ ሕቡል ነፍሶሂ ይዌስክ ።

ክፉ ሰው ብዙን ያጠፋል፣ ጽኑ ደፋር ቢሆን ግን ነፍሱንም ያጠፋል ።

፳ ስማዕ ወልድየ ተግሣፀ አቡከ፣ ከመ ትኩን ጠቢበ በደኃሪትከ ።

ልጄ፤ በፍጻሜህ አዋቂ ትሆን ዘንድ፣ የአባትህን ምክር ስማ ። መዝ፡ ፴፯ ፴፯ ።

፳፩ ብዙኅ ሕሊና ውስተ ልበ ብእሲ መምክር፣ ወምክሩሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም ።

በሚመክር ሰው ልቡና ብዙ ምክር አለ፣ (ይህ ፈራሽ ነው) የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘለዓለም ይኖራል ።

፳፪ ፍሬሁ ለብእሲ ምጽዋት፣ ይኄይስ ነዳይ ጻድቅ እምብዕል ሐሳዊ ።

የሰው ፍሬ ነገሩ ምጽዋት መመጽወት ነው፣ ከሐሰተኛ ባለጸጋ እውነተኛ ድኻ ይሻላል ።

፳፫ ፈሪሀ እግዚአብሔር ሕይወተ ብእሲ፣ ዘኢይፈርህሰ የኃድር ውስተ መካን ኀበ ኢያስተርኢ አእምሮ ።

የሰው ሕይወቱ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፣ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰው ግን እግዚአብሔር በማይታወቅበት ቦታ ይኖራል ። ምሳ፡ ፲ ፲፮ ።

፳፬ የኀብእ ሀካይ እዴሁ ውስተ ኅፅኑ፣ ወኀበ አፉሁ ኢያቀርብ ።

ሰነፍ ሰው እጁን ከብብቱ አግብቶ ይቀመጣል፣ ወደ አፉም አያቀርብም ። ምሳ፡ ፳፮ ፲፭ ።

፳፭ ሕቡል እንዘ ይትቀሠፍ ዐብድ ጠቢበ ይከውን፣ ወእመሰ ዘለፍከ ለብእሲ ጠቢብ ይሔሊ አእምሮ ።

ደፋር መከራ ሲቀበል አይቶ አላዋቂ ሰው ብልህ ይሆናል፣ ብልህ ሰው ግን ብትቈጣው ዕውቀትን ያስባል ።

፳፮ ዘያኀሥር አቡሁ ወእሞ ይትከላእ፣ ወይትኀፈር ወምኑነ ይከውን ።

እናት አባቱን የሚያዋርድ ሰው (ከመንግሥተ ሰማያት) ተከልክሎ ያፍራል፣ የተናቀም ይሆናል ።

፳፯ ወልድ ዘይትከላእ እምዓቂበ ትምህርተ አብ፣ ይትሜሀር ቃለ እኩየ ።

የአባቱን ትምህርት ከመስማት የሚከለከል ልጅ፣ ክፉ ነገርን ይማራል ።

፳፰ ዘይትኄበይ ዐብደ ወልደ ይጼእል ፍትሐ፣ ወለአፈ ረሲዓን ይውኅጦ እኩይ ኵነኔ ።

አላዋቂን ልጅ የሚዋስ ሰው ፍርድን ያስነቅፋል፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች አፍን ክፉ ፍርድ ይዘጋዋል ።

፳፱ ወይጸንሕ ሎሙ መቅሠፍት ለእኩያን፣ ወኵነኔ ከማሁ ለዐብዳን ።

ክፉ ሰዎችን መቅሠፍት ይጠብቃቸዋል፣ እንደዚሁም አላዋቆችን ፍርድ ይጠብቃቸዋል ።

## ምዕራፍ ፳ ።

፩ እኩይ ወይን ለጸአሊ ወለሰካሪ፣ ወኵሉ ዘያስተፍንዎ ለጽዋዕ ኢይከውን ጠቢበ ወኵሉ ዐብድ ዘከመዝ ይዴመር ።

ለሰካርና ለተሳዳቢ ሰው ወይን ክፉ ነው፣ ጽዋውን ጭልጥ ጭልጥ አድርጎ የሚመልስ ሰው ሁሉ ብልህ አይደለም፣ እንደዚህ ያለው አላዋቂ ሁሉ ከሰካራም ሰው ጋራ አንድ ይሆናል ። ዘፍ፡ ፱ ፳፩ ። ኤፌ፡ ፭ ፲፰ ።

፪ ኢየሐፅፅ መዓተ ንጉሥ እመዓተ አንበሳ፣ ወዘየሀውኮሰ ይኤብስ ላዕለ ነፍሱ ።

የንጉሥ ቍጣ ከአንበሳ ቍጣ አያንስም፣ ንጉሡን የሚያውከው ሰው ግን ሰውነቱን ይበድላል ።

፫ ክብሩ ለብእሲ ተከልኦ እምጽእለት፣ ወኵሉ ዐብድ ዘከመዝ ይጸመር ።

የሰው መከበሩ ከስድብ መከልከል ነው፣ አላዋቂ ሰው ሁሉ ግን ከተሳዳቢ ሰው ጋራ አንድ ይሆናል ።

፬ እንዘ ይዘነጕግዎ ሀካይ ኢየኃፍር፣ ይስእል በማእረር ወእልበ ዘይሁብ፣ ከማሁ ዘይትሌቃሕ ሥርናየ እንዘ በ ውስተ ክምሩ ።

ሰነፍ ሰው ሲያሽሟጥጡት አያፍርም፣ በመከር ጊዜ ይለምናል የሚሰጠውም የለም፣ እንደዚሁም በክምሩ ሳለ ሥንዴን የሚበደር ሰው የሚሰጠው የለም ።

| | | |
|---|---|---|
| ማይ ዕሙቅ ውስተ ልበ ብእሲ መምክር ፡ ወብእሲ ጠቢብ ይዘልሖ ። | ፭ | በመከር ሰው ልቡና ጥልቅ ምክር አለ ፡ ብልህ ሰው ይቀዳዋል (ይማረዋል) ። |
| ዓቢይ ወክቡር ብእሲ መሐሪ ፡ ወለብእሲ ምእመን በሥራሕ ተረክቦቱ ። | ፮ | የሚሰጥ የሚመጸውት ሰው ገናና ነው ፡ የከበረም ነው ፡ የደግ ሰው መገኘቱ በሥራ ነው ። |
| ዘየሐውር ንጹሐ ውስተ ሕገ እግዚአብሔር ፡ ብፁዓነ ይሬስዮሙ ለውሉዱ ። | ፯ | በሕገ እግዚአብሔር ንጹሕ ሆኖ የሚኖር ሰው ልጆቹን የተመሰገኑ ያደርጋቸዋል ። መዝ፡ ፴፯ ፩ ። |
| ወሶበ ጻድቅ ንጉሥ ይነብር ዲበ መንበሩ ቅድመ አዕይንቲሁ ኢይትቃወሞ ምንትኒ እኩይ ። | ፰ | እውነተኛ ንጉሥ በዙፋኑ በተቀመጠ ጊዜ ፡ ምንም ክፉ ነገር በፊቱ አይቃወመውም ። |
| መኑ ዘይትሜከሕ ልብ ንጹሕ ዘብ ፡ ወመኑ ያስተርኢ ንጹሐ ከዊኖ እምኃጢአት ። | ፱ | ንጹሕ ልቡና አለኝ ብሎ የሚመካ ሰው ማን ነው ፤ ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ የሚታይ ሰውስ ማነው ! ። |
| ዘየሐሚ አባሁ ወእሞ ይጠፍእ ብርሃኑ ፡ ወበእንተ አዕይንቲሁ ይኔጽር ጽልመተ ። | ፲ | እናት አባቱን የሚያማ ልጅ ተድላ ደስታው ይጠፋል፡ የዓይኖቹም ብለኔ ጨለማን ይመለከታል (ይጠፋል) ። |
| መክፈልተ ዘይጌጕእ አቅዲሞ በደኃሪቱ ኢይትባረክ ። | ፲፩ | አስቀድሞ ሰርቆ ቀምቶ ለመክበር የሚቸኩል ሰው ፡ ገንዘቡ በፍጻሜ አይባረክለትም ። |
| ኢትበል እትቤቀሎሙ ለጸላእትየ ፡ አላ ተሰፈዎ ለእግዚአብሔር ከመ ይርዳእከ ። | ፲፪ | ይረዳህ ዘንድ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገው እንጂ ፡ ጠላቶቼን እበቀላቸዋለሁ አትበል ። |
| መዳልው ዓቢይ ወንኡስ ወመሣፍርት ክልኤቱ ርኩሳን በኀበ እግዚአብሔር ኵሎሙ ፡ ወዘይገብሮሙ በምግባሪሁ ይትዓቀፍ ። | ፲፫ | ታናሽ ሚዛንና ታላቅ ሚዛን ፡ ታናሽ ላዳንና ታላቅ ላዳን ሁለቱ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩሳን ናቸው ፡ የሚሠራቸውም ሰው በሥራው ይሰነካከላል ። |
| ለወሬዛ ጻድቅ ርቱዕ ፍኖቱ ። | ፲፬ | የደግ ጕልማሳ ሥራው የቀና ነው ። ማቴ፡ ፯ ፲፯ ። |
| ዕዝን ዘይሰምዕ ፡ ወዓይን ዘይሬኢ ግብረ እግዚአብሔር ኵሎሙ ። | ፲፭ | የሚሰማ ጆሮ የሚያይ ዐይን ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ሥራዎች ናቸው ። ምሳ፡ ፳፭ ፲፪ ። |
| ኢታፍቅር ሐምየ ከመ ኢትትአተት ፡ ወኢትኑም ከመ ኢትንዲ ፡ ክሥት አዕይንቲከ ወጽግብ ኅብስተ ። | ፲፮ | በሞት እንዳትርቅ ማማትን አትውደድ ፡ እንዳትቸገርም አትተኛ (እረስ ቁፍር) ፡ ዐይንህን ገልጠህ ሥራህን ሠርተህ እንጀራህን ጥገብ ። |
| ምኑናን በኀበ እግዚአብሔር ክልኤቱ መዳልው ፡ መዳልው ሰራቂ አከ ሠናይ በቅድሜሁ ። | ፲፯ | ሁለት ሚዛኖች በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቁ ናቸው ፡ አባይ ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት በጎ አይደለም ። |
| እምኀበ እግዚአብሔር ይረትዕ አሠሩ ለብእሲ ፡ ወመዋቲስ እፎ የአምር ፍናዊሁ ። | ፲፰ | የሰው ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ይቀናለታል ፡ የሚሞት ሰው ግን የእግዚአብሔርን ሥራ እንዴት ያውቃል ! ። |
| መሥገርቱ ለብእሲ ጕጕዕ ዘእምዚአሁ ይቄድስ ፡ እስመ እምድኅረ በፅዐ ንስሐ ይከውኖ ። | ፲፱ | ከተሣለ በኋላ ፀፀት ይሆንበታልና ፡ የሰው ጥፋት ቸኩሎ ከገንዘቡ ለይቶ የተሣለው ስእለት ነው ። |
| መሥኤሆሙ ለረሲዓን ንጉሥ ጠቢብ ፡ ወይወዲ ሎሙ መንኰራኵረ ። | ፳ | እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች መንሽቸው ብልህ ንጉሥ ነው ፡ ግብርንም ይጥልባቸዋል ። |
| ብርሃነ እግዚአብሔር እስትንፋሰ ብእሲ ። | ፳፩ | የሰው ዕውቀት ከእግዚአብሔር የተገኘ ዕውቀት ነው ። |
| ዘከመ ማኅቶት ይፈትን መዛግብተ ፡ ከማሁ ጠቢብ ንጉሥ ይፈትን መዛግብተ ከርሥ ። | ፳፪ | መብራት የተሠወረውን ሣጥን እንዲመረምር ፡ እንደዚሁም ብልህ ንጉሥ በሆድ የተሠወረውን ይመረምራል ። |
| ምጽዋተ ወጽድቀ ይዕቀብ ንጉሥ ፡ ወይሚግቡ በጽድቅ መንበሮ ። | ፳፫ | ንጉሥ ምግባር ሃይማኖትን ይጠብቅ ፡ በእውነትም መንበረ መንግሥቱን ይጠብቁለታል ። |
| ሠርጉሆሙ ለወራዙት ጥበብ ፡ ወክብሮሙ ለልሂቃን ሢበት ። | ፳፬ | የጕልማሶች ጌጣቸው ጥበብ ነው ፡ የሽማግሎችም ክብራቸው ሽበት ነው ። ምሳ፡ ፲፮ ፴፩ ። |
| ምማቴ ወግኅሠት ይዳደቆሙ ለእኩያን ፡ ወዝብጠት ውስተ መዛግብተ ከርሥ ። | ፳፭ | ሽብር ስደት ክፉ ሰዎችን ይገናኛቸዋል ፡ በሆዳቸው ክፉ ነገር በሚያስቡ ሰዎች መቀራደድ ይመጣል ። |

## ምዕራፍ ፳፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ከመ ውኂዘ ማይ ከማሁ ልበ ንጉሥ ውስተ እደ እግዚአብሔር ኀበ ፈቀደ ይመይጣ ፡ ወህየ ትመሲ ። | ፩ | በእግዚአብሔር እጅ የተያዘ የንጉሥ ልቡና በገበሬ እጅ እንደ ተያዘ መስኖ ውኃ ነው ፡ ወደ ወደደው ይመልሳታል ፡ በዚህም ትዘገያለች ። |

፪ ኵሉ ብእሲ ያስተርኢ ለርእሱ ጻድቀ ፣ ወያረትዕ እግዚአብሔር አልባበ ።

፫ ገቢረ ጽድቅ ሀልው ወሥሙር በኀበ እግዚአብሔር ፈድፋደ እምዘቢሐ መሥዋዕት ።

፬ ዓቢይ ሕሊና ኢጕጕዖ ልብ ለጽእለት ፣ ወብርሃኖሙ ለረሲዓን ኃጢአት ።

፭ ዘይትቀነይ መዝገበ ልሳነ ሐሰት ፣ ከንቶ ይዴግን ፣ ወያበጽሖ ውስተ መሥገርተ ሞት ።

፮ ሥራዊ ረሲዓን ይትነገድ እምርኁቅ ፣ እስመ ኢይፈቅዱ ይግበሩ ጽድቀ ።

፯ ለዕልዋን ዕልወ ፍኖተ ይፌኑ ሎሙ እግዚአብሔር እስመ ርቱዕ ወንጹሕ ምግባሩ ።

፰ ይኄይስ ነቢር ውስተ ማዕዘንት ዘኢኮነ ጥፉረ ፣ እምነቢር ምስለ ብእሲት መግዝእት ውስተ ቤት ምሩግ ።

፱ ነፍሰ ረሲዓን ኢትትመሐር ወኢ በኀበ አሐዱሂ ሰብእ ።

፲ እንዘ የኃሥር ጸዋግ ማእምረ ይከውን የዋሀ ፣ ወዘይጤቅስ ጠቢበ ይትዌከፍ አእምሮ ።

፲፩ ኢየአምር ጠቢበ ልበ ረሲዓን ፣ ወየአክዮሙ ለረሲዓን እከይ ።

፲፪ ዘይፈዕም ዕዘኒሁ ከመ ኢይስማዕ ነዳያነ ፣ ውእቱኒ ይጼውእ ወአልቦ ዘይሰምዖ ።

፲፫ ሀብት ዘበጽሚት ይገፍዕ መዓተ ፣ ወዘሰ ይምህክ ሀብተ ያነሥእ ጽኑዐ መዓተ ።

፲፬ ፍሥሐ ጻድቃን ገቢረ ፍትሕ ፣ ወጻድቅ በሕቱ ርኩስ በኀበ እኩያነ ምግባር ።

፲፭ ብእሲ ዘይስሕት እምፍኖተ ጽድቅ ውስተ ማኅበረ ረሲዓን የዓርፍ ።

፲፮ ብእሲ ጽኑዕ ያፈቅር ፍሥሐ ፣ ወዘያፈቅር ወይነ ወቅብዐ ኢይብዕል ።

፲፯ ምኑን ኃጥእ በኀበ ጻድቅ ፣ ወቤዛሁ ለጻድቅ ይትወሀብ ረሲዕ ።

፲፰ ይኄይስ ነቢር ውስተ ገዳም ፣ እምነቢር ምስለ ብእሲት መግዝእት ፣ ወነባቢት ፣ ወመዓትምት ።

፲፱ መዝገብ መፍትው ውስተ አፈ ጠቢባን ፣ ዐብዳንሰ ሰብእ የኃጥእዎ ።

፳ ዘይዴግን ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ፣ ይረክብ ክብረ ወሕይወተ ።

፳፩ ለሀገር ጽንዕት በአ ጠቢብ ፣ ወነሠተ ጽንዐ በዘይትዌከሉ ረሲዓን ።

፳፪ ዘየዐቅብ አፉሁ ወልሳኖ ይትመኀፀን ለነፍሱ እምንዳቤ ።

፳፫ ጕጉዕ ወመግዝእ ወነባቢ ብድብድ ስሙ ፣ ወዘይዜክር ሰ እከየ ኃጥእ ውእቱ ።

፳፬ ፍትወት ይቀትሎ ለሀካይ ፣ እስመ ኢይፈቅድ እደ

ሰው ሁሉ ራሱን ለመጥቀም ጻድቅ መስሎ ይታያል ፣ ነገር ግን የልቡናን ቅንነት የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው ። ምሳ፣ ፲፪ ፲፭ ። ሉቃ፣ ፲፮ ፲፭ ።

በጎ ሥራን መሥራት ደግ ነው ፣ መሥዋዕትን ከመሠዋትም ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው ።

ሰውን ለመሰደብ በልቡና አለመቸኮል በጎ ዕውቀት ነው ፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችም ተድላ ደስታቸው ኃጢአት ነው ። ምሳ፣ ፯ ፲፮ ።

ሐሰተኛ አንደበት ለተናገረው ገንዘብ የሚገዛ ሰው ከንቱ ነገርን ይከተላል ፣ ለሞት ወደሚያበቃ መከራም ያደርሰዋል ።

በጎ ሥራ መሥራትን አይወዱምና ፣ እግዚአብሔርን በዘነጉ ሰዎች ከሩቅ ጥፋት ይመጣል ። ምሳ፣ ፲ ፪ ።

የእግዚአብሔር ሥራው የቀና ንጹሕ ነውና ፣ እግዚአብሔር በጠማሞች ሰዎች ጠማማ ሥራን ያመጣባቸዋል ።

በተመረገ ቤት ከተነዛናዥ ሴት ጋር ከመኖር ፣ አንድ ወገኑ በፈረሰ ቤት መኖር ይሻላል ። ምሳ፣ ፳፭ ፲፱ ።

እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ሰውነት በንዱ ሰው ዘንድ ስንኳ ይቀር አትበልም ። ኢዮ፣ ፳፫ ፲፫ ።

ጠማማ ሰው ሲዋረድ አይቶ ያልተማረ ሰው ብልህ ይሆናል ፣ ጥበብን የሚረዳ ሰው ግን ዕውቀትን ይቀበላል ።

እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ልቡና ጥበብን አይወድም ክፋት እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ያከፋቸዋል ።

ድኾችን እንዳይሰማ ጆሮውን የሚዘጋ ሰው እሱም ይለምናል ነገር ግን የሚሰማው የለም ።

ሠውሮ የሰጡት ገንዘብ ቍጣን ይመልሳል ፣ መስጠትን የሚሸልግ ሰው ግን የፀና መዓትን ያመጣል ።

የጻድቃን ደስታቸው እውነትን መፍረድ ነው ፣ ጻድቅ ሰው ግን ሥራቸው በከፋ ሰዎች ዘንድ የረከሰ ነው ።

ከእውነተኛ ሕግ ወጥቶ የሚበድል ሰው ፣ ሰብአ ትከት በጠፉበት መቅሠፍት ይጠፋል ።

በኃጢአት የፀና ሰው ተድላ ደስታን ይወዳል ፣ ቅቤና ወይን የሚወድ ሰው አይከብርም ።

ኃጢአተኛ ሰው በእውነተኛው ዘንድ የተናቀ ነው ፣ እግዚአብሔርንም የዘነጋ ሰው ለእውነተኛው ሰው ቤዛ ሁኖ ይሰጣል ።

ከተከራካሪ ከተነዛናዥ ከቍጡ ሴት ጋራ ከመኖር ፣ በምድረ በዳ መኖር ይሻላል ። ምሳ፣ ፳፭ ፱ ።

የተወደደ ሕግ በመምህራን አፍ ሲነገር ይኖራል ፣ ያልተማሩ ሰዎች ግን ያጡታል (አያስተምሩትም) ።

የሕይወትና የእውነትን ሥራ የሚከተል ሰው ፣ ሕይወትን ክብርን ያገኛል ። ምሳ፣ ፲፭ ፱፤ ፬ ፳፪ ።

የፀኖች አገርን ብልህ ሰው ገበት ፣ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች የሚመኩበት ፅናቷንም አፈረሰ ።

አፉን አንደበቱን ከመናገር የሚጠብቅ ሰው ፣ ሰውነቱን ከመከራ ይጠብቃታል ። ምሳ፣ ፲፰ ፳፩፤ ፳፪ ፭ ።

ችኩል ፣ ተነዛናዥ ፣ ቀባጣሪ ሰው ስሙ ቸነፈር ይባላል ፣ ክፉ ነገር የሚያስብ ሰው ግን ኃጢአተኛ ነው ።

ምንም እጆቹ መሥራት አይወዱምና ፣ ሰነፉን ሰው

| | | |
|---|---|---|
| ዊሁ ይገበሩ ምንተኒ ። | | ምኖት ይገድለዋል ። ምሳ፡ ፲፫ ፬ ። |
| ረሲዕ ይፈቅድ ወይፈቱ ኵላ ዕለተ ፍትወተ እኪተ፡ ጻድቅሰ ይምሕር ወይመጽውት ኵሎ አእሚሮ ። | ፳፭ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው ሁል ጊዜ ክፉ ፈቃድን ይወዳል፡ ደግ ሰው ግን ሞቱን አውቆ ሁሉ ጊዜ ራርቶ ይመጸውታል ። |
| መሥዋዕተ ረሲዓን ምኑን በኀበ እግዚአብሔር፡ እስመ በአከይ ያቀርብዎ ። | ፳፮ | ሰርቀው ቀምተው ያቀርቡታልና፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች መሥዋዕታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነው ። |
| ሰማዕተ ሐሰት ይትኀጐል፡ ወብእሲሰ ሰማዒ ዕቁበ ይትናገር ። | ፳፯ | ሐሰተኛ ምስክር ይጠፋል፡ የሰማውን የሚመሰክር ሰው ግን ከሐሰት ነገር ተጠብቆ ይናገራል ። |
| ረሲዕ ብእሲ ዘእንበለ ኀፍረት ይትቃወም ለገጽ፡ ወራትዕሰ ይጤይቅ ፍኖቶ ። | ፳፰ | እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው የሰውን ፊት ሳያፍር ይቃወማል፡ ቀና ሰው ግን ሕጉን ይረዳል ። |
| አልቦ ጥበብ፡ ወአልቦ እዘዝ በኀበ ዐብድ፡ ወአልቦ ምክር በኀቡ ረሲዕ ። | ፳፱ | ባልተማረ ሰው ዘንድ ጥበብ ጽናት የለም፡ እግዚአብሔርንም በዘነጋ ሰው ዘንድ በጎ ምክር የለም ። |
| ፈረስ ያስተዳልዉ ለዕለተ ጸብእ፡ ረድኤትሰ እምኀበ እግዚአብሔር ይከውን ። | ፴ | ለሰልፍ ቀን ፈረስን ያዘጋጃሉ፡ ድል መንሣት ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ። መዝ፡ ፫ ፫ ። |
| ምዕራፍ ፳፪ ። | | ምዕራፍ ፳፪ ። |
| ይኄይስ ስም ሠናይ እምብዙኅ ብዕል፡ ወእምብሩር ወወርቅ ሞገስ፡ አዳም ። | ፩ | ከብዙ ባለጠግነት በጎ ስም ይሻላል፡ ከወርቅና ከብርም የእግዚአብሔር ባለሟል መሆን ያማረ ነው ። |
| ባዕል ወነዳይ ይትራከቡ ኅቡረ፡ ወክልኤሆሙ እግዚአብሔር ገብረ ። | ፪ | ድኻና ባለጸጋ በአንድነት ይገናኛሉ፡ (ድኻ በጸሎት፡ ባለጸጋ በምጽዋት) ሁለቱንም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ። |
| ማእምር ርእዮ እንዘ ይትኬነን እኩይ ኀዩል ይትጌሠፅ፡ ወዐብዳንሰ እንዘ የኀልፉ ኀሠሩ ። | ፫ | አዋቂ ሰው ክፉ ሰው ሲጠፋ አይቶ ደፋር ሰው ይገሠፃል፡ አላዋቂዎችም ሲሄዱ ጠፉ ። |
| ትወልዳ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር፡ ለክብር፡ ወለብዕል፡ ወለሕይወት ። | ፬ | እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብን ታስገኛለች፡ ክብርንም ባለጠግነትም ደኅንነትንም ታስገኛለች ። |
| አሜከላ ወመሣግር ውስተ ፍናው ጠዋያት፡ ወዘየዐቅብሰ ነፍሶ ያድኅን ፡ ወያመስጦን ። | ፭ | ወጥመዶችና አሜከላ በጠማማ ጐዳናዎች አሉ፡ እንደበቱን ከክፉ ነገር የሚጠብቅ ሰው ግን፡ ሰውነቱን ያድናል፡ ጠማማ ሥራዎችንም ያመልጣቸዋል ። |
| አብዕልት ነዳያነ ይኬንኑ ፡ ወአግብርት ለአጋእዝቲሆሙ ይሌቅሑ ። | ፮ | ባለጸጎች ድኾችን ይገዛሉ ባሮችም ለጌቶቻቸው ያበድራሉ ። |
| ወዘይዘርእ ሕብለ የአርር እከየ፡ ወመቅሠፍተ ምግባሪሁ ይፌጽም ። | ፯ | ሐሰትን የሚናገር ሰው ክፋት ፍሬውን ይለቅማል፡ (መቅሠፍት ይቀበላል) በሥራው የመጣበትን መቅሠፍት ፈጽሞ ይቀበላል ። |
| ብእሴ ፍሡሐ ወሀቤ ያፈቅር እግዚአብሔር፡ ወከንቶ ምግባሪሁ ይጸልእ ። | ፰ | ደስ ብሎት የሚሰጠው ሰው እግዚአብሔር ይወደዋል፡ ከንቱ ሥራውን ንፍገቱን ግን ይጠላል ። |
| ዘይምሕርሰ ነዳየ ውእቱ በልዐ፡ እስመ ኅብስቶ ወሀበ ለምስኪናን፡ ወእከ ለበዕል ዘይፈዲ ለዘወሀበ ። | ፱ | እንጀራውን ለጠም አዳሮች ሰጥቷልና ለድኻ የሚመጸውት ሰው ግን እሱ መብላቱ ነው፡ የሰጠውን ለሚሰጥ ባለጸጋ የሰጠው አይደለምና ። |
| መዊአ ወክብረ ይረክብ ዘወሀበ ሕልያነ፡ ወባሕቱ ነፍሶ ያአትት ዘነሥአ ። | ፲ | መማለጃ የሰጠ ሰው ድል መንሣትን ክብርን ያገኛል ነገር ግን የተቀበለውን ሰውነት ያጠፋል ። |
| አውጽእ እምእንግልጋ ቀታሌ፡ ወይትልዎ ሞት እስመ ሶበ ይነብር ውስተ እንግልጋ ኵሎ ያኀሥርሥር ። | ፲፩ | ነፍሰ ገዳይን ከሸንጎ አውጣ፡ ሞትም ይከተለው በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ ሁሉን ይቀበልና ። |
| ያፈቅር እግዚአብሔር የዋሃተ ልብ፡ ወኅሩያን በኀቤሁ ኵሎሙ ንጹሓን ወበከናፍሪሁ ይሬእዮ ንጉሥ ። | ፲፪ | እግዚአብሔር የልቡናን ቅንነት ይወዳል፡ ንጹሐን የሆኑ ሰዎች ሁሉ በሱ ዘንድ የተመረጡ ናቸው፡ ንጉሥም በከንፈሩ ያያል ። መዝ፡ ፺፩ ፯ ። |
| አዕይንተ እግዚአብሔር የዓቅባ አእምሮ፡ ወይሜንን ቃለ ጥበብ ኃጥእ ። | ፲፫ | የእግዚአብሔር ዓይኖች (ካህናት) ዕውቀትን ይጠብቃሉ፡ ኃጢአተኛ ሰው ግን የጥበብን ነገር ይንቃል ። |

፲፬ ያመክኒ ሀካይ ሰበ ይልእክዎ ወይብል ፣ ሀሎ አንበሳ ውስተ ፍኖት ፣ ወውስተ መራኅብት ቀትል ።

፲፭ ግብ ዕሙቅ አፈ ዐማፂ ፣ ወዘተጸልአ በኀበ እግዚአብሔር ይወድቅ ውስቴቱ ።

፲፮ በፍናው እኩያት ቅድሜሁ ለብእሲ ፣ ወኢያፈቅር ይትገኀሥ እምኔሆን ፣ ወተግኅሦስ መፍትው እምፍኖት ጸዋግ ወእኪት ።

፲፯ ኢያእምሮ አልዓለቶ ለልበ ወሬዛ ፣ እስመ በትር ወመቅሠፍት ርኁቀ እምኔሁ ።

፲፰ ዘይትዔገሎ ለነዳይ ብዙኀ ይሬሲ ጥሪቶ ፣ ወይሁብ ለባዕል በተጽናሱ ወአኮ ለነዳይ ።

፲፱ ኀበ ቃለ ጠቢባን አቅርብ ዕዝነከ ለአዕምኦ ፣ ወስማዕ ቃለ ዚአየ ፣ ወልበከ አቅርብ ከመ ሠናየ ታእምር ።

፳ ወእመ ወደይኮሙ ውስተ ልብከ ያስተፌሥሑከ ኀቡረ በከናፍሪከ ፣ ከመ ይኩን በኀበ እግዚአብሔር ተስፋከ ፈድፋደ ወያኤምረከ ፍኖቶ ።

፳፩ ናሁ ጸሐፍኩ ለከ ትሥልስተ ለምክር ፣ ወለአእምሮ ፣ ወአንተ ጸሐፎን ለርእስከ ውስተ ራኅበ ልብከ ።

፳፪ እሜሀረከ ሀልወ ቃለ አእምሮ ኄረ ፣ ከመ ትስማዕ ወከመ ታውሥእ ቃለ ጽድቅ ለእለ ይሴእሉከ ።

፳፫ ኢትትዓገሎ ለነዳይ እስመ ምስኪን ውእቱ ፣ ወኢትመንን ድውየ በአናቅጽ ።

፳፬ እስመ እግዚአብሔር ይፈትሕ ሎቱ ወይበልሖ እምእንቲአከ ነፍስ እንተ ኢትሰረቅ ወይትቤቀል ሎቱ ።

፳፭ ኢትኩን መጽመረ ለብእሲ መዓትም ፣ ወምስለ ዐርክ መግዝእ ኢትኅድር ፣ ከመ ኢትትመሀር ፍኖቶ ።

፳፮ ወትነሥእ መሥገርተ ለነፍስከ ፣ ወኢተሀብ እዴከ ለሀቢት በኀፈረ ገጽ እመ አልብከ ዘትፈዲ ፣ ወይነሥእከ ከዳነከ ዘታሕተ ገቦከ ።

፳፯ ወኢትንሥት ሥርዐተ ዘለዓለም ዘአንበሩ አበዊከ ።
፳፰ ጥዩቀ በእሲ ወበሊኀ በምግባሩ ለነገሥት ፣ ሀለዎ ይቅርብ ወኢይቀውም ለሰብእ ፅኑሳን ።

ምዕራፍ ፳፫ ።

፩ ለእመ ነበርከ ትደረር ውስተ ማእደ መኳንንት አእምሮ አእምር ዘአቅረቡ ለከ ።

፪ ወተመጠው በእዴከ ፣ ወአእምር ከመ ዘከማሁ ሀለወከ ታለትዳሉ ።

፫ ወእመሰ ነዳይ አንተ ኢትፍቱ መባልዕቲሁ ወዝ ውእቱ ኅብስተ ሐሰት ።

፬ ወኢትትአከል ምስለ ባዕል እንዘ ነዳይ አንተ ፣ ወበሕሊናከ ረኃቅ ።

ሰነፍ ሰው በላኩት ጊዜ ያመክኛል ፣ በመንገድ አንበሳ በአደባባይም ጦር አለ ይላል ። ምሳ፡ ፳፮ ፲፫ ።

የበደለኛ ሰው አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው ፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተጠላ ሰው በዚያ ይወድቃል ።

በሰው ፊት ክፉዎች የሆኑ ሥራዎች አሉ (ዓለም ቤት) ከክፋትና ከጠማማ ሥራ መራቅ ይገባ ነበር ፣ ነገር ግን ሰው ከነዚያ ይርቅ ዘንድ አይወድም ።

ብትር ግርፋት ከሱ ርቋልና የጕልማሳን ልቡና አለማወቅ ከፍ ከፍ አደረገችው ።

ድኻውን የሚቀማ ሰው ገንዘቡን ብዙ ያደርጋል ፣ ለድኻ ያይደለ በችጋር ላለ ባለጸጋ ይሰጣል ።

ከመምህራን ቃል ትምህርትን ለመስማት ጆሮህን አቅርብ ፣ የኔንም ነገር ስማ በጎ ዕውቀትን ታውቅ ዘንድ ልቡናህንም አቅርብ ። ምሳ፡ ፩ ፳ ፤ ፳፬ ፴፪ ።

በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝታህ ፈጽሞ ይደረግልህ ዘንድ በልቡናህ አንድነት ብታሳድራቸው በከንፈርህ ስታስተምራቸው ደስ ያሰኙኻል ሥራውንም ይገልጥልኻል ።

ምክር ዕውቀትን ሊሆኑህ እነሆ ሦስት ነገሮችን ጻፍኩልህ ፣ አንተም በልቡናህ ሰሌዳነት ለራስህ ብለህ ጻፋቸው ። ምሳ፡ ፫ ፯ ። መክ፡ ፩ ፲፪ ።

በጎ ነገርን ትሰማ ዘንድ ለሚጠይቁህም ሰዎች እውነት ነገርን ትመልስላቸው ዘንድ ነዋሪ የሚሆን የዕውቀት ነገርን አስተምርኻለሁ ።

ጦም አዳሪ ነውና ድኻውን አትቀማው ፣ በሽተኛውንም በአደባባይ አትናቀው ። ዘፀ፡ ፳፫ ፯ ።

እግዚአብሔር ፍርዱን ይፈርድለታልና ኃጢአት ሠርታ ከእግዚአብሔር ከማትሰሳት ካንተም ሰውነት ያድነዋልና ይበቀልለታልምና ድኻውን አትናቅ ።

ከቍጡ ሰው ጋራ ተባባሪ አትሁን ፣ ሥራውንም እንዳትማር ከተነዛናኸ ባልንጀራ ጋራ አትኑር ።

እምቢ ብትል ግን በሰውነትህ መከራ ትቀበላለህ ፣ የምትከፍለው ከሌለህ ፊት በማፈር ቃልህን ለውልና አትስጥ ብትጥስ ግን ከጐድንህ በታች ያለ ምንጣፍህን ይወስድብኻል ። ምሳ፡ ፮ ፩ ።

አባቶችህ ያኖሩት የዘለዓለም ሥርዓትን አታፍርስ ።

ነገር የሚረዳ በሥራው አዋቂ የሆነ ሰው ወደ ነገሥታት ይቀርብ ዘንድ አለው ፣ ለድኾች ዘመዶቹም አይደናላቸውም ። ምሳ፡ ፳ ፭ - ፯ ። ፩ኛ ነገ፡ ፲ ፰ ።

ምዕራፍ ፳፫ ።

በመኳንንቱ ማእድ ትመገብ ዘንድ ብትቀመጥ ያቀረቡልህን ፈጽመህ ዕወቅ ።

አውቀህ በእጅህ ተቀበለው እንደዚህ ታዘጋጅ ዘንድ እንዳለህም ዕወቅ ።

ድኻ ከሆንክ ግን የዚህን የባለጸጋን ምግብ አትውደድ የሐሰት እንጀራ ይሉኻል ፣ ይህ ነው ።

ድኻ ሳለህ ከባለጸጋው ጋራ አትተካከል በልቡናህም ፈጽመህ ራቅ ። ምሳ፡ ፲፭ ፳፯ ።

፭ ለእመ አውተርከ ዓይነከ ኀቤሁ ኢትረክቦ፡ ወእደ ያስተርኢ አልቦ፡ እስመ ተደለወ ሎቱ ክንፈ ንስር ወያገብእ ውስተ ቤተ ዘይቀውም ።

፮ ኢትድረር ምስለ ብእሲ መታሒ፡ ወኢትፍቱ መብልዐቲሁ ከመ ዘይውኅጥ ሣዕረ ከማሁ ይበልዕ ወይሰቲ ።

፯ ወነቤከኒ ኢታብእ ወኢትብላዕ ኅብስተ ምስሌሁ፡ ብላዕ ወስተይ ይብለከ ወልቡሰ ኢሀሎ ምስሌከ ።

፰ ይቀይዕ ወያቀያዕዮ ወያማስን ነገረከ ሠናየ ።

፱ ውስተ ዕዝነ ዐብድ አልቦ ዘትነግር፡ ከመ ኢይመንን ነገረከ ሠናየ ጠቢበ ።

፲ ወኢታፍልስ ደወለ ገራሀት ዘአንበሩ አበዊከ ።

፲፩ ወውስተ ጥሪተ እጓለ ማውታ ኢትባእ እስመ ዘይበልሐሙ እግዚአብሔር አዚዝ ውእቱ ወይትኳነን ኵነኔሆሙ ምስሌከ ።

፲፪ ሀብ ለተግሣፅ ልበከ፡ ወዕዝነከ አስተዳሉ ለቃለ አእምሮ ።

፲፫ ኢትትኀየይ ገሥፆ ደቂቅከ፡ እስመ እመ ዘበጥኮሙ በበትር ኢይመውቱ ።

፲፬ አንተ ትዘብጦሙ በበትር፡ ወነፍሶሙ ትባልሕ እሞት ።

፲፭ ወልድየ እመ ጠቢበ ኮነ ልብከ ያስተፌሥሕ እንተ እየ ልበ ።

፲፮ ወእመ ነበረት ቃልየ በከናፍሪከ፡ ለከናፍሪ ዚአየ ርቱዓተ ይከውና ።

፲፯ ኢትቅናእ ልብከ ላዕለ ኃጥአን፡ አላ በፍርሃተ እግዚአብሔር ሀሉ በኵሉ ጊዜ ።

፲፰ ወለእመ ዐቀብኮን ይከውናከ ትዝምደ ወተስፋከ ኢይትአተት ።

፲፱ ስማዕ ወልድየ ወጠቢበ ኩን ወአርትዕ ሕሊና ልብከ ።

፳ ወኢትኩን ሰታዬ ወይን፡ ወኢትኩን ተማያጤ ሥጋ ሐናት ።

፳፩ ወኵሉ ሰታዪ ወዘማዊ ይነድድ ወይለብስ ስጡጠ አጽርቅተ ወኵሉ ነዋሚ ።

፳፪ ስማዕ ወልድየ ነገረ አቡከ ዘወለደከ፡ ወኢታስተአክያ ለእምከ ለእመ ረስዓት ።

፳፫ ሠናየ ያልህቅ አብ ጻድቅ፡ ወበወልድ ጠቢብ ትትፌሣሕ ነፍሱ ።

፳፬ ወይትፌሥሑ ብከ አቡከ ወእምከ ወትትኃሠይ እንተ ወለደተከ ።

፳፭ ሀበኒ ወልድየ ልበከ፡ ወአዕይንቲከኒ ፍናወ ዚአየ ይዕቀባ ።

፳፮ ዕዕድ ስቍርት ዘማዊት፡ ወንዘቅት ፀባብ ነኪርት ።

፳፯ ዘሐረ ኀቤሃ ፍጡነ ይትኃጐል፡ ወኵሉ ጸዋግ የኃልቅ ።

፳፰ ወልድየ ለመኑ ወይሌ፡ ወለመኑ ሀከክ፡ ወለመኑ ባእስ፡ ወለመኑ ጋእዝ፡ ወለመኑ ኵነኔ ወለመኑ ቅጥቃጤ

አጋፋሪ ቁሞበታልና ዓይንህን አራምደህ ብትመለከት አታገኘውም፡ የቆመው አጋፋሪውም አንተን አዳፍቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል ።

ከስሱ ሰው ጋራ አትመገብ፡ ምግቡንም አትውደድ፡ በሬ ሣርን እየሳሳ እንዲበላ እየሳሳ ይበላል ይጠጣል ።

ወደ አንተም አታግባው ከሱም ጋራ እንጀራ አትብላ ብላ ጠጣ ይልኻል ልቡናው ግን ከንተ ጋራ የለም ።

ይተፋል ይተፋፋል በጎ ነገርህንም ያበላሽብኻል ።

ብልህ መስሎ በጎ ነገርህን እንዳይንቅብህ በላዋቂ ሰው ዘንድ የምትናገረው ነገር አይኑርህ ።

አባቶችህ ያኖሩትን ድንበር አታፍርስ ።

የሚያድናቸው እግዚአብሔር ፅኑዕ ነውና ከአንዱም ጋራ ፍርዳቸውን ይፋረድላቸዋልና፡ ወደ ድኻ አደጉ ገንዘብ አትግባ ። ኢዮ፡ ፲፱ ፳፭ ። ምሳ፡ ፳፪ ፳፫ ።

ልቡናህን ለምክር ለእዝናት ስጥ፡ ጆሮህንም የዕውቀት ነገርን ለመስማት አዘጋጅ ። ምሳ፡ ፲፭ ፲ ።

በብትር ብትመታቸው አይሞቱምና ልጆችህን መሥራት መቅጣት ቸል አትበል ።

አንተ በብትር ትመታቸዋለህ ሰውነታቸውን ከሞት ታድናለህ ።

ልጄ! ልቡናህ አዋቂ ቢሆን የኔን ልቡና ደስ ያሰኛል ።

የነገርኩህ ነገር በከንፈርህ ብትኖር (ብትነገር) ለከንፈሮቼ የቀኑ ይሆናሉ ።

በየጊዜው እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር እንጂ በኃጢአተኞች ላይ ልቡናህ አትቅና ።

ሕግጋቱን ብትጠብቃቸው ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያዛምዱህ ይሆናሉ፡ አለኝታህም አይርቅም ።

ልጄ! የምነግርህን ስማ ብልህ አዋቂም ሁን፡ የልቡናህንም አሳብ አቅና ።

መሸታ ጠጭ አትሁን፡ የበጋማች (የሉከንዳ) ሥጋንም የምትገዛ አትሁን ። ምሳ፡ ፳፫ ፳፱ - ፴ ።

አመንዝራ መሸታ ጠጭ ሁሉ ይቸገራል፡ የተቀደደ ጨርቅንም ይለብሳል፡ ሥራ ትቶ የሚተኛም ሰው ሁሉ ይቸገራል ። ዘዳ፡ ፳፩ ፩ ። ምሳ፡ ፯ ፲፩ ።

ልጄ! የወለደህ የአባትህን ነገር ስማ፡ ብታረጅም እናትህን አታክፋፋት ። ምሳ፡ ፴ ፲፯ ።

በጎ አባት ሠርቶ ቀጥቶ ያሳድጋል፡ በተማረ ልጅም ልቡናውን ደስ ይላታል ። ምሳ፡ ፳፫ ፲፭ - ፳፭ ።

እናትና አባትህ በአንተ ደስ ይላቸዋል፡ ይልቁንም የወለደችህ እናትህ ደስ ይላታል ።

ልጄ! ልብህን ስጠኝ፡ ዓይነ ልቡናዎችህም የኔን ሕግ ይጠብቁ ።

አመንዝራ ሴት የተነደለች ማድጋ ናት፡ ልዩ የሆነች ጸባብ ጕድጓድም ናት ።

ወደሷ የሄደ ሰው ፈጥኖ ይጠፋል፡ ጠማማ ሰውም ሁሉ በሷ ይጐዳል ። ምሳ፡ ፯ ፲፱ ።

ልጄ! ልቅሶ ለማነው፤ ክርክርስ ለማነው፤ ጠብስ ለማነው፤ ፍርድስ ለማነው፤ መቀራደድስ ለማነው፤ በከ

በከንቱ ፡ ወለመኑ ስጉዳት አዕይንቲሁ ።

፳፱ አኮኑ ለእለ ይጐነድዩ ውስተ ስታየ ወይን ፡ ወአኮኑ ለ
እለ ይተልዉ አሠረ ወይን ።
፴ ወእደ ይከውን ሰንቢል ኢትስክሩ ወይነ ፡ አላ ተናገሩ
ምስለ ሰብአ ጻድቃን ፡ ወተናገሩ በነሶሳው ።

፴፩ እመ ውስተ ፍያላት ወጽዋዓት ወሀብከ ዓይነከ ተሐ
ውር ድኅረ ዕራቀከ ከመ ናሕስ ።
፴፪ ወደኃሪተከ ከመ ንስከተ አርዌ ምድር ትሰፍሕ ፡ ወከ
መ ዘእምቃግሥት ይስሕብ ኅምዘ ።

፴፫ ወአዕይንቲከ ይኔጽራ ነኪራተ ፡ ወውእተ ጊዜ ይነብብ
አፉከ ጠዋየ ።
፴፬ ወትሰክብ ከመ ዘውስተ ልበ ባሕር ወከመ ዘየኃድፍ
ውስተ ብዙኅ ሞገድ ።
፴፭ ወትብል ዘበጡኒ ወኢሐመምኩ ፡ ወዓዲ ትብል ተሣ
ለቁ ላዕሌየ ወአንስ ኢያእመርኩ ማእዜ ነግሀ ይከውን
ከመ እምጻእ ወእኅሥሥ ምስለ እለ አሐውር ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወልድየ ኢትትቀሐው ምስለ ሰብአ እኩያን ፡ ወኢት
ፍቱ ሀልዎ ምስሌሆሙ ።
፪ እስመ ሐሰተ ይትሜሀር ልቦሙ ፡ ወሕመሚ ይትናገር
አፉሆሙ ።
፫ ምስለ ጥበብ ይትሐነጽ ቤት ፡ ወምስለ አእምሮ ይት
ነሣእ ።
፬ ወምስለ ጠይቆ ይመልእ መዛግብተ ፡ ኵሉ ክብር ወብ
ዕል ሠናይ ።
፭ ይኄይስ ጠቢብ እምጽኑዕ ፡ ወብእሲ ዘቦ አእምሮ እም
ወፍር ዓቢይ ።
፮ በሕዳፌ ይከውን ጸብእ ፡ ወረድኤትሰ ዘምስለ ልብ
መከሪት ።
፯ ጥበብ ወአእምሮ ሠናይ ውስተ አንቀጸ ጠቢባት ይት
ረከብ ፡ ወጠበብት ኢይትገኀሡ እምቃለ እግዚአብሔር
አላ ይሄልዉ በማኅበር ።
፰ ለዐብዳን ይዳደቆሙ ሞት ።
፱ ይመውት ዐብድ በኃጣውእ ።

፲ ርኵሱ ለብእሲ ቀታሊ ያጠልቆ በዕለት እኪት ።

፲፩ ወበዕለተ ምንዳቤ እስከ የኃልቅ አድኅን እለ ይሰሐቡ
ውስተ ሞት ፡ ወተሣይጦ ዘይትቀተል ኢትምሃክ ።

፲፪ ወእመሰ ትቤ ኢየአምሮ ለዝ ፡ አእምር ከመ እግዚአ
ብሔር የአምር ልበ ኵሉ ፡ ወዘገብረ እስትንፋሰ ለኵሉ
ውእቱ የአምር ኵሎ ፡ ወይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ ።

ንቱ ጥፋትስ ለማነው ፧ ዓይኖችን ግልብጥብጥ አድርጎ
ማየት ለማን ነው ፧ ዘፍ፡ ፵፱ ፲፪ ። ምሳ፡ ፳፫ ፳፩ - ፴፭ ።
ወይን ወደሚጠጣበት ገብተው ለሚቈዩ ሰዎች አይ
ደለምን ፧ የወይንንስ ፍለጋ ለሚከተሉ አይደለምን ! ።
ከደጋጎች ሰዎች ጋራ በመደማመጥ በመስማማት ተነ
ጋገሩ እንጂ ማኅበር (ጋሬዳ) ከተደረገ ዘንድ ወይን ጠጥ
ታችሁ አትስከሩ ። መዝ፡ ፻፳፯ ፬ ።
ወደ ፍንጃሎች ወደ ጽዋዎች ብትመለከት ኋላ እንደ
ግንብ ራቁትህን ትሄዳለህ ።
በፍጻሜህ የምድር እባብ እንደነከሰው ሰው ትዘረጋ
ለህ ፡ ከፉኝት እባብ ወገንም መርዙ እንደተሠራጨበት
ሰው ትዘረጋለህ ። ምሳ፡ ፳፫ ፲፰ ።
ዓይኖችህ ልዩ ልዩን ያያሉ ፡ ያን ጊዜ አፍህ ጠማማ
ነገርን ይናገራል ።
በባሕር ውስጥ እንዳለ አዘ ትተኛለህ ፡ በብዙ ማዕበል
መካከልም ሲቀዝፍ እንደዋለ ሰው ትተኛለህ ።
መቱኝ አላመመኝም ትላለህ ፡ ዳግመኛም ሳቁብኝ
(ዘበቱብኝ) ፡ እኔ ግን አላወቅሁትም ትላለህ ፡ አብሬያቸው
ከኔ ጋራ የሚሄዱትን ሰዎች እፈልግ ዘንድ መቼ ይነጋል ፧
ትላለህ ። ምሳ፡ ፳፯ ፳፪ ። ኤር፡ ፭ ፫ ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

ልጄ ! ከክፉ ሰዎች ጋራ አትከራከር ፡ ከነሱ ጋራ መኖ
ርንም አትውደድ ። መዝ፡ ፴፮ ፩ ።
ልቡናቸው ሐሰትን ይማራልና ፡ አፋቸውም ምቀኝነ
ትን ይናገራልና ።
ቤት ከጥበብ ጋራ ይታነጻል ፡ ከዕውቀትም ጋራ ይነ
ሣል ።
ሕገ እግዚአብሔርን ከመረዳት ጋራ ሬቁ ጐተራው
ይመላል ፡ ክብርም ሰለጸግነትም ሁሉ በጎ ነው ።
(በኃጢአት) ከጸና ሰው ብልህ ሰው ይሻላል ፡ ብዙ
ርስት ጕልት ካለው ሰውም ዕውቀት ያለው ይሻላል ።
በምክር ጦርነት ይደረጋል ፡ ድል መንሣት ግን ሕገ
እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ከምትመክር ልቡና ጋራ ነው ።
ጥበብ በጎ ዕውቀት በመምህራን አደባባይ (ጉባኤ)
ይገኛል ፡ መምህራንም ዐሥርቱ ቃላትን በማስተማር ይኖ
ራሉ እንጂ ፡ ዐሥርቱ ቃላትን ከማስተማር አይርቁም ።
አላዋቆች ሰዎችን ሞት ይገናኛቸዋል ።
አላዋቂ ሰው ንስሓ ሳይገባ በኃጢአቱ እንደተያዘ
ይሞታል ።
ነፍሰ ገዳይ ሰው በተፈረደበት ቀን ኃጢአቱ ጥል
ቅልቅ ያደርገዋል ።
ችግር በጸናበትም ቀን ገንዘብህ እስኪያልቅ ድረስ
በቀጠና ተይዘው ወደ ሞት የሚሄዱትን አድን ፡ በቀጠና
የሚሞትንም ሰው ማዳን አትሸልግ ። መዝ፡ ፹፪ ፬ ።
ይህን አላውቀውም ብትል ግን ፡ እግዚአብሔር የሰ
ውን ሁሉ ልቡና እንዲያውቅ ዕወቅ ፡ ለሰውም ሁሉ ነፍ
ስን የፈጠረ እሱ ሁሉን እንዲያውቅ አውቆም እንደ
ሥራው ለሰው ሁሉ ይከፍለዋል ። ምሳ፡ ፳፪ ፫ ።

፲፫ ብላዕ መዓረ ወልድየ እስመ ሠናይ ፀቃውዕ ፡ ከመ ያምዕርዕር ለጒርዔከ ።

፲፬ ከማሁ ተመሀር ጥበበ ወአእምሮ ለእመ ረከብከ ወይነ ሠናየ ይከውን ሞትከ ወተስፋከ ኢየኀድገከ ።

፲፭ ወኢታብእ ረሲዓነ ውስተ መከነ ጻድቃን ፡ ወኢትስሐት በጽጋብ ከርሥከ ።

፲፮ ስብዐ ይወድቅ ጻድቅ ፡ ወስብዐ ይትነሣእ ፡ ወረሲዓንሰ ይደውዩ በእኩይ ።

፲፯ ለእመ ወድቀ ጸላኢከ ኢትትፈሣሕ በቱ ፡ ወበተዓቅፎቱ ኢትትዓበይ ።

፲፰ እስመ ይሬኢ እግዚአብሔር ወኢይኤድሞ ፡ ወይመይጥ መዓቶ እምኔሁ ።

፲፱ ኢትትፈሣሕ በገበርተ እከይ ፡ ወኢትቅናእ ላዕለ እኩያን ።

፳ እስመ ኢይከውን ዘመን ለእኩያን ፡ ወብርሃኖ ረሲዓን ይጠፍእ ።

፳፩ ወልድየ ፍርሆ ለእግዚአብሔር ፡ ወለንጉሥኒ ፡ ወኢበአሐዱ እምኔሆሙ ኢትትዓበይ ።

፳፪ እስመ እሙንቱ ግብተ ይትቤቀልዎሙ ለረሲዓን ፡ ወዘነኔ ከልኤሆሙ መኑ የአምር ።

፳፫ ቃለ ዘየዓቅብ ወልድ ርኁቅ ውእቱ እምተኀጕሎ ወዘሰ ይትዌከፎ ሎቱኒ ይትዌከፎ ።

፳፬ ምንትኒ ሐሰት እምልሳነ ንጉሥ ኢይትበሀል ፡ ወአልቦ ሐሰት እምልሳኑ ዘይወፅእ ።

፳፭ መጥበሕት ቃለ ንጉሥ ወአኮ እንተ አበል ለዘተውህበት ትቀጥቅጦ ።

፳፮ ወእመሰ ተስሕለት ሰይፈ መዓቱ ምስለ ሥረዊሁ ሰብአ ታኀልቅ ፡ ወአዕፅምተ ሰብእ ታኀቊ ፡ ወታውዒ ከመ ነበልበል እስከ እመ ኢይትበላዕ እምእኩለ እንስርት ።

፳፯ ወልድየ ፡ ዘዚአየ ነገረ ፍራህ ወተወከፍ ወነስሕ ፡ ዘንተ እቤ ለአለ ፡ አምኑ በእግዚአብሔር ወፈጸምኩ ።

፳፰ እስመ አነ ዐብድ እምኵሉ ፡ ወጥበበ ሰብእኒ ኢሀሎ ኀቤየ ።

፳፱ ወእግዚአብሔር ወሀበኒ ጥበበ ወአእምሮ ቅዱሳን አእመርኩ ።

## ምዕራፍ ፳፭ ።

፩ መኑ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ወወረደ ፡ ወመኑ አስተጋብአ ነፋሳተ ውስተ ኀፅኑ ፡ ወመኑ ዓቈረ ማያተ በልብሱ ።

፪ ወመኑ አኀዘ ኵሎ አጽናፈ ምድር ፡ መኑ ስሙ ፡ ወመኑ ስመ እቡሁ ፡ ከመ ታእምሩ ኵሎ ።

፫ ነገረ እግዚአብሔር ርሱን ወይትቃወም ሎሙ ለእለ ይፈርህዎ ።

ጕሮሮህን ያጣፍጠው ዘንድ ማር ወለላ መልካም ነውና ፡ ልጄ ! ማር ብላ ። መኃ ፬ ፲፩ ።

እንደዚሁም ዕውቀትን ጥበብን ብታገኝ ተማር ፡ ወይንንም ብታገኝ ሞትህ ያማረ ይሆናል ፡ አለኝታህም አይለይህም ። መዝ ፲፱ ፲ ፤ ፻፲፱ ፱ - ፫ ።

እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችን በደጋጎች ቦታ አታግባ ፡ ሰውነትህም በጽጋብ አትሳሳት ።

ደግ ሰው ሰባት ጊዜ (በኃጢአት) ይሰነካከላል ፡ ሰባት ጊዜም (በንስሐ) ይነሣል ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በክፉ ኃጢአት ይያዛሉ ። መዝ ፴፮ ፳፬ ።

ጠላትህ በመከራ ቢሰነካከል ደስ አይበልህ ፡ በመሰነካከሉም አትታበይ ። ምሳ ፲፯ ፭ ።

እግዚአብሔር ይህን አይቶ ደስ አይለውምና ፡ መዓቱንም ወደ አንተ ይመልሰዋልና ። ዘኍ ፲፩ ፲ ።

ክፋትን በሚሠሩ ሰዎች ደስ አይበልህ ፤ በክፉ ሰዎችም አትቅና ።

ለክፉ ሰዎች ዘመን አይሰጥምና ፡ እግዚአብሔርን የዘነጉም ሰዎች ተድላ ደስታቸው ይጠፋል ።

ልጄ ! እግዚአብሔርን ፍራው ንጉሥንም አክብረው ከነዚሁም በአንዱ አትታበይ ። ምሳ ፴፩ ፫ ።

እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችን እነዚህ ድንገት ይበቀላቸዋልና ፡ የሁለቱንም ፍርድ ማን ያውቃል ፤ ።

የነገሩትን ቃል የሚጠብቅ ልጅ ከጥፋት የራቀ ነው ፡ የነገሩትንም የሚቀበል ሰው እሱንም እግዚአብሔር ይቀበለዋል ።

ከንጉሥ አንደበት ምንም ሐሰት ይነገራል አይባልም ከአንደበቱም የሚወጣ ሐሰት የለም ።

የንጉሥ ቃል ሾተል ናት ለጥፋት የተሰጠችውን ሰው ሰውነት ታጠፋዋለች እንጂ አንድ አካል ብቻ የምታጠፋ አይደለም ።

ሰይፈ መዓቱ ብትሳል ግን ከወገኑ ጋራ ሰውን ታጠፋለች ፡ የሰውንም ወገኖች ታጠፋለች ፡ ከአሞሮች ግልግል ወገን የማይበላ እስኪሆን ድረስ እንደ እሳት ነበልባል ታቃጥላለች ።

ልጄ ! የኔን ነገር ፈርተህ ተቀበለው ንስሓም ግባ ፡ በእግዚአብሔር ለሚያምኑ ሰዎች ይህን ተናግሬ ጨረስኩ ።

እኔ ከሰው ሁሉ ተለይቼ ሰነፍ ነበርኩ ፡ የሰውም ጥበብ በኔ ላይ አልነበረምና ።

እግዚአብሔር ጥበብን አስተማረኝ ደጋግ ሰዎች የሚያውቁትንም ዕውቀት አወቅሁ ።

## ምዕራፍ ፳፭ ።

ወደ ሰማይ የወጣ ከሰማይ የወረደ ማን ነው ፤ ነፋሳትን በክንዱ የሰበሰበ (በሥልጣኑ የፈጠረ) ማን ነው ፤ ውኃዎችንስ በልብሱ የቋጠረ ማን ነው ፤

የምድርን ዳርቻ ሁሉ የያዘ ማን ነው ፤ ይህን ሁሉ ታውቁ ዘንድ ስሙ ማን ነው ፤ የአባቱስ ስም ማን ነው ፤

የእግዚአብሔር ነገሩ የጋለ ነው ፡ ለሚፈሩትም ሰዎች ዋስ ጠበቃ ሁኖ ይቆምላቸዋል ።

፬ ወኢትወስከ ውስተ ነገሩ ከመ ኢይዝልፍከ ፡ ወሐሳዌ ኢትኩን ።
፭ ክልኤተ ነገረ እስእል እምኀቤከ እግዚእየ ፡ ወኢትክልአኒ ጸጋከ ዘእንበለ እሙት ።
፮ ከንቶ ነገረ ወሐሰተ አርኅቅ እምኔየ ፡ ብዕለ ወንዴተ ኢተሀበኒ ፡ አላ ሥራዕ ሊተ ዘይትፈቀድ ወዘየአክለኒ ።

፯ ከመ እስኪ ልየ ሐሳዌ ኢይኩን ወኢይበል መኑ እግዚአብሔር ፡ ወእመ አኮ ነዳየ ኢይሰርቅ ፡ ወኢይምሐል በስመ እግዚአብሔር በሐሰት ።

፰ ወኢታግብእ ገብረ ውስተ እደ እግዚኡ ፡ ከመ እመበ ዘረገመከ ኢትማስን ።
፱ ወልድ እኩይ ይረግም አቡሁ ፡ ወእሞሂ ይበርክ ።
፲ ወልድ እኩይ ጽድቀ ርእሱ ይፈትሕ ፡ ወፀአቶሂ ኢይጤይቅ ።
፲፩ ለወልድ እኩይ አዕይንተ ዕበይ ቦቱ ፡ ወቀራንብቲሁኒ ያሌዕል ።
፲፪ ወልድ እኩይ ስነነ መጥባሕት ቦቱ ፡ ወጥረሲሁ መከርከር ከመ ያኅልቅ ነዳያነ እምድር ፡ ወምስኪናኒሆሙ እምሰብእ ።
፲፫ ዘንተ አየድዓክሙ ለጠቢባን ከመ ታእምሩ ኀፊረ ገጽ ፡ ለፍትሕ አከ ሠናይ ።
፲፬ ዘይብሎ ለረሲዕ ጻድቅ ውእቱ ፡ ርጉመ ይከውን በሕዝብ ፡ ወጽሉአ በአሕዛብ ።
፲፭ ወእለሰ ይዘልፉ በጽድቅ ያሤንዩ አስተርእዮ ፡ ወላዕሌሆሙ ትመጽእ በረከት ሠናይት ።
፲፮ ከናፍር ያወሥኡ እለ ያፈቅሩ ነገረ ጥበብ ።

፲፯ አስተዳሉ ለመንገድከ ምግባሪከ ፡ ወተደለው ውስተ ወፍር ወትሉ ድኅሬየ ወታነሥእ ቤተከ ።
፲፰ ወኢትኩን ስምዐ በሐሰት ላዕለ ሰብአ ብሔርከ ፡ ወኢትጌጊ በከናፍሪከ ።
፲፱ ወኢትበል በከመ ረሰየኒ እሬስዮ ፡ ወእፈድዮ በከመ ገፍዐኒ ።
፳ ውስተ ገራህተ ብእሲ ዐብድ ኀለፍኩ ፡ ወውስተ ዐፀደ ወይነ ብእሲ ነዳየ አእምሮ ሖርኩ ።
፳፩ ናሁ በቍለ ላዕሌሁ ሦክ ወየዐብር ሣዕሩ ፍጹመ ወይከውን በድወ ወፀቈኒ እበኒሁ ይነኀል ።

፳፪ ድኅረ አነ ነሳሕኩ ፡ ወነጸርኩ እኅረይ ተግሣፀ ።

፳፫ ሕቀ ድቃስ ፡ ወሕቀ ንዋም ፡ ወሕቀ አስተጋብኦ እደ ዲበ እንግድዓ ።

፳፬ ወእመ ዘንተ ትገብር ትመጽእ እንዘ ትትቄደም ከመ እኩይ ሐዋርያ ንዴት ፡ ወተጽናስ ከመ ኄር ረዋጺ ።

እንዳይዘልፍህ ሐሰተኛም እንዳትሆን በነገሩ ላይ አትጨምር ።
ጌታየ ! ከንተ ዘንድ ሁለት ነገርን እለምናለሁ ፡ ሳልሞት የሰጠኸኝንም አትንሣኝ ።
ሐሰትንና ከንቱ ነገርን ከኔ አርቅ የሚወደደውን የሚበቃኝን ስጠኝ እንጂ ፍጹም ባለጸግነትን ፍጹም ድኽነትን አትስጠኝ ።
ብዕልን አብቅቼ ሐሰተኛ እንዳልሆን ፡ እግዚአብሔርም ማን ነው ! እንዳልል ፡ ይህም ባይሆን ተቸግሬ እንዳልሰርቅ ! በሐሰትም በእግዚአብሔር ስም እንዳልምል የሚበቃኝን ስጠኝ እንጂ ።
የረገመህ መርገም ቢኖር ራስህን እንዳታጠፋ ስታስታርቅ ባርያን በጌታው እጅ አሳልፈህ አትስጥ ።
ክፉ ልጅ አባቱን ይረግማል ፡ እናቱንም ይረግማል ።
ክፉ ልጅ የራሱን በጎነት ይናገራል ፡ ከዚህ ዓለም በሞት መውጣቱን (መለየቱን) አያውቅም ።
ለክፉ ልጅ ከፍና ዝቅ አድርጎ የሚያይባቸው የትዕቢት ዓይኖች አሉት ፡ ቅንድቦቹንም ስቀል ስቀል ያደርጋል ።
ለክፉ ልጅ የሾተል ጥርስ አለው ፡ ድኾችን ከዚህ ዓለም ጦም አዳሪዎችንም ከሰው ለይቶ ያጠፋ ዘንድ መንጋጋው መጋዝ ነው ።
ታውቁ ዘንድ አዋቆች ለምትሆኑ ለናንተ ይህን እነግራችኋለሁ ፡ በፍርድ ጊዜ የሰው ፊት ማፈር ደግ አይደለም ።
ይሙት በቃውን ይድን በቃ ብሎ የሚፈርድ ሰው በሕዝቡ ዘንድ የተረገመ በአሕዛብም ዘንድ የተጠላ ይሆናል ።
በእውነት የሚቈጡ ሰዎች ግን በባለሟልነት ይገለጻሉ ፡ በጎ በረከትም ለነሱ ትመጣላቸዋለች ።
የጥበብ ነገር የሚወዱ ከንፈሮች የጥበብን ነገር ያስተምራሉ ።
ለመንገድህ ሥራህን አዘጋጅ ፡ ወደምትሠማራበትም ተዘጋጅ እኔንም ተከተለኝ ቤትህን ታነሣለህ ።
በአገርህ ሰዎች ላይ በሐሰት አትመስክር ፡ በከንፈሮችህም አትሳሳት ። ምሳ ፳፭ ፲፰ ።
እንዳደረገኝ አደርጋዋለሁ እንደ በደለኝም አበድለዋለሁ አትበል ። ምሳ ፮ ፳፪ ።
ወደ ሰነፍ ሰው እርሻ ሄድኩ ፡ ከዕውቀት ወደ ተቸገረ ሰው ወይን በታም ሄድኩ ። ኢዮ ፩ ፫ ።
እነሆ እሾኽ በላዩ በቀለበታል ፡ ሣሩም ፈጽሞ ደርቆበታል ፡ ምድረ በዳም ሆኖአል የደንጊያውም ቅጥር ፈርሷል ።
ከዚህ በኋላ እኔ አዘንኩ ፡ ምክር እዝናትን እመርጥ ዘንድ ወደድኩ ።
አንድ ጊዜ ምኝታ ፡ አንድ ጊዜ እንቅልፍ ፡ አንድ ጊዜ እጅን ከብብት አግብቶ እንደ መቀመጥ ነው ብየ አዘንኩ ።
ይህን ብታደርግ እንደ ክፉ ቀላጤ ችጋር አስቀድማ ትመጣብኻለች ፡ ጦም አደርም እንደ በጎ ቀላጤ ትመጣብኻለች ። ምሳ ፮ ፲፩ ።

| ምዕራፍ ፴፯ ። | | ምዕራፍ ፴፯ ። |
|---|---|---|
| ለዓለቅት ሠላስ አዋልድ ላቲ፡ ተፋቅሮ እለ ይትፋቀራ፡ ወሠለስቲሆን እለ ኢይጸግባ፡ ወራብዕቶንሰ ስእነት ብሂለ ከንየ ። | ፩ | ለዓለቅት (ዓለም) ሦስት ልጆች አሏት፡ እነዚሁም የሚዋደዱ ናቸው፡ ሦስቱ ሁሉ ቢወዱ ቢወዱ የማይጠግቡ ናቸው፡ አራተኛቸው ግን በቃኝ ማለትን ተሳናት ። |
| ሲኦል፡ ወፍቅረ ብእሲት፡ ወገሃነም፡ ምድር እንተ ኢተመልእ ማየ፡ ወማይ፡ ወእሳት ኢይብል ከንየ ። | ፪ | መቃብር፡ ብትቀበል ብትቀበል ሴትም ብትወድ ብትወድ በቃኝ አትልም፡ ገሃነም የምትሆን ውቅያኖስም ውኃን ብትቀበል ብትቀበል በቃኝ አትልም፡ ውኃም ቢወስድ ቢወስድ፡ እሳትም ቢያቃጥል ቢያቃጥል በቃን አይሉም ። |
| ዓይን ዘይስሕቅ አበሁ ወዘያስተአኪ ርስዓ እሙ ይመልሕዎ ቋዓት እምግቡ፡ ወይበልዕዎን እጕለ አንስርት ለአዕይንቲሁ ። | ፫ | በአባቱ የሚስቅ የናቱን እርጅና የሚያከፋፋውን ዓይን ቊራዎች ከጕድጓዳቸው ወጥተው ያወልቁታል፡ የአንስርትም ልጆች ዓይኖቹን ከመቃዳቸው ያጠልቁዋቸዋል ። |
| ሠለስቱ እሙንቱ ዘኢይክል አእምሮሙ፡ ወራብዐሙሰ ኢይጤየቅ ። | ፬ | ፍለጋቸውን ማወቅ የማይቻለኝ ሦስት ናቸው፡ አራተኛቸው ግን አይመረመርም (አይታወቅም) ። |
| አሠረ ንስር ዘይሠርር፡ ወፍኖተ አርዌ ምድር ዲበ ኰኵሕ ወአሠረ ሐመር ዲበ ሞገድ እንዘ ተሐውር ወፍናወ ብእሲ በውርዙቱ ። | ፭ | በአየር የሚበር የንስር ፍለጋ፡ በአለት ላይ የሚሄድ የምድር እባብ መንገድ፡ በባሕር ሞገድ ላይ ስትሄድ የመርከብ ፍለጋ አይታይም አይታወቅም፡ ሰውም በሕፃንነቱ የሚሠራው ሥራ አይታወቅም ። |
| ወከመዝ ውእቱ ፍኖታ ለብእሲት እንተ መሐዝ እንተ ገቢራ ትትሐጸብ፡ ወአልቦ እንከሰ ዘገብረት እኩየ ። | ፮ | ሥራዋን ሠርታ የምትታጠብ፡ ከሠራችም በኋላ ክፉ ሥራን የሠራች የማትመስል የአመንዝራ ሴትም ሥራ አይታወቅም ። |
| በእንተ ሠለስቱ ነገር ታድለቀልቅ ምድር፡ ወራብዖሙሰ ኢትክል ፀዊረ ። | ፯ | ስለ ሦስት ነገር ምድር ትነዋወጣለች፡ አራተኛውን ግን መታገሥ አትችልም ። |
| ገብር እመ ነግሠ፡ ወዐብድ ለእመ ጸግበ እክለ ። | ፰ | ባርያ ቢነግሥ፡ አላዋቂ ሰው እኽል ቢጠግብ ። |
| ወአመት እመ አውፅአት እግዝእታ፡ ወጽእልት ብእእሲት እመ አድምዐት ብእሴ ኄረ ። | ፱ | ሴት ባርያ እመቤቷን ብታስወጣ፡ ተጠቅታ ተንቃ ትኖር የነበረች ሴትም ደግ ሰውን ብታገኝ ምድር ትነዋወጣለች ። |
| ወአርባዕቱ ሕፁፃን ውስተ ምድር፡ ወእሉ እሙንቱ ጠቢባን ጠበብት ። | ፲ | በምድር ጥቃቅን የሚሆኑ አራት ፍጥረታት አሉ፡ እነዚሁም የብልህ ብልሆች ናቸው ። |
| ሰኳዕት እለ አልቦሙ ኃይል ወያስተዳልዉ በማእረር ሲሳዮሙ ። | ፲፩ | እነዚሁም ኃይል የሌላቸው በመከር ጊዜ ምግባቸውን የሚሰበስቡ ግብረ ጕንዳኖች ናቸው ። |
| ወግሔያት ሕዝብ ዘኢኮኑ ፅኑዓነ፡ እለ ረሰዩ ውስተ ግበበ ኰኵሕ አብያቲሆሙ ። | ፲፪ | (ሁለተኛዎችም) ሕዝቡ አይተው የሚያደንቁዋቸው የፀኑ ያይደሉ ቤቶቻቸውን በደንጊያ ዋሻ ያደረጉ አሽከኮዎች ናቸው ። መዝ፡ ፻፬ ፲፰ ። |
| ወዘእንበለ መንግሥት ውእቱ አንበጣ፡ ዘየሐውር በአሐዱ ትእዛዝ ኅቡረ ። | ፲፫ | (ሦስተኛው) ንጉሥ የሌለው በአንድ ትእዛዝ (አንዱ በአፏጨበት) የሚሄድ አንበጣ ነው ። |
| ወላጽቂት ዘበእደዊሁ የሐውር እንዘ ጽኑስ ውእቱ የኀድር ውስተ አብያተ ነገሥት ። | ፲፬ | (አራተኛው) በደረቱ የሚሄድ ደካማ ሲሆን፡ በነገሥታቱ ቤት የሚኖር እንሽላሊት ነው ። |
| ሠለስቱ እሙንቱ ዘአዳመ የሐውሩ፡ ወራብዕሰ ዘሠናይ ፍናዊሁ ። | ፲፭ | አካሄዳቸው ያማሩ ሦስት ናቸው፡ አራተኛው ግን አካሄዱ ያማረ ነው ። |
| እጓለ አንበሳ ዘይፀንዕ እምእንስሳ ኢይትመየጥ ወኢደነግፅ እምእንስሳ ። | ፲፮ | (አንደኛ) ከእንስሳት የሚበረታ ከእንስሳ የተነሣ ደንግጦ የማይመለስ የአንበሳ ግልገል ነው ። |
| ዶርሆ ተባዕት ዘየሐውር ኀበ አንስት እንዘ ያስተናፍስ ከነፊሁ፡ ወበሐኵ እንዘ ይሚጥል ላዕለ መርዔት፡ ወንጉሥ እንዘ ይገሥፅ ሕዝበ ። | ፲፯ | (ሁለተኛው) ክንፉን ሰብርብር እያደረገ ወደ ሴት ዶሮዎች የሚሄድ አውራ ዶሮ ነው፡ (ሦስተኛው) በመንጋዎች ላይ ሲያገር የሚታይ የበግ አውራ ነው፡ (አራተኛውም) ንጉሥ ሠራዊቱን ሲሠራ ሲቀጣ ያማረ ነው ። |
| ለእመ መጠውከ ርእሰከ ለተፈርሆ፡ ወሰፋሕከ እደ | ፲፰ | ራስህን ለመፈርዘዝ (ለቦዘን) ብትሰጥ፡ እጅህን ወደ |

ከ ለጋእዝ ተኀሥር።

፴፫ ሕሊብ ሐሊበ ወይከውነከ ለስደ፡ ወለእመ አጸርከ አንፈከ ይወፅእ ደም፡ ወለእመ ሰሐብከ ነገረ ይመጽእ ጋእዝ ወኍነኔ።

፩ ቃለ ዚአየ ተየድአ በኀበ እግዚአብሔር ንጉሥ ራ{ማ} ውእቱ ዘመሀረቶ እሙ።

፪ ኦ ወልድየ ተዐቀብ ምንት ቃለ እግዚአብሔር።

፫ በኵርየ ለከ እብለከ ወልድየ ሚ ወልደ ከርሥየ፡ ወሚ ወልደ ጸሎተ ዚአየ።

፬ ኢተሃበ ለብእሲት ብዕለ ዚአከ፡ ወልበከ ከመ ኢትነስሕ ድኅረ፡ ወኢትግበር ዘኢይደሉ ለንጉሥ ወለእግዚአብሔር።

፭ ወኲንን ኵሎ ሰብአ በጽድቅ፡ ወምስለ ምክር ኵሎ ግበር፡ ወምስለ ምክር ወይነ ስተይ።

፮ ወባሕቱ መኳንንት መዓትማን ወይነ ኢይስተዩ ከመ በስታይ ኢይርስዕዋ ለጥበብ፡ ወኢይክሉ አርትዖ ፍትሐ ለድኩማን።

፯ ሀብዎሙ ወይነ ለኅዙናን፡ ወይስተዩ ወይነ ትኩዛን፡ ከመ ይርስዕዋ ለኀዘን፡ ወሕማመኒ ኢይዝክሩ እንከ።

፰ ክሥት አፉከ በቃለ እግዚአብሔር፡ ወኲንን ኵሎ ሕያዋነ።

፱ ክሥት አፉከ ወኲንን በጽድቅ፡ ፍታሕ ለነዳይ ወለሕሙም።

ፀብ ወደ ክርክር ብትዘረጋ ትዋረዳለህ።

ወተቱን እለብ ለስታ ቅቤ ይሆንልሃል፡ አፍንጫህን ብትጠምቀው ደም ይወጣዋል፡ ነገርንም ብትፈልግ ፀብ ክርክር ቅጣት ይመጣብሃል።

እናቱ ያስተማረችው ብልህ የምሆን የኔ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ተወደደ። ምሳ፡ ፲፩ ፴፩።

ልጄ! የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሆነ አውቀህ ተጠበቅ።

የበኵር ልጄ እለሃለሁ፡ ከበሕርዬ የተከፈልክ ልጄ በብፅዓት የወለድኩህ ልጄ! ቃለ እግዚአብሔር ምን እንደሆነ አውቀህ ተጠበቅ።

ኋላ እንዳታዝን ለሴት ገንዘብህን ልብህን አትስጣት፡ በእግዚአብሔርም በንጉሥም የማይገባ ሥራ አትሥራ።

ለሰዎች በእውነት ፍረድላቸው፡ ከምክር ጋር ሁሉን አድርግ፡ ከምክር ጋራ ወይንን ጠጣ። ምሳ፡ ፳ ፱።

ነገር ግን ጠጥተው ፍርድን እንዳይዘነጉዋት ቍጡ የሆኑ መኳንንት ወይንን አይጠጡ፡ ለድሆች ፍርድን ማቅናት አይችሉምና።

ላዘኑ ሰዎች ወይንን ስጡዋቸው፡ ኃዘንን ይረሱዋት ዘንድ፡ መከራንም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳያስቡ ያዘኑ ሰዎች ወይንን ይጠጡ።

በነፍስ ሕያዋን የሆኑትን ሰዎች ሁሉ አስተምራቸው።

አፍህን ገልጠህ እውነት ፍርድን ፍረድ፡ ለድሃውም ላዘነውም ፍረድለት።

ተ ፈ ጸ መ  ም ሳ ሌ ያ ተ  ሰ ሎ ሞ ን  ወ ል ደ  ዳ ዊ ት፡
ወ ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር  ስ ብ ሐ ት  ወ አ ኰ ቴ ት
አ ሜ ን።

እነሣሥቶ ላስጀመረን እስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና
የዳዊት ልጅ ሰሎሞን የተናገረው ነገር ደረሰ፡
ተፈጸመ።

# መኃልየ ሰሎሞን

## መኃልየ መኃልይ ዝ ውእቱ ዘሰሎሞን።

### ምዕራፍ ፩።

፩ ይስዕመኒ በስዕመተ አፉሁ፣ አዳም አጥባትኪ እም ወ
ይን ወመዓዛ ዕፍረትኪ እምኵሉ አፈው።

፪ ዕፍረት ዘተሠውጠ ስምከ፣ ወበእንተዝ ደናግል አፍ
ቀራከ፣ ወሰሐባከ ድኅሬከ።

፫ በመዓዛ ዕፍረትከ ንረውፅ፣ አብአኒ ንጉሥ ውስተ ጽ
ርሑ፣ ንትፌሣሕ ወንትኃሠይ ብኪ፣ ናፍቅር አጥባተኪ
እምወይን፣ ወርቱዕ አፍቅሮትኪ።

፬ ጸላም አነ ወሠናይት እምአዋልደ ኢየሩሳሌም፣ ከመ
ምጽላላተ ቄዳር ወሐይመታተ ሰሎሞን።
፭ ኢትርአያኒ እስመ አነ ጸላም፣ እስመ ኢርእየኒ ፀሐይ።

፮ ደቂቀ እምየ ተባአሱ በእንቲአየ፣ አንበሩኒ ዓቃቢተ
ዓፀደ ወይን፣ ዓፀደ ወይን ዘዚአየ ኢዓቀብኩ።
፯ ንግረኒ ዘአፍቀረት ነፍስየ፣ አይቴ ትሬኢ ወአይቴ
ትሰክብ ጊዜ ቀትር፣ ከመ ኢይኩን እንዘ አንጌጊ ውስተ
መራዕየ ካልአኒከ።
፰ እመ ኢያእ ምርኪ ርእሰኪ ሠናይት እምአንስት፣ ፃኢ
አንቲ ውስተ ሰኰናሆሙ ለመርዔት፣ ወረዐዪ መሐስአ
አጣሊኪ ውስተ አዕፃዳቲሆሙ ለኖሎት።

፱ ለፈረስየ ወለሠረገላተ ፈርዖን፣ አስተማሰልኩኪ አንተ
ኀቤየ።
፲ ጥቀ አዳም መላትሕኪ ከመ ማዕነቅ፣ ወክሳድኪ ከመ
አርማስቆስ።
፲፩ አምሳለ ወርቅ ይግበሩ ለኪ ኵስኵሰ ዘብሩር፣ እስከ
ሶበ ንጉሥ ያሰምክ በቱ።
፲፪ ናርዶስ ወሀበ መዓዛሁ።
፲፫ ዕቍረ ማየ ልብን ዘወልድ እኁየ ሊተ ማእከለ አጥባ
ትየ የዓርፍ።

## ሰሎሞን የተናገረው የምስጋና ምስጋና ይህ ነው።

### ምዕራፍ ፩።

በአፉ አሳሳም ይስመኛል ከወይን ይልቅ ጡትሽ ያማ
ረ ነው፣ (ሁለቱ ጽላቶችሽ) የሽቱሽም መዓዛ ከሽቱ ሁሉ
መዓዛ ይልቅ ያማረ ነው። ምሳ፡ ፳፯ ፯።

ስምህ ከስሜ ጋራ የተቀላቀለው ነው፣ ስለዚህም
ነገር ቆነጃጅቶች ወደዱህ፣ አንተንም ከወደ ኋላህ (በሃ
ይማኖት) ሳቡሕ።

በሕግህ ጸንተን እንኖራለን፣ ንጉሡም ወደ አዳራሹ
(ቤተ መቅደስ) አገባኝም በአንቺ ፈጽሞ ደስ ይለናል፣
ከወይን ይልቅ ጡትሽን እንወዳለን፣ አንቺንም መው
ደድ የተገባ ነው። ዮሐ፡ ፯ ፴፬። መዝ፡ ፪፲፱ ፴፪።

ከኢየሩሳሌም ልጆች ይልቅ እንደ ሰሎሞን ድንኳን
እንደ ዘላን ጐጆ አምሬ የነበረ እኔ በመከራ ጠቍሬ አለሁ።

ፀሐይ (ረድኤቱ) ስላላየኝ በመከራ ጠቍሬ አለሁና
አትዩኝ።

የናቴ ልጆች ስለኔ ተጣሉ፣ የወይን ቦታ ጠብቂ ብለው
አኖሩኝ፣ እኔ ግን የወይኔን ቦታ አልጠበቅሁም።

ሰውነቴ የወደደችውን ንገረኝ በባልንጀሮችህ መንጋ
ዎች መከከል ስቅበዘበዝ እንዳልገኝ ወዴት ትሠማራለህ፤
በቀትር ጊዜስ በየት ትተኛለህ፤ አለች።

ከሴቶች ይልቅ አምረሽ ተወደሽ ትኖሪ የነበረ (ቤተ
እስራኤል) ራስሽ እግዚአብሔርን ካላወቅሽ የአሕዛብን
(የናቡከደነፆር) ፍለጋ ተከትለሽ ውጪ በሞግዚቶች በታ
ተተከተሽ ልጆቻቸውን አሳድጊ። ሉቃ፡ ፩ ፵፪።

የግብጽ ፈረስ ፈረሴን የግብፅ ሠረገላ ሠረገላዬን ልታ
ጠፊ የኔ ሆይ (ቤተ እስራኤል) በኔ መሰልኩሽ።

ፊትሽ እንደ ዋኖስ ፊት እጅግ ያማረ ነው፣ አንገት
ሽም እንደ ብር ዘንግ ነው። ሕዝ፡ ፲፮ ፲፩ - ፲፫።

ንጉሥ እስኪጠጋበት ድረስ በወርቅ አምሳል የብር
ዝንጕርጕር ይሠሩልሽ።

ናርዶስ የሚባል ሽቱ መዓዛውን ሰጠ።

የተቋጠረ የልጅ ወንድሜ ልባንጃ ሽቱ የኔ ገንዘብ
ነው፣ በጡቶቼ (በሁለት ጽላቶቼ) መከከል ያርፋል።

፲፬ እስከል ዘጸገየ ዘወልድ እኁየ ሊተ ውስተ ዐፀደ ወይን ዘበጋዲ ።

፲፭ ነያ ሠናይት አንተ ኀቤየ ነያ ሠናይት ፡ አዕይንትኪ ዘርግብ ።

፲፮ ናሁ ሠናይ አንተ ወልድ እኁየ አዳም በውስተ ምስካቢነ ዘበሕቍ ።

፲፯ ወመዋጽፍተ ቤትነ ዘአርዝ ፡ ወመሥዕርቲነ ዘሕቍ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

፩ አነ ጽጌ ገዳም ፡ ጽጌ ደንጐላት ዘውስተ ቈላት ።

፪ ወከመ ጽጌ ደንጐላት በማእከለ አሥዋክ ፡ ከማሁ አንቲኒ አንተ ኀቤየ በማእከለ አዋልድ ።

፫ ወከመ ከል ዘውስተ ዕፀወ ገዳም ከማሁ ዘአፈቅር በማእከለ አኃው ታሕተ ጽላሎቱ ፈተውኩ ወነበርኩ ፡ ወፍሬሁኒ ጥዑም ለጕርዔየ ።

፬ አብኡኒ ቤተ ወይን ገብሩ ላዕሌየ ፍቅረ ።

፭ አጽንዑኒ በዕፍረት ፡ ሰደቁኒ በአክዋል እስመ ተነደፍኩ በፍቅሩ ።

፮ የማኑ ተሐቅፈኒ ወጸጋሙ ታሕተ ርእስየ ።

፯ አምሐልኩክን አዋልደ ኢየሩሳሌም ፡ በኃይሉ ወበጽንዑ ለገዳም ፡ እመ ተንሥአ ወአንሥአ ዘሎ ሙታነ አፈቅር እስከ አመ ፈቀደ ።

፰ ቃለ ወልድ እኁየ ናሁ ውእቱ መጽአ እንዘ ይቀንጽ ማእከለ አድባር ወያንበሰብስ ዲበ አውግር ።

፱ ይመስል ወልድ እኁየ ከመ ወይጠል ፡ ወከመ ወሬዛ ኃየል ውስተ አድባረ ቤቴል ፡ ናሁ ውእቱ ይቀውም ድኅረ አረፍት ፡ ወይሔውፅ እንተ መሳክው ወይደንን እንተ ተድባብ ።

፲ ያወሥእ ወልድ እኁየ ወይብለኒ ተንሥኢ ወንዒ ቅርብትየ እንቲአየ ሠናይት ርግብየ ።

፲፩ እስመ ናሁ ክረምት ኃለፈ ፡ ወዝናም ገብአ ለሊሁ ፡ ጽጌ አስተርአየ በውስተ ምድርነ ።

፲፪ ጊዜ ገሚድ በጽሐ ፡ ቃለ ማዕነቅ ተሰምዐ በምድርነ ፡ በለስ አውጽአ ሠርፀ አውያን ጸገዩ ወወሀቡ መዓዛ ።

፲፫ ተንሥኢ ወንዒ ቅርብትየ እንቲአየ ሠናይት ርግብየ ውስተ ጽላሎተ ኰኵሕ ቅሩበ ጥቅም ።

፲፬ አርእየኒ ገጸከ ወአስምዐኒ ቃለከ እስመ ቃልከ አዳም ወገጽከ ላሀይ ።

ጋዲ በሚባል በወይን በታ ያበበ የልጅ ወንድሜ የሆነ የወይን ዘለላ ለኔ ነው ። ፩ ሳሙ ፡ ፳፫ ፳፱ ።

እነሆ በኔ ዘንድ ያማርሽ ነሽ ያማርሽ ነሽ ፡ ዓይኖችሽ የርግብ ዓይኖች ይመስላሉ ።

እነሆ አንተ ልጅ ወንድሜ ያማርህ ነህ ዘጸ. በሚሆን መኝታችን ያማርን የተወደድን ነበርን ፡ (በሀገራችን በረድኤቱ ተጠብቀን) ሳለን ።

የዋንዛ የዝግባ በሆነ ቤታችን መዋቅር ዘጸ. በሆነ ትራሳችንም እነሆ ያማርን የተወደድን ነበርን ።

## ምዕራፍ ፪ ።

እኔ የምድረ በዳ አበባ ነኝ ፡ ከአበባም አበባ በቈላ ያለ የሱፍ አበባ ነኝ ። ኢሳ፡ ፴፭ ፩ ።

በእሾኽ መካከል ያለ የሱፍ አበባ እንዲወደድ ፡ አንቺም በቈነጃጅት መካከል ያለሽ አንችም በኔ ዘንድ እንደዚያ የተወደድሽ ነሽ ።

በምድረ በዳ ያለ እንኮይ የተወደደ እንደሆነ በወንድሞቹ መካከል ያለ የምወደው (አብርሃም) እንደዚያ የተወደደ ነው ፡ (በአብርሃም) ድንኳን አድር ዘንድ ወደድሁ ፡ ፍሬውም ለጕሮሮየ የጣፈጠ ነው ።

ወደ ወይኑ ቤት አገቡኝ እኔንም ወደዱኝ ።

ሽቱን ቀቡኝ ፡ በእንኮይ ኰሉኝ በፍቅሩ ፍላፃ ተወግቻለሁና ።

ቀኙ ታቅፈኛለች ፡ ግራው ታንተርሰኛለች ፡ ረድኤቱ ታጸናኛለች ። ዘዳ፡ ፴፫ ፳፯ ።

የኢየሩሳሌም ልጆች በከሃሊነቱ በምድረ በዳ በደረገው ተአምራቱ አማጽኛችኋለሁ በሙዓት በተነሣብን ጊዜ ሙታን ልብ አሕዛብንም በስነሣብን ጊዜ ፡ ጠልቶ እስኪወደን ድረስ እንወደዋለን እንድትሉ አማጽኛችኋለሁ ።

እነሆ ልጅ ወንድሜ እግዚአብሔር (በሙሴ በአሮን) በሰብዐ ሊቃናትም አድሮ መጣ ኢ.ሳ፡ ፶፪ ፯ ።

ልጅ ወንድሜ እግዚአብሔር ፈጥኖ ሲረዳኝ ፈቆ ይመስላል በቤቴል ተራራ የተሠማራ የዋልያ ወይፈንንም ይመስላል ፡ አረፍት በይምን ፡ ወአረፍት በጸግም ፡ ከለው በኋላ ይቆማል ፡ ወደ መስኮቱም ይመለከታል ፡ እንደ ቀስተ ደመና ወደ ሆነውም ውኃ ያዘነብላል ።

ልጅ ወንድሜ እግዚአብሔር ይመልስልኛል እንዲህም ይለኛል ፡ መልካሚ ርግቤ የኔ ሆይ (ቤተእስራኤል) ተነሥተሽ ነዪ ይለኛል ።

ክረምት አልፏልና ዝናሙም ወደ ኋላው ተመልሷልና ፡ በአገራችን አበባ ታዩ ። መሳ፡ ፲፰ ፲፬ ።

የወይኑን ዘለላ የምንቈርጥበት ጊዜ ደረሰ ፡ የዋኖስም ድምፅ በአገራችን ተሰማ ፡ በለስም ሰብልን አወጣ ፡ ወይኖች አበቡ ፡ መዓዛቸውንም ሰጡ ።

አቅራቢያዬ መልካሚም ርግቤ የኔ ሆይ! በቅጥሩ አጠገብ ወደ አለው ዋሻ ጥላ ነዪ ።

ፊትህ ያማረ ነውና ፊትህን አሳየኝ ፡ ቃልህ ያማረ ነውና ቃልህን አሰማኝ ። ሕዝ፡ ፴፰ ፭ ።

፲፭ አሥግሩ ለነ ቈናጽለ ንኡሳነ እለ ያማስኑ ዓፀደ ወይንነ
ዓፀደ ወይንነ ይጽጊ ።
፲፮ ወልድ እኁየ ሊተ ወአነ ሎቱ መኑ ይትዓደዎ ለወልድ
እኁየ እስመ ልዑል መዝራዕተ የማኑ ።
፲፯ ዘይትረዐይ ውስተ ጽጌያት ፡ እስከ ሶበ ያስተናፍስ ዕለ
ት ወያንቀለቅል ጽላሎት ።
፲፰ ተመየጥ አንተ ወልድ እኁየ ፡ ወተመሰላ ለወይጠል ፡
ወይርአያከ አዋልደ ኢየሩሳሌም ወንበር ዲበ ሳሬል ወዲበ
አርባዕቱ አርባብ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወከመ ወሬዛ ኃየል ውስተ አድባረ ድኁኃን ቅንጽ
አንተ ወልድ እኁየ ከመ ወይጠል በዐራትየ ወበለያልይየ
ኃሠሥክዎ ወኢረከብክዎ ጸዋዕክዎ ወኢተሠጥወኒ ።

፪ እትነሣእ ወአዐውድ ሀገረ ውስተ ምሥያጣት ወው
ስተ መራኅብት ፡ እኅሥሥ ዘአፍቀረት ነፍስየ ፡ ኃሠሥክዎ
ወኢረከብክዎ ጸዋዕክዎ ወኢተሠጥወኒ ።
፫ ረከቡኒ መዓቅብት እለ የዓቅቡ ሀገረ ፡ ርኢክሙኑ ዘአ
ፍቀረት ነፍስየ ።
፬ ንስቲተ ኃሊፍየ እምኔሆሙ ይእተ ጊዜ ረከብኩ ዘአ
ፍቀረት ነፍስየ አኀዝክዎ ወኢየኃድጎ እስከ ሶበ አባእክዎ
ውስተ ቤተ እምየ ወውስተ ውሣጥያቲሃ ለእንተ ሐፀነተኒ ።

፭ አምሐልኩክን አዋልደ ኢየሩሳሌም በኃይሉ ወበጽ
ንዑ ለገዳም ፡ አመ ተንሥአ ወአንሥአ ኵሉ ሙታነ አፈ
ቅሮ እስከ አመ ፈቀደ ።

፮ መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ተዓርግ እምገዳም ከመ ደመና
ዘጠፈረ ሰማይ ወከመ ሠርፀ ጢስ ዕጣነ ።

፯ ከልኤ አጥባትኪ ያውኅዛ ሐሊበ ፡ ከርቤ ወስኂን እም
ኵሉ ጸበለ ኤፌኔዎስ ።

፰ ናሁ ዓራቱ ለሰሎሞን ስሳ ኃያላን ዓውዳ እምኃያላነ
እስራኤል ።
፱ ኵሎሙ እኁዛነ አስይፍት ወምሁራነ ቀትል ፡ ብእሲ
ብእሲ ሰይፉ ዲበ መንቀዕቱ ፡ ይትሜሰሉ በድንጋጼ ሌሊት ።

፲ መያረ ገብረ ለርእሱ ንጉሥ ሰሎሞን እምዕፀወ
ሊባኖስ ።
፲፩ አዕማዲሁ ገብረ ዘብሩር ፡ ሰርዲኖስ ዘምስለ ተርሴስ
ኢዮጳሎግዮስ ዘምስለ ሶፎር ።

፲፪ ምስማኩ ዘወርቅ አቍላፊሁ ወአቍፋሊሁ ኢያሴሚር ፡
መንበሩ ዘሜላት ኅንብርቱ ዘቢረሌ ዘምስላ ኢያስጲድ

የወይን በታችንን የሚያጠፉ ታናናሽ ቀበሮችን
አጥፉልን ፡ ወይናችንም ያብብ ያፍራ ።
ልጅ ወንድሜ የኔ ነው ፡ እኔም የሱ ነኝ ፡ ሥልጣኑ
ገናና ነውና ፡ ፍርዱን የሚተላለፈው ማን ነው !
ቀኑ እስኪመሽ ጥላው እስኪመለስ ድረስ ወደ አበባ
ዎች የሚሠማራ እሱ ነው ።
አንተ ልጅ ወንድሜ እግዚአብሔር ከመዓት ወደ ምሕ
ረት ተመለስ ፡ ፌቆንም ምሰላት እኔንም ስትራዳ የኢየሩሳ
ሌም ልጆች ይዩህ በሱራፌል ላይ ተቀምጠህ ተራዳኝ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ልጅ ወንድሜ (እግዚአብሔር በሌሊተ መከራ ተይዤ
ሳለሁ ፅኑዓን በሚሆኑ ተራሮች (አብርሃም ይስሐቅ ያዕ
ቆብ) እንደተሠማራ የዋልያ ወይፈን መር ብለህ ከባቢ
ሎን አውጣኝ ፡ ሰውነቴ የወደደችውን ሚጠትን ፈለግ
ሁት አላገኘሁትም ፡ ጠራሁት አልሰማኝም ።
ሰውነቴ የወደደችውን ሚጠትን እፈልግ ዘንድ ተነ
ሥቼ አገር ለአገር ወደ ገበያ ወደ አደባባይ እዞራለሁ ፡ ፈለ
ግሁት አላገኘሁትም ፡ ለመንሁት ልመናዬን አልሰማኝም።
አገርን የሚጠብቁ ዘበኞች አግኝተውኝ ሰውነቴ የወ
ደደችውን ሚጠተ ሥጋ አያችሁን ፤ አልኳቸው ።
ከነሳቸው ጥቂት እልፍ ብዬ ያን ጊዜ ሰውነቴ የወደ
ደችው ሚጠትን አገኘሁ ፡ ወደ እናቴ ቤት ወደ አሳ
ደገችኝ ወደ ሞግዚቴ እልፍኝም እስከገባው ድረስ ያዝ
ሁት ፡ አልለየውም ።
የኢየሩሳሌም ልጆች በከሃሊነቱ በምድረ በዳ ባደረ
ገው ተአምራቱ ልጆች አማጽኛችኋለሁ ፡ በመዓት በተነ
ሣብን ጊዜ ሙታነ ልብ አሕዛብንም በስነሣብን ጊዜ ጠል
ቶ እስከ ወደደን ድረስ እንወደዋለን እንድትሉ አማጽኛ
ችኋለሁ ።
ሰማይ በሚባል ጠፈር እንዳለ ደመና አቅንታ ከም
ድረ በዳ የምትወጣ ይች ማናት ፤ አወጣጧም እንደ ጢስ
አወጣጥ የሆነ ይህች ማን ናት ! ።
ሁለቱ ጡቶችሽ ወተትን ያፈሳሉ ፡ (ሁለቱ ጽላቶችሽ
ሕግጋትን ያስገኛሉ) ከርቤ ስሂን የሚባሉ ሽቱዎች ከሽቱ
ቅመሞች ሁሉ ጋራ አሉሽ ። ፩ ነገ፡ ፲ ፲፭ ።
እነሆ የሰሎሞን አልጋ እንዲህ ናት ፡ ከእስራኤል ኃይ
ለኞች የተመረጡ ስድስት ኃያላን በዙሪያዋ አሉ ።
ሁሉም ሰይፍ ሰይፍ የያዙ ሰልፍንም የተማሩ ናቸ
ው ፡ አንዱም አንዱም ሰው ሰይፉ በብብቱ ነው ፡ በሌ
ሊት አደጋም ይመሰላሉ ።
ንጉሡ ሰሎሞን ከደጋ ዕንጨቶች ለራሱ አልጋን
ሠራ ።
ሽንከሩን የብር አደረገው ፡ ሰርዲኖስ የሚባል ዕንቍ
ተርሴስ ከሚባል ዕንቍ ጋራ ኢዮጳሎግዮስ ሶፎር ከሚ
ባል ዕንቍ ጋራ አደረገበት ።
የአልጋው ዘንግ የወርቅ ነው ፡ ብሱ ጥምጥሙ ኢያ
ሴሜር የሚባል ዕንቍ ነው ፡ መለበሚያው የነጭ ሐር ነው

በባሕርይ ክዱን ፡ ውስጡ ንጡፍ በእብነ ሰንፔር ፡ አፈቅሮ ፈድፋደ እምአዋልደ ኢየሩሳሌም ።

ቢረሌ የሚባል መገናኛው ኢያስጲድ ከሚባል ዕንቍ ጋራ ባሕርይ በሚባል ዕንቍ የተለበጠ ነው ፡ ውስጡም ሰንፔር በሚባል ዕንቍ ተለብጧል ፡ ከኢየሩሳሌም ልጆች ይልቅ እወደዋለሁ (ሰሎሞንን) ።

፲፩ ፃኣ ትርአያ አዋልደ ጽዮን ለንጉሥ ሰሎሞን ፡ በአክሊል ዘአስተቈጸለቶ እሙ ፡ አመ ዕለተ ሕማሙ ፡ ወአመ ዕለተ ስቅለቱ ፡ ወአመ ዕለተ ሞቱ ፡ ወአመ ዕለተ መርዓሁ ፡ ወአመ ዕለተ ፍሥሐ ልቡ ።

መከራ በተቀበለበት ቀን ፡ በተሰቀለበት ቀን ፡ በሞተበት ቀን ፡ በነገሠበት ቀን ፡ ነግሦ ልቡናውን ደስ ባለው ቀን ፡ እናቱ (ቤርሳቤህ) ያቀዳጀችውን ዘውድ ደፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን ታዩ ዘንድ የጽዮን ልጆች ኑ ውጡ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

፩ ነያ ሠናይት አንተ እምኀቤየ ነያ ሠናይት ፡ አዕይንትኪ ዘርግብ ፡ ሥዕርትኪ ከመ መርዔተ አጣሊ እለ ተከሥታ እምአድባረ ገለዓድ ።

ቤተ እስራኤል በኔ ዘንድ ያማርሽ ነሽ ፡ ያማርሽ ነሽ ፡ ዓይኖችሽም እንደ ርግብ ዓይኖች ፡ ጠጕርሽም በገለዓድ ተራራ እንደ ተሠማሩ ፍየሎች መንጋ ናቸው ።

፪ ስነንኪ ከመ መራዕይ እለ ተቀርፃ ወእለ ወጽአ እምሕፃብ ኵሎን እለ ይመነትዋ ፡ ሰብዓ ወሰብዓቱ እለ ይወልዳ ፡ ወአልበ እምኔሆን መከን ።

ጥርሶችሽ ከመታጠቢያ ወጥተው እንደ ተሸለቱ መንጋዎች ናቸው ፡ ሁሉም መንታ መንታ እንደሚወልዱ ፡ ሰባ ሰባትም እንደሚወልዱ ናቸው ፡ ከነሳቸውም መኻን እንደሌላቸው እንደነዚያ ናቸው ።

፫ ከመ ፍሕሦ ቀይሕ ከናፍርኪ ንባብኪ አዳም ከመ ቅርፍተ ሮማን መላትሕኪ እንበለ አርምሞትኪ ።

ከንፈሮችሽ እንደ ጕሚት አበባ ቀይ ናቸው ፡ ከዝርፍታሽ በስተቀር ጨዋታሽ ያማረ ነው ጕንጭሽም እንደ ሮማን ቅርፍት ያማረ ነው ።

፬ ወከመ ማኅፈደ ዳዊት ክሳድኪ እለ ተሐንፃ ዲበ ተልፍዮስ ፡ ዓሠርቱ ምእት ንዋየ ሐቅል ሰቁል ውስቴቱ ፡ ኀበ ኢይሬእዮ ሰብእ ወኢይበጽሖ ፀሐይ ፡ ወኵሉ መዋጽፍተ ሴቱ ኃያላን ወጽኑዓን እለ የዓቅብዎ ሠለስቱ እደው ።

አንገትሽ ተልፍዮስ በሚባል ተራራ እንደ ተሠራ በውስጡም ሺሕ የበዳ ፀብት እንደተሰቀለበት ሰው ከማያየው ፀሐይም ከማይደርስበት ቦታ እንደ ተሠራ እንደ ዳዊት ግንብ ነው ፡ በምድር ነጕድ የቤቱን ዙሪያ የሚጠብቁ ኃያላኖች ፅኑዓን የሚሆኑ ሦስቱ አርበኞች ናቸው ።

፭ ክልኤ አጥባትኪ ከመ ክልኤ እጐለ መንታ ዘወይጠል ዘይትረዓይ ውስተ ጽጌያት ፡ እስከ ሶበ ያስተናፍስ ዕለት ወይትሐወስ ጽላሎት ።

ሁለቱ ጡቶችሽ መንታነት እንዳላቸው እንደ ሁለት ፊቆ ገላግልት ናቸው ፡ ቀኑ እስኪመሽ ፡ ጥላው እስኪመለስ ድረስ ወደ አበባዎች የሚሠማራ እሱ ነው ።

፮ አሐውር ለልየ ኀበ ደብረ ከርቤ ወውስተ አውግረ ስኂን ምዑዝ ወይትቀበዕ እመዓዛሁ አውልዐ ገዳም ፡ ወይበልዓሁ አዕዋፈ ቈላት ፡ ወኢይመውታ እሰመ ይሔድሳ ውርዙቶን ።

ከርቤ ወደአለበት ተራራ የሚሸት ነጭ ዕጣን ወደ አለበት ኮረብታም እሄዳለሁ ፡ በምድረ በዳ ያለ ወይራም መዓዛውን ይቀበል በቈላ ያሉ ወፎች ይበሉታል ፡ ሰውነታቸውን ያድሳሉና አይሞቱም ።

፯ ኵለንታኪ ሠናይት አንተ ኀቤየ ፡ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ ።

በኔ ዘንድ ሁለንትናሽ ያማረ ነው ፡ በአንቺ ላይ ምን ምን ነውር ነቀፋ የለብሽም ።

፰ ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ ፡ ንዒ ወትወጽኢ እምቅድመ ሃይማኖት ወታስተርእዩ ውስተ አድባረ ጽባሕ ።

መርዓት ነዪ ፡ ከደጋ ነዪ ፡ ከደጋ መጥተሽ ሃይማኖትሽን ፊታውራሪ አድርገሽ ከፋርስ ከባቢሎን ወጥተሽ በምሥራቅ ተራራዎች ትታይያለሽ ።

፱ እምርእሰ ሳኔር ወኤርሞን እንዘ ትሠቀዪ ጠለ ፡ እምግበበ አናብስት ወእምአድባረ አናምርት (ወጻእኪ) ።

ከሰማይ ከእግዚአብሔር ጠለ ረድኤትን አግኝተሽ ከአንበሶች ጕድጓድ ከነብሮችም ጕድጓድ ወጣሽ ።

፲ አራኅራኅክኒ እኅትየ መርዓት አራኅራኅክኒ ምዕረ በአዕይንትኪ በአሐቲ ንብረተ ክሳድኪ ።

አንገትሽን ደፍተሽ በመኖርሽ አንድ ጊዜ በዓይኖችሽ ቀና ብለሽ ባለማየትሽ እኅቴ መርዓት አሳዘንሽኝ አሳዘንሽኝ ። መሳ ፰ ፳፯ ።

፲፩ሚ አዳም አጥባትኪ እኅትየ መርዓት ፡ ወሐሊበን ይጥዕም እመዓር ወሦከር ወእምተምር ዘውስተ ገነት ፡ ጥቀ አዳም አጥባትኪ እምወይን ፡ ወመዓዛ ዕፍረትኪ እምኵሉ አፈው ።

እኅቴ መርዓት ጡቶችሽ ምን ያምሩ ! ወተታቸውም ከማርና ከሱካር በተክል መካከል ካለ ተምርም ይልቅ ይጣፍጣል ፡ ጡቶችሽ ከወይን ይልቅ እጅግ ያማሩ ናቸው ፡ ሽቱሽም ከሽቱ ይልቅ መዓዛው እጅግ ያማረ ነው ።

፲፪ ጸቃውዕ ይውኅዝ እምከናፍርኪ ፡ ሐሊብ ወመዓር እምታሕተ ልሳንኪ ፡ ወፄና አልባስኪ ከመ ፄና ስኂን ።

ከከንፈሮችሽ የማር ወለላ ይፈሳል ፡ ወተት ማር ከንደበትሽ በታች ባለ በሆድሽ አለ ፡ የልብስሽም መዓዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዓዛ ነው ። ምሳ ፳ ፫ ።

፲፫ ገነት ዕፁት እኅትየ መርዓት፣ ገነት ዕፁት ዓዘቅት ኅትምት ።
፲፬ ፍናወ ዚአኪ ኀበ ኢይበጽሖ ወኢይከርዮ ኬንያ፣ ገነት ምስለ ፍሬ አቅማሕ ሰንድሮስ ምስለ ጽርስቅላ፣ ቆዕ ምስለ ናርዶስ ።

፲፭ ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጺመታት ወቀናንሞስ፣ ምስለ ኵሉ ዕፀወ ሊባኖስ፣ ከርቤ ወዓልው ምስለ ኵሉ መቅድመ ዕፍረታት ።

፲፮ ነቅዐ ገነት ዓዘቅተ ማየ ሕይወት፣ ዘይውኅዝ እምሊባኖስ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

፩ ተንሥኢ ሰሜን፣ ወነዓ ደቡብ፣ ንፋሕ ገነትየ፣ ለየኅዝ አፈዋተ ዚአየ፣ ለይረድ ወልድ እኁየ ውስተ ገነቱ ወይብላዕ እምፍሬ አቅማሒሁ ።
፪ በእኩ ውስተ ገነትየ እኅትየ መርዓት አረርኩ ከርቤ ምስለ አፈዋትየ በላዕኩ ኅብስትየ ምስለ መዓርየ፣ ሰተይኩ ወይንየ ምስለ ሐሊብየ፣ በልዑ ካልአንየ ወጸግቡ ሰትዩ ውሉደ አኃውየ ወሰከሩ፣ እስመ እንቡዛን እሙንቱ።

፫ ወትእኅዘሙ ቅንአት ከመ ሰልብልያኖስ፣ ሐረገ ወይን ከነ መድኃኒትየ፣ ዘእምኃሚሦን ይትገዘም ወበጎልጎታ ይተክል ።

፬ ቃል ወልድ እኁየ መጽአ እንዘ ይጐደጕድ ኆኅተ፣ አነ ንውም ወልብየ ንቅሕት ።
፭ አርኅውኒ እኅትየ ካልእትየ ርግብየ ፍጽምትየ ከመ ፋፃ ቀጢን፣ ወከመ መሰንቆ ሐዋዝ ያስተፌሥሐኒ ልብየ በሰሚዖቱ፡ እስመ ርእስየኒ ምሉእ ጠለ፣ ወድምድማየኒ ነፍኒፈ ሌሊት ።

፮ አውፃእኩ ልብስየ እፎኑ እለብሶን፣ ሐፀብኩ እገርየ እፎኑ እጌምኖን፣ እስመ ተሐጸብኩ አነ በስኂን ወበአቅራኅዮ ።
፯ ወልድ እኁየ ፈነወ እዴሁ እንተ ስቊረት እስመ በሊሕ ልቡ እምኵናት ከርሥየ ደንገፀት በቱ ።
፰ ተንሣእኩ አነ አርኅዎ ለወልድ እኁየ እደውየ ያውኅዛ ከርቤ፣ ወአፃብዕየ ከርቤ ምሉእት ።
፱ ውስተ እደ መንሠግ ተንሣእኩ አነ አርኅዎ ለወልድ እኁየ፣ ወልድ እኁየ ኀለፈ ነፍስየ ደገፀት እምቃሉ፣ ኃሠሥክዎ ወኢረከብክዎ፣ ጸዋዕክዎ ወኢተሠጥወኒ ።

፲ ረከቡኒ መዓቅብት እለ የዓቅቡ ሀገረ፣ ዘበጡኒ ወፈቀሙኒ፣ ነሥኡ ግልባቤየ እምላዕለ ርእስየ እለ የዓቅቡ ቅጽረ።

፲፩ አምሐልኩክን እዋልደ ኢየሩሳሌም በኃይሉ ወበጽንዑ ለገዳም፣ እመ ረከብክሁ ለወልድ እኁየ ከመ ታይድ

እኅቴ መርዓት የታጠረች ተክል ናት የታጠረች ተክል የታተመች ጉድጓድ ናት ። መሳ ፫ ፳፫ ።

መንገድሽ ሰው የማይደርስበት ብልህ የማይቈፍረው ነው፣ ከሽቱ ቅመም ጋራ ሽቱ አለ፣ ሰንድሮስ የሚባል ሽቱ፣ ጽርስቅላ ከሚባል ሽቱ ጋራ፣ ቆዕ የሚባል ሽቱ ናርዶስ ከሚባል ሽቱ ጋራ አለሽ ።

ናርዶስም የሚባል ሽቱ መጽርይ (ቀጋ) ከሚባል ሽቱ ጋራ አለሽ፣ ቀጺመታት፣ ቀናንሞስ የሚባሉ ሽቱዎች ከደጋ ሽቱዎች ጋራ አሉሽ፣ ከሽቱ ሁሉ የሚበልጡ ከርቤ ዓልው የሚባሉ ሽቱዎች ከነዚህ ሁሉ ሽቱዎች ጋራ አሉሽ።

የተክል ቦታ ምንጭ (የሕግ መገኛ) የሕይወት ውኃ ጉድጓድ ከሊባኖስም የሚፈስስ ወንዝ ነሽ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

ሰሜናዊ ነፋስ ተነሥ፣ ደቡባዊ ነፋስም ና፣ ለተክሌ በታ ንፈስ ሽቱዬ ይፍሰስ፣ ልጅ ወንድሜ ወርዓዊ ወደ ተክሉ በታ ይውረድ፣ ከሽቱውም ቅመም ፍሬ ይብላ ።

እኅቴ መርዓት ወደ ተክሌ በታ መከከል ገብቻለሁ፣ ከሽቱዬ ጋራ ከርቤን ለቀምሁ፣ ከማሬም ጋራ እንጀራዬን በላሁ፣ ከወተትም ጋራ ወይኔን ጠጣሁ፣ ወዳጆቼ ይህን በልተው ጠገቡ፣ የወንድሞቼ ልጆች ወይን ጠጥተው ሰከሩ፣ እነሳቸው አእምሮአቸውን ያጡ ናቸው ።

እንደ ዲያብሉስም ቅንአት ትይዛቸዋለችና ከኃሚሦን ተቈርጦ በጎልጎታ የተተከለው የወይን ሐረግ ድኅነቴ ሆነ (በፋርስ ተጀምሮ በጎልጎታ የተፈጸመ ሚጠት) መድኃኒት ሆነኝ ።

ልጅ ወንድሜ ቃል ደጃፍ እየመታ መጣ፡ እኔ ተኝቼ ነበር፣ ልቡናዬ ግን ነቅታ ነበር ። ሉቃ፡ ፹ ።

ፍጽምት የምትሆኚ ርግቤ ወዳጄ እኅቴ፣ ደጃፉን ክፈችልኝ የሚል ቃሉን በሰማሁ ጊዜ እንደ ረቂቅ ፉጨት እንደ አማረ መሰንቆ ልቡናዬን ደስ ይለዋል፣ ራሴ ጠልን የተመላ ነውና፣ ጕተናየም የሌሊት ከፊያን ተመልቷልና ። እሞ፡ ፯ ፲፩ ።

ልብሴን አውልቄዋለሁ እንደምን አድርጌ እለብሰዋለሁ፣ እኔ አቅራኅዮና ስኂን በሚባል ሽቱ ታጥቤአለሁና እግሬን እንዴት አሳድፈዋለሁ ! ።

ልቡ ከጦር ይልቅ ፈጣን ነውና ልጅ ወንድሜ እጁን ወደ ወንዳወንዴው ሰደደ፣ ሰውነቴ በሱ ደነገጠች ።

እኔ ለልጅ ወንድሜ ደጃፉን እከፍትለት ዘንድ ተነሣሁ እጆቼ ሽቱን ያፈሳሉ፣ ጣቶቼም ሽቱን የተመሉ ናቸው ።

ለልጅ ወንድሜ እከፍትለት ዘንድ ወደ ወንዳወንዴው ለመሄድ ተነሣሁ፣ ልጅ ወንድሜ ሄዶ ሰውነቴም ከቃሉ የተነሣ ደነገጠች፣ ፈለግሁት አላገኘሁትም፣ ለመንሁት ልመናዬን አልሰማኝም ።

ሀገሩን የሚጠብቁ ዘበኞች አግኝተው ደበደቡኝ፣ ገሙሉኝ አምባውን የሚጠብቁ ዘበኞችም ኵፌቴን ከራሴ ላይ አውልቀው ወሰዱብኝ ።

ልጅ ወንድሜን ብታገኙት እኔ በሐፀ ፍቅሩ የተነደፍሁ እንደሆንኩ ትነግሩት ዘንድ የኢየሩሳሌም ልጆች በከ

ዓሁ እስመ ንድፍት አነ በፍቅሩ ።
፲፪ ምንት ውእቱ ወልድ እኁኪ ሠናይት እምአንስት፡
ወምንት ውእቱ ወልድ እኁኪ እምውሉደ እኃው፡ ዘከ
መዝ መሐላ አምሐልከነ፡ በፀ ኦይኑ፡ ወበያርስኑ፡ ወበከ
ማንዮስኑ ።

፲፫ እኁየ ፀዓዳ ወቀይሕ፡ ወየዓውድዎ አልፍ ወትእል
ፌተ አእላፋት፡ ውሉድ እምአእላፍ ።
፲፬ ርእሱ ወርቀ ቄፋዝ፡ ድምድማሁ ድሉል ወጸሊም
ከመ ቋዕ ።
፲፭ አዕይንቲሁ ከመ ርግብ ምሉእ ውስተ ምዕቃለ ማያት፡
ስነኒሁ ሕፁባት በሐሊብ እለ ይነብራ ውስተ ምዕቃለ ማ
ያት ምሉእ ።
፲፮ መላትሒሁ ከመ ርኄ አፈው እለ ይፈርያ አፈዋተ፡
አዕይንቲሁ ከመ ኮከበ ጽባሕ እለ ይጼድላ፡ ከናፍሪሁ ጽጌ
እለ ያውኅዛ ከርቤ ፍጹመ፡ ወልድ እኁየ ይዔኑ ዘርቤነ
ምዑዘ አልባሲሁ ዘእብን ከመ ሰብአ ተርሴስ ።

፲፯ እደዊሁ ፍሑቃት እለ ወርቀ ሥርግዋተ ተርሴስ፡ ከር
ሡ ሰሌዳ ከመ ቀርነ ነጌ ዲበ እብነ ሰንፔር፡ አእኑገ ክብር
ወውዕበ ዘኢያውፀበ እደ ኬንያ ።

፲፰ ቍየጺሁ አዕማደ በላቀ ሡሩራት ዲበ መንበረ ወርቅ፡
ርእሱ ከመ ስኂን፡ ወኅሩይ ከመ ቄድሮስ ።

፲፱ ጕርዔሁ መዓርዒር ወኵሉ ፍትው፡ ወልድ እኁየ
ውእቱ ፍቁርየ ።

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወትቤ መርዓት አይቴ ሖረ ወልድ እኁየ እዋልደ ኢ
የሩሳሌም፡ ወትቤ አከሲጦስ፡ አይቴ ሖረ ወልድ እኁኪ
ወንኅሥሦ ምስሌኪ ።

፪ ወልድ እኁየ ወረደ ውስተ ገነቱ ውስተ አብያተ አፈ
ው ይርአይ ገነተ ወያስተጋብእ ጽጌያተ ።

፫ ናሁ አንቲኒ አንተ ኅቤየ ከመ ሥምረት ።

፬ አዳም ከመ ኢየሩሳሌም መደንግፅት ከመ ሥርዓት ።

፭ ሚጢ አዕይንተኪ እምአንፃርየ፡ እስመ እማንቱ
አፍርሃኒ ወአሠረራኒ ውስተ አየር ።
፮ ሥዕርትኪ ከመ መርዔተ አጣሊ እለ አስተርአያ እም
አድባረ ገለዓድ፡ ስነንኪ ከመ መራዕይ እለ ዓርጋ እምሕ
ፃብ፡ ኵሎን እለ ይመነትዋ፡ ወአልበ እምኔሆን መከን ።

፯ ከመ ፍሕሦ ቀይሕ ከናፍርኪ፡ ንባብኪ አዳም ከመ
ቅርፍተ ሮማን መላትሕኪ እንበለ አርምሞትኪ ።

ሀሊነቱ በምድረ በዳ በደረገው ተአምራቱ አማፅኛችኋለሁ።
ከሴቶች ይልቅ ተወደሽ፡ አምሮብሽ የነበርሽ መርዓት
ልጅ ወንድምሽ ማንን ይመስላል ፤ ይህን ያሀል መሐላ ያማ
ልሽን ልጅ ወንድምሽ ከወንድማማች ልጆች ማንን ይመ
ስላል ፤ በጨረቃና በፀሐይ፡ በአስታርቦሽሽ ኮከብ ትመስ
ይዋለሽን ፤ ።
ልጅ ወንድሜስ ነጭ ነው ቀይ ነው፡ እልፍ አእላፍ
መላእክት ይከቡታል፡ ከብዙ ወገኖችም የተመረጠ ነው ።
ራሱ የቄፋዝ ወርቅ ነው፡ ጐተናውም ስርሹ ነው፡
እንደ ቍራም የጠቈረ ነው ። መዝ፡ ፲፱ ፲ ።
ዓይኖቹ በመላ ሦሬ ውኃ እንዳሉ ርግቦች ናቸው
ጥርሶቹም በወተት የታጠቡ ይመስላሉ፡ በሦሬ ውኃ እን
ደሚኖሩ ርግቦች ናቸው ።
ሽቱ ሽቱ የሚሸቱ ጕንጮቹ ርኄ እንደሚባሉ ሽቱ
ዎች ናቸው፡ ዓይኖቹም እንደ አጥቢያ ኮከብ የሚያበሩ
ናቸው፡ ሽቱ ሽቱ የሚሸቱ ከንፈሮቹ እንደ አበባ ናቸው፡
ልጅ ወንድሜ ያማረ ሽቱ ይሸታል፡ ሽቱ ያለበቸው ልብ
ሶቹ እንደ ተርሴስ ነጋዴዎች ልብስ ናቸው ።
ወርቅ የሚመስሉ በዕንቍ በጌጥ ያጌጡ እጆቹ የለዘቡ
ናቸው፡ ሆዱ ሰንፔር በሚባል ዕንቍ ላይ እንደ ተሠራ
እንደ ዝሆን ጥርስ የለዘበ ነው፡ የብልፀ እጅ ያልሠራው
የተደነቀ ክብር ያለው ንጽ ነው፡ ዘፀ፡ ፳፰ ፳ ።
ጭኖቹ በወርቅ ለከተት ላይ የተሠሩ የዕንቍ ምሰሰ
ዎች ይመስላሉ፡ ራሱ እንደ ነጭ ዕጣን ነው፡ እንደ ዋን
ዛም የተመረጠ ነው ።
አንደበቱ ያማረ ነው፡ ሁለንትናውም የተወደደ ነው፡
ልጅ ወንድሜ ወዳጄ ነው ። ነሐ፡ ፰ ፲ ።

ምዕራፍ ፮ ።

መርዓተ (ቤተ እስራኤል) የኢየሩሳሌም ልጆች ፤ ልጅ
ወንድሜ ወዴት ሄደ አለች ፤ የነቢያት ጉባኤም ልጅ ወን
ድምሽ (እግዚአብሔር) ወዴት ሄደ፤ ከአንቺ ጋራ እንፈ
ልገው አለች ።
ልጅ ወንድሜ (እግዚአብሔር) ተክል ያይ ዘንድ አበ
ባንም ይሰበስብ ዘንድ ወደ ተክሉ ቦታ ወደ ሽቱው ቤቶ
ች ወረደ ።
እነሆ አንቺም በኔ ዘንድ ፈቃድ እንደሚፈጽም ወዳጅ
ነሽ ።
እንደ ኢየሩሳሌምም ያማርሽ ነሽ፡ እንደ ሥርዓተ መን
ግሥትም የምታስደነግጪ ነሽ ።
እነሳቸው አስፈርተውኛልና፡ ወደ ሰማይም አብርረው
ኛልና ከአፍዘዣዬ (ከጣዖታቱ) ዓይኖችሽን መልሺ ።
ፀጕርሽ በገለአድ ተራራዎች እንደታዩ ፍየሎች መንጋ
ናቸው፡ ጥርሶችሽም ከመታጠብያው ወጥተው እንደ ተሸ
ለቱ መንጋዎች ናቸው፡ ሁሉም መንታ መንታ እንደሚወ
ልዱ ናቸው፡ ከነሳቸው መኻን የለም ።
ከንፈሮችሽ እንደ ጕሚት አበባ ቀይ ናቸው፡ ከኵር
ፍታሽ በቀር ጨዋታሽ ያማረ ነው፡ ጕንጭሽም እንደ
ሮማን ቅርፍት ነው ።

፰ ስሳ እማንቱ ንግሥታት ወሰማንያ ዕቁባት ፡ አዋልድ እለ አልቦን ኍልቍ ።

ስሳ ንግሥታቶች ናቸው ፡ ሰማንያዎቹም ዕቁባቶች ናቸው ፡ ሥፍር ቍጥር የሌላቸው ልጃገረዶች አሉ ።

፱ አሐቲ ይእቲ እምኔሆን ርግብየ ፍጽምትየ ፡ ክነፊሃ ክንፈ ብሩር ወገበዋቲሃኒ በሐምልማለ ወርቅ ።

ከነሳቸው ተለይታ አንዲቱ ርግቤ የዋህ ናት ፡ በሕግም ፍጽምት ናት ፡ ክንፎቿም የብር ክንፍ ናቸው ፡ ወገቦቿም በጥሩ ወርቅ የተጌጡ ናቸው ።

፲ አሐቲ ይእቲ ለእማ ወኅሪት ለእንተ ወለደታ ፡ ርእያሃ አዋልድ ወአስተብፅዓሃ ፡ ንግሥታት ወዕቁባት ወይሰሃ ።

ለእናቷ አንዲት ናት ፡ ለወለደቻት ለእናቷም የተመረጠች ናት ፡ ቈነጃጅቶችም አይተው አደነቋት ፡ ንግሥታቶችና ዕቁባቶችም አመሰገኗት ። ዘፍ፡ ፴ ፲፫ ።

፲፩ መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትሔውፅ ከመ ጎህ ፡ ሠናይት ከመ ወርኅ ፡ ወብርህት ከመ ፀሐይ ፡ ሑረታቲሃ በምሥጢር መደንግፅ ከመ ምጽአት ።

እንደ ጎህ የምትጐበኝ ይህች ማናት ፡ እንደ ጨረቃ ያማረች ናት ፡ እንደ ፀሐይም የበራች ናት ፡ አካሄዷም በምሥጢር ነው ፡ እንደ ንጉሥ አመጣጥ የምታስደነግጥ ናት ።

፲፪ ውስተ ገነተ ከርካዕ ወረደ ወልድ እኁየ ወትቤ አቅሌስያ ፡ ወልድ እኁየ ወረደ ውስተ ዘርአ ሙኃዝ ፡ ኀበ ፈረየ አከያሞስ ይርአይ ለእመ ጸገየ ወይን ፡ ወለእመ ፈረየ ሮማን ።

ልጅ ወንድሜ ወደ ተክል ቦታ (ጉባኤ ነቢያት) ወረደ ወይን አብቦ እንደሆነ ፡ ሮማንም አፍርቶ እንደ ሆነ ፡ ያይ ዘንድ አክያሞስ የሚባል ሽቱ ከፈራ ዘንድ ልጅ ወንድሜ ወደ መስኖ ውኃ ወረደ አለች ።

፲፫ በሀየ እሁበከ አጥባትየ ለከ ፡ ነፍስየ ኢያአመረት ፡ ረሰየኒ ሠረገላተ አሚናዳብ ።

በዚያ ሁለቱን ጡቶቼን (ዓሠርቱ ቃላት) እሰጥሃለሁ ፡ ሰውነቴ አእምሮዋን አላወቀችም ፡ ሚጠቴን የአሚናዳብን ሠረገላዎች አድርጋልኝ አለች ።

፲፬ ወይቤላ ተመየጢ ተመየጢ ሱላማጢስ ፡ ተመየጢ ወንርአይ ብኪ ሰላመ ።

ፍቅር አንድነት የተሰጠሽ ሱላማጢስ (ምእመን) ተመለሺ ፡ ተመለሺ ፡ በአንቺ የተደረገውን ፡ ፍቅር አንድነትን እንይ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ምንተኑ ትኔጽሩ በእንተ ሰላመ ሰጣዊት እንተ ትሔውጽ እምርኁቅ ከመ መድፀለ ማኅበር ።

ፍቅር አንድነትን የምትሰጥ በሸንጎ የምትጐበኝ የምእመንን ነገር ምን ትመለከታላችሁ ፤ ።

፪ ጥቀ አዳም ሑረትኪ ዘበሥን ወለተ አሚናዳብ ፡ ወንብረተ መናቅዕትኪ ከመ አርማስቆስ ግብረ እደ ኬንያ ።

የአሚናዳብ ልጅ በምሥጢር የሚሆን አካሄድሽ እጅግ ያማረ ነው የአንገትሽ ቀጥታ የብልሀ ሰው እጅ እንደ ሠራው እንደ ብር ዘንግ ነው ። መዝ፡ ፵፭ ፲፫ ።

፫ ኅንብርትኪ ከመ ማዕከክ ፍሑቅ ዘኢየዐርቅ እምቱስሕቱ ፡ ከርሥኪ ሥውጠ ሥርናይ ወሕፁር በጽጌ ።

እምብርትሽ ከመላ እንደማይጐድል እንደ ሙሴ መቅለድ ነው ፡ ሆድሽም ሥንዴን የተመላ ነው ፡ በአበባ የተከበበ ነው ። ኢሳ፡ ፷፪ ፷፬ ።

፬ ክልኤ አጥባትኪ ከመ ክልኤ እጕለ መንታ ዘወይጠል እለ ያፈለፍላ ሐሊበ መንፈስ ።

ሁለቱ ጡቶችሽም መንታነት እንዳላቸው እንደ ፊቆ ገላግልት ናቸው ፡ ረቂቅ ወተትንም የሚያስገኙ ናቸው ።

፭ ወክሳድኪ ከመ ማኅፈደ ቀርነ ነጌ ፡ አዕይንትኪ ከመ ምሉእ ምዕቃለ ማያት ፀኤሴቦን በአናቅጽ ወለተ ብዙኃን እኃው ።

አንገትሽም በዝሆን ጥርስ እንደ ተሠራ ግንብ ነው ፡ በኤሴቦን (በኢየሩሳሌም) የብዙ ወገን የወንድማማቾች ልጅ (ቤተ እስራኤል) ዓይኖችሽ እንደ መላ ኵሬ ውኃ ናቸው ።

፮ ንግሥታት ይፈቅዳ ሥነኪ ወአሕዛብኒ የሐውሩ በጸዳልኪ ፡ አንፍኪ ይመስል ከመ ማኅፈደ ሊባኖስ ዘይኔጽር መንገለ ገጸ ደማስቆ ።

ነገሥታቱ ደም ግባትሽን ይወዳሉ ሠራዊቶቻቸውም በብርሃንሽ ይሄዳሉ ፡ አፍንጫሽ በደማስቆ አንፃር እንደተሠራ እንደ ደጋ ግንብ ነው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፮ ።

፯ ሥዕርትኪ ዘድቤኪ ከመ ቀርሜሎስ ፡ ወጽፍሮ ሥዕርትኪ ከመ ሜላት ፍሑስ ።

በራስሽ ላይ ያለ ጠጕርሽ እንደጓስሳ ነው ፡ የጸጕርሽም ሥራ እንደ ተፈተለ ሐር ነው ።

፰ ማኅፈደ ወርቅ ለሰሎሞን ፡ ወመሠረቱ ዘዕንቈ አድማርስጲስ ።

ለሰሎሞን መሠረቱ አድማርስጲስ የሚባል ዕንቍ የሆነ የወርቅ ግንብ ነበረው ። ዘፀ፡ ፱ ፲፯ ። ኢያ፡ ፲፱ ፳፯ ።

፱ አሠረ ንጉሥ ለረዊፅ ጥቀ ሠነይኪ ወጥቀ አደምኪ ።

የንጉሥ ፍለጋን ተከትለሽ ለመሄድ እጅግ ተወደድሽ፣

፲ አፈቅሮ ለፍግዕኪ ፡ ዘቆምኪ ይመስል በቀልተ ፡ ወአጥባትኪ ከመ ሄላ ።

ቁመትሽ ዘንባባ የሚመስል ጡቶችሽም እንደ ምንጭ የሆኑ ምእመን ተድላ ደስታሽን እወደዋለሁ ።

፲፩ ወእቤ እዐርግ ውስተ በቀልት ወአኀዝ መልዕልቶ፣
ኮኑ ሉዓሌሁ ለአርያም ።
፲፪ ወከና አጥባትኪ ከመ አስከለ ወይን፣ ወጼና አንፍኪ
ከመ ከል ወጕርዔኪኒ ከመ ወይን ሠናይ ።

፲፫ እንዘ የሐውር ወልድ እኁየ ወእንዘ ይዴሉ ለከናፍ
ርየ ወለልሳንየ፣ አዛብ ወሲላን፣ ወጼናታሆ የዓውዱ ጸፍ
ጸፈ ቤትኪ፣ ከመ ጽጌረዳ ወከመ ሮማን፣ ወጸባንዮስ
ይምዕዘኒ አፉሁ ።

፲፬ አነ ዘወልድ እኁየ ወኀቤየ ምግባኢሁ ።
፲፭ ነዓ ወልድ እኁየ ንፃእ ሐቅለ ወናዕርፍ ውስተ አድ
ያም፣ ወንጊሥ ውስተ ዐፀደ ወይን ንርአይ ለእመ ጸገየ ወ
ይን፣ ወለእመ ጸገየ ቆዕ፣ ወለእመ ፈረየ ሮማን ።

፲፮ ልብነ ወሰግላጠ ይምዕዘኒ አፉሁ፣ በሀየ እሁበከ አጥ
ባትየ ለከ፣ ወይትፈተው እምከልአን መፍቅድ ።

፲፯ እንጐታት ወሀቡ መዓዛ፣ ውስተ አዕፃዲነ ኵሉ አቅማሕ
ሐዲስ ምስለ ብሉይ ወልድ እኁየ አነ ዓቀብኩ ለከ ኵሉ ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ መኑ ይሁበከ ወልድ እኁየ ትጥቡ አጥባቲሃ ለእምከ
ረኪብየ በአፍአ እስዕመከ ወኢይሜንኑኒ ።

፪ እነሥአከ ወአበውአከ ውስተ ቤተ እምየ፣ ወውስተ
ውሣጥያቲሃ ለእንተ ሐፀነተኒ፣ አስትየከ እምርጌ አፈውየ
ወእምፅቴ ሮማንየ ።
፫ የማኑ ተሐቅፈኒ ወጸጋሙ ታሕተ ርእስየ ።
፬ አምሐልኩክን አዋልደ ኢየሩሳሌም በኃይሉ ወበዕ
ንዑ ለገዳም፣ እመ ተንሥአ ወአንሥአ ኵሉ ሙታነ አፈ
ቅሮ እስከ አመ ፈቀደ ።

፭ መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትሔውፅ ከመ ጎህ፣ ፅዕዱት
ወብርህት፣ እንተ ትትመረጐዝ በወልድ እኁሃ፣ ወልድ
እኁየ እምኀበ ከል አንሣእኩከ፣ ከልኬ ዘበአብራይስጢ
እለ ቅቡዓን እደዊሁ በደመ ሐርጌ ዘገለዓድ ።

፮ በሀየ ሐመት ብከ እምከ፣ ወበሀየ ሐመት ብከ እምከ
ወላዲትከ፣ ደቂቀ ይሳከር ይሣለቁ ላዕሌከ ።
፯ አንብረኒ ከመ ኅልቀት ውስተ ልብከ፣ ወከመ ማዕተብ
በመዝራዕትከ፣ እስመ ፍቅር ከመ ሞት ፅንዕት፣ ወርቀ ወ
ዮሣር ኢይከውኑ ሤጣ፣ ወድርከት ከመ ሲኦል ።

ምጥቀቱ ወደ ሰማይ የደረሰ ጫፉን እይዝ ዘንድ ወደ
ዘንባባ ልውጣ አልሁ ።
ጡቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ ናቸው፣ የአፍንጫሽም
መዐዛ እንደ ሽቱ ነው፣ የጕሮሮሽም ጣዕም እንደ ወይን
ያማረ ነው ።
ልጅ ወንድሜ እኔን ለመራዳት ሲመጣ ምስጋናው
ለከንፈሬ ለአንደበቴ ምስጋና ተዘጋጅቶ ሳለ እኔ ለልጅ
ወንድሜ ማደርያ ነበርኩ፣ ልጅ ወንድሜም ከኔ ዘንድ
ያድር ነበር፣ አውያን ድንብላል ጤናአዳም የቤትሽን ዙር
ያ ይከቡታል፣ አፉ እንደ ረዳ አበበ እንደ ሮማንም እንደ
ጸባንዮስም ይሸታል ።
እኔ የልጅ ወንድሜ ነበርኩ እሱም ያድርብኝ ነበር ።
ልጅ ወንድሜ ና ወደ ምድረ በዳ እንውጣ በአውራጃ
ውም እንረፍ፣ ወይን አብበ እንደሆነ፣ ቆዑም አብበ እን
ደሆነ፣ ሮማንም አፍርቶ እንደሆነ፣ እናይ ዘንድ ወደ
ወይን ቦታ እንሂድ ።
አንደበቱ ልብን (የሎሚ ውኃ) ሰግላጥ እንደሚባል
ሽቱ ይሸተኛል፣ በዚያም ሁለቱን ጡቶቼን እሰጥኻለሁ
ከወርቅ ከብር ይልቅ ይወደዳሉ ። መኃ፣ ፯ ፲፩ ።
ትርንጎዎች መዐዛቸውን ሰጡ በቦታችንም ከከረ
መው ሽቱ ጋራ አዲስ ቅመም ሁሉ አለ፣ ልጅ ወንድሜ
ሕግን ሁሉ ጠበቅሁልህ ። ዘፍ፣ ፴ ፲፬ ።

ምዕራፍ ፰ ።

የናትህ ጡት ትጠባ ዘንድ ልጅ ወንድሜ ማን ይሰጥህ
ነበር፣ በውጭም አግኝቼ እስምኻለሁ ሰዎችም አይንቁ
ኝም (በባቢሎን አመልክኻለሁ) ።
ይዤ ወደ እናቴ ቤት አገባኻለሁ ወደ አሳደገችኝም
ወደ አልፍኝዋ ውስጥ አገባኻለሁ ከሮማን መጠጤና ርጌ
ከሚባል ሽቱዬ አጠጣኻለሁ ። ኢሳ፣ ፵፱ ፳፯ ።
ቀኝ እጁ ታቅፈኛለች ግራ እጁም ታንተርሰኛለች ።
የኢየሩሳሌም ልጆች በምድረ በዳ በደረገው በኃይሉ
በከሃሊነቱ አማጽኛችኋለሁ፣ በተአምራት በተነሣ ጊዜ
ምውታን ልቡና አሕዛብንም አስወጥቶ በሰደደ ጊዜ የወደ
ድሁትን ያህል እንወደዋለን እንድትሉ አማጽኛችኋለሁ ።
እንደ ጎህ የምትጐበኝ ይህች ማናት፣ እንደ ፀሐይ
ሞቃ እንደ ጨረቃ ደምቃ በልጅ ወንድሟ የምትታመን
ይህች ማናት፣ ልጅ ወንድሜ (እግዚአብሔር) ከእንከይ
(ከአብርሃም) አግኝቼ አመለከሁህ ይኸውም ከል ያልሁት
በዕብራይስጥ ቋንቋ የገለዓድን ጊደር ሲሠዋ እጆቹ በደ
ም የታለሉ አብርሃም ነው ።
በዚያ እናትህ ታመመች፣ በዚያም ወላጅ እናትህ
መከራን ተቀበለች የይሳከርም ልጆች ይዘብቱብኻል ።
ቀለበትን በጣት እንዲይዙ በልብህ አኑረኝ፣ ሀቲም
ቀለበትን በክንድ እንዲይዙ በሥልጣንህ ጠብቀኝ ፍቅር
እንደሞት የፀናች ናትና እንደ መቃብርም የፀናች ናትና
ወርቅና ዮሳር የሚባል ዕንቍ ለፍቅረ እግዚአብሔር ዋጋ
ዋ አይሆንም ።

፮ ቅንአት ትበልዖሙ ለልበ ብዙኃን በመዓት፡ እስመ በቅንአትሰ ኢይትረከብ ጸጋ እግዚአብሔር፡ ክነፊሃ ክንፈ እሳት ላህበ።

ቅንአት የብዙ ሰዎችን ልቡና ታጠፋለች፡ በቅንአት ግን ጸጋ እግዚአብሔር አይገኝምና የፍቅር ላንቃዋም የእሳት ላንቃ ነው። ኢሳ፡ ፶፱ ፲፯።

፯ ማይ ብዙኅ ኢይክል አጥፍኦታ ለፍቅር፡ ወአፍላግኒ ኢያንቀለቅልዋ፡ ለእመ ወሀበ ብእሲ ኵሎ ንብረቶ ለፍቅር፡ መንኖ ኢይሜንንዎ።

ብዙ ውኃ ፍቅርን ማጥፋት አይችልም (ሠራዊት) ፈሳሾችም አያነዋውጧትም (ነገሥታቱ) ሰው ገንዘቡን ሁሉ ለፍቅረ እግዚአብሔር ቢሰጥ (አሕዛብ) አይንቁትም።

፰ እኅትነ ንስቲት ይእቲ ወአጥባት አልባ፡ ምንተ ንግበር ለእኅትነ በዕለት አመ ይትናገሩ ባቲ።

እኅታችን (ምእመን) ታናሽ ናት ጡቷም አላጐጠጐጠም እናጥፋት ብለው በተናገሩባት ቀን ለእኅታችን ምን እንናድርግላት፤። ሕዝ፡ ፲፮ ፯።

፱ ለእመ አረፍት ይእቲ ንሕንጽ ዲቤሃ ተድባበ ዘብሩር፡ ወለእመ ኆኅት ይእቲ ንግበር ላቲ ማዕፆ ዘቄድሮስ፡ ማኅፈድ ቀይሕ ዘያከንት ለሰሎሞን በኬብሮን።

እሷ ግድግዳ ብትሆን እኛ የብር መዋቅር እንሠረላት ነበር፡ ደጃፍም ብትሆን የዋንዛ የዝግባ መዝጊያ እንሠራላት ነበር፡ ለሰሎሞን በኬብሮን በቀይ ዕንቍ የተሠራ ግንብ ነበረው። መዝ፡ ፸፱ ፹፩። ፩ ነገ፡ ፯ ፲፩።

፲ አነ ቅጽር ወአጥባትየ ከመ ማኅፈድ፡ አነ እንተ በአዕይንቲሁ እረክብ ሰላመ።

እኔ ቅጽር ነኝ ጡቶቼም እንደ ግንብ ናቸው፡ በፊቱ ተድላ ደስታ የማገኝ እኔ ነበርሁ። ሮሜ ፭ ፩።

፲፩ ዓፀደ ወይን ከነ ለሰሎሞን በብኤላሞን፡ ወወሀበ ዓፀደ ወይኑ ለእለ የዓቅቡ ፍሬሁ፡ ብእሲ ብእሲ ይሁብ ፍሬሁ በበጊዜሁ።

ለሰሎሞን በብኤላሞን የወይን ቦታ ነበረው፡ የወይኑንም ቦታ ፍሬውን ለሚጠብቁ ሰዎች ሰጠ፡ አንዱም አንዱም ሰው ፍሬውን በየጊዜው ይሰጣል።

፲፪ ዓሠርተ ወክልኤተ ምእተ ብሩረ፡ ዓሠርቱ ምእት ለሰሎሞን፡ ወክልኤቱ ምእት ለእለ የዓቅቡ ፍሬሁ፡ እእላፍ ፍሬሁ በበጊዜሁ፡ ዓሠርተ ምእተ ለጽዮን ይሁብ።

ሺሕ ከሁለት መቶ ብር ይሰጣል፡ ሺሕ ብር ለሰሎሞን ሁለቱ መቶ ብር ፍሬውን ለሚጠብቁ ሰዎች ነው፡ በየጊዜው የሚገባው ፍሬውም ብዙ ነው፡ ሺሑውን ለጽዮን ይሰጣል። ማቴ፡ ፳፩ ፴፫። መዝ፡ ፹ ፰።

፲፫ ዓፀደ ወይን ሊተ አንፃርየ እንዘ ይነብር ውስተ ገነት ክልአን ርእይዎ፡ ጉቡአን ወስንዕዋን እንዘ ይነብሩ በሰላም ክልአን ርእይዎሙ።

በአፍዝዝሮ የወይን ቦታ ነበረኝ በተክል መካከል ተቀምጦ ሳለ ሌሎች ሰዎች አዩት ተሰብስበው ተስማምተው በተድላ በደስታ ተቀምጠው ሳሉ ሌሎች አዩዋቸው።

ወእንዘ ይትረአዩ በማእከላ፡ ወእንዘ የሐውሩ ውስተ ገነት ክልአን ርእይዎሙ።

በመካከሏም ተሠማርተው ሳሉ ወደ ተክል መካከል ሂደው ሌሎች ሰዎች አዩዋቸው።

፲፬ ቃለከ አስምዓኒ፡ ጕይ አንተ ወልድ እኁየ ከመ ወይጠል፡ ወእመ አከ ወከመ ወሬዛ ኃየል ውስተ አድባረ ድጉኃን።

ቃልህን አሰማኝ አንተ ልጅ ወንድሜ እንደ ፈቶ ፈጥነህ ሂድ ያም ባይሆን (በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ) ተራራ እንዳለ እንደ ዋልያ ወይፈን እኔን ለመራዳት ስትመጣ መር ብለህ አውጣኝ። ዘፍ፡ ፲፯ ፯ ፰።

ተፈጸመ መኃልየ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

አስጀምሮ ለአስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና፡ የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ምስጋና ደረሰ ተፈጸመ፡ በእውነት ያለ ሐሰት።

# መጽሐፈ መክብብ

| ምዕራፍ ፩ ። | | ምዕራፍ ፩ ። |
|---|---|---|
| ቃለ ሰሎሞን መክብብ ወልደ ዳዊት ንጉሠ እስራኤል በኢየሩሳሌም ። | ፩ | በኢየሩሳሌም ለእስራኤል የነገሠ የዳዊት ልጅ መክብብ ሰሎሞን የተናገረው ነገር ይህ ነው ። |
| ከንቱ ከንቱ ይቤ መክብብ ኵሉ ከንቱ ። | ፪ | መክብብ ሰሎሞን ከንቱ ነው ፣ ከንቱ ነው ፣ ሁሉ ከንቱ ነው አለ ። |
| ምንት ፍድፋዴሁ ለሰብእ በኵሉ ፃማሁ ዘይፃሙ እምታሕተ ፀሐይ ። | ፫ | ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካሙ ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድር ነው ! አለ ። |
| ትውልድ የኀልፍ ፣ ትውልድ ይመጽእ ወምድርሰ ለዓለም ትቀውም ። | ፬ | ፊት የተወለደው ሰው ይሞታል ፣ ኋላ የተወለደው ይተካል ፣ ምድር ግን ለዘለዓለሙ ጸንታ ትኖራለች ። |
| ይሠርቅ ፀሐይ ወየዐርብ ፀሐይ ፣ ወውስተ መከኑ ይገብእ ፣ እንዘ ይሠርቅ ውእቱ ህየ ይገብእ በይምን ወየዐውድ መንገለ ሰሜን ። | ፭ | ፀሐይ ከምሥራቅ ይወጣል ፣ በምዕራብ ይገባል ፣ እሱ ከምሥራቅ ወጥቶ ወደ ቀኝ ይመለሳል ፣ ወደ ሰሜንም ይዞራል ። |
| ዓውደ የዓውድ ወየሐውር መንፈስ ፣ ወበዐውደቱ ይገብእ መንፈስ ። | ፮ | በመዞሪያው በኩል ተመልሶ ይዞራል ፣ ነፋስም ይነፍሳል ፣ ነፋስ ነፍሶ ከዞረም በኋላ ወደ ቦታው ይመለሳል ። |
| ወኵሎሙ ውኂዛት የሐውሩ ውስተ ባሕር ፣ ወባሕርኒ ኢከነት እንተ ትመልእ ውስተ መከና ። | ፯ | ውኆዎች ሁሉ ወደ ውቅያኖስ ይሄዳሉ ፣ ውቅያኖስ ግን በቦታዋ ተጨመሩልኝ ብላ የም ትሞላ አይደለችም ። |
| ወእደ የሐውሩ አፍላግ ህየ ከዐበ ይትመየጡ ለሐዊር ። | ፰ | ፈሳሾችም በዚያ ከሄዱ ዘንድ ዳግመኛ ወደ ውቅያኖስ ለመሄድ ይመለሳሉ ። ኢዮ፣ ፴፮ ፳፯-፳፰ ። |
| ኵሉ ቃል ዘበሕማም ኢይክል ብእሲ ለተናግሮ ወኢይጸግብ ዓይን በርእይ ፣ ወኢይመልእ ዕዝን በአጽምኦ ። | ፱ | የሰው ሁሉ ቃል በድካም ይኖራል ፣ ሰው አንድ ጊዜ ተናግሮ ዝም ማለት አይችልም ፣ ዓይን ቢያይ ቢያይ አይሰለችም ፣ ጆሮም ቢሰማ ቢሰማ አይመላም ። |
| ወምንት ውእቱ ዘገብረ እምዘተገብረ ፣ ወምንት ውእቱ ዘከነ እምዘከነ ፣ ወአልቦ ምንትኒ ዘተገብረ በመትሕተ ፀሐይ ። | ፲ | ከተፈጠረው ፍጥረት የተፈጠረው ፍጥረት ፣ ምንድር ነው ! ከተገኘውም ፍጥረት የተገኘው እንግዳ ፍጥረት ምንድር ነው ፤ ከፀሐይ በታች ምንም እንግዳ ፍጥረት የለም ። |
| ዘይነብብ ወይብል ናሁ ዝ ሐዲስ ውእቱ ፣ ወናሁ ተገብረ ዓለም እምዓለም ዘከነ እምቅድሜነ ። | ፲፩ | እነሆ ይህ እንግዳ ፍጥረት ነው ብሎ የሚናገሩት የለም እነሆ ሰው ከኛ አስቀድሞ ከተፈጠረው ሰው ተፈጠረ ። |
| አልቦሙ ዝክር ለቀደምት ምስለ ደኃርት ፣ ወለእለ ደኃርትኒ ምስለ ዘይትገበር በደኃርት ። | ፲፪ | ለቀደሙ ሰዎች ኋላ ከሚነሡ ሰዎች ጋራ ስም አጠራር የላቸውም ፣ ከነሳቸውም በኋላ ለሚነሡ ሰዎች ከነሳቸው በኋላ ከሚነሡ ሰዎች ጋራ ስም አጠራር የላቸውም ። |
| አነ መክብብ ከንኩ ንጉሠ እስራኤል በኢየሩሳሌም ። | ፲፫ | እኔ መክብብ (ሰሎሞን) በኢየሩሳሌም የእስራኤል ንጉሥ ሆንኩ ። |
| ወወሀብኩ ልብየ ለኀሢሥ ወለፈቲን በጥበብ በእንተ ኵሉ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ ፣ እስመ ሥራኀ እኩየ ወሀበ እግዚአብሔር ለውሉደ ሰብእ ከመ ይሥርኁ በቱ ። | ፲፬ | ከፀሐይ በታች ስለ ተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ጥበብን ፈጽሜ ለመመርመር ልቡናዬን ሰጠሁ ፣ ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች ብርቱ ድካምን ሰጥቷልና ። |

| | | |
|---|---|---|
| ርኢኩ ኵሎ ፍጥረተ ዘተገብረ በመትሕተ ፀሐይ ወናሁ ኵሉ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፲፬ | ከፀሐይ በታች የተፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ መረመርኩ እነሆ ሁሉ ከንቱ ነው ፤ የልብ አምሮትም ነው ። |
| ጠዋይ ኢይክል ረቲዐ ፡ ወሕፁፅ ኢይክል ተኈልቆ ። | ፲፭ | ጐባጣ ቀንቶ መሄድ አይችልም ፤ ድንክም ከረዥም ሰው ጋራ መቈጠር አይችልም ። |
| ተናገርኩ አነ በልብየ በብሂል ወናሁ አፈድፈድኩ ወአዕበይኩ ጥበበ እምእለ ኮኑ እምቅድሜየ በኢየሩሳሌም ፤ ወልብየ ርእየት ብዙኀ ጥበበ ወአእምሮ ። | ፲፮ | እኔ በልቡናዬ እስቤ ያለ ይሉኝታ ተናገርኩ ፤ እነሆ እኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ከነገሡ ሰዎች ይልቅ ፈጽሚ ጥበብን አበዛሁ ፤ ልቤም ዕውቀትንና ብዙ ጥበብን መረመረች ። |
| ወወሀብኩ ልብየ ለአእምሮ ወለጥበብ ፡ ጥበበ ወአእምሮ ወምሳሌ ፡ ወትምህርተ አእመርኩ ፡ እስመ ዝኒ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፲፯ | ልቤን ለጥበብና ለዕውቀት ሰጠሁ ፤ እውቀትንና ጥበብን ፤ ትምህርትንና ምሳሌንም አወቅሁ ፤ ይህም ማወቁ ከንቱ ነው ፤ የልብ አምሮትም ነው እኮ ! ። |
| እስመ በብዝኀ ጥበብ ብዙኀ ኀዘን ፡ ወዘአፈድፈደ አእምሮ አፈድፈደ ሕማመ ። | ፲፰ | በጥበብ ብዛት ብዙ ኀዘን አለና ፤ እውቀትንም ያበዛ ሰው መከራን አብዝቷልና ይህንንም ማወቁ ከንቱ ነው ። |

## ምዕራፍ ፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| እቤ አነ በልብየ ነዓ እምክርከ በፍሥሓ ወርኢ በሠናይ ፡ ወናሁ እቤ ዝኒ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፩ | እኔ በልቤ አስቤ ና በተድላ ደስታ ልምከርህ አልኩ ፤ ንስሓ ገብተህ ጸጋ ክብር እንድታገኝ ሁን ፤ እነሆ ይህም ከንቱ ነው ፤ የልብም አምሮት ነው አልኩ ። |
| ለሰሐቅ እብሎ አስፍጦ ፡ ወለፍሥሓ ምንት ውእቱ ዝ ግብር ። | ፪ | ሳቅን ሽንገላ እለዋለሁ ፤ ተድላ ደስታንም ይህ ሥራ ምንድር ነው ! እለዋለሁ ። ምሳ፡ ፲፬ ፲፫ ። |
| ወመከርኩ እምልብየ ፡ ጥበብ ሰሐበቶ ከመ ወይን ለሥጋየ ፡ ወልብየ መሀረኒ ጥበበ ፡ ወዝኒ እኂዝ ለፍሥሓ እስከ ሶበ እሬኢ ምንት ውእቱ ሠናይ ለውሉደ ሰብእ ፡ ዘይገብሩ እምታሕተ ፀሐይ ፡ በኍልቈ መዋዕለ ሕይወቶሙ ። | ፫ | ከልቡናዬ አንቀቼ ጥበብን መከርኩ ፤ ጥበብ እንደ ወይን ሰውነቴን ሳበችው ፤ ልቤም ጥበብን አስተማረኝ ፤ በሕይወት በሚኖርበት ዘመን ቍጥር ከፀሐይ በታች በሚሠሩት ሥራ ለአዳም ልጆች ያማረ የተወደደ ምን እንደ ሆነ እስከመረምር ድረስ ይህንንም ጥበብ መያዜ ለተድላ ደስታ ሆነኝ ። |
| እንሰ መክብብ አዕበይኩ ምግባርየ ወሐነጽኩ ሊተ አብያተ ፡ ወተከልኩ አዕፃዳተ ወይን ። | ፬ | እኔ መክብብ ሥራዬን አበዛሁ ፤ ቤቶችንም ሠራሁ ፤ የወይን በታንም አበጀሁ ። ፩ ነገ፡ ፯ ፩-፲፪ ። |
| ወገበርኩ ሊተ አዕፃዳተ ሐምል ፡ ወገነታተ ወተከልኩ ውስቴቶሙ ኵሎ ዕፀወ ዘይፈርዩ በበዖታሆሙ ወኵሉ ዘኢይፈሪ ። | ፭ | የተክል በታን አበጀሁ ፤ ተክል ተከልኩ ፤ በየወገናቸው የሚያፈሩ ዕንጨቶችን ሁሉ የማያፈራውንም ሁሉ ተከልኩ ። |
| ወገበርኩ ሊተ ምዕቃለ ማያት ከመ እሥቂ እምኔሆሙ አመ ወዕፀ ዘይፈሪ ገራህተ ወገራውሀ አጥረይኩ ። | ፮ | የሚያፈራውን ዕንጨትንና ዛፉን ከነሳቸው አጠጣ ዘንድ ለኔ የውኃዎችን ኩሬ አበጀሁ ፤ ሁዳዱንና እርሻውንም ገዛሁ ። |
| አግብርተ ወአእማተ ወልደ ቤት አጥረይኩ ጥሪተ ወኖሎተ አልሕምት ወመራዕየ አባግዕ ብዙኀ አጥረይኩ እምኵሎሙ እለ ኮኑ እምቅድሜየ በኢየሩሳሌም ። | ፯ | ሴቶች ባሮችንና ወንዶች ባሮችን ፤ የቤት ውላጅንም ገዛሁ ፤ ከኔ አስቀድሞ በኢሩየሳሌም ከነገሡ ነገሥታት ይልቅ ብዙ የሆኑ የበጎች መንጋዎችንና ላሞችን የሚጠብቁ ዘላኖችን ገዛሁ ። |
| ወአስተጋባእኩ ብዙኀ ብሩረ ወወርቀ ወጥሪተ መንግሥት ወበሐውርት ፡ ኀላይተ ወኃላይያነ ወፍግዐ ምስለ ውሉደ ሰብእ ። | ፰ | ወርቅን ብዙ ብርን ሰበሰብኩ የመንግሥት ገንዘብ የሚሆን ዘውድንም አሠራሁ ፤ መንደርን መነደርኩ ፤ የወንድ ዘፋኞችንና የሴት ዘፋኞችን አበጀሁ ፤ ከአዳም ልጆችም ጋራ ተድላ ደስታን አደረግሁ ። ፩ ነገ፡ ፱ ፳፰ ። |
| መዘርተ ወመዛርያነ አዕበይኩ ወአፈድፈድኩ እምእለ ኮኑ እምቅድሜየ በኢየሩሳሌም ወጥበብየኒ ቆመተኒ ። | ፱ | የጠጅ አዛዦችንና የጠጅ አሳላፊዎችን ሾምኩ ፤ ከኔ አስቀድሞ በኢየሩሳሌም ከነበሩ ሰዎች ይልቅ ይህን ሁሉ አበዛሁ ፤ ጥበቤም ጸናችልኝ ። ፩ ዜና መ፡ ፳፱ ፳፭ ። |
| ኵሎ ዘሰአላ አዕይንትየ ኢተመቄስኩ ወኢከላእክዎ ለልብየ እምኵሉ ፍሥሓ እስመ ልብየ ተፈሥሐ በኵሉ የማየ ወዝንቱ ኮነ መክፈልትየ እምኵሉ ሥራኅየ ። | ፲ | ዓይኖቼ ያዩትን ሁሉ አላጣሁም ፤ በድካሜ ሁሉ ልቡናዬን ደስ ብሎታልና ፤ በድካምኩበትም ገንዘቤ ሁሉ ዕድል ፈንታዬ ይህ ሆኗልና ፤ ልቡናዬን ከተድላው ከደስታው አልከለከልኩትም ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወነፀርኩ ዲበ ኵሉ ግብረትየ ዘገብራ እደውየ፡ ወበሥራኅየ ዘሠራዕኩ ለገቢር፡ ወናሁ ኵሉ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ፡ ወአልቦ ፍድፋዴ እምታሕተ ፀሐይ ። | ፲፩ | እጆቼ ያጠራቀሙትን ገንዘቤን ሁሉ አየሁ፡ ተድላ ደስታንም ለማድረግ ድካሜን ሁሉ አበዛሁ፡ እነሆ ይህ ከንቱ ነው፡ የልብ አምሮትም ነው፡ ከፀሐይ በታች ለሰውትርፍ የለውም ። |
| ወነፀርኩ አነ ከመ እርአይ ጥበበ ወተሰፍጦ ወዕበደ መኑ ብእሲ ዘይተሉ ድኅሬሃ ለምክር፡ ወኵሉ ምሳሌ ዘገብረ ላቲ ። | ፲፪ | ጥበብን ሽንገላን ስንፍናን አውቅ ዘንድ እኔ ተመለከትኩ፡ ምክርን የሚከተላት ማን ነው፤ ምሳሌውንስ ሁሉ የሚመስላት ማን ነው፤። መክ፡ ፪ ፫ ። |
| ወርኢኩ አነ ከመቦ ፍድፍድና ለጠቢብ እምዐብድ፡ ከመ ፍድፋዴ ብርሃን እምጽልመት ። | ፲፫ | ከጨለማ ይልቅ ለብርሃን ብልጫ እንዳለው፡ ከሰነፍም ለብልህ ሰው ብልጫ እንዳለው እኔ ተመለከትኩ ። |
| እስመ ለጠቢብ አዕይንቲሁ ዲበ ርእሱ፡ ወዐብድሰ ውስተ ጽልመት የሐውር ወአእመርኩ አነ ከመ አሐዱ ድድቅ ይዳደቆሙ ለክልኤሆሙ ። | ፲፬ | የብልህ ሰው ዓይኖቹ በራሱ ላይ ናቸውና፡ (ሰማያዊ ነገር ያስባሉ) አላዋቂ ሰው ግን በድንቍርና ፀንቶ ይኖራልና፡ አዋቂውንም አላዋቂውንም አንድ ሞት እንዳገናኘቸው አወቅሁ ። ምሳ፡ ፲፯ ፲፬ ። |
| ወሰቤሃ አነ እቤ በልብየ በከመ ይዳደቆ ለዐብድ ከማሁ ሊተኒ ይዳደቀኒ፡ ወለምንት ጠበብኩ አነ አሜሃ በከአፈድፈድኩ ነቢበ እስመ ዝኒ ከንቱ ። | ፲፭ | የዚያን ጊዜ እኔ በልቡናየ አላዋቂውን ሞት እንዲያገኘው እኔንም ያገኘኛል አልሁ፡ እኔ ከዚህ ሞት ሳልድን ለምን አዋቂ ሆንሁ አልኩ፡ ያን ጊዜ በከንቱ መቀባጠርን ለምን አበዛሁ፤ ለምን አዋቂ ሆንኩ ማለቴም ከንቱ ነው ። |
| እስመ አልቦ ዝክር ለጠቢብ ምስለ ዐብድ ለዓለም እስመ ናሁ መዋዕል ይመጽእ ወኵሉ ይትረሳዕ ወእፎ ይመውት ጠቢብ ምስለ ዐብድ ። | ፲፮ | ላዋቂ ሰው ካላዋቂ ሰው ጋራ ለዘለዓለሙ ስም አጠራር የለውምና፡ ይህም እነሆ እንዲህ ያለ ወራት ይመጣልና ሁሉም ይዘነጋልና፡ አዋቂ ሰው ካላዋቂ ሰው እንዴት ይሞታል፤ አልሁ ። |
| ወጸላእኩ ኵሉ ሕይወትየ እስመ እምእኩይ ፍጥረት ላዕሌየ ሀሎ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ፡ እስመ ኵሉ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፲፯ | ከፀሐይ በታች የተፈጠረ ክፉ ፍጥረት (ሞት) በኔ ላይ አለና ኑሮዬን ሁሉ ጠላሁ፡ ሁሉ ከንቱ ነውና፡ የልብ አምሮትም ነውና ። |
| ጸላእኩ አነ ኵሎ ሥራኅየ ዘአነ እሠርኅ እምታሕተ ፀሐይ እስመ አኀድጎ ለሰብእ ዘይትወለድ እምድኅሬየ ። | ፲፰ | እኔ ከፀሐይ በታች የምደክምበትን ድካሜን ሁሉ ጠላሁ፡ ከኔ በኋላ ለሚወለድ ልጅ እተዋለሁና ። |
| ወመኑ የአምር እመ ጠቢበ ይከውን ወእመ አኮ ዐብድ ወእመ አኮ ይሜለጥ በኵሉ ዘሥራኅየ ዘሠራኅኩ ወተጠበብኩ እምታሕተ ፀሐይ ወዝኒ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፲፱ | ያውቅበትም እንደሆነ አያውቅበትም እንደሆነ ከፀሐይ በታች በተራቀቅሁበትና በደከምኩበት ገንዘቤ ሁሉ አይሠለጥንበትም እንደሆነ ማን ያውቃል፤ ይህም እንዲህ ማለት ከንቱ ነው፡ የልብ አምሮትም ነው ። |
| ወተመየጥኩ አነ ከመ አትዋገዝ ለልብየ በኵሉ ሥራኅየ ዘሠራኅኩ እምታሕተ ፀሐይ ። | ፳ | ከፀሐይ በታች በደከምኩበት ድካሜ ሁሉ ልቡናዬን አከራከረው ዘንድ ወደ መከራከር ተመለስኩ ። |
| እስመቦ ሰብእ ዘይሠርኅ ሎቱ በጥበብ ወአእምሮ በጽኑዕ ወበምክር፡ ወለብእሲ ዘኢሠርኀ በቱ ይሁብ መክፈልቶ፡ ወዝኒ ከንቱ ወእኩይ ዓቢይ ። | ፳፩ | በሥጋዊ ጥበብ በሥጋዊ እውቀት በሥጋዊ ኃይል በሥጋዊ ምክርም የሚደክም ሰው አለና፡ ገንዘቡን ላልደከመበት ሰው ይሰጣል፡ ይህም ከንቱ ነው፡ ፅኑ መከራም ነው ። |
| እስመ ኢይከውኖ ለብእሲ በኵሉ ፃማሁ ወፍትወተ ልቡ ዘውእቱ ይሠርኅ እምታሕተ ፀሐይ ። | ፳፪ | ሰውን በደከመበት ገንዘብ ሁሉ ከፀሐይ በታች በሚደክምበት በልቡናውም ፈቃድ ደስ አይለውም ። |
| እስመ ኵሉ መዋዕሊሁ ሕማም ወመዓት ወንታፌ ሎቱ፡ ወበሌሊትኒ ኢይነውም ልቡ፡ ወዝኒ ከንቱ ውእቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | ፳፫ | ዘመኑ ሁሉ መከራ ቍጣ ነውና፡ ሌላውም ሰው እሱን ሲቀማ ይኖራልና፡ በሌሊትም ልቡ አያርፍምና፡ ይህም ከንቱ ነው፡ የልብ አምሮትም ነው ። ኢዮ፡ ፲፬ ፩ ። |
| ወአልቦ ሠናይ ለሰብእ ዘእንበለ ዘበልዐ ወሰትየ ወዘያሬእያ ሠናየ ለነፍሱ፡ ወዝኒ ዘርኢኩ አነ ከመ እምእደ እግዚአብሔር ውእቱ ። | ፳፬ | ከመጠጣትና ከመብላት ለሰውነቱም ተድላ ደስታን ከማሳየት በቀር ለሰው በጎ ነገር የለውም፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሀብት እንደሆነም እኔ ያየሁት ይህ ነው ። |
| ወመኑ ውእቱ ዘይበልዕ ወይሰቲ ዘእንበሌሁ ። | ፳፭ | ያለሱ ፈቃድ የሚበላ የሚጠጣ ማነው፤ ። |
| እስመ ለብእሲ ኄር ቅድመ ገጹ ወሀበ ጥበበ ወአእምሮ ወፍሥሐ ። | ፳፮ | በሰው ፊት ደግ (መንግሥተ ሰማይ) አለና እውቀትንና ጥበብን፡ ተድላ ደስታንም ሰጠው ። |
| ወለዘሰ ይኤብስ ወሀበ ሥራኅ ከመ ይወስክ ወያስተጋብእ ብዕለ ከመ የሀብ ለኄር ዘሀሎ ቅድመ ገጹ ለእግዚአብሔር፡ ወዝኒ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ። | | በገንዘብ ላይ ገንዘብን ያጠራቅም ይሰበስብ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ጸንቶ ለሚኖር ለደግ ሰው ገንዘቡን ይሰጥ ዘንድ፡ ለሚበድል ሰው ግን ማጠራቀምን ሰጠው ። |

## ምዕራፍ ፫ ።

፩ በ ለኵሉ ዘመን ወበ ጊዜ ለኵሉ ምግባር እም ታሕተ ፀሐይ ።
፪ ጊዜ ለጸኒስ፡ ወጊዜ ለወሊድ ።
፫ ጊዜ ለሕይወት፡ ወጊዜ ለሞዊት፡ ጊዜ ለተኪል፡ ወጊዜ ለመሊኅ ዘተከሉ፡ ጊዜ ለአቅትሎ፡ ወጊዜ ለፈውሶ፡ ጊዜ ለሐኒፅ፡ ወጊዜ ለነሚት ።

፬ ጊዜ ለብካይ፡ ወጊዜ ለሰሐቅ፡ ጊዜ ለላሀዎ፡ ወጊዜ ለዘፊን ።
፭ ጊዜ ለወርዎ እብን፡ ወጊዜ ለአስተጋብኦ እብን፡ ጊዜ ለተሐቅፎ፡ ወጊዜ ለተራኅቆ እምተሐቅፎ ።

፮ ጊዜ ለኅሢሥ፡ ወጊዜ ለኀጕል፡ ጊዜ ለአቂብ፡ ወጊዜ ለአውፅኦ ።
፯ ጊዜ ለሰጢጥ፡ ወጊዜ ለረፊእ፡ ጊዜ ለአርምሞ፡ ወጊዜ ለተናግሮ ።
፰ ጊዜ ለአፍቅሮ፡ ወጊዜ ለጽልእ፡ ጊዜ ለጸብእ፡ ወጊዜ ለሰላም ።
፱ ምንት ፍድፋዴሁ ለዘይገብር በዘውእቱ ይሠርኅ ።

፲ ርኢኩ ኵሎ ሥራኀ ዘወሀበ እግዚአብሔር ለውሉደ ሰብእ፡ ሥራኅ ከመ ይሥርኆ ቦቱ ።
፲፩ ኵሎ ሠናይ ዘገብረ በጊዜሁ ወኵሎ ኀቡረ ወሀበ ለዓለም ውስተ ልቡ ከመ ኢይርከብ ሰብእ ግብረ ዘገብረ እግዚአብሔር እምጥንቱ እስከ ተፍጻሜቱ ።

፲፪ አእመርኩ ከመ አልቦ ሠናይ እምውስቴቶሙ ዘእን በለ ዘተፈሥሐ፡ ወገብረ ሠናየ በሕይወቱ ።

፲፫ ወኵሉ ዘበልዐ ወሰትየ ወርእየ ሠናየ እምኵሉ ፃማሁ ዝኒ ሀብተ እግዚአብሔር ውእቱ ።
፲፬ አእመርኩ ከመ ኵሉ ዘገብረ እግዚአብሔር ውእቱ ይሄሉ ለዓለም ወእምውስቴቶሙ ኢይትከሃል ወስኮ፡ ወእምውስቴቶሙ ኢይትከሃል ነቲግ፡ ወእግዚአብሔር ገብረ ከመ ይፍርሁ እምቅድመ ገጹ ።

፲፭ ወዘተገብረ ናሁ ውእቱ ሀሎ፡ ወኵሉ እምዘተገብረ ናሁ ተገብረ፡ ወእግዚአብሔር የኀሥሦ ለዘይሰድዶ ።

፲፮ ወዓዲ በ ዘርኢኩ እምታሕተ ፀሐይ፡ በመከነ ጻድቅ ህየ ረሲዕ፡ ወበመከነ ረሲዕ ህየ ጻድቅ ።

፲፯ ወበህየ አነ እቤ በልብየ ኅቡረ ጻድቀ ወረሲዐ ይኴንን እግዚአብሔር፡ እስመ በ ጊዜ ለኵሉ ምግባር ።

፲፰ ወበህየ እቤ አነ በልብየ በእንተ ነገረ ውሉደ ሰብእ

## ምዕራፍ ፫ ።

ለሁሉ ዘመን አለው፡ ከፀሐይ በታች ላለ ሥራ ሁሉ ጊዜ አለው ።
ለመጽነስ ጊዜ አለው፡ ለመውለድም ጊዜ አለው ።
ለሕይወት ጊዜ አለው፡ ለሞትም ጊዜ አለው፡ ተክል ለመትከል ጊዜ አለው፡ የተከለትንም ለመንቀል ጊዜ አለው፡ ለማቍሰል ጊዜ አለው፡ ለማዳንም ጊዜ አለው፡ ቤት ለመሥራት ጊዜ አለው፡ ለማፍረስም ጊዜ አለው ።
ለልቅሶ ጊዜ አለው፡ ለሳቅም ጊዜ አለው፡ ለማልቀስ ጊዜ አለው፡ ለመዝፈንም ጊዜ አለው ።
ደንግያን ለመወርወር ጊዜ አለው፡ ደንጊያንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው፡ ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፡ ከመተቃቀፍም ለመራራቅ ጊዜ አለው ።
ለመፈለግ ጊዜ አለው፡ ለማጥፋትም ጊዜ አለው፡ ለመጠበቅ ጊዜ አለው፡ ለማውጣትም ጊዜ አለው፡
ለመቅደድ ጊዜ አለው፡ ለመስፋትም ጊዜ አለው፡ ለዝምታ ጊዜ አለው፡ ለመናገርም ጊዜ አለው፡
ለመፋቀር ጊዜ አለው፡ ለመጣላትም ጊዜ አለው፡ ለጥል ጊዜ አለው፡ ለፍቅርም ጊዜ አለው ።
እሱ በሚደክምበት ድካሙ ሁሉ ሥራ ለሚሠራ ሰው ትርፉ ምንድር ነው፤
ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች የሰጠው ድካሙን ሁሉ አየሁ ።
በጊዜው ጊዜ የፈጠረው ሁሉ ያማረ ነው፡ ሰው ከመጀመርያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት መርምሮ እንዳያገኝ ሁሉን በአንድነት ለሰው በልቡ አሳደረበት ።
ከነህ ከአዳም ልጆች በልቶ ጠጥቶ ደስ ካለው በሕይወቱም ሳለ ተድላ ደስታ ከደረገ ሰው በቀር በጎ ነገር እንደሌለ አወቅሁ ። መዝ፡ ፴፬ ፲፬ ።
የጠጣና የበላ በገንዘቡ ሁሉ ተድላ ደስታ ያደረገ ሰው ሁሉ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ።
እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር አወቅሁ፡ ከነዚህም አንሰ ብሎ መጨመር አይቻልም፡ ከነዚህም በዛ ብሎ መከፈል አይቻልም፡ እግዚአብሔርም ገጸ መዓቱ ከመግለጥ የተነሣ እንዲፈሩ አደረገ ።
እነሆ የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ፀንቶ አለ፡ እነሆ ሁሉ ከፈጠረው ፍጥረት ተፈጠረ፡ ድኻውን ከደጁ አስወጥቶ የሚሰደውንም እግዚአብሔር በፍዳ ይመራመረዋል።
ዳግመኛም ከፀሐይ በታች ያየሁት አለ፡ በዚያ በደግ ሰው በታ ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጋ ሰው አለ፡ በዚያ ሕገ እግዚአብሔርን በዘነጋ ሰውም በታ ደግ ሰው አለ።
ለሥራ ሁሉ ጊዜ አለውና እኔ በልቤ ይህን አሰቤ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውንና እውነተኛውን አንድነት ይገዛል አልሁ ።
እኔም በልቤ አሰቤ በዚያ እግዚአብሔር እንዲፈርድባ

ከመ ይኩንኖሙ እግዚአብሔር ወከመ ዠ ርኢኩ ከመ እን
ስሳ እሙንቱ ።
፲፱ ወሎሙኒ ድድቅ ለውሉደ ሰብእ ፡ ወድድቅ ለእንስሳ
አሐዱ ድድቅ ሎሙ ከመ ሞተ ዝ ከማሁ ሞቱ ለዝ ፡ ወአ
ሐዱ መንፈስ ለኵሎሙ ፡ ምንት ፍድፋዴሁ ለሰብእ እም
እንስሳ ወኢምንትኒ እስመ ኵሉ ከንቱ ።

፳ ኵሉ የሐውር ውስተ አሐዱ መካን ፡ ኵሉ ኮነ እመሬት ፡
ወኵሉ ይገብእ ውስተ መሬት ።
፳፩ መኑ የአምር መንፈሰ ውሉደ ሰብእ ከመ የዐርግ ላዕለ
ወመንፈሰ እንስሳ ከመ ይወርድ ታሕተ ውስተ ምድር ።

፳፪ ወርኢኩ ከመ አልቦ ሠናይ ዘእንበለ ዘተፈሥሐ ሰብእ
በተግባሩ ፡ እስመ ውእቱ መክፈልቱ ወመኑ ያመጽኦ ከመ
ይርአይ ዘይከውን እምድኅሬሁ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወተመየጥኩ አነ ወርኢኩ ኵሎ ኅቡረ ትዕግልተ ዘይ
ትገበር እምታሕተ ሰማይ ።

፪ ወናሁ አንብዕ ላዕለ እለ ይትዔገልዎሙ ፡ ወአልቦ
ዘይናዝዞሙ እምእለ ይትዔገልዎሙ በኃይል ።

፫ ወአስተኃየስክዎሙ አነ ለእለ ሞቱ ኅቡረ እለ ወድኡ
ሞተ እምሕያዋን ፡ ወእለ እሙንቱ ሕያዋን እስከ ይእዜ ።
፬ ወእምክልኤሆሙ ይኄይስ ዳሕፅ ፡ ወዓዲ ኢተፈጥረ
ዘኢየአምር ኵሎ ግቢረ እኩየ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ ።

፭ ወርኢኩ አነ ኵሎ ሥራኅ ኅቡረ ፡ ወኵሎ ኃይለ ምግ
ባር ከመ ውእቱ ቅንአ ለብእሲ እምኀበ ቢጹ ፡ ወዝኒ ከንቱ
ወፍትወተ መንፈስ ።

፮ ዐብድ ሐቀፈ እዴሁ ወበልዐ ሥጋሁ ።
፯ ሠናይ ምልአ እድ በጽድቅ እምነ ክልኤቱ ሕፍን ዘበ
ዓመፃ ፡ ወዝኒ ከንቱ ፡ ወፍትወተ መንፈስ ።
፰ ወተመየጥኩ አነ ወርኢኩ ከንቶ መትሕተ ፀሐይ ።

፱ ወሀሎ አሐዱ ወአልቦ ካልእ ወልድ ፡ ወእኁ አልቦ ፡ ወአ
ልቦ ፍጻሜ ለኵሉ ሥራሑ ፡ ወዓይኑኒ ኢይመልእ ብዕለ
ወኢይቤ ለመኑ እሠርኅ አነ ወእቄቅያ ለነፍስየ እምብዕል
ወዝኒ ከንቱ ወሥራኅ እኩይ ውእቱ ።

፲ ይኄይሱ ክልኤቱ እምአሐዱ ፡ እለ በሙ ዐስብ ሠናይ
በፃማሆሙ ።
፲፩ እስመ እመ ወድቀ አሐዱ ያነሥኦ ካልኡ ፡ አሌ ሎቱ
ለአሐዱ እመ ወድቀ አልቦ ካልእ ዘያነሥኦ ።
፲፪ እስመ እመ ኖሙ ክልኤሆሙ ይትማወቁ ፡ ወአሐዱሰ
እፎ ይትማወቅ ።

ቸው የአዳምን ልጆች ነገር ተናገርኩ ፡ የሰዎች ሞት እንደ
እንስሳ እንደሆነ እንዲህ አድርጌ አየሁ ።
የሰዎች ሞት የእንስሳም ሞት (ከደመ ነፍስ በመለየት)
አንድ ነው ፡ የሰው ሞት አሁን እንደ ተናገርሁት እንደ
እንስሳ ሞት ነው ፡ ሁሉንም አንድ ሞት ይገድላቸዋል ፡
የሰው ከእንስሳ ብልጫው ምንድር ነው ፤ ሁሉም ከንቱ
ነውና ምንም አይበልጥም ።
ሁሉም ወደ አንድ መቃብር ይሄዳል ፡ ሁሉ ከመሬት
ተገኝቶ ሁሉም ወደ መሬት ይመለሳል ። ዘፍ ፡ ፫ ፲፱ ።
የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ (ገነት) ይወጣ እንደሆነ
የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች (ገሃነም) ይወርድ እንደሆነ
ማን ያውቃል ። ዘፍ ፡ ፪ ፯ ።
ዕድሉ እሱ ነውና ፡ በልቶ ጠጥቶ ደስ ካለው ሰው በ
ቀር በጎ ነገር እንደሌለ አወቅሁ ፡ እሱም ከሞተ በኋላ የሚ
ደረገውን ያይ ዘንድ የሚያመጣው ማን ነው ፤ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

እኔ አንዱን ነገር ከማየት አንዱን ነገር ወደ ማየት
ተመልሼ ከሰማይ በታች የሚደረገውን ቅሚያ ሁሉ አን
ድነት (ሞት እየቀማ የሚወስዳቸውን) አየሁ ።
ሞት መቃብር በሚቀሙዋቸው ሰዎች እነሆ ልቅሶ
አለ ፡ በኃይል ቀምተው ከሚወስዱዋቸው ከሞትና ከመ
ቃብር በኃይል የሚያረጋጋቸው የለም ።
እኔ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት ካሉ ሰዎች የሞቱትን
ሰዎች ፈጽሜ አሸሸልኳቸው ። ኢዮ ፡ ፫ ፲፩ ።
ካሉትና ከሞቱትም ከሁለቱ ሁሉ ከፀሐይ በታች የተ
ደረገውን ክፉውን ሥራ መሥራት የማያውቅ ውራጅ ይሻ
ላል ፡ ዳግመኛም አለመፈጠር ይሻላል ።
እኔ ድካሙን ሁሉ አንድነት አየሁ ፡ የሰው ሥራው
በባልንጀራው መቅናት እንደሆነ ፡ የሥራውን ሁሉ ምሥ
ጢር መረመርኩ ፡ ይህም በባልንጀራ መቅናት ከንቱ ነው ፡
የልብም አምሮት ነው ።
ሰነፍ ሰው እጁን ያዘ (ዘመዱን አማ) ሥጋውንም በላ ።
በሐሰት ከሚሆን ሁለት እፍኝ በእውነት አንድ እፍኝ
በጎ ነው ፡ ይህም ከንቱ ነው የልቡናም አምሮት ነው ።
አንዱን ነገር ከማየት አንዱን ነገር ወደ ማየት ተመ
ልሼ ከፀሐይ በታች ያለውን ከንቱን ነገር አየሁ ።
አንድ ሰው አለ ፡ ሌላ ልጅ የለውም ፡ ወንድምም የለ
ውም ለድካሙም ሁሉ መጨረሻ የለውም ፡ ዓይኑም ባለ
ጸግነትን አይጠግብም እኔ ለማን እደክማለሁ አይልም ከባ
ለጸግነት ለምን ሰውነቴን እነፍጋታለሁ ፤ አይልም ይህም
ከንቱ ነው ፡ ዕኑ ድካምም ነው ። ምሳ ፡ ፳፯ ፳ ።
ከአንድ ሰው በድካማቸው በጎ ዋጋ ያላቸው ሁለት
ሰዎች ይሻላሉ (ባልና ሚስት) ።
አንዱ ቢወድቅ አንዱ ያነሣዋልና ቢታመም የሚያስ
ታምመው ለሌላው ለአንድ ሰው ወዮለት ።
ሁለቱ ቢተኙ ይሟሟቃሉና አንድ ሰው ግን ብቻውን
ቢተኛ እንዴት ይሞቀዋል ፤

፲፫ ወእመ ፀንዐ ክልኤሆሙ ይትቃወምዎ ፡ ወፈትል ሥሉስ ፍጡነ ኢይትበተክ ።

፲፬ ይኄይስ ቅኑይ ነዳይ ወጠቢብ ፡ እምንጉሥ ልሂቅ ወዐብድ ዘኢየአምር ለነጽሮ ፡ ከመ እምቤተ ሞቅሕ ይወጽእ ለነጊሥ እስመ በመንግሥቱ ከነ ነዳየ ።

፲፭ ወርኢኩ እነ ኵሎ ኀቡረ እለ ሕያዋን እለ ያንሶሱ መትሕተ ፀሐይ ምሳሌ ወሬዛ ካልእ ህየንቴሁ ይትነሣእ ።

፲፮ ወአልቦ ፍጻሜ ለኵሉ ሕዝብ ለኵሎሙ እለ ኮኑ እምቅድሜሁ እስመ ደኃርትኒ ኢይትፌሥሑ ቦቱ ፡ እስመ ዝኒ ከንቱ ወፍትወተ መንፈስ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

፩ ዕቀብ እገሪከ ሶበ ተሐውር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ወቅረብ ለሰሚዐ ትምህርቶሙ ለጠቢባን ፡ ዓዲ ተዓቀብ እምነ ሀብቶሙ ለዓብዳን መሥዋዕተ ፡ እስመ ኢኮኑ ማእምራነ ለገቢረ ሠናይ ።

፪ ወዓዲ ተዓቀብ ከመ ኢትጉጒዕ በአፉከ ወበልብከኒ ኢትጕጒዕ ለአውጽኦ ቃል ቅድመ ገጸ እግዚአብሔር ፡ እስመ እግዚአብሔር ውስተ ሰማይ ላዕለ ፡ ወአንተሰ ውስተ ምድር ታሕተ ፡ ወበእንተዝ ይኩን ነገርከ ኅዳጠ ።

፫ እስመ ይመጽእ ሕልም በብዙኅ መከራ ወቃለ ዐብድ በብዙኅ ነገር ።

፬ እምከመ ጸለይከ ጸሎተ ኢታጕንዲ ውኂቦታ ፡ እስመ ኢኮነ ፈቃዱ ፡ አንተሰ በከመ ጸለይከ ጸሎተ ሀብ ።

፭ ይኄይስ ኢጸልዮትከ እምጸልዮትከ ዘበኢውሂብ ።

፮ ኢተሀብ አፉከ ለአበሳ ሥጋከ ፡ ወኢትበል በቅድመ እግዚአብሔር በኢያአምሮ ውእቱ ፡ ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር ላዕሌከ በእንተ ቃልከ ፡ ወኢያማስን ግብረ እደዊከ ።

፯ እስመ ብዙኅ ሕልም ከንቱ ፡ ወንባብኒ ብዙኅ ከንቱ ፡ ወኅቡረ እግዚአብሔርሃ ፍራህ ከመ ቀዳሚ ።

፰ እመ ትዕግልተ ነዳይ ወሀይደ ርኢከ በብሔር ፍትሕ ጽድቀ ፡ ወኢታንክር በምግባሩ ፡ እስመ ልዑል መልዕልተ ልዑላን የዓቅበከ ወልዑል ዲቤሆሙ ፈድፋደ እምድር ወላዕለ ኵሉ ውእቱ ።

፱ ወንጉሥ ዲበ ወፍረ ሐረስት ።

፲ ዘያፈቅር ብሩረ ኢይጸግብ ብሩረ ፡ ወዘኒ አፍቀረ ብዙኀ እክለ ፡ ወዝኒ ከንቱ ውእቱ ።

ቢፀና ሁለቱ ይቃወሙታል (ፈቃደ ሥጋ ቢነሣባቸው ባልና ሚስቱ ያበርዱታል) ሦስት ሁኖ የተታታ ፈትል ፈጥኖ አይቈረጥም ።

መልክዐ ፍትሕን ከማያውቅ ገና ለመንገሥ ከውህኒ ቤት እንደሚወጣ ከሽማግሌ ካለዋቂ ንጉሥ ግዞተኛ የሚሆን ብልህ ድኻ ይሻላል ፡ በግዞቱ ከዕውቀት የተቸገረ ሁኖአልና ። ፩ኛ ነገ፡ ፲፩ ፳፮ ፤ ፲፪ ፪ ።

ሕያዋን የሚሆኑ ሰዎችን ሁሉ እኔ አንድነት አየሁ የሞተው ምሳሌ የሚሆን ሁለተኛ ስለሞተው ፈንታ ይነሣል ። ዘፍ፡ ፵፩ ፲፬ ። ፩ኛ ነገ፡ ፲፩ ፲፩ ።

ለወገኖች ሁሉ ከሱም በፊት ለሞቱቱ ሰዎች ሁሉ ቍጥር የላቸውም ፡ ኋላ የተነሡ ሰዎች በዚህ በሞተው ሰውደስ አይላቸውምና ፡ የሞተው ምሳሌ የሚሆን ሁለተኛው ስለሞተው ፈንታ ይነሣል ፡ ይህም ከንቱ ነው የልብም አምሮት ነው ።

## ምዕራፍ ፭ ።

ወደ ቤተ እግዚአብሔር በሄድክ ጊዜ እግርህን ጠብቅ ፡ የመምህራንንም ትምህርት ለመስማት ቅረብ ፡ በጎ ሥራ ለመሥራት አዋቂዎች አይደሉምና ፡ ሰነፎች ከሚሰጡት ከብት ምጽዋት ከመቀበል ተጠበቅ ።

ዳግመኛም በአፍህ ቸኵለህ ይህን እሰጣለሁ ከማለት ተጠበቅ ፡ እግዚአብሔር በሰማይ ይኖራልና አንተ ግን በምድር ትኖራለህና በልብህም በእግዚአብሔር ፊት ስእለትን ለመሳል አትቸኵል ፡ ስለዚህም መጥነህ ተሳል ።

ሐሰት በብዙ መከራ ይመጣልና ፡ የስንፍናም ነገር በብዙ ነገር ይመጣልና ።

ከተሳልክም በኋላ ፈጥነህ ስጥ ለእግዚአብሔር የተሳሉትን ማስቀረት ፈቃዱ አይደለምና ፡ አንተ ግን እንደ ተሳልክ ስእለትህን ስጥ ። ዘኍ፡ ፴ ፪ ። መዝ፡ ፶ ፲፬ ።

ካለመስጠት ጋራ ከመሳልህ ፡ ጭንቱን አለመሳልህ ይሻላል ።

በ'ውነትህ በደል ሊሆንብህ ስእለት አትሳል እግዚአብሔር እንዳይቈጣብህ እርሻህ ቍፋሮህንም እንዳያጠፋብህ በእግዚአብሔር ፊት ደዌው አእምሮዬን አሳጥቶኝ ነው የተሳልኩ አትበል ። ፩ኛ ቆሮ፡ ፲፩ ፩ ።

ብዙ ሐሰት መናገር ከንቱ ነውና ፡ ብዙ ነገርም ከንቱ ነውና እግዚአብሔርን በደዌህ ጊዜ ትፈራው እንደ ነበረ አሁንም እንደ ቀድሞህ አንድ አድርገህ ፍራው ።

ድኻ በአገር ሲበደል ሲቀማ ብታይ እውነተኛ ፍርድን ፍረድ ፡ ከፍ ካሉ ከፍ ያለ እግዚአብሔር ይጠብቃኻልና ፡ ፈጽሞ በዚህ ዓለም ባሉ ዳኞች ላይ ልዑል ነውና ከሁሉም በላይ ከፍ ያለ ነውና ። ሕዝ፡ ፲፰ ፲፰ ።

ከመሳፍንቱ በላይ ንጉሥ ነውና ፡ ዳኛውን በፍርድ ጊዜ አትፍራ ።

ብርን የሚወድ ሰው ብርን አይጠግብም ፡ ብዙ እኽልንም የሚወድ ሰው እኽልን አይጠግብም ፡ ይኸውም ከንቱ ነው ።

፲፩ እስመ ለብዙኅ ጥሪት ብዙኃን ይበልዕዎ፡ ወምንት ጽንዑ ለዘይቀርብ ዘእንበለ ርእየ ዓይን ።

ብዙ ገንዘብን ብዙ ሰዎች ይበሉታልና፡ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ሲያላምጡት በዓይን ከማየት በቀር በዝቶ ለሚቀርበው ምግብ ትርፉ ምንድር ነው፤

፲፪ ጥዑም ንዋሙ ለገብር ለእመ ኅዳጠ በልዐ፡ ወለእመ ብዙኀ በልዐ፡ ወለዘአብዝኀሰ ብዕለ አልቦ ዘየኃድጎ ይኑም ።

ብዙም ቢበላ ጥቂትም ቢበላ የባርያ እንቅልፉ ጤና ነው፡ ባለጸግነትን ያበዛ ሰው ግን ይተኛ ዘንድ የሚያሳርፈው የለም ።

፲፫ ቦ ደዌ እንተ ርኢኩ መትሐተ ፀሐይ፡ ብዕል ዘይትዓቀብ በኀበ ዘአጥረዮ በእከይ ።

ከፀሐይ በታች ያየሁት ደዌ አለ፡ ይኸውም ሰርቶ ቀምቶ በጠራቀመው ሰው ዘንድ የሚጠበቅ ገንዘብ ነው ።

፲፬ ወይትኀጐል ውእቱ ብዕል በንታፌ እኩይ፡ ወወለደ ወልደ አልቦ ውስተ እዴሁ ወኢምንትኒ ።

ያም ገንዘብ በክፉ ቅሚያ ያልቃል ልጅን ወለደ በእጁ ምንም የለውም ።

፲፭ በከመ ወፅአ እምከርሠ እሙ ዕራቆ ይትመየጥ ለገቢእ በከመ ወፅአ ወአልቦ ዘይነሥእ እምፃማሁ ከመ ይሑር ምስሌሁ ።

ከናቱ ማኅፀን ዕራቁቱን እንደ ወጣ ዕራቁቱን ወደ መቃብር ይመለሳል፡ ከሱ ጋራ ይሄድ ዘንድ ከደከመበት ገንዘቡ የሚወስደው የለም ። ኢዮ፡ ፩ ፳፪ ።

፲፮ ወዝኒ እኩይ ደዌ ውእቱ፡ እስመ በከመ ወፅአ ከማሁ የሐውር ።

ከናቱ ማኅፀን ዕራቁቱን እንደ ወጣ እንዲሁ ዕራቁቱን ይሄዳልና ይህም ክፉ ደዌ ነው ። መክ፡ ፩ ፫ ።

፲፯ ምንት ፍድፋዴሁ ለዘይፃሙ ለነፍሱ፡ እስመ ኵሎን መዋዕሊሁ ውስተ ጽልመት ወላሀ ወቍጥዓ ብዙኀ ወደዌ ወኀዘን ።

ዘመኖቹ ሁሉ በመከራ በልቅሶ በብዙ ቍጣ፡ በደዌ በኃዘን ይፈጸማሉና፡ ለሰውነቱ የሚደክም ሰው ትርፉ ምንድር ነው፤ መዝ፡ ፻፳፯ ፪ ።

፲፰ ወበሕቱ ናሁ ዘርኢኩ አነ ኄርት ዘይእቲ ሠናይት፡ በሊዕ ወሰትይ ወርእየ ፍግዕ በኵሉ ሥራሑ ዘሠርኀ መትሕተ ፀሐይ በኍልቈ መዋዕሊሁ ዘወሀበ እግዚአብሔር እስመ ውእቱ መክፈልቱ ።

ነገር ግን እነሆ እኔ ያየኋት ደግ ነገር አለች፡ ይህችውም ያየኋት በጎ ነገር መብላት፡ መጠጣት ዕድሉ እሱ ነውና እግዚአብሔር በሰጠው ዘመን ቍጥር ሁሉ ከፀሐይ በታች በደከመበት ድካሙ ሁሉ ተድላ ደስታ ማየት ነው ።

፲፱ ወኵሉ ሰብእ ዘወሀበ እግዚአብሔር ብዕለ ወጥሪተ ወአሥለጠ በቱ ከመ ይብላዕ እምውስቴቱ ወይንሣእ መክፈልቶ ወይትፈሣሕ እምፃማሁ ዝኒ ሀብተ እግዚአብሔር ውእቱ ።

እግዚአብሔር ገንዘብንና ባለጸግነትን የሰጠው ከገንዘቡም ይበላ ዘንድ ዕድሉንም ይቀበል ዘንድ በሱም ያሠለጠነው በደከመበት ገንዘቡም ሁሉ ደስ የሚለው ሰው ሁሉ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ።

፳ እስመ አኮ ብዙኀ ዘይዜክር በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ እስመ እግዚአብሔር ያሠርኖ በፍትወተ ልቡ ።

እግዚአብሔር በልቡናው ፈቃድ የሚያደክመው ስለ ሆነ ባለ በዘመኑ ብዙ ዘመን እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ አይደለምና ።

## ምዕራፈ ፮ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

፩ ቦ እኩይ ዘርኢኩ እምታሕተ ፀሐይ፡ ወብዝኀት ይእቲ በላዕለ ኵሉ ሰብእ ።

ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፡ ይህችውም በሰው ሁሉ ላይ የበዛች ናት ።

፪ ብእሲ ዘወሀበ እግዚአብሔር ብዕለ ወጥሪተ ወክብረ ወአልቦ ዘይከልኦ ለነፍሱ እምኵሉ ዘፈተወት፡ ወኢያሥለጦ እግዚአብሔር ከመ ይብላዕ እምኔሁ እስመ ብእሲ ነግድ ይበልዖ፡ ወዝኒ ከንቱ ውእቱ ወደዌ እኪት ።

እግዚአብሔር ገንዘብን ባለጸግነትን ክብርን የሰጠው ሰውነቱ ከወደደችው ሁሉ ሰውነቱን የሚከለክላት የሌለ ከገንዘቡ ይበላ ዘንድ እግዚአብሔር ያሠለጠነው ሰው መሸ አዳሪ(ባዕድ) ሰው ይበላበታልና ይህም ከንቱ ነው፡ ክፉ ደዌም ናት ። መክ፡ ፭ ፲፱ ።

፫ ወለእመ ወለደ ብእሴ ምእተ ወብዙኀ ዓመታተ ሐይወ ወብዙኀ ኮነ መዋዕለ ዓመታቲሁ ወነፍሱሂ ኢትጸግብ እምሠናይት ወገንዘቱሂ ኢኮነ እቤ አነ ይኄይስ እምኔሁ ዳሕፅ ።

ሰው መቶ ልጅ ቢወልድ ብዙ ዘመንም ቢኖር የዘመኑም ቍጥር ብዙ ቢሆን ሰውነቱ ከተድላው ከደስታው ካልጸገበች ከፈን ካልተረፈው ከእንደዚህ ያለ ሰው እኔ ውራድ ይሻላል አልኩ ።

፬ እስመ በከንቱ መጽአ ወውስተ ጽልመት የሐውር ወበጽልመት ስሙ ይትከደን ።

በከንቱ ወደዚህ ዓለም መጥቷልና፡ ወደ መቃብርም ይሄዳልና፡ በመቃብርም ስሙ ይዘጋል (ይዘነጋል) ።

፭ ወፀሐየኒ ኢርእየ ወኢያእመረ ዕረፍቱ ለዝ እምዝ ።

ፀሐይ ምሳሌው እንደሆነ አይቶ ካላወቀ ከእንዲህ ያለው ሰው ኑሮ የዚህ የውራድ ዕረፍት ይሻላል ።

፮ ወሰበ ሐይወ ዓሥርተ ምእተ ምሕዋረ ዓመት ወሠናይተ ኢርእየ፡ አኮኑ ውስተ መካን አሐዱ ኵሉ የሐውር ።

ቀጥሎ ቀጥሎ ሺሕ ዘመን ቢኖር ተድላ ደስታውን ካላየ ሰው ሁሉ ወደ አንዱ መቃብር ይሄዳልና፡ የውራጁ ዕረፍት ይሻላል ።

፯ ወኵሉ ሥራኁ ለሰብእ በአፉሁ ፡ ወነፍሱስ ኢትመልእ ብዕለ ።

የሰው ሁሉ ድካሙ በአፉ ነው ፡ ሰውነቱ ግን ብልጽግናን አትጠግብም ። ምሳ፡ ፲፮ ፳፮ ።

፰ ምንት ፍድፋዴሁ ለጠቢብ እምዐብድ ፡ በእንተ ምንት ነዳይ የአምር ሐዊረ ቅድመ ሕይወት ።

ከላዋቂም ላዋቂ ትርፉ ምንድር ነው ፤ ድኻ በሕይወት ሳለ በሞት መሄድን ለምን ይወዳል ፤

፱ ይኄይስ ርእይ በዓይን እምሐዊር በነፍስ ፡ ወዝኒ ከንቱ ወፍትወተ ነፍስ ።

በራሱ ተገብዞ ልሙት ከማለትስ እግዚአብሔርን ምግብ ስጠኝ ብሎ መለመን ይሻለው ነበር ፡ ይህም ከንቱ ነው የልብም አምሮት ነው ። ዘዳ፡ ፳፰ ፴፱ ።

፲ ኵሉ ዘከነ ናሁ ተሰምየ ስሙ ወተአምረ ከመ ውእቱ ሰብእ ፡ ወኢይክል ተጋእዞ ምስለ ዘይፀንዕ እምኔሁ ።

እነሆ የተፈጠረው ሰው ሁሉ በስሙ ተጠራ ፈራሽም እንደሆነ ታወቀ ከሱ ከሚፀና ከሞት ጋራ መከራከር አይችልም ። ኢዮ፡ ፱ ፴፪ ።

፲፩ እስመቦ ከንቶ ነገረ ዘያበዝኅ ፡ ምንት ፍድፋዴሁ ለሰብእ ።

ከንቱ ነገርን የሚያበዛ ሰው አለና ፡ እንዲህ ከሆነ የሰው ትርፉ ምንድር ነው ፤

፲፪ መኑ ውእቱ ዘየአምር ምንት ውእቱ ሠናይ ለሰብእ በሕይወቱ እንዘ ኍልቊ መዋዕለ ሕይወቱ ከንቱ ፡ ወገብሩ ከመ ጽላሎት መኑ ያየድዖ ለሰብእ ዘይከውን እምድኅሬሁ በታሕተ ፀሐይ ።

በሕይወት የሚኖርበት የዘመኑ ቍጥር ከንቱ ሲሆን ሥራውም እንደ ጥላ ሲሆን በሕይወቱ ሳለ ለሰው ያማረ የተወደደ ምን እንደሆነ የሚያውቅ ማን ነው ፤ ከሱ በኋላ ከፀሐይ በታች የሚደረገውንስ የሚነግረው ማን ነው ፤

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ይኄይስ ስም ሠናይ እምቅብዐ መዐዛ ፡ ወዕለተ ሞት እምዕለተ ልደት ።

መዓዛ ያለው ሽቱ ከመቀባት በጎ ስም ይሻላል ከሚወለዱበትም ቀን የሚሞቱበት ቀን ይሻላል ።

፪ ይኄይስ ሐዊረ ቤተ ላህ እምሐዊረ ቤተ ግዝዕ ፡ እስመ ውእቱ ዝ ደኃሪቱ ለኵሉ ሰብእ ፡ ወዘሕያው የሀብ ሠናየ ውስተ ልቡ ።

ሙሾ ፍሪዳ ወዳለበት ቤት ከመሄድ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል ፡ የሰው ሁሉ ፍጻሜው ይህ ነውና ፡ ሕያው የሆነ ሰውም ሁሉ በልቡናው በጎ ነገርን ያስብ ።

፫ ይኄይስ መዓት እምሰሐቅ ፡ እስመ በእእክዮ ገጽ ይሤኒ ልብ ።

ፊትን በማጥቈር ልቡናን ደስ ይለዋልና ላላዋቂ ሰው ከመሳቅ መቈጣት ይሻላል ። ፪ ቆሮ፡ ፯ ፲ ።

፬ ልበ ጠቢባን ውስተ ቤተ ላህ ፡ ወልበ ዐብዳንሰ ውስተ ቤተ ፍሥሓ ።

የብልህ ሰዎች ልቡና የልቅሶ ቤትን ያስባል ፡ የሰነፎች ልቡና ግን የተድላ የደስታ ቤትን ያስባል ።

፭ ይኄይስ ሰሚዐ ተግሣፀ ጠቢብ ፡ እምብእሲ ዘይሰምዕ ማኅሌተ ሀብድ ።

ያላዋቂውን ዘፈን ከሚሰማ ሰው ፡ የመምህራንን ትምህርት የሚሰማ ሰው ይሻላል ። መዝ፡ ፻፵፪ ፭ ።

፮ ከመ ቃለ አሥዋክ ታሕተ ጽሕርት ፡ ከማሁ ሰሐቆሙ ለዐብዳን ፡ ወዝኒ ከንቱ ውእቱ ።

ያላዋቂዎች ሰዎች ሳቃቸው ከምጣድ በታች እንዳለ እሾኽ ድምፅ ነው ፡ ይህም ከንቱ ነው ።

፯ እስመ ትዕግልት ያንጐገዎ ለጠቢብ ፡ ወያኀጕል ትግዕሥተ ልቡ ።

የድኻው መቀማት አዋቂውን ሰው አእምሮውን ያሳጠዋልና ፡ የልቡናውንም ትዕግሥት ያጠፋበታልና ።

፰ ይኄይስ ደኃሪ ቃል እምቀዳሚሁ ፡ ወይኄይስ መስተዓግስ እምዕቡየ መንፈስ ።

ከቀደመው ቃል የኋለኛው ቃል ይሻላል ፡ ከልበ ትዕቢተኛ ሰው ትዕግሥተኛ ሰው ይሻላል ።

፱ ኢትጕጕዕ በመንፈስከ ለተምዕዖ ፡ እስመ መዓት ውስተ ጎዕነ ዐብዳን ተዐርፍ ።

ቍጣ በሰነፎች ዘንድ ፀንታ ትኖራለችና በቃልህ ለመቈጣት አትቸኵል ። ምሳ፡ ፲፬ ፴፫ ።

፲ ኢትበል ምንተ ከነ እስመ መዋዕለ ትካት ይኄይስ እምእላንቱ ፡ እስመ አኮ በጥበብ ዘተስእልከ ።

ከጠየቅህበት ወራት ያልጠየቅህበት ወራት ይሻላልና በአገሬ ምን ተደረገ ብለህ አትጠይቅ በጥበብ የጠየቅህ አይደለምና ።

፲፩ ወበእንተዝ ሠናይ ጥበብ ምስለ ውቃቤ ፡ ወፈድፋደሰ ለእለ ይሬእዩ ፀሐየ ።

ስለዚህ ነገር ከለመጠየቅ ጋራ ያለ ጥበብ በጎ ነገር ነው ይልቁንም ፀሐይ ምሳሌያቸው እንደሆነ ለሚያውቁ ሰዎች በጎ ነገር ነው ።

፲፪ እስመ ጽላሎታ ለጥበብ ይኄይስ እምጽላሎታ ለብሩር ወፈድፋደሰ አእምሮታ ለጥበብ ወታሕይዎ ለዘአጥረያ ።

ብርን ድብ ከማድረግ ጥበብን ድብ ማድረግ ይሻላል ፡ ፈጽሞ ጥበብን ማወቅ ይሻላልና ገንዘብ ያደረጋትን ሰው ታድነዋለች ። ምሳ፡ ፫ ፲፰ ።

፲፫ ርኢ ተግባር ለእግዚአብሔር ፡ ወመኑ ውእቱ ዘይክል አርትዖቶ ለዘእግዚአብሔር አጥወዮ ።

የእግዚአብሔር ሥራውን ተመልከት እግዚአብሔር ያጠመመውን የሚያቀናው ፡ ማነው ፤

፲፬ በመዋዕለ ሠናይ ሕየው በፍሥሓ፡ ወርኢ በዕለት እኪት ዝኒ ናሁ መምሰሉ ለዘውእቱ ገብረ እግዚአብሔር ።

በበጎ ወራት ንስሓ ገብተህ በተድላ በደስታ ኑር በዕለተ ሞት (በምጽአት ቀን) ክብርን ውረስ እነሆ ይህ እንዲህ ያለው ሰው እግዚአብሔር የፈጠረው የአዳም ምሳሌ ነው።

፲፭ በእንተ ነገረ ውሉደ ሰብእ ከመ ኢይርከቡ ሰብእ ዘእምድኅሬሁ ወኢምንትኒ፡ ኵሎ ኀቡረ ርኢኩ በመዋዕለ ሥራኅየ፡ በ ጻድቅ ዘይትኀጐል በጽድቁ፡ ወበ ረሲዕ ዘይሄሉ በእከዩ ።

ከሞተ በኋላ ሰው የሚደረገውን ነገር ምንም እንዳያውቅ ንስሓ በገባሁበት ወራት የሰውን ነገር ሁሉ አንድነት አየሁ፡ በእውነተኛነቱ የሚጠፋ ጻድቅ አለ፡ በክፋቱም ፀንቶ የሚኖር ረሲዕ አለ ።

፲፮ ኢትኩን ጻድቀ ፈድፋደ፡ ወኢትጠበብ ፈድፋደ ከመ ኢትጌጊ፡ ወኢትኅጣእ ፈድፋደ ።

ፈጽመህ ደግ አትሁን እንዳትበድል፡ ፈጽመህም አትራቀቅ፡ ፈጽመህም ኃጢአተኛ አትሁን ።

፲፯ ወኢትኩን ድሩከ ከመ ኢትሙት ዘእንበለ ጊዜሁ ።

ያለ ጊዜህም እንዳትቀሠፍ በክፋት የፀናህ አትሁን ።

፲፰ ይኄይስ ሀሎምትከ በዝ እምዝ ወኢታርኵስ እዴከ ፍርሆ ለእግዚአብሔር፡ እስመ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር ይወፅእ እምኵሉ ።

ከዚህ በዚህ መኖር ይሻልሃል ቃልህን ሐሰተኛ አታድርግ እግዚአብሔርን የሚፈራው ሰው ከመከራው ሁሉ ይድናልና፡ እግዚአብሔርን ፍራው ።

፲፱ ጥበብ ትረድኦ ለጠቢብ እምዓሠርቱ ምእት መኳንንት፡ እለ ሀለዉ ውስተ ሀገር ።

በአገር ካሉ ከሺሕ መኳንንት ይልቅ ጥበብ አዋቂ ሰውን ትረዳዋለች ። ዘፍ፡ ፵፪ ፲ ።

፳ እስመ አልቦ ሰብእ ጻድቅ ውስተ ምድር ዘይገብር ሠናየ፡ ወኢይኤብስ ።

በዚህ ዓለም በጎ ሥራ የሚሠራ የማይበድል ደግ ሰው የለምና ። ፩ ነገ፡ ፰ ፵፮። ፪ ዜና መዋ፡ ፮ ፴፮።

፳፩ ወውስተ ኵሉ ነገር ዘይትናገሩ ኢትስድ ልበከ ከመ ኢትስማዕ ገብርከ እንዘ ይረግመከ፡ እስመ ብዙኀ ይትመዓዓከ ልብከ፡ ወበፍናው ብዙኀ የአክያ ለልብከ ከመ አንተኒ ረገምከ ባዕደ ።

ልቡናህ ብዙ ይበሳጭብሃልና በብዙ ወገንም ልቡናህን ያበሳጫልና አንተ ሌላውን እንዳማህ በርያህ ሲያማህ እንዳትሰማ ልቡናህን ወደሚናገሩት ነገር ሁሉ አትውሰድ።

፳፪ ወዘንተ ኵሎ አምከርኩከ በጥበብ ወእቤ እጠበብ ።

ይህን ሁሉ እኔ በጥበብ ፀንቼ መከርኩህ፡ እራቀቃለሁም አልኩ ። ሮሚ ፩ ፳፪ ።

፳፫ ወይእቲ ርኅቅት እምኔየ ርኁቀ፡ እንዘ ሀለወት ወዕመቀ ዕመቅ መኑ ይረክባ ።

ይህች ጥበብ ከኔ የራቀች ናት በሩቅ ሳለች በጥልቅም ሳለች ማን ያገኛታል፤ ሮሜ ፲፩ ፴፫ ።

፳፬ ዖድኩ አነ በልብየ ለአእምሮ ከመ አሐሊ ወእኅሥሣ ለጥበብ ወለሐሳብ፡ ወከመ አእምር ለረሲዓን ዕበዶሙ ወአጽሕቆ ስሕተታት ።

አስብ ዘንድ ጥበብንም ግምገማንም እመራመራት ዘንድ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ስንፍናቸውን እውቅ ዘንድ ኃጢአቶችም ሥሩኝ ሥሩኝ ማለታቸውን አውቅ ዘንድ ጥበብን ለማወቅ እኔ በልቤ መረመርኩ ።

፳፭ ወእረከብ ኪያሃ አነ መራረ እሞት፡ ብእሲት እንተ ይእቲ መሥገርት ወመርበብት ልበ ወማእሰር ውስተ እደሃ ኄር በቅድመ እግዚአብሔር ዘይትበላሕ እምኔሃ ወዘይኤብስስ ይሠገር ባቲ ።

እኔ ከሞት የመረረች እሷን አገኘሁ ይህችውም ወጥመድ የምትሆን ልቡናዋም መረብ የሚሆን በእጅዋም ማሰርያ ያለ ሴት ናት ከሷ የሚድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት ደግ ነው፡ የሚበድል ሰው ግን በሷ ይጠፋል ።

፳፮ ናሁ ዘንተ ረከብኩ ይቤ መክብብ አሐተ እምአሐቲ ለረኪበ ሕሊና ዘኀሠሠት ነፍስየ ።

እኔ መክብብ ልቡናዬ የመረመረችውን ነገር ለማግኘት ከአንዲቱ ነገር አንዲቱን ብመረምር እነሆ ይህን አላገኘሁም (ደግ ሴትን) ።

፳፯ ወኢረከብኩ፡ ወብእሴሰ አሐደ እምዓሠርቱ ምእት ረከብኩ፡ ወብእሲተሰ እምውስተ ዝ ኵሉ ኢረከብኩ ።

ደግ ሴትን አላገኘሁም ከሺሕ ወንዶች ግን አንድ ወንድ (አብርሃምን) አገኘሁ ነገር ግን በዚህ ዓለም ካሉ ሴቶች ሁሉ አንዲት ደግ ሴት አላገኘሁም ።

፳፰ ባሕቱ ናሁ ዘንተ ረከብኩ ዘገብረ እግዚአብሔር በጊዜሁ፡ ብእሴ ራትዐ ወውእቱ የኃሥሥ ሕሊና ብዙኀ ።

እነሆ እግዚአብሔር በጊዜው ጊዜ የፈጠረው ቅን ሰውን (አብርሃምን) አገኘሁ፡ እሱም ብዙ ዕውቀትን ይመረምራል ። ዘፍ፡ ፩ ፳፯ ። ፫ ፮-፯ ።

## ምዕራፍ ፰ ።

፩ መኑ የአምሮሙ ለጠቢባን፡ ወመኑ የአምር ፈክሮ ቃሎሙ፡ ጥበቡ ለብእሲ ያበርህ ገጾ ወዘአልበ ኀፍረት ውስተ ገጹ ይጸላእ ።

አዋቆች ሰዎችን ማን ያውቃቸዋል፤ ቃላቸውንስ መተርጐም ማን ያውቃል፤ የሰው ጥበቡ ፊቱን ያበራዋል፡ በፊቱ ሰውን ማፈር የሌለው ሰው ግን ይጠላል ።

፪ ወልድየ፡ አፈ ንጉሥ ዕቀብ፡ ወለቃለ መሐላ ኢትጕጕዕ።

ልጄ! የንጉሥን አፍ ጠብቅ፡ ለመሐላም ንጉሥ (ይሙት ለማለት) አትቸኵል ።

፫ ወእምቅድመ ገጹ ኅልፍ ወኢትቁም በነገር እኩይ እስመ ኵሎ ዘፈቀደ ይገብር ።

ከፊቱም ፈጥነህ ሂድ ክፉ ነገርንም ይዘህ በፊቱ አትቁም ፡ የወደደውን ሁሉ ያደርጋልና ።

፬ ወከመ ንጉሥ ሥሉጠ ይትናገር ፡ ወመኑ ይብሎ ምንተ ገበርከ ።

ንጉሥም እንደ መሆኑ የሠለጠነ ሆኖ ይናገራልና ለምን እንዲህ አደረግህ የሚለው ማን ነው ፤

፭ ዘየዓቅብ ትእዛዘ ኢየአምር ቃለ እኩየ ፡ ወጊዜሁ ለፍትሕ የአምር ልበ ጠቢብ ።

ትእዛዙን የሚጠብቅ ሰው ክፉ ነገርን አይወድም የብልህም ሰው ልቡና የፍርድ ጊዜውን ያውቃል ።

፮ እስመ ለኵሉ ግብር በ ጊዜ ወፍትሕ ፡ እስመ አእምሮቱ ለብእሲ ጽኑዕ ላዕሌሁ ።

ለሥራ ሁሉ ለፍርድም ጊዜ አለውና የሰው ዕውቀቱ በሰው የፀና ስለሆነ የብልህ ሰው ልቡና የፍርድ ጊዜውን ያውቃል ።

፯ እስመ አልበ ዘየአምር ምንተ ዘከነ ወዘይከውንሂ መኑ ይነግር ።

ከሞት በኋላ ያለፈውን የሚመጣውን ምንም የሚያውቅ የለምና ፡ ከሞተ በኋላ የሚሆነውን የሚነግረው ማን ነው ፤ ምሳ፡ ፳፬ ፳፪ ።

፰ ወአልበ ብእሲ ዘይሜልጥ በመንፈሱ ለከሊአ መንፈስ ኅቡረ ፡ ወአልበ ዘይሜልጥ በዕለተ ሞት ፡ ወአልበ መልእክት በዕለተ ቀትል ፡ ወኢታድኅን ረሲዓነ ዘኀቤሃ ።

በአንድነት ሞትን ለመከልከል በሰውነቱ የሚሠለጥን ሰው የለም ፡ በሚሞትበትም ቀን የሚሠለጥን የለም ፡ በሰልፍም ቀን መልእክት የለም ፡ ይህችም ዓለም ከሷ ዘንድ ያሉ ረሲዓን ሰዎችን ከሞት አታድናቸውም ።

፱ ኵሎ ኅቡረ ርኢኩ ወወሀብኩ ልብየ ውስተ ኵሉ ፍጥረት ዘተፈጥረ መትሕተ ፀሐይ ፡ ዘመጠነ ተሠልጠ ሰብእ ለአእከዮተ ሰብእ ።

አንድነት ሁሉን አየሁ ከፀሐይ በታች የተፈጠረውን ሁሉ ለመመርመር ልቡናየን ሰጠሁ ፡ ሰው ሰውን ለማክፋፋት እንደ ሠለጠነ አየሁ ።

፲ አሜሃ ርኢኩ ረሲዓነ ውስተ መቃብር ቅዱስ እንዘ ይበውኡ ፡ ወዘእምቅዱሳን ሖሩ ወተወደሱ በውስተ ሀገር እስመ ከመዝ ገብሩ ፡ ዝኒ ከንቱ ።

ያን ጊዜ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ወደ ዕኑ መቃብር ሲገቡ አየሁ ፡ እንደዚህ ያለ በጎ ሥራ ሠርተዋልና ፡ በዚህ ዓለም ተመስግነው ከጻድቃንም ወገን ወደ መቃብር የሄዱ አሉ ፡ ይህም ከንቱ ነው ።

፲፩ እስመ አልበ ዘይከውን ቅስት እምእለ ገብሩ እኩየ ፀፍጡን በእንተ ዝንቱ አዕረፈ ልበ ውሉደ ሰብእ በሙ ለገቢረ እከይ ዘአበሰ ወገብረ ኃጢአተ እምትከት ፡ ወእምቅድሜሁ ።

ክፉ ሥራን በሚሠሩ ሰዎች ፈጥኖ የሚደረግ ጸብ ክርክር የለምና ፡ ከጥንት ጀምሮ የበደለ ኃጢአት የሠራ የሰው ሁሉ ልቡና ስለዚህ ነገር ኃጢአት ለመሥራት በነሳቸው ዐረፈ ። መዝ፡ ፲.፮ ። ኢሳ፡ ፳፮ ፲ ።

፲፪ እስመ አእምር አነ ከመ በ ሠናይት ለእለ ይፈርህዎ ለእግዚአብሔር ከመ ይፍርሁ እምቅድመ ገጹ ።

ከፊቱ የተነሣ ይፈሩት ዘንድ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሰዎች እኔ በጎ ነገር እንዳላቸው አውቃለሁና ።

፲፫ ወአልበ ሠናይት ለረሲዕ ወኢይነውኅ መዋዕለ ጽላሎቱ ዘኢይፈርህ እምቅድመ ገጹ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ለዘነጋ ሰው በጎ ነገር የለውም ከእግዚአብሔር ፊት የተነሣ የማይፈራ ሰው (እንደ ጥላ) የሚያልፍ ዘመኑ አይበዛለትም ። ኢሳ፡ ፫ ፲፩ ። ኢዮ፡ ፲፪ ፪ ።

፲፬ ወበ ከንቱ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ ውስተ ምድር እስመበ ጻድቃን ዘይበጽሕ ላዕሌሆሙ ግብረ ረሲዓን ወበ ረሲዓን ዘይበጽሕ ላዕሌሆሙ ግብረ ጻድቃን ፡ ወእቤ ዝኒ ከንቱ ።

የረሲዓን ሥራ የሚደርስባቸው ጻድቃን አሉና የደጋግ ሰዎች ሥራ የሚደርስባቸውም ሰዎች አሉና ፡ ከፀሐይ በታች የተሠራ ከንቱ ሥራ አለ ፡ ይህም ከንቱ ነው እላለሁ ።

፲፭ ወወደስክዋ አነ ለኵላ ፍግዕ ፡ እስመ አልበ ሠናይ ለሰብእ እምታሕተ ፀሐይ ፡ ዘእንበለ ዘበልዐ ወሰትየ ወተፈሥሐ ፡ ወውእቱሰ ዘሎቱ እምፃማሁ በመዋዕለ ሕይወቱ ዘወሀበ እግዚአብሔር እምታሕተ ፀሐይ ።

ከፀሐይ በታች እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወት በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ከደከመበት ገንዘቡ በልቶ ጠጥቶ ደስ ካለው ሰው በቀር ለሰው በጎ ነገር የለምና እኔ ተድላ ደስታን ሁሉ አመሰገንኋት ።

፲፮ እስመ ወሀብኩ ልብየ ለአእምሮ ጥበብ ወከመ እርአይ ሥራኀ ዘተገብረ ዲበ ምድር እስመ በመዓልትኒ ወበሌሊትኒ ንዋም ውስተ አዕይንቲሁ ዘይሬኢ አልቦ ።

በዚህ ዓለም የተሠራውን ድካም አይ ዘንድ ጥበብን ለማወቅ ልቡናዬን እንደ ሰጠሁ በሌሊትና በቀንም በዓይኖቹ እንቅልፍ የሚያይ የለምና ።

፲፯ ወርኢኩ ኵሎ ግብሮ ለእግዚአብሔር ከመ ኢይክል ሰብእ ረኪበ ኅቡረ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ እመ ሚ መጠነ ይቤ ጠቢብ ከመ ያእምር ኢይክል ሰብእ ረኪበ ፡ ወእመ ሚ መጠነ ኃሠሠ ኢይክል ሰብእ ረኪበ ።

ከፀሐይ በታች የተፈጠረውን ፍጥረት ሰው አንድነት ማወቅ እንዳይቻለው የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ አየሁ ፡ ብልህ ሰው ያውቅ ዘንድ ምንም አዋቂ ነኝ ቢል መርምሮ ማወቅ አይቻለውም ፡ ምንም ቢመረምር ሰው አንድነት መርምሮ ማወቅ አይቻለውም ።

## ምዕራፍ ፱ ።

፩ እስመ ኅቡረ ዘንተ ኵሎ ወሀብኩ ልብየ ፣ ወልብየ ዘንተ ኵሎ ርእየት ከመ ለጻድቃን ወለጠቢባን ምግባሮሙ ውስተ እደ እግዚአብሔር ፍቅረ ወጽልአ አልቦ ዘየአምር ሰብእ ኵሉ ቅድመ ገጾሙ ወከንቱ ውእቱ ውስተ ኵሉ ።

፪ ወአሐዱ ድድቁ ለጻድቅ ወለረሲዕ ፣ ለኄር ወለእኩይ ፣ ለርኩስ ወለንጹሕ ፣ ለዘይሠውዕ ወለዘኢይሠውዕ ፣ ለኄር ወለዘሂ የኃጥእ ፣ ለዘይምሕል ወለዘሂ ይፈርህ መሐላ ።

፫ ዝከቱ በኵሉ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ እስመ አሐዱ ድድቁ ለኵሉ ወልበሙ ለውሉደ ሰብእ ትፌጽም እኩየ ፣ ወበሁከተ ልበሙ ሕይወቶሙ ወእምድኅሬሆሙ ኀበ ምውታን ።

፬ እስመ መኑ ውእቱ ዘይሳተፍ ምስለ ሕያዋን በተስፉ ከልብ ሕያው ይኄይስ እምአንበሳ ምውት ።

፭ እስመ ሕያዋን የአምሩ ከመ ይመውቱ ፣ ወሙታንሰ ኢየአምሩ ወኢምንትኒ ወአልቦሙ እንከ ዓስብ ።

፮ እስመ ተረስዐ ዝክሮሙ ወፍቅሮሙ ፣ ወጽልአሙኒ ወቅንአቶሙኒ ናሁ ተኃጕለ ወመክፈልት አልቦሙ እንከ ውስተ ዓለም በኵሉ ዘተገብረ መትሕተ ፀሐይ ።

፯ ነዓ ብላዕ በፍሥሓ ኅብስተከ ፣ ወስተይ በልብ ኄር ወይነከ ፣ እስመ እግዚአብሔር ሠምረ ምግባሪከ ።

፰ በኵሉ ጊዜ ይኩን ንጹሐ አልባሲከ ፣ ወቅብዕ እምርእስከ ኢይርኃቅ ።

፱ ወርኢ ሕይወተ ምስለ ብእሲትከ እንተ አፍቀርከ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትከ እለ ተውህበከ እምታሕተ ፀሐይ ኵሎ መዋዕለ እለ ከና ለከ ፣ እስመ ውእቱ መክፈልትከ በሕይወትከ ።

፲ ወበሥራኅከ ዘትሠርኅ እምታሕተ ፀሐይ ኵሎ ዘትክል እዴከ ለገቢር መጠነ ኃይልከ ግበር ፣ እስመ አልቦ ግብር ወሕሊና ወጥበብ ወአእምሮ ውስተ ገሃነም ኀበ ተሐውር አንተ ህየ ።

፲፩ ወተመየጥኩ ወርኢኩ መትሕተ ፀሐይ ከመ አኮ ለቀሊላን ረዊፅ ፣ ወአኮ ለጽኑዓን ቀትል ፣ ወአኮ ለጠቢባን እክል ፣ ወአኮ ለማእምራን ብዕል ፣ ወአኮ ለእለ ይሌብዉ ጸጋ እስመ ጊዜ ወድድቅ ይዳደቆሙ ለኵሎሙ ።

፲፪ እስመ ኢየአምር ሰብእ ጊዜሁ ከመ ዓሣት እለ ይሠገሩ በመርበብት እኩይ ፣ ወከመ አዕዋፍ ዘይትአኀዙ በመሥገርት ፣ ከማሁ ይሠገሩ ውሉደ ሰብእ በጊዜ እኩይ ሶበ ይወድቅ ዲቤሆሙ ግብተ ።

፲፫ ወናሁ ዘንተኒ ርኢኩ ጥበበ መትሕተ ፀሐይ ።

፲፬ ወዓበይ ይእቲ በኀቤየ ሀገር ንስቲት ወሰብእ እለ ውስ

## ምዕራፍ ፱ ።

አንድነት ይህን ሁሉ ለመመርመር ልቡናየን ሰጥቻለሁና የደጋግ ሰዎች ሥራቸው በእግዚአብሔር እጅ ተይዞ እንዳለ ይህን ሁሉ ልቡናዬ መረመረች ከሞት በኋላ ፍቅርን ጥልን የሚያውቅ ሰው የለም ፣ ጥሉም ፍቅሩም ሁሉ ከሞት አስቀድሞ ነው ፣ በሰውም ሁሉ ከንቱ ሞት አለ ።

የጻድቁም የኃጥኡም ሞቱ አንድ ነው ፣ የደጉም የክፉም የርኩሱም የንጽሑም መሥዋዕት የሚሠዋውም የማይሠዋውም የኃጢአተኛውና የደግ ሰው መሐላ የሚፈራና የሚምልም ሰው ሞቱ አንድ ነው ። ኢዮ ፣ ፱ ፳፪ ።

የሁሉ ሞቱ አንድ ነውና ፣ ከፀሐይ በታች ለተፈጠረው ፍጥረት ይህ ሞት አለበት ፣ እንዲህ መሆን ሳለ የሰዎች ልቡና ክፉ ነገርን ፈጽማ ታስባለች በልቡናቸው ሁከት ዘመናቸውን ያጣሉ ከሞቱ በኋላ የሞቱም ሰዎች ወዳሉበት ወደ መቃብር ይመለሳሉ ።

የሞቱ ሰዎች በተስፋ ከሕያዋን ጋራ አንድ አይሆኑምና ከሞተ አንበሳ ሕያው የሆነ ውሻ ይሻላል ።

ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና የሞቱ ሰዎች ግን ምንም አያውቁምና ከሞቱም በኋላ ዋጋ የላቸውምና ።

ስም አጠራራቸው ተረስቷልና ፍቅራቸው ጥላቸው ቅንአታቸውም እነሆ ጠፋ ፣ ከፀሐይ በታች በተሠራው ሥራ ሁሉ እንግዲህ ወዲህ ዕድል ፈንታ የላቸውም ።

እግዚአብሔር ሥራሕን ወዷልና ደስ ብሎህ ና እንጀራህን ብላ በበጎ ልቡናም ወይንህን ጠጣ ።

በየጊዜው ልብስህ ንጹሕ ይሁን ቅቤም ከራስህ አይራቅ ። ራእ ፣ ፫ ፬ ።

ከፀሐይ በታች በተሰጡህ በሕይወት በምትኖርባቸው ዘመኖች ሁሉ ከወደድካት ከሚስትህ ጋራ በሕይወት ሳለህ ዕድልህ እሱ ነውና በተሰጡህ ዘመኖች ሁሉ ተድላ ደስታን አድርግ ። መክ ፣ ፪ ፩ - ፳፱ ።

አንተ በምትሄድበት በዚያ በመቃብር አሳቧና ሥራ ዕውቀትና ጥበብ የለምና ከፀሐይ በታች በምትደክምበት ድካምህ ሁሉ እጅህ ለማድረግ የሚቻላትን ያህል አድርግ።

አንዱን ነገር ከማየት አንዱን ነገር ወደ ማየት ተመልሼ ከፀሐይ በታች የሚሠራውን ሥራ አየሁ ፣ ለፈጣኖች ሩጫ እንዳልረባቸው ለአርበኞችም ሰልፍ ከሞት እንዳላዳናቸው ለብልሆች እኽል ከሞት እንዳላዳናቸው ለአዋቆችም ብዕል እንዳልጠቀማቸው አየሁ ፣ ሁሉንም ጊዜ ሞት ይገናኛቸዋልና ፣ ትንቢት ለሚያውቁም ሰዎች ትንቢት እንዳልረባቸው አየሁ ። አሞ ፣ ፪ ፱ - ፲፱ ።

